41_1996.pdf

43_1996.pdf

44_1996.pdf

45_1996.pdf

46_1997.pdf

47_1997.pdf

50_1997.pdf

52_1998.pdf

53_1998.pdf

54_1998.pdf

55_1998.pdf

56_1998.pdf

57_1998.pdf

58_1998.pdf

59_1998.pdf

60_1998.pdf

የሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት

# ሐረር ነጋሪ ጋዜጣ
# HARAR NEGARI GAZETA

፩ ዓመት ቁጥር 10
፩ Year No 10

HARARI PEOPLE NATIONAL REGIONAL STATE

ሐረር መጋቢት 1ቀን 1996
HARAR 11th March, 2004

| የአንዱ ዋጋ<br>Unit Price 3.00 | በሐረሪ ህዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ | የፖስታ ሳጥን ቁጥር<br>P.O.Box 272 |
|---|---|---|

## ማውጫ

አዋጅ ቁጥር 41/1996ዓም

የሐረሪ ህዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 41/1996 ....................ገፅ 329

## አዋጅ ቁጥር 41/1996
## የሐረሪ ህዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት
## የገቢ ግብር አዋጅ

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ የኢኮኖሚ ፖሊሲ በአገሪቱ ውስጥ የማህብራዊና የኢኮኖሚ ግንኙነቶችን ተቋሞችን ለማሳደግና ለማስፋፋት አዲስ ምዕራፍ የከፈተ በመሆኑ፣

የሐረሪ ህዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት በነዚህ ሁኔታዎች መፈጠር ምክንያት በክልሉ በሚገኙት የገቢ ምንጮች ላይ በነፃ ገበያ ሥርአት ውስጥ ከሚሰራባቸው የገንዘብ ነክ ጉዳዮች ወይም መርሆዎች ጋር እንዲዋሐድ ማድረግ አስፈላጊ በመሆኑ፣

የክልሉን የግብር ስርዓትን ዘመናዊ በማድረግ እና የግብር መሠረቱን በማስፋት በክልሉ ቁጠባንና ኢንቨስትመንትን በማበረታታት ፈጣን የኢኮኖሚ እድገት ለማምጣት የሚያግዝ መሆኑ ስለታመነበት፣ በሐረሪ ህዝብ ብሄራዊ ክልላዊ መንግሥት ሕገ መንግስት አንቀጽ 26/2/ሀ/ መሰረት የሚከተለው ታውጇል።

## ምዕራፍ አንድ
## መሠረታዊ ድንጋጌዎች
## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ

1. **አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ "የሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 41/1996" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. **ትርጓሜ**

በዚህ አዋጅ ውስጥ የተለየ ትርጉም በግልፅ ካልተሰጣቸው በስተቀር በሌሎች የኢትዮጵያ ሕጎች ትርጉም የተሰጣቸው ቃላት የተተረጎሙበት ሕግ የተሰጣቸውን ትርጉም ይይዛሉ። ለዚህ አዋጅ አፈፃፀም የሚከተሉት ቃላትና ሐረጎች ከዚህ በታች የተሰጣቸው ትርጓሜ ይኖራቸዋል።

1. ሰው"ማለት ማንኛውም ግለሰብ፣ ድርጅት ወይም ኅበር ሲሆን ሌላን ሰው በመወከልተተማጭነቱ በኢትዮጵያ ውስጥ ሆኖ የንግድ ሥራ የሚያካሂድ የንግድ ወኪልን ይጨምራል።
2. "ድርጅት"ማለት የንግድ ሥራ የሚያካሂድ ማናቸውም ኩባንያ ወይም የተመዘገበ የሽርክና ማኅበር ወይም ከኩባንያ ወይም ከተመዘገበ የሽርክና ማኅበር ጋር ተመሳሳይ የሆነና በውጭ አገር ሕግ መሠረት የተቋቋመ ድርጅት ወይም ማናቸውም የመንግሥት የልማት ሥራ ድርጅት ወይም የገንዘብ ድርጅት ሲሆን በውጭ አገር ያለን አካል በመወከል በኢትዮጵያ ወይም በክልሉ ውስጥ የንግድ ሥራ የሚያካሂደውን ወኪል እና ፀንቶ በሚሠራበት በኢትዮጵያ ወይም በክልሉ ወይም በሌላ አገር ሕግ የተመሠረተ ወይም ዕውቅና ያገኘ ቢሆንም ባይሆንም እንደ ድርጅት የሚንቀሳቀስን ይጨምራል።
3. "የሰዎች ኅብረት" ማለት ግለሰቦች አባል የሆኑበት ማኅበር ወይም ግለሰብ ያልሆኑ አንድ ወይም ከአንድ በላይ አባላትን የሚጨምር ማኅበር ሲሆን "ለድርጅት" በተሰጠው ትርጉም ውስጥ የሚካተቱ ማኅበራትን አይጨምርም፡
4. ግንኙነት ያላቸው ሰዎች" ማለት
   i. የተፈጥሮ ሰው እና
   ሀ/ የዚህ የተፈጥሮ ሰው ማናቸውም ዘመድ ወይም ዘመዱ ተጠቃሚ የሆነበት ወይም ሊሆንበት የሚችል የባለአደራ ተቋም ወይም
   ii. ባለ አደራ ተቋም እና የዚሁ ባለአደራ ተቋምተጠቃሚ የሆነ ወይም ሊሆን የሚችል ሰው፣
   iii. የሽርክና ማኅበር የጋራ ልማት ማኅበር የሕግ የሰውነት መብት ያላገኘ ድርጅት ወይም የግል ኩባኒያ እና
   ሀ/ የነዚህ አባል የሆነ ማንኛውም ሰው፣
   ለ/ እንደሁኔታው የሽርክና ማህበር፣ የጋራ ልማት ማህበር ወይም በሕግ የሰውነት መብት ያላገኘ ድርጅት ወይም የግል ኩባንያ አባል የሆነና ማናቸውም በዚህ አንቀጽ ግንኙነት ያላቸው ሰዎች በሚል በተተረጎመው የሚሸፈን ሌላ ሰው፣
   iv. ዝግ ከሆነ ኮርፖሬሽን በስተቀር በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው ድርጅት እና፣
   ሀ/ በሕግ የሰውነት መብት ከተሰጠው ድርጅት በስተቀር ማንኛውም ሰው ወይም ይህ ሰው እና በዚህ ትርጉም መሠረት ከዚህ ሰው ጋር ግንኙነት ያላቸው ሰዎች፣
   (i) በአንድ ኩባንያ ውስጥ ያለው ድምፅ የመስጠት መብት
   (ii) የአንድን ኩባንያ ካፒታል ወይም ትርፍ የመከፋፈል መብት በቀጥታ ወይም በአንድ ወይም ከአንድ በላይ በሆኑ ኩባንያዎች መካከል ባለአገናኝ ኩባንያ፣ የሽርክና ማኅበር ወይም ባለአደራ ተቋም አማካኝነት፣ 10 ፐርሰንት /አሥር በመቶ/ እና ከዚያ በላይ የያዙ በሚሆንበት ጊዜ፣
   ለ/ በተራ ፊደል /ሀ/ በመጀመሪያ የተጠቀሰው ሰው ወይም ይህ ሰው እና በዚህ ትርጉም መሠረት ከዚህ ሰው ጋር ግንኙነት ያለው ሰው በሕግ የሰውነት መብት በተሰጠው ኩባንያ ውስጥ፣
   (i) በኩባንያው ውስጥ ያለውን ድምፅ የመስጠት መብት፣

www.chilot.me

ለ/ በተራ ፊደል /ሀ/ በመጀመሪያ የተጠቀሰው ሰው ወይም ይሀ ሰው እና በዚህ ትርጉም መሠረት ከዚህ ሰው ጋር ግንኙነት ያለው ሰው በሕግ የሰውነት መብት በተሰጠው ኩባንያ ውስጥ፣

(i) በኩባንያው ውስጥ ያለውን ድምፅ የመስጠት መብት፣

(ii) በመጀመሪያ የተጠቀሰውን ኩባንያ ካፒታል ወይም ትርፍ የመከፋፈል መብት፣ በቀጥታ ወይም በአንድ ወይም ከአንድ በላይ በሆኑ ኩባንያዎች መካከል ባለ አገናኝ ባለ አደራ ተቋም አማካኝነት 10ፐርሰንት /አሥር በመቶ/ እና ከዚያ በላይ የያዘ በሚሆንበት ጊዜ

ሐ/ ማንኛውም ሰው ይሀ ሰው እና በተራ ፊደል/ሀ/ የተመለከተው ሰው ወይም በተራ ፊደል /ለ/ የተመለከተው በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው ድርጅት በዚሀ ትርጉም መሠረት ግንኙነት ያላቸው ሰዎች ሆነው የተቆጠሩ በሚሆንበት ጊዜ፣ ወይም

መ/ ማናቸውም ሰው በዚህ ትርጉም መሠረት በተራ ፊደል /ሐ/ ከተመለከተው ሰው ጋር ግንኙነት ያለው ሆኖ የተቆጠረ በሚሆንበት ጊዜ ፣

5. "ዝምድና" ማለት

(i) ጋብቻ እና የትዳር ጓደኛ

(ii) በቀጥታ ወደላይ ወይም ወደታች የሚቆጠሩ ዘመዶች፣ ወንድም፣ እህት፣ አጎት፣ አክስት፣ የአክስት ወይም የአጎት ልጅ፣ የእንጀራ አባት፣ የእንጀራ እናት፣ የእንጀራ ልጅ፣ የጋብቻ፣ ወይም የትዳር ጓደኛው የጉዲፈቻ ልጅ እና የጉዲፈቻ ልጅን በተመለከተ የጉዲፈቻ/አሳዳጊዎች፣

ወይም

(iii) በንዑስ አንቀፅ ii የተመለከተው ማንኛውም ሰው የትዳር ጓደኛ እና ለዚህ ትርጉም አፈፃፀም ማንኛውም የጉዲፈቻ ልጅ ከጉዲፈቻ አሳዳጊው ጋር የመጀመሪያ ደረጃ ዝምድና እንዳለው ይቆጠራል

6. "የንግድ ሥራ" ወይም "ንግድ" ማለት በማናቸውም ሰው አማካኝነት ለትርፍ የሚከናወን የኢንዱስትሪ፣ የንግድ፣ የሙያ ወይም የማልቃ ገብ ሥራ እንቅስቃሴ ወይም በኢትዮጵያ የንግድ ሕግ እንደ ንግድ ሥራ ዕውቅና የተሰጠው ማናቸውም ሌላ እንቅስቃሴ ነው

7. ግብር ከፋይ" ማለት በዚህ አዋጅ መሠረት ግብር የመክፈል ግዴታ ያለበት ማንኛውም ሰው ነው፣

8. "ግብር ተገቦ ገቢ የማድረግ ኃላፊነት የተጣለበት ሰው" ማለት ማንኛውም በዚሀ አዋጅ መሠረት ግብር ሰብስቦ ገቢ የማድረግ ኃላፊነት ያለበት ሰው ነው

9. "በቋሚነት የሚሠራ ድርጅት" ማለት አንድ ሰው የንግድ ሥራውን በሙሉ ወይም በከፊል የሚያከናውንበት ቋሚ የንግድ ሥራ ቦታ ነው። የሚከተሉት በተለይ በቋሚነት የሚሠሩ የንግድ ድርጅት በመባል ይታወቃሉ።

ሀ/ የንግድ ሥራው የአስተዳደር ማዕከል፣ ቅርንጫፍ፣ ፋብሪካ፣ የቴክኒክ ሥራዎች የሚከናወኑበት ሥፍራ፣ ለዚህ አዋጅ አግባብነት እስካለው ድረስ ማናቸውም ሌላ የተፈጥሮ ሀብቶች ጥቅም ላይ በሚውሉበት ሁኔታ የሚዘጋጁበት ሥፍራ ሕንፃ የሚገነባበት ቦታ ወይም የግንባታ ወይም የመገጣጠም ሥራ የሚከናወንበት ሥፍራ፣

ለ/ አንድ ሰው በቋሚነት የሚሠራ ድርጅት የለውም የሚባለው ከዚሀ በታች የተመለከቱትን ብቻ የሚያከናውን ከሆነ ነው፣

(i) ድርጅቱን የራሱ የሆኑትን ዕቃዎች ሸቀጦች ለማከማቸት ወይም በናሙናነት ለማሳየት ብቻ የሚጠቀምበት ሲሆን፣

(ii) ራሱ የሆነውን የዕቃ ወይም ሸቀጥ ክምችት የሚይዘው በመጋዘን ለማስቀመጥ ወይም በናሙናነት ለማሳየት ብቻ ሲሆን፣

(iii) የራሱ የሆነውን የዕቃ ወይም የሸቀጥ ክምችት የያዘው በሌላ ሰው በማምረት ሂደት ውስጥ ጥቅም ላይ እንዲውል ለማድረግ ከሆነ፣

(iv) የተወሰነ ሥፍራ ያለውን የንግድ ሥራ ቦታውን የሚጠቀምበት ለንግድ ሥራው የሚውሉ ዕቃዎችን ወይም ሸቀጦችን ለመግዛ ወይም መረጃዎችን ለማሰባሰቢያ ብቻ የሆነ እንደሆነ፣

(v) የተወሰነ ሥፍራ ያለውን የንግድ ሥራ ቦታውን የሚጠቀምበት ለንግድሥራው የሚጠቅሙ ዝግጅቶችን ወይም ለዚሁ ሥራ ብቻ የሚያግዙ ተግባሮችን ለማከናወን ከሆነ ነው፣

ሐ/ ከዚህ በላይ በተራ ፊደል /ሀ/ እና /ለ/ የተነገረው ቢኖርም ወኪል ከዚህ በታች በፊደል /ሠ/ የተመለከተው ተፈፃሚ የሚሆንበትን ራሱን ችሉ የሚሠራን ወኪል ሳይጨምር አንድን ሰው ወክሎ የሚሠራ ከሆነ ወይም በወከለው ሰው ስም ውል የመፈፀም ሥልጣን ያለውና ይህንን ሥልጣኑን አዘውትሮ የሚጠቀምበት ከሆነ፣ ወካዩ ወኪሉ እርሱን ወክሎ የሥራ እንቅስቃሴውን በሚያከናውንበት ቦታ በቋሚነት የሚሰራ ድርጅት እንዳለው ይቆጠራል። ሆኖም ወኪሉ ሥራውን የሚያከናውንበት የተወሰነ ሥፍራ ያለው ቢሆንም በቋሚነት እንደሚሠራ ድርጅት በማያስቆጥሩት ከዚሀ በላይ በፊደል/ለ/ በተዘረዘሩት የሥራ እንቅስቃሴዎች የተወሰነ ከሆነ፣ በተወሰነ ሥፍራ ያለው የሥራ እንቅስቃሴ በክልሉ በቋሚነት የሚሰራ የንግድ ድርጅት አያሰኘውም፣

መ/ ማንኛውም ሰው በደላላ በጠቅላላ የኮሚሽን ወኪል ወይም ራሱን ችሎ በሚሰራ በማናቸውም ሌላ ወኪል አማካኝነት የንግድ ሥራ እንቅስቃሴን በማከናወኑ ብቻ እንደዚህ ያሉት ወኪሎች የንግድ ሥራ እንቅስቃሴውን የሚያከናውኑት መደበኛ የንግድ ሥራቸውን በሚያከናውኑበት ወቅት ካልሆነ በስተቀር በቋሚነት የሚሠራ ድርጅት እንዳለው አይቆጠርም፣

ሠ/ አንድ ኩባንያ ሌላውን ኩባንያ በመቆጣጠሩ ወይም በሌላ ኩባንያ ቁጥጥር ሥር የሚሠራ በመሆኑ ምክንያት ብቻ አንዱ የሌላው በቋሚነት የሚሠራ ድርጅት እንደሆነ ተደርጎ አይወሰድም።

10. "ገቢ" ማለት ማናቸውም የኢኮኖሚ ጥቅም ሲሆን በመደበኛነት የተገኘ ባይሆንም ከማናቸውም ምንጭ በጥሬገንዘብ ወይም በዓይነት በማናቸውም መልክ ለግብር ከፋዩ የተከፈለው በስሙ የተያዘለትን ወይም የተቀበለውን ጥቅም ሁሉ ይጨምራል፣

11. "ግብር የሚከፈልበት ገቢ" ማለት በዚህ አዋጅና በአዋጁ መሠረት በሚወጡት ደንቦች መሠረት ማናቸውም ወጪ እና ሌሎች ተቀናሽ ሂሳቦች ከተቀነሱ በኋላ የሚቀረው የገቢ መጠን ነው፣

12. "ተቀጣሪ" ማለት የተወሰነ አገልግሎት ለመስጠት በውል የሚቀጠርን ሰው ሳይጨምር በቀጣሪው ቁጥጥር እና በሚሰጠው መመሪያ መሠረት በቋሚነት ወይም በጊዜያዊነት ተቀጥሮ አገልግሎት የሚሰጥ ግለሰብ ነው፣

ሀ/ "ባለ ሙያ ያልሆነ ተቀጣሪ" ማለት መደበኛ የሙያ ሥልጠና ያልወሰደ ልዩ ሙያ በሚጠይቁ ማሽኖችና መሣሪያዎች የማይጠቀም በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ በጠቅላላው ከ30 ቀናት ለማይበልጥ ጊዜ የተቀጠረ ግለሰብ ነው፣

ለ/ "የተወሰነ አገልግሎት ለመስጠት በውል የሚቀጠር ሰው" ማለት ሥራውን በራሱ የመምራትና የመቆጣጠር በቂ ሥልጣን በሚሰጠው ውል መሠረት ሥራውን የሚያከናውን ግለሰብ ነው።

13. "የግብር አስገቢ ባለሥልጣን" ማለት በሐረሪ ህዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የፋይናንስ ቢሮ እና እነደአስፈላጊነታቸው የተቋቋሙ የቢሮው ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ናቸው።

14. ፋይናንስ ቢሮ እና "ቢሮ ሀላፊ" ማለት የሐረሪ ሕዝብ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ፋይናንስ ቢሮ እና የቢሮው ሃላፊ ነው።

15. መስተዳድር ምክር ቤት " ማለት የሐረሪ ህዝብ ብሔራዊ ክልል መስተዳድር ም/ቤት ነው።

16. "የበጀት ዓመት" ማለት የኢትዮጵያ መንግሥት የበጀት ዓመት ነው፣

17. "የደረጃ'ሀ' ግብር ከፋይ "የደረጃ'ለ' ግብር ከፋይ" እና "የደረጃ 'ሐ' ግብር ከፋይ" በዚሀ አዋጅ መሠረት በሚወጣ ደንብ የተሰጣቸውን ትረጉም ይይዛሉ።

18. "ክ/ ል" ማለት በኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ሕገ-መንግሥት አንቀጽ47 ንዑስ አንቀፅ (1) ተ.ቁ9 ላይ የተመለከተው የሐረሪ ህዝብ ክልል ነው።

19. ሥራ አስፈፃሚ ማለት በክልሉ ህገ መንግሥት አንቀጽ31 መሠረት የተቋቋመው የሥራ አስፈፃሚ አካል ነው።

20. የግብር ይግባኝ ጉባኤ ማለት በዚሀ አዋጅ አንቀጽ 112 መሠረት የተቋቋመው የይግባኝ ጉባኤ ነው።

www.chilot.me

## 3. የተፈፃሚነት ወሰን

1. ይህ አዋጅ በገቢ ግብር አዋጅ 286 /94 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በክልሉ ነዋሪ የሆኑ ሰዎች በክልሉ ውስጥም ሆነ ከክልሉ ውጪ ባገኙት ገቢ ላይ ተፈፃሚ ይሆናል።
2. በክልሉ ነዋሪ ያልሆኑ ሰዎችን በተመለከተ አዋጁ ተፈፃሚ የሚሆነው በክልሉ ውስጥ ባገኙት ገቢ ላይ ብቻ ይሆናል።

## 4. ግብር የመክፈል ግዴታ

ማንኛውም በዚህ ሕግ የሚሸፈን ገቢ ያገኘ ሰው በዚህ አዋጅ በተደነገገው መሠረት ግብር የመክፈል ግዴታ አለበት።

## 5. ነዋሪ

1/ ማንኛውም ግለሰብ በክልሉ ነዋሪ ነው የሚባለው:

ሀ/ በክልሉ ውስጥ ቋሚ የመኖሪያ አድራሻ ያለው

ለ/ በክልሉ ውስጥ የሚያዘወትረው ማረፊያ ቦታ ያለው እና/ ወይም

ሐ/ የኢትዮጵያ ዜግነት ያለው እና ኢትዮጵያ ውጭ ከመንሱላር፣ በዲፕሎማቲክ ወይም በተመሣሣይ ሥራ ተመድቦ የሚሰራ ሲሆን

2/ በአሥራ ሁለት ወራት ጊዜ ውስጥ በክልሉ ውስጥ ሳያቋርጥ ወይም በመመላለስ ከ183 ቀናት በላይ የኖረ ግለሰብ ለዚያው የታክስ ዘመን በክልሉ ውስጥ ነዋሪ እንደሆነ ይቆጠራል።

3/ ድርጅት በክልሉ ነዋሪ ነው የሚባለው፣

ሀ/ ዋና ጽ/ቤቱ በክልሉ ውስጥ ከሆነ፣

ለ/ ለውጥ የሚያስከትል ውሣኔ ለመስጠት የሚችል የአመራር አካል በክልሉ ውስጥ ያለው ከሆነ እና/ወይም

ሐ/ እንደ አግባብነቱ በንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ወይም በየክልሉ የንግድ ቢሮዎች የንግድ መዝገብ ላይ የተመዘገበ ከሆነ፣

4/ "ነዋሪ የሆነ ሰው" በክልሉ ነዋሪ ያልሆነ ሰው ንብረት የሆነውን በቋሚነት የሚሠራ ድርጅት ይጨምራል።

## 6. የገቢ ምንጭ

በዚህ አዋጅ መሠረት ግብር የሚከፈልበት ገቢ በእነዚህ ሳይወሰን ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ይጨምራል፣

ሀ/ ከቅጥር የሚገኝ ገቢ ፣

ለ/ ከንግድ ሥራ እንቅስቃሴ የሚገኝ ገቢ

ሐ/ የማዝናናት ሥራ የሚሠራ መዚቀኛ ወይም ስፖርተኛ በግል ካከናወነው ሥራ የሚያገኘው ገቢ፣

መ/ ነዋሪነቱ በክልሉ ውስጥ ያልሆነ ሰው በቋሚ የንግድ ሥራ ድርጅት አማካኝነት ከሚያከናውነው ንግድ ሥራ የሚያገኘው ገቢ፣

ሠ/ በክልሉ ውስጥ ከሚገኙ ቋሚ የንግድ ሥራ ድርጅት ተንቀሳቃሽ ንብረት የሚገኝ ገቢ፣

ረ/ ከማይንቀሳቀሱ ንብረቶች እና ከተቀፅላዎቻቸው የተገኘ ገቢ ከቁም ከብት ከግብርና እና ከደን የሚገኝ ገቢ ከማይንቀሳቀሱ ንብረቶች አላባ እና ማናቸውም ሌላ መብት የሚገኝ ገቢ እነዚህ ንብረቶች በክልሉ ውስጥ የሚገኙ እስከሆነ ድረስ፣

ሰ/ በፊደል /ሠ/ የተመለከቱትን ንብረቶች በመሸጥ የሚገኝ ገቢ፣

ሸ/ ነዋሪነቱ በክልሉ የሆነ ኩባንያ የሚያከፋፍለው የአክሲዮን ድርሻ፣

ቀ/ ነዋሪነቱ በክልሉ የሆነ የተመዘገበ የሽርክና ማኅበር የሚያከፋፍለው የትርፍ ድርሻ፣

በ/ በፌደራልና በክልል መንግሥታት ወይም ከከተማ መስተዳደሮች ወይም በኢትዮጵያ ነዋሪ የሆነ ሰው ወይም በኢትዮጵያ ውስጥ ነዋሪ ባይሆንም፣ በኢትዮጵያ ውስጥ ባለው ቋሚ የንግድ ሥራ ድርጅት የተከፈለ ወለድ

ተ/ የራስ በሆነ ነገር ሌላ ሰው እንዲጠቀምበት የተሰጠ ፈቃድ ክፍያ /በሊዝ መብት መጠቀምን ጨምሮ /እና በኢትዮጵያ ውስጥ ነዋሪ በሆነ ሰው ወይም በክልሉ ውስጥ ነዋሪ ባይሆንም በክልሉ ውስጥ ባለው ቋሚ የንግድ ሥራ የተከፈለ የፈጠራ መብትን በማከራየት የሚገኝ ገቢ ፣

## 7. በውጭ አገር የተከፈለን ግብር ስለማካካስ

1. በክልሉ ውስጥ ነዋሪ የሆነ ሰው በአንድ የግብር ዘመን ውስጥ ምንጩ ከኢትዮጵያ ውጪ የሆነ ገቢ ያገኘ እንደሆነ፣ በዚህ ገቢ ላይ በውጭ አገር መከፈል በሚገባው ግብር መጠን ነዋሪው በክልሉ ውስጥ መክፈል ከሚገባው ግብር ላይ ይቀነስለታል።
2. በውጭ አገር የተከፈለው ግብር እንደግብር ውሣኔ ማስታወቂያ ከተከፋይ ሂሳብ ግብር ተቀናሽ መደረጉን በሚያረጋግጥ የምስክር ወረቀቱ ወይም በግብር ባለሥልጣኑ ዘንድ ተቀባይነት ባለው ሌላ ተገቢ ማስረጃ መረጋገጥ አለበት።
3. ሆኖም ከዚህ በላይ በንዑስ አንቀጽ/1/ መሠረት የሚቀነሰው ግብር በክልሉ ውስጥ መክፈል ካለበት ግብር ሊበልጥ አይችልም።
4. በሠንጠረዥ'ሐ' ገቢ ላይ የሚከፈለውን ግብር መክፈል ያለበትን ግብር ከፋይ በተመለከተ በንዑስ አንቀጽ/1/ መሠረት የሚደረገው ማናቸውም ተቀናሽ ግብር ይህ ቅናሽ ባይኖር ኖሮ በክልሉ ውስጥ ሊከፈል የሚገባው ግብር መጠን የሚወሰን ሆኖ ስሌቱ የሚከናወነው በዚህ አዋጅ አንቀጽ26 የተመለከተው /ኪሣራን ማሸጋገር/ ከእያንዳንዱ አገር የተገኘውን ትርፍ እና ኪሣራ በተናጠል እንደሚመለከት ተደርጎ ነው።
5. በዚህ አንቀጽ የተፈቀደው ተቀናሽ ግብር ገቢ ወይም ትርፍ የተገኘበትን እያንዳንዱን አገር በሚመለከት በተናጠል መሰላት ይኖርበታል።

## 8. የግብር ዓይነቶች

ይህ አዋጅ በሚከተሰው ዓይነት በተመደቡ አራት ሠንጠረዦች ግብር እንዲከፈል ይደነግጋል፣

1. ሠንጠረዥ "ሀ" ከመቀጠር የሚገኝ ገቢ
2. ሠንጠረዥ "ለ" ከቤት ኪራይ የሚገኝ ገቢ
3. ሠንጠረዥ "ሐ" የክልል ምክር ቤት በሚያወጣው የገጠር መሬት መጠቀሚያ ክፍያና የእርሻ ሥራ ገቢ ግብር አዋጅ ሥር የተመደበ ካልሆነ በስተቀር በአንቀጽ 2/6/ ከተገለፁት የንግድ ሥራዎች የሚገኝ ገቢ:
4. ሠንጠረዥ "መ" ሌሎች ገቢዎች የሚከተሉትን ጨምሮ:

ሀ/ የፈጠራ መብትን በማከራየት የሚገኝ ገቢ፣

ለ/ ከኢትዮጵያ ውጭ ከሚሰጥ አገልግሎት የሚገኝ ገቢ፣

ሐ/ ከአክሲዮን ድርሻ፣

መ/ ቋሚ ባልሆነ ሁኔታ ከንብረት ኪራይ የሚገኝ ገቢ፣

ሠ/ በወለድ ገቢ፣

ረ/ ከንግድ ሥራ ጋር ካልተያያዘ የካፒታል ዋጋ እድገት ትርፍ

## 9. በውጭ ምንዛሪ የሚደረግ ግብይት

በወጭ ምንዛሪ በሚደረግ ግብይት የተገኘ ትርፍ ወይም የደረሰ ኪሣራ ለግብር አከፋፈል ሲባል ግብይቱ በተከናወነበት የግብር ዓመት ውስጥ እንደተገኘ ትርፍ ወይም እንደ ደረሰ ኪሣራ ሆኖ መገለጽ አለበት:

# ክፍል 2
# የሠንጠረዥ "ሀ" ገቢ
# ከመቀጠር የሚገኝ ገቢ

## 10. ግብር የሚከፈልበት ገቢ

1. ማንኛውም ሰው በመቀጠር ምክንያት በሚያገኘው ማናቸውም ገቢ ላይ ከዚህ በታች በአንቀጽ11 በተመለከተው ሠንጠረዥ "ሀ"መሠረት የገቢ ግብር ይከፍላል። በመቀጠር የሚገኝ የመጀመሪያው ብር 150 /አንድ መቶ አምሳ ብር/ የገቢ ግብር ከሚከፈልበት ገቢ ውስጥ አይካተትም፣
2. ማንኛውም ቀጣሪ ለተቀጣሪው ከሚከፍለው ከእያንዳንዱ ክፍያ ላይ ግብሩን መቀነስ የተቀነሰውን ግብር በየወሩ ለግብር አሰገቢው ባለሥልጣን ገቢ ማድረግ አለበት። ከዚህ በላይ ለተነገረው አፈፃፀም የነሐሴ ወርና የጳጉሜ ገቢ በአንድነት ተጠቃለው እንደ አንድ ወር ገቢ ይቆጠራል።

## 11. የግብር ማስከፈያ መጣኔ

ሠንጠረዥ "ሀ"

| ከመቀጠር የሚገኝ የወር ደመወዝ | | የሚከፈለው ግብር በመቶኛ |
|---|---|---|
| ከብር | እስከ ብር | |
| 0 | 150 | ከግብር ነፃ |
| 151 | 650 | 10 |
| 651 | 1400 | 15 |
| 1401 | 2350 | 20 |
| 2351 | 3550 | 25 |
| 3551 | 5000 | 30 |
| ከ5000 | በላይ | 35 |

www.chilot.me

## 12. ከመቀጠር የሚገኝን ገቢ ስለመወሰን

1. ከመቀጠር የሚገኝ ገቢ ከመቀጠር በጥሬ ገንዘብ ወይም በዓይነት የተገኘ ማናቸውም ክፍያ ጥቅም ሲሆን ከቀድሞ ቅጥር የተገኘን ገቢ እና ወደፊት ለመቀጠር አስቀድሞ የሚደረግ ክፍያን ይጨምራል።
2. ግብር የሚከፈልባቸው በዓይነት የሚሰጡ ጥቅሞች እና እነዚህ ጥቅሞች የሚሰሉበት ሁኔታ በክልሉ ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ በሚወጣ ደንብ ይወሰናል።
3. በደመወዝ መልክ የተገኘ ጥቅም መ/ቤቱን ወክሉ በተለያዩ ቦታዎች ለመገኘት የሚደረገውን እና ሌሎች ተመሳሳይ ወጪዎችን /በማኅበራዊ ተግባሮች እንግዳ ለማስተናገድ የወጡትን ወጪዎች ወ.ዘ.ተ/ አይጨምርም።

## 13. ከግብር ነፃ ስለማድረግ

የሚከተሉት ገቢዎች በዚህ አዋጅ መሠረት ከሚከፈል ግብር ነፃ ይሆናሉ:

ሀ/ በማንኛውም የአሥራ ሁለት /12/ ወራት ጊዜ ውስጥ ለአንድ ቀጣሪ ከአንድ/1/ወር ለበለጠ ጊዜ ያላገለገለ ማንኛውም ባለሙያ ያልሆነ ተቀጣሪ የሚያገኘው ገቢ:

ለ/ በቀጣሪዎች የሚዋጣ ከሠራተኛው የወር ደመወዝ 15 ፐርሰንት ያልበለጠ የጡረታ መዋጮ ፕሮቪደንት ፈንድ እና ማናቸውም ዓይነት የጡረታ ጥቅም:

ሐ/ ተመሳሳይ ሁኔታ ለኢትዮጵያዊያን ተፈፃሚ ሲገኝ

(I) የዲፕሎማቲክና ቆንስላዎች ወኪሉች እና

(II) በማንኛውም ኤምባሲ ሌጋሲዮን ቆንስላዎች ወይም የውጭ አገር መንግሥት ውስጥ ተቀጥረው የዚያን ሀገር ጉዳይ የሚፈፅሙና የዲፕሎማቲክ ይለፍ ፈቃድ የያዙ ወይም በዓለም አቀፍ አሠራር ወይም ልማድ መሠረት አብዛኛውን ጊዜ ከግብር ነፃ የሆኑ ሰዎች ተቀጥረው በሚሰጡዋቸው አገልግሎቶች ምክንያት የሚያገኙቸው ገቢዎች

መ/ በተለይ ከገቢ ግብር ነፃ እንዲሆን

(i) በዚህ አዋጅ በተለይ ካልተሻሻለ ወይም ካልተሰረዘ በስተቀር በኢትዮጵያ ወይም በክልሉ ውስጥ በሥራ ላይ ባሉ ሕጎች:

(ii) በዓለም ዐቀፍ ስምምነቶች ወይም

(iii) በፋይናንስ ቢሮ በፀደቀ ወይም በተደረገ ።ምምነት የተፈቀደ ገቢ

ሠ/ የክልሉ ሥራ አስፈፃሚ ለኢኮኖሚ ለማኅበራዊ ወይም ለአስተዳደር ምክንያቶች በዚህ አዋጅ ገቢ ተብሎ ዕውቅና የተሰጠውን ማናቸውንም ገቢ በደንብ ነፃ ሊያደርግ ይችላል።

ረ/ ከዚህ በታች ከተዘረዘሩት ጋር በተያያዘ ለአንድ ሰው የሚፈፀም ካሣ ወይም ስጦታ:-

i) በተቀባዩ ሰው ላይ በደረሰ የአካል ጉዳት:

ii) በሌላ ሰው ላይ በደረሰ የሞት አደጋ:

## ክፍል 3
## የሠንጠረዥ "ለ" ገቢ
## ከቤት ኪራይ የሚገኝ ገቢ

## 14. ግብር የሚከፈልበት ገቢ

በማናቸውም ሁኔታ ከተከራየ ቤት በሚገኝ ገቢ ላይ ግብር ይከፈላል።

## 15. የግብር ማስከፈያ ልክ

ከተከራዩ ቤቶች በሚገኝ ገቢ ላይ የሚከፈለው ግብር የሚወሰነው የሚመደበውና የሚከፈለው ከዚህ በታች በተመለከተው ልክ ነው:-

ሀ/ በሕግ የሰውነት መብት ከተሰጣቸው ድርጅቶች ገቢ ላይ ሲሆን ግብር ከሚከፈልበት ገቢ ላይ 30 ፐርሰንት /ሠላሳ በመቶ/ ለ/ በግለሰቦች ገቢ ላይ ሲሆን ከዚህ በታች በተመለከተው ሠንጠረዥ"ለ" መሠረት:

ሠንጠረዥ "ለ"

| ግብር የሚከፈልበት የዓመት የኪራይ ገቢ | | የሚከፈለው የገቢ ግብር በመቶኛ |
|---|---|---|
| ከብር | እስከ ብር | |
| 0 | 1,800 | ከግብር ነፃ |
| 1,801 | 7,800 | 10 |
| 7,801 | 16,800 | 15 |
| 16,801 | 28,200 | 20 |
| 28,201 | 42,600 | 25 |
| 42,601 | 60,000 | 30 |
| ከ60,000 | በላይ | 35 |
| | | |

## 16. ግብር የሚከፈልበትን ገቢ ስለመወሰን

1. በቤት ኪራይ ገቢ ላይ የሚከፈለው ግብር የሚታሰበው ከዚህ በታች በተመለከተው መሠረት ይሆናል:

ሀ/ ቤቱ ወይም ግቢው ከነዕቃው የተከራየ እንደሆነ: የዕቃው ወይም የመሣሪያው ኪራይ ከጠቅላላው ገቢ ጋር ይደመራል፣

ለ/ ተከራይቶ በማከራየት የሚገኘው ገቢ የቤቱ ባለቤት ለሆነው አከራይ ከሚከፈለው የኪራይ ዋጋ የበለጠ ከሆነ ተከራይተው የሚያከራዩ ግብር ከፋዮች ግብሩን የሚከፍሉት በሚያገኙት የገቢ ልዩነት ላይ ነው።

ሐ/ ግብር የሚከፈልበት ገቢ በሚሠላበት ጊዜ የሚከተሉት ከጠቅላላ ገቢ ላይ ተቀናሽ ይደረጋሉ:

(i) ከገቢ ግብር በስተቀር ከተከራየው ቤት ጋር በተያያዘ የተከፈለ የመሬት ግብር እና የሕንፃ ታክስ:-

(ii) መዝገብ ለማይዙ ግብር ከፋዮች ለቤቶች ለቤት ዕቃና ለመሣሪያ ማደሻ መጠገኛና ለእርጅና መተኪያ /ዲፕሪሲየሽን/ የሚሆን ከቤት ዕቃና ከመሣሪያ ከሚገኘው ጠቅላላ የኪራይ ገቢ አንድ አምስተኛው:

(iii) መዝገብ ለሚይዙ ግብር ከፋዩች ግብር ከፋዩ ወጪዎቹን በማስረጃ መረጋገጥ እስከቻለ ድረስ በዚህ አዋጅ የተመለከቱት ገደቦች እንደተጠበቁ ሆነው የኪራዩን ገቢ ለማግኘት ለኪራዩ ንግድ ሥራ የሰጠና ለመስጠት እንቅስቃሴውን ለማስቀጠል የተደረጉ ወጪዎች ተቀናሽ ይደረጋሉ። ተቀናሽ የሚደረጉት ወጪዎች በእነዚህ ሳይወሰኑ ለመሬት ሊዝ /ኪራይ/ ለቤቶች ለቤት ዕቃና ለመሣሪያ ማደሻ መጠገኛና ለእርጅና መተኪያ /ዲፕሪሲየሽን/በዚህ አዋጅ አንቀጽ 23 መሠረት እንዲሁም የባንክ ወለድ የኢንሹራንስ አረቦን የሚሆነው ወጪ በሚይዙት መዝገብ መሠረት ተቀናሽ ይደረጋሉ።

2. ተከራይ የተከራየውን ቤት መልሶ እንዲያከራይ የሚፈቅድ የቤት ባለቤት ተከራዩ ግብሩን ባይከፍል በለእርሱ ሆኖ ግብሩን የመክፈል ኃላፊነት ይኖርበታል።
3. ለኪራይ የሚሠሩ ቤቶች ተሠርተው እንዳለቁ ወይም ቤቱ እንደተከራየ ከሁለቱ በሚቀድመው ጊዜ የቤቱ ባለቤትና የሕንፃው ሥራ ተቋራጭ የቤቱ ግንባታ የተጠናቀቀ ወይም ቤቱ የተከራየ መሆኑን ከቤቱ ኪራይ በሚገኘው ገቢ ላይ የሚፈለገውን ግብር መክፈል ያለበትን ሰው /ሰዎች/ሰም አድራሻና የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር ቤቱ ለሚገኝበት ቀበሌ መስተዳድር ማስታወቅ አለባቸው። የቀበሌው መስተዳድርም በራሱ ክትትል ወይም ከዚህ በላይ በተገለፀው መሠረት የሚያገኘውን መረጃ ለሚመለከተው የግብር አስገቢ ባለሥልጣን የማስተላለፍ ግዴታ አለበት።

## ክፍል 4
## የሠንጠረዥ"ሐ" ገቢ
## የንግድ ሥራ ትርፍ ግብር

## 17. በሠንጠረዥ "ሐ" ገቢ ላይ የሚጣለው ግብር ጣሰን

ከንግድ ሥራ እንቅስቃሴ በተገኘ ግብር የሚከፈልበት ገቢ ላይ የገቢ ግብር እየተጣለ ይሰበሰባል።

## 18. ግብር የሚከፈልበት የንግድ ሥራ ገቢ

ግብር የሚከፈልበት የንግድ ሥራ ገቢ ተቀባይነት ያገኘውን የሂሳብ አያያዝ መርህ በመከተል የሚዘጋጀውን የትርፍና ኪሣራ ሂሳብ ወይም የገቢ መግለጫ እና ይህንን አዋጅ እና የግብር አስገቢው ባለሥልጣን የሚያወጣውን መመሪያ መሠረት በማድረግ በእያንዳንዱ የግብር ዘመን ይወሰናል።

## 19. የግብር መጠን

1. በሕግ የሰውነት መብት የተሰጣቸው ድርጅቶች ግብር ከሚከፈልበ ገቢ ላይ 30 ፐርሰንት/ ሠላሳ በመቶ/ ግብር ይከፍላሉ። •

2. በንግድ ሥራ ላይ የተሠማሩ ሌሎች ግብር ከፋዮች በሚያገኙት ግብር የሚከፈልበት የንግድ ሥራ ገቢ ላይ ከዚህ በታች በተመለከተው ሠንጠረዥ "ሐ" መሠረት ግብር ይከፍላሉ።

ሠንጠረዥ "ሐ"

| ግብር የሚከፈልበት የዓመትየንግድ ሥራ ገቢ | | የሚከፈለው የገቢ ግብር በመቶኛ |
|---|---|---|
| ከብር | እስከ ብር | |
| 0 | 1,800 | ከግብር ነፃ |
| 1,801 | 7,800 | 10 |
| 7,801 | 16,800 | 15 |
| 16,801 | 28,200 | 20 |
| 28,201 | 42,600 | 25 |
| 42,601 | 60,000 | 30 |
| ከ60,000 | በላይ | 35 |

## 20. *ተቀናሽ ወጪዎች*

በክልሉ ውስጥ ግብር የሚከፈልበትን ከንግድ ሥራ የሚገኝ ገቢ በሚመለከት በዚህ አዋጅ የተመለከቱት ገደቦች እንደተጠበቁ ሆነው ግብር ከፋዩ ወጪዎችን ማረጋገጥ እስከቻለ ድረስ ለንግድ ሥራው ገቢ ለማግኘት ለንግድ ሥራው ዋስትና ለመስጠትና እንቅስቃሴውን ለማስቀጠል የተደረጉ ወጪዎች ተቀናሽ ይደረጋሉ።

## 21. *ተቀናሽ የማይደረጉ ወጪዎች*

1. የሚከተሉት ወጪዎች ተቀናሽ አይደረጉም፣
   - ሀ/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 23 መሠረት የእርጅና ቅናሽ የሚደረግለትን የንግድ ሥራውን ሀብት ለማግኘት ለማሻሻል ለማደስ እና መልሶ ለመገንባት የተደረገ ወጪ፣
   - ለ/ የኩባንያውን አክሲዮን ወይም ለተመዘገበ የሽርክና ማኅበር መሠረት የሆነውን ካፒታል ማሳደግ፣
   - ሐ/ ከተቀማጩ የወር ደመወዝ 15 ፐርሰንት /አሥራ አምስት በመቶ/ በላይ የጡረታ መዋጮ ወይም የፕሮቪደንት ፈንድ፣
   - መ/ ባለአክስዮኖች እንዲያውቁት የተደረገ የአክሲዮን ድርሻ እና የተከፈለ የትርፍ ድርሻ፣
   - ሠ/ በብሔራዊ የባንክና በንግድ ባንኮች መካከል በተደረገ ብድር ከሚታሰብ የወለድ መጣኔ 1,2ፐርሰንት /ሁለት በመቶ/ በላይ የሆነ የወለድ ወጪ፣
   - ረ/ የመድን ዋስትና ሽፋን ያለው ጉዳት፣
   - ሰ/ በጥፋት ምክንያት የተከፈለ የጉዳት ካሣ እና መቀጫ፣
   - ሸ/ በዚህ አዋጅ ከተፈቀደው ወጪ እዲስ መጠባበቂያ ሂሣብ ማቋቋም ወይም ከተፈቀደው መጠን በላይ የመጠባበቂያውን መጠን ማሳደግ ወይም ለተለየ ዓላማ የሚውል ገንዘብ ማስቀመጥ፣
   - ቀ/ በሠንጠረዥ "ሐ" ገቢ ላይ የተከፈለ ግብር ወይም ተመላሽ የሚደረግ የተጨማሪ እሴት ታክስ፣
   - በ/ የንግድ ድርጅቱን ወክሎ በተለያዩ ቦታዎች ለመገኘት የሚደረግ ወጪ ሠራተኛው ደመወዝ ከ10 ፐርሰንት /አሥር በመቶ/የሚበልጥ ከሆነ፣
   - ተ/ የግል ፍጆታ ወጪዎች፣
   - ቸ/ በዚህ አዋጅ ወይም ይህንን አዋጅ መሠረት በማድረግ በሚወጣ ደንብ ከተደረገ ገደብ በላይ የተደረገ ወጪ፣
   - ነ/ የመዝናኛ ወጪዎች፣
   - ኘ/ ስጦታ ወይም ዕርዳታ፣
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ/1/ኘ/ የተመለከተው ቢኖርም በክልሉ ሥራ አስፈፃሚ ሕዝብ ጥቅም የሚውል ዕርዳታ ወይም ስጦታ ተቀናሽ እንዲሆን ሊፈቅድ ይችላል።
3. ባለ አክሲዮኖች ለኩባንያው የሰጡት ብድር እና የቅድሚያ ክፍያ በአንድ የታክስ ዘመን ውስጥ በአማካኝ ከኩባንያው አክሲዮን ካፒታል ዋጋ እራት ዕጥፍ በላይ ከሆነ ብድሩ እና ለቅድሚያ ክፍያው የሚከፈለው ወለድተቀናሽ አይደረግም። ከዚህ በላይ የተነገረው በባንክ እና በመድን ኩባንያው ላይ ተፈፃሚ አይሆንም።
4. በኩባንያ ውጭ ያሉ ሌሎች ድርጅቶችን በሚመለከት ከዚህ በላይ አክሲዮን ካፒታል የሚለው ሐረግ መሠረታዊ ካፒታል በሚል የተተካ በሚሆንበት ጊዜ የንዑስ አንቀጽ /3/ ድንጋጌ ተፈፃሚ ይሆናል።

## 22. *በመጋዘን የሚገኝ የንግድ ዕቃ*

1. ግብር ከፋዩ ያገኘው ገቢ በሚሠላበት ጊዜ በግብር ዘመኑ ውስጥ ለተሸጠ በመጋዘን ለሚገኝ የንግድ ዕቃ የተደረገው ወጪ ተቀናሽ ይደረጋል።
2. በግብር ዓመት ውስጥ ለተሸጡ በመጋዘን የሚገኙ የንግድ ዓቃዎች የተደረገ ወጪ የሚሰላው በአማካኝ የወጪ ስሌት ዘዴ ማለትም በመጋዘን የሚገኘው የእየንዳንዱ ዕቃ ዋጋ በአማካኝ ወጪ እንዲሠላ በሚያስችለው እጠቃላይ ተቀባይነት ባገኘው የሂሳብ አያያዝ ስሌት መሠረት ነው።
3. ለዚህ አንቀጽ አፈፃፀም "በመጋዘን የሚገኝ የንግድ ዕቃ" ማለት በምርት ሂደት ውስጥ ጥቅም ላይ የዋለ ወይም የምርት አካል እንዲሆን የተደረገ የንግድ ሥራ ሀብት ወይም ለሽያጭ የተያዘ ማናቸውም ዕቃ ነው።

## 23. *የእርጅና ቅናሽ*

1. ግብር የሚከፈልበትን የንግድ ሥራ ገቢ ለመወሰን የንግድ ሥራው ሀብት ባለቤት ለንግድ ሥራው ሀብቶች የእርጅና ቅናሽ ማድረግ ይችላል።
2. ሥነ ጥበብ የጥንት ዕቃዎች ከከበሩ ማዕድናት የተሠሩ ጌጣጌጦች እና ሌሎች ዋጋቸው የማይቀንስ እና ጊዜ የማያልፍባቸው የንግድ ሥራ ሀብቶችን በሚመለከት የእርጅና ቅናሽ አይፈቀድም።
3. የሕንፃ ወይም የሌሎች ግንባታዎች ባለቤት ለመሆን ሕንፃ ወይም ሌሎች ግንባታዎችን ለማሻሻል ለማደስ እና መልሶ ለመገንባት የተደረጉ ወጪዎች ለእያንዳንዱ በተናጠል በቀጥተኛ የእርጅና አቀናነስ ዘዴ መሠረት 5 ፐርሰንት የእርጅና ቅናሽ ይደረጋል።
4. ግዙፋዊ ህልዎት የሌላቸው ሀብቶች ባለቤት ለመሆን ወይም እነዚህን ሀብቶች ለማሻሻል፣ ለማደስ እና መልሶ ለመገንባት የተደረጉ ወጪዎች ለእያንዳንዱ በተናጠል በቀጥተኛ የእርጅና አቀናነስ ዘዴ ምሠረት 10ፐርሰነት የእርጅና ቅናሽ ይደረጋል።
5. ከዚህ በታች በሁለት ምድብ የተመለከቱት የንግድ ሥራ ሀብቶች በጥቅል የእርጅና አቀናነስ ሥርዓት መሠረት ቀጥሎ በተመለከተው መጣኔ የእርጅና ቅናሽ ይደረግላቸዋል፣
   - ሀ/ ኮምፒውተሮች የመረጃ ሥርዓቶች የሶፍትዌር ውጤቶች እና የመረጃ ማከማቻ መሣሪያዎች 25 ፐርሰንት
   - ለ/ ሌሎች ማናቸውም የንግድ ሥራ ሀብቶች...20 ፐርሰንት
6. ከዚህ በላይ በንዑስ አንቀጽ /5/ ለተመለከተው ለእያንዳንዱ ምድብ የተወሰነው የእርጅና. ቅናሽ መጣኔ በየምድቡ ለእርጅናው ቅናሽ መሠረት በሆነው ሂሳብ ላይ ተፈፃሚ ይደረጋል።
7. የእርጅናው ቅናሽ መሠረት በታክሱ ዘመን መጀመሪያ የመነሻ ሂሳብ ሚዛን ላይ የተመዘገበው የመዝገብ ዋጋ ሲሆን በዚህ ሂሳብ ላይ:
   - ሀ/ በየምድቡ ያሉ ሀብቶች ባለቤት ለመሆን ወይም አዳዲስ ሀብቶችን ለመመሥረት ወይም እነዚህን ሀብቶች ለማሻሻል፣ ለማደስ፣ መልሶ ለመገንባት በታክስ ዘመኑ የተደረገ ወጪ ተወምሮ፣
   - ለ/ በታክስ ዘመኑ የተወገዱ ዕቃዎች የሽያጭዋጋ በተፈጥሮ አደጋ ለወደሙ ወይም በሌላ ከቁጥጥር ውጪ በሆነ ምክንያት ለውጥ ላጋጠማቸው ሀብቶች የተገኘ ካሣ ተቀንሶ ይሆናል።
8. የእርጅናው ቅናሽ መሠረት ከዜሮ በታች ከሆነ ከዜሮ በታች የሆነው መጠን ግብር ከሚከፈልበት ትርፍ ላይ ተደምሮ የእርጅናው ቅናሽ መሠረት ዜሮ ይደረጋል።
9. የእርጅናው ቅናሽ መሠረት ከብር 1,000 የማይበልጥ በሚሆንበት ጊዜ ይህ መጠን በአንድ ጊዜ ከንግድ ሥራው ሂሳብ ላይ ተቀናሽ ይደረጋል።
10. የንግድ ሥራው ሀብት እንደገና እንዲገመት ተደርጎ ተጨማሪ እሴት የተገኘ እንደሆነ ተጨማሪው እሴት የእርጅና ቅናሽ መሠረት ሆኖ አይወሰድም።
11. ግብር የሚከፈልበትን ከንግድ ሥራው ንብረት የተደረገ የጥገና እና የማሻሻያ ትክክለኛ ወጪ እንዲቀነስ ይደረጋል። ሆኖም በዚህ ዓይነት የሚቀነሰው ወጪ መጠን ለእያንዳንዱ የንግድ ሥራ ንብረት የእርጅና ቅናሽ መሠረት ከሆነው ሂሣብ 20 ፐርሰንት ሊበልጥ አይችልም። ከ20 ፐርሰንት በላይ የሆነውን ትክክለኛ ወጪ የእርጅናው ቅናሽ መሠረት ከፍ ለማድረግ ይውላል።

www.chilot.me

## 24. የንግድ ሥራ ንብረት ዝውውር

1. በንግድ ሥራ እንቅስቃሴ ውስጥ ጥቅም ላይ የዋለ ንብረት የተሸጠ፣ የተለወጠ ወይም በማናቸውም ሌላ መንገድ የተላለፈ እንደሆነ፣ በእንዲህ ዐይነቱ ዝውውር የተገኘ ጥቅም ወይም ኪሣራ ከገቢ ግብር ውስጥ የሚገባ ይሆናል፡፡
2. እንደገና የመደራጀት ሂደት ተፈፃሚ የሚሆንባቸው ኩባንያዎች የንግድ ሥራ ንብረት በአንዱ ወደ ሌላው መተላለፍ ንብረቱ እንደተሸጠ አያስቆጥርም፡፡
3. እንደገና የመደራጀት ሂደት ተፈፃሚ የሆነበት /የሆንባቸው ኩባንያ/ ኩባንያዎች የንግድ ሥራ ንብረት እሴት እንደገና የመደራጀቱ ሂደት ከመፈፀሙ በፊት ከነበረው ከንብረቱ እሴት ጋር አንድ ይሆናል፡፡ በመሆኑም ቀሪው የእርጅና ቅናሽ ሂሳብ እንደጋና በመደራጀት ወደ የተፈጠረው ኩባንያ ይዛወራል፡፡
4. "እንደገና መደራጀት" ማለት
   ሀ/ ነዋሪነታቸው በክልሉ የሆነ ሁለት ወይም ከሁለት በላይ የሆኑ ኩባንያዎች መዋሀድ
   ለ/ በኢትዮጵያ ነዋሪ የሆነውን ኩባንያ ድምፅ የሚያሰጥ አክሲዮን ዋጋ /50ፐርሰንት/ ሃምሳ በመቶ ወይም የሌሎች ጠቅላላ አክሲዮኖችን ዋጋ ሃምሳ በመቶ እንደገና በሚደራጀው ኩባንያ አባል የሆነ ድርጅት በሚያገኘው አክሲዮን ለውጥ ብቻ የተሸጠ ወይም በማናቸውም ሌላ መንገድ ተላለፈ እንደሆነ፡
   ሐ/ እንደገና በሚደራጀው ኩባንያ ውስጥ አባል ለሆነ ኩባንያ በአክሲዮን ድርሻ ከፍያ ረገድ ልዩ መብት በማያሰጥና የድምፅ ተሳትፎ ብቻ በሚያልስገኝ አኳኋን በክልሉ ነዋሪ ከሆነ ኩባንያ ሀብት ውስጥ /50 ፐርሰንት/ ሀምሳ በመቶ ወይም ከዚያ በላይ ለሌላ በክልሉ ነዋሪ ለሆነ ኩባንያ የተሰጠ ወይም የተላለፈ እንደሆነ
   መ/ በክልሉ ነዋሪ የሆነ ኩባንያ ወደሁለት ወይም ከዚያ በላይ ወደሆኑ ኩባንያዎች መከፋፈል፡
   ሠ/ አንድ የንግድ ሥራ ድርጅት የተቀፅላዎቹን ካፒታል የድርጅቱን ካፒታል ለያዙ ሲያከፋፍል ነው፡፡ የዚህ አይነቱ እንደገና መደራጀት ማለትም ውህደት በሌላ መያዝ መተላለፍ መከፋፈል ወይም የተቀጽላዎች ካፒታል ወደያዙ መሸጋገር ዋንኛ ዓላማ የታክስ ከለላ ለማግኘት ያለመሆኑን የግብር አስገቢው ባለሥልጣን ማረጋገጥ አለበት፡፡
5. ከዚህ በላይ በንዑስ አንቀጽ (1-4) የተነገረው በአንቀጽ 23/5/ የተመለከተውን ንብረት ዝውውር በሚመለከት ተፈፃሚ አይሆንም፡፡
6. ለኪሣራ ዕውቅናን ስለመስጠት የተነገረው በአንቀጽ 2/4/ መሠረት ግንኙነት ባላቸው ሰዎች መካከል የሚደረገን የንግድ ሥራ ንብረት ዝውውር አይመለከትም፡፡

## 25. የማይሰበሰብ ዕዳ

ከዚህ በታች የተመለከቱት ሁኔታዎች ሲሟሉ ግብር የሚከፈልበት የንግድ ሥራ ገቢ በሚወሰንበት ጊዜ የማይሰበሰቡ ዕዳዎች ተቀናሽ ይደረጋሉ፡፡
ሀ/ ከማይሰበሰበው ዕዳ ጋር ተመጣጣኝ የሆነ ሂሳብ ቀደም ሲል በንግድ ሥራው ገቢነት ተይዞ ከሆነ እና፡
ለ/ ዕዳው ከግብር ከፋዩ የሂሳብ መዝገብ የተሠረዘ ከሆነ እና
ሐ/ ዕዳውን ለማስመለስ ተገቢው የሕግ እርምጃ ተወስዶ ገቢ ለማድረግ ያለመቻሉ የተረጋገጠ ከሆነ፡፡

## 26. ለፋይናንስ ድርጅቶች የተፈቀደ ልዩ መጠባበቂያ

ግብር የሚከፈልበት የፋይናንስ ድርጅቶች የንግድ ሥራ ገቢ በሚወሰንበት ጊዜ በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ በወጣ መመሪያ የተፈቀዱ ልዩ/የቴክኒክ/ መጠባበቂያዎች ተቀናሽ ይደረጋሉ፡፡ ሆኖም ግብር የሚከፈልበት የፋይናንስ ድርጅቶች የንግድ ሥራ ገቢ ከልዩ መጠባበቂያው ሂሳብ ወጪ በተደረገው መጠን ከፍ እንዲል ይደረጋል፡፡

## 27. ተቀናሽ የሚደረግ የካፒታል ተሳትፎ

1. ከዚህ በታች በንኡስ አንቀጽ /2/እና /3/ የተመለከቱት ሁኔታዎች ሲሟሉ በክልሉ ውስጥ ነዋሪ የሆነ ኩባንያ ወይም የተመዘገበ የሽርክና ማኅበር ያገኘውን ትርፍ የሌላን ኩባንያ ወይም የሽርክና ማኅበር ካፒታል ለማሳደግ ያዋለው ከሆነ ለዚህ ዓላማ የዋለው ትርፍ ግብር ከሚከፈልበት የንግድ ሥራ ገቢ ላይ ተቀናሽ ይደረጋል፡፡
2. ከዚህ በላይ በንዑስ አንቀጽ /1/የተመለከተው ተቀናሽ አክሲዮንን በሚመለከት ተፈፃሚ የሚሆነው አክሲዮን የተገዛባት ኩባንያ በኢትዮጵያ ውስጥ ነዋሪ እና በሠንጠረዥ "ሐ መሠረት ግብር የመክፈል ግዴታ ያለበት ሲሆን እና አክሲዮኑን የገዛው ኩባንያ ወይም የተመዘገበ የሽርክና ማኅበር ውስጥ በቁጥር ወይም በዋጋ ቢያንስ 25ፐርሰንት የአክሲዮን ካፒታል የያዘ ወይም በዚሁ መቶኛ መጠን ድምፅ የመስጠት መብት ያለው ከሆነ ነው፡፡
3. ከዚህ በላይ በንዑስ አንቀጽ 1 የተመለከተው ተቀናሽ የትርፍ ድርሻ በተመለከተ ተፈፃሚ የሚሆነው የካፒታል መዋጮ የተደረገበት የሽርክና ማኅበር በክልሉ ነዋሪ የሆነ እና በሠንጠረዥ "ሐ" መሠረት ግብር የመክፈል ግዴታ ያለበት ሲሆን እና የካፒታሉን መዋጮ ያደረገው ኩባንያ ወይም የተመዘገበ የሽርክና ማኅበር የሽርክና ማኅበሩ መሠረት ከሆነው ካፒታል ዋጋ ውስጥ ቢያንስ 25 ፐርሰንት የያዘ እንደሆነ ነው፡፡
4. በዚህ አንቀጽ የተፈቀደው ማበረታቻ ተፈፃሚ የሚሆንበት ዝርዝር ሁኔታ በክልሉ ምክር ቤት ደንብ ይወሰናል፡፡

## 28. ኪሣራን ስለማሸጋገር

1. በአንድ የግብር ዘመን ግብር የሚከፈልበት ገቢ በሚወሰንበት ጊዜ በዚያው የግብር ዘመን ውስጥ የታየው ኪሣራ በሚቀጥሉት ሦስት /3/ የግብር ዘመናት ከተገኘው ግብር የሚከፈልበት በመጀመሪያ ያጋጠመውን ኪሣራ በኋላ ካጋጠመው ኪሣራ አስቀድሞ በማካካስ ነው፡፡
2. በአንድ የግብር ዘመን ውስጥ የአንድ ኩባንያ የካፒታል ባለቤትነት ወይም ድምፅ የመስጠት መብት በዋጋ ወይም በቁጥር ከ25 ፐርሰንት በላይ በቀጥታ ወይም ቀጥተኛ ባልሆነ መንገድ የተለወጠ እንደሆነ ኩባንያው በዚያው የግብር ዘመንም ሆነ ቀደም ባሉ የግብር ዓመታት የደረሰበትን ኪሣራ በሚመለከት የንዑስ አንቀጽ/1/ ድንጋጌ ተፈፃሚነት ያቋርጣል፡፡
3. ማናቸውም ሰው በንግድ ሥራው እንቅስቃሴ ያጋጠመው ኪሣራ በማናቸውም ሁኔታ በሁለት የሦስት ዓመታት ጊዜ ከሚቆጠሩ 6 አመታት በላይ ሊሸጋገርና ተቀናሽ ሊሆን አይችልም፡፡

## 29. የማስተላለፊያ ዋጋ

1. በሁለት በተለያዩ ሰዎች መካከል ከሚደረገው የንግድ ወይም የፋይናንስ ግንኙነት የተለየ እንዲሆን የሚያደርግ ወይም የሚያስገድድ ሁኔታ የተፈጠረ እንደሆነ የግብሩ ባለሥልጣን ከተሳሰሩት ሰዎች መካከል የአንዱ ወይም ከአንድ በላይ የሆኑት ገቢ የዚህ ዓይነቱ ትስስር ባይኖር ኖሮ ሊያስገኝ የሚችለውን ትርፍ እንዲጨምር ሊወስን ይችላል፡፡ የግብሩ ባለሥልጣን ከዚህ በላይ በተገለፀው መሠረት የሚወስነው ከቢሮ ኃላፊው በሚሰጠው መመሪያ መሠረት ይሆናል፡፡
2. ለዚህ አንቀጽ ትክክለኛ እና ውጤታማ አፈፃፀም እንዲያመች በተሳሰሩ ሰዎች መካከል የሚደረገው ግንኙነት በሁለት በተለያዩ ሰዎች መካከል ከሚደረገው ግንኙነት የተለየ እንዳይሆን የሚያስችል እንደአስፈላጊነቱ ሁኔታዎች የተካተቱበት ስምምነት የግብሩ ባለሥልጣን የንግድ ሥራ እንቅስቃሴ ከሚያከናወኑ ሰዎች ጋር አስቀድሞ ሊያደርግ ይችላል፡፡

## 30. ከግብር ነፃ ስለማድረግ

1/ የሚከተሉት ገቢዎች በዚህ አዋጅ መሠረት ሊከፈልባቸው ከሚገባው የንግድ ሥራ ገቢ ግብር ነፃ ናቸው ፡
   ሀ/ አንድን ቴክኖሎጂ ለተወሰነ ሁኔታ እንዲስማማ በማድረግ ወይም አዲስ የፈጠራ ሀሳብ በማቅረብ እና ወጪን ለመቀነስ የሚያስችሉ አሠራሮችን ሥራ ላይ በማዋል የሚሰጥ ሽልማት፡
   ለ/ በማናቸውም መስክ የላቀ ተግባር ላከናወኑ ሰዎች የሚሰጥ ሽልማት፡
   ሐ/ በኢትዮጵያ ወይም በክልሉ ውስጥ ፀንቶ በሚሠራበት ሕግ ወይም በዓለም አቀፍ ስምምነት ወይም ፋይናንስ ቢሮ በሚያደርገው ወይም በሚፈቅደው ስምምነት መሠረት በተለይ ግብር እንዳይከፈልበት የተደረገ ገቢ፡
2/ የሚከተሉት በሥራቸው አጋጣሚ የሚያገኙት ገቢ በሠንጠረዥ "ሐ" መሠረት ከሚከፈል ግብር ነፃ ይሆናል፡፡

www.chilot.me

ሀ/ የፌደራልና እና የክልላዊ መንግሥታት እንዲሁም የከተማ መስተዳድሮች እና የመንግሥት መ/ቤቶች፣
ለ/ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ፣

## ክፍል 5
## የሠንጠረዥ "መ" ገቢ/ሌሎች ገቢዎች

### 31. የፈጠራ መብትን በማከራየት የሚገኝ ገቢ

1. በማንኛውም የፈጠራ መብትን በማከራየት የተገኘ ገቢ ላይ /አምስት በመቶ ግብር ይከፈልበታል።
2. ግብር ቀንሶ ገቢ የማድረግ ኃላፊነት የተጣለበት ሰው በዚህ አዋጅ በተወሰነው የጊዜ ገደብ ውስጥ የተጠቀሰውን ግብር ቀንሶ በመያዝ ለግብር አሰገቢው መ/ቤት የማስታወቅና የመክፈል ግዴታ አለበት።
3. ከፋዩ ነዋሪነቱ በውጭ አገር ሆኖ ተቀባዩ ነዋሪነቱ በክልሉ ውስጥ የሆነ እንደሆነ ተቀባዩ በዚህ አዋጅ በተወሰነው የጊዜ ገደብ ውስጥ የፈጠራ መብት በማከራየት ባገኘው ገቢ ላይ የሚከፈለውን ግብር ይከፍላል።
4. በዚህ ዓይነት የተከፈለው ግብር ታክስ ከዚህ እንቅስቃሴ የተገኘውን ገቢ በሚመለከት የመጨረሻ ይሆናል።
5. በዚህ አዋጅ ውስጥ "የፈጠራ መብትን በማከራየት የሚገኝ ገቢ" ማለት ተንቀሳቃሽ ፊልም እና ለሬዲዮ ወይም የቴሌቪዥን ሥርጭት የሚውል የተንቀሳቃሽ ፊልም ወይም የድምፅ ክሮችን ማናቸውም በአንድ ሰው መብት ለመጠቀም የተሰጠ ፈቃድ የንግድ ምልክት ንድፍ ወይም ሞዴል ፕላን በሚስጥር በተያዘ ፎርሙላ ወይም የአመራረት ሂደት ወይም የማናቸውንም የኢንዱስትሪ የንግድ ወይም የሣይንስ መሣሪያ ወይም በኢንዱስትሪ በንግድ ወይም በሣይንስ ከተገኘ ልምድ የተሰበሰበ መረጃን መጠቀምን ወይም የመጠቀም መብትን ወምር ማናቸውንም የሥነ-ጽሑፍ የኪነጥበብ ወይም የሣይንስ ሥራ ልዩ መብትን መጠቀምን ወይም የመጠቀም መብትን ለጥቅም በማከራየት ምክንያት የሚገኝ ማናቸውም ክፍያ ነው።

### 32. የቴክኒክ አገልግሎት በመስጠት የሚገኝ ገቢ

1. በኢትዮጵያ ወይም በክልሉ ነዋሪ ለሆኑ ሰዎች ከኢትዮጵያ ውጪ ለተሰጠ የቴክኒክ አገልግሎት የተፈፀመ ክፍያ 10 ፐርሰንት /አሥር በመቶ/ ብር ይከፈልበታል። ይሆንንም ግብር አገልግሎት የተፈፀመለት ከፋይ እየቀነሰ በማስቀረት ለግብር አሰገቢው መ/ቤት ገቢ ማድረግ አለበት።
2. "የቴክኒክ አገልግሎት" ማለት ማናቸውም የባለሙያ ምክር ወይም የቴክኖሎጂ አገልግሎት ነው።

### 33. የአክሲዮን ትርፍ ድርሻ

1. የአክሲዮን ማኅበር ካከፋፈለው የአክሲዮን ድርሻ ወይም ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኅበር ከሚያከፋፍለው ትርፍ ገቢ የሚያገኝ ማናቸውም ሰው ባገኘው ገቢ ላይ 10 ፐርሰንት /አሥር በመቶ/ ግብር ይከፍላል።
2. ከፋዩ ግብሩን ቀንሶ በማስቀረት ለግብር አሰገቢው ባለሥልጣን ገቢ ማድረግ አለበት።
3. በዚህ ዓይነት የተከፈለው ግብር ከዚህ እንቅስቃሴ የተገኘውን ገቢ በተመለከተ የመጨረሻ ታክስ ይሆናል።

### 34. ከንብረት ኪራይ የሚገኝ ገቢ

በዚህ አዋጅ አንቀጽ 17 ከተመለከተው ግብር ከሚከፈልበት የንግድ እንቅስቃሴ ጋር በማይገናኝ አኳኋን ንብረት አልፎ አልፎ በማከራየት ገቢ ያገኘ ማናቸውም ሰው በገኘው የዓመት ጠቅላላ ገቢ ላይ 15 ፐርሰንት /አሥራ አምስት በመቶ ግብር ይከፍላል። በዚህ ዓይነት የተከፈለው ግብር የመጨረሻ ይሆናል።

### 35. በተቀማጭ ገንዘብ ላይ የሚከፈል የወለድ ገቢ

1. ማናቸውም ሰው ከተቀማጭ ገንዘብ በሚያገኘው ወለድ ላይ አምስት በመቶ /5ፐርሰንት/ ግብር ይከፍላል።
2. ከፋዩ ግብሩን ቀንሶ በማስቀረት በአንቀጽ 67 በተደነገገው መሠረት ለግብር አሰገቢው ባለሥልጣን ገቢ ማድረግ አለበት።
3. በዚህ ዓይነት የተከፈለው ግብር ከወለድ የተገኘውን ገቢ በተመለከተ የመጨረሻ ግብር ይሆናል።

### 36. የተወሰኑ የካፒታል ንብረቶችን በማስተላለፍ የሚገኝ ጥቅም

1. በዚህ አንቀጽ የተዘረዘሩ ንብረቶችን በሰጦታ ወይም በሽያጭ በማስተላለፍ የሚገኘው ጥቅም ከዚህ በታች በተመለከተው የማስከፈያ ልክ ግብር የሚከፈልበት ይሆናል።
   ሀ/ ለንግድ ለፋብሪካ ለቢሮ የተያዙ ሕንፃዎች 15 ፐርሰንት /አሥራ አምስት በመቶ/፣
   ለ/ የኩባንያዎች አክሲዮን 30 ፐርሰንት /ሠላሳ በመቶ/፣
2. በግል መኖሪያነት የተያዘ ቤት በማስተላለፍ የሚገኝ ጥቅም ግብር አይከፈልበትም።
4. በዚህ አንቀጽ ግብር ከተጣለባቸው ንብረቶች የተገኘውን ጥቅም ለማስላት የሚያስችለው ዘዴ በክልሉ ሥራ አስፈፃሚ በሚወጣ ደንብ ይወሰናል።
5. በአንቀጽ 24/4/ በተመለከተው መሠረት በሚከናወን እንደገና የመደራጀ ሂደት በክልሉ ነዋሪ በሆነ ኩባንያ ውስጥ የሚደረግ ማናቸውም የአክሲዮን መተላለፍ በዚሁ የመደራጀት ሂደት ተሳታፊ ለሆነ ለሌላ በኢትዮጵያ ነዋሪ ለሆነ ኩባንያ የሚደረግ የአክሲዮን ልዋጭ በሆነ አክሲዮን እንደተሸጠ አይቆጠርም።
6. በንዑስ አንቀጽ/4/ መሠረት በልዋጭ የተሰጠው አክሲዮን ዋጋ የመጀመሪያው አክሲዮን ዋጋ ይሆናል።
7. ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ገደቦች እንደተጠበቁ ሆነው እንደዚህ ያሉ ንብረቶችን በማስተላለፍ ሂደት የሚደርስ ኪሣራ ዕውቅና ተሰጥቶት ከተገኘ ጥቅም ጋር እንዲካካስ ይደረጋል።
   ሀ/ በዚህ አንቀጽ መሠረት በተደረገ የካፒታል ንብረት መተላለፍ ያጋጠመ ኪሣራ በዚሁ አንቀጽ መሠረት በተደረገ የንብረት መተላለፍ በተገኘ ጥቅም ላይ እንጂ በማናቸውም ሌላ አኳኋን በተገኘ ገቢ ወይም ጥቅም ጋር እንዲካካስ አይደረግም። ከዚህ በላይ በተመለከተው መሠረት ያልተካካሰ ኪሣራ ላልተወሰነ ጊዜ ወደፊት ሊሸጋገር ይችላል።
   ለ/ በዚህ አዋጅ በአንቀጽ 2/4/ ግንኙነት ላላቸው ሰዎች በተሰጠው ትርጉም የሚሸፈኑ ድርጅቶች በመካከላቸው በሚያደረጉት እንቅስቃሴ የሚያጋጥማቸው ኪሳራ እንደሚካካስ ኪሣራ ተደርጎ አይወሰድም።
7. ማናቸውም በዚህ አንቀጽ ግብር የተጣለበትን የካፒታል ንብረት ዝውውር የመቀበል ወይም የመመዝገብ ወይም በማናቸውም መንገድ የማፅደቅ ሥልጣን የተሰጠው ሰው ግብሩ መከፈሉን ያረጋግጥ ዝውውሩን ይቀበልም፣ አይመዘግብም፣ አያፀድቅም።

## ምዕራፍ 2
## የአፈፃፀም ድንጋጌዎች
## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

### 37. የግብር አሰገቢ ባለሥልጣን ሥልጣንና ተግባር፡

1. ይህን አዋጅ እና በዚህ አዋጅ መሠረት የሚወጡ ደንቦችን በሥራ ላይ የማዋል እና የማስፈጸም ኃላፊነት የግብር አሰገቢው ባለሥልጣን ይሆናል።
2. በማንኛውም በሌላ ሕግ ውስጥ ተቃራኒ የሆኑ ድንጋጌዎች ቢኖሩም የግብር አሰገቢው ለሥልጣን በማናቸውም ጊዜ በግብር ከፋይ የቀረቡ ማንኛቸውንም መግለጫዎች ሠነዶችና የሂሣብ መዝገቦች ለማረጋገጥ፣
   ሀ/ ሕጋዊ ሥልጣን የተሰጣቸው ቀጣጣሪዎችን ወደ ግብር ከፋዩ የንግድ ወይም የሙያ ሥራ ቦታ በመላክ ገቢና ወጪን የሚያሳዩ ሠነዶችን ለንግድ የተከማቹ ዕቃዎችን፣ ሌሎች ዕቃዎችን ወይም የሂሣብ መዛግብትንና ሠነዶችን ለማመሳከርና ለመመርመር፣
   ለ/ ግብር ከፋዩን ወይም የሂሣብ መዝገቦችን እና ሠነዶችን ወይም መረጃን ለማግኘት የሚችለውን ወይም እነዚህኑ መጠበቅ ኃላፊነት የተሰጠውን ማንኛውንም የግብር ከፋዩን ተቀጣሪ በእመቺ የግብር አሰገቢ መሥሪያ ቤት የሥራ ሰዓቶች እና ጽ/ቤት ተገኝቶ ለሚቀርቡለት ለጉዳዩ አግባብ ያላቸው ጥያቄዎች መልስ እንዲሰጥና የተባሉትንም ሠነዶች እንዲያቀርብ ለማድረግ፣
   ሐ/ ማዘጋጃ ቤት፣ ድርጅት፣ የፋይናንስ ተቋም ወይም ማንኛውንም የፌደራል መንግሥት ወይም የክልል መሥሪያ ቤት ወምር ማናቸውም ሰው ስለግብር ከፋይ የሚያውቀውን መረጃ ወይም የሥራ እንቅስቃሴ እንዲሁም የመበደር ወይም የማበደር ግንኙነቶችን ዝርዝር እንዲገለፅ ለማድረግ ይችላል።

www.chilot.me

## 38. መረጃዎችን በሚስጥር ስለመጠበቅ

1. የገቢር አሰገቢው ባለሥልጣን የባለሥልጣኑ ወኪል ሆነው የሚሠሩ ወይም ወኪል የነበሩ ወይም ተቀጣሪዎች ወይም ተቀጣሪ የነበሩ በኢትዮጵያ ንግድ ሕግ በንግድ ጋዜጣ ታትሞ እንዲወጣ ከታዘዘው ዓይነት መረጃ በስተቀር በሥራቸው አጋጣሚ ያወቀቸውን አንድን ግብር ከፋይ የሚመለከቱ ሌሎች መረጃዎች ለማንም አሳልፈው ሳይሰጡ በሚስጥር መጠበቅ አለባቸው። ከዚህ በላይ የተደነገገው ቢኖርም እንዲህ ያሉትን መረጃዎች ለሚከተሉት መግለጽ ይችላሉ

 ሀ/ ኃላፊነታቸውን ለመወጣት አስፈላጊ እስከሆነ ድረስ ለግብር አሰገቢው ባለሥልጣን ተቀጣሪዎች፣ ወይም ለፌደራል እና ለክልላዊ መንግሥታት እንዲሁም የከተማ መስተዳደሮች የገቢ ሰብሳቢ አካላት፣

 ለ/ የግብር ሕጉን በመተላለፍ ወንጀል የፈፀመውን ሰው ለፍርድ ለማቅረብ ለሕግ አስፈጻሚ አካላት፣

 ሐ/ የግብር ዕዳ መቀጫ ወይም ወለድ ወይም ማናቸውንም ሌላ የወንጀል ጉዳዮች በማየት ላይ ላለ ፍ/ቤት፣

 መ/ ኢትዮጵያ ፈራሚ በሆነችበት ዓለም ዓቀፍ ስምምነት መሠረት ሲጠየቅ ለውጭ አገር የግብር ባለሥልጣናት፣

3. በንዑስ አንቀጽ /1/ መሠረት መረጃ በእጃቸው የገባ ሰዎች መረጃው እንዲሰጣቸው ያደረገውን ምክንያት ግቡን ለማሳካት በሚያስችል አነስተኛ መጠን ካልሆነ በስተቀር እንዲህ ያለውን መረጃ በሚስጥር የመጠበቅ ኃላፊነት አለባቸው። በዚህ ክፍል ሚስጥርነታቸው እንዲጠበቅ የተደረጉ መረጃዎች የደረሷቸው ሌሎች ሰዎች እነዚህን መረጃዎች ለማንም ሌላ ሰው ተላልፈው እንዲሰጡ ማድረግ አይኖርባቸውም። እነዚህን መረጃዎች የያዙ ሠነዶችን ወዲያውኑ ለግብር አሰገቢው ባለሥልጣን መመለስ አለባቸው።

4. አንድን ግብር ከፋይ የሚመለከቱ መረጃዎች ከዚህ ውጭ ለሆኑ ሌሎች ሰዎች እንዲሰጡ ማድረግ የሚቻለው የግብር ከፋዩ ስምምነት በጽሑፍ ሲገኝ ብቻ ይሆናል።

## 39. የግብር አሰገቢው ባለሥልጣን ሠራተኞች የሚመሩበት የሥነ-ምግባር ደንብ

1. እያንዳንዱ የግብር አሰገቢው ባለሥልጣን ሠራተኛ፣

 ሀ/ ታማኝ እና ትክክለኛ ግብር ከፋዩን በትህትናና በአክብሮት የሚቀበል፣

 ለ/ ሕጎችን ደንቦችን እና መመሪያዎችን የጉዳዩ ፍሬ ነገር በሚመራው መሠረት ሥራ ላይ ማዋል፣ ለዘመዶቹ ወይም ለወዳጆቹ ልዩ አስተያየት ወይም አድልዎ ያለማድረግ፣

 ሐ/ የራሱን እና የባለቤቱን የግብር ዕዳ በሚመለከት ውጤት ሊያስከትል በሚችል ውሣኔ ላይ ያለመሳተፍ፣

 መ/ የሚታወቅ የቤተሰብ ዝምድና ወይም የንግድ ሥራ ጥቅም በተቀጣሪነቱ በሚሰጠው ውሣኔ ላይ ተፅዕኖ ሊያሳድር የሚችል ከሆነ እንዲህ ያለውን የዝምድና ግንኙነት ወይም ጥቅም ይፋ ማድረግ /አግባብ ባለው ሕግ በተወሰነው መሠረት/፣

 ሠ/ በአንቀጽ 38 የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ ማናቸውንም የግብር የታክስ ወይም የቀረጥ መረጃ በሚስጥር መጠበቅ፣

 ረ/ ማናቸውንም መደለያ አለመጠየቅ፣ ያለመቀበል ወይም ማናቸውንም ግብርን ከመወሰን ወይም ከመሰብሰብ ተግበሩ ጋር የሚጋጩ ሌሎች ተገቢ ያልሆኑ ተግባሮችን ያለመፈጸም፣

3. ማንኛውም የግብር ባለሥልጣኑ ሠራተኛ የግብር ሂሣብ ባለሙያ ወይም አማካሪ ሆኖ ለማገልገል ወይም የግብር ማስታወቂያ ለማዘጋጀት ወይም በግብር ላይ ምክር ለመስጠት ለሌላ ሰው ተቀጥር መሥራት የለበትም።

## 40. የሌሎች መሥሪያ ቤቶች ትብብር

1. ይህን አዋጅ በሥራ ላይ ለማዋል የፌደራል እና የክልል መንግሥታት ባለሥልጣናችና ወኪሎቻቸው በተጨማሪም ድርጅቶች የቀበሌ መስተዳድሮች ማኅበራት ሁሉ ከግብር አሰገቢው ባለሥልጣን ጋር የመተባበር ግዴታ አለባቸው።

 ሀ/ በደንባኝ ቀጠሮ ላይ ካልሆነ ወይም በግብር አሰገቢው ባለሥልጣን የተራዘመ የግብር መክፈያ ጊዜ ካልተሰጠ በስተቀር፣ ግብር ከፋዩ የሚፈለግበትን ግብር በወቅቱ የከፈለ ስለመሆኑ ወይም አዲስ ግብር ከፋይን በሚመለከት የተመዘገበ ስለመሆኑ ከግብር አሰገቢው ባለሥልጣን የተሰጠውን የምስክር ወረቀት ካላቀረበ በስተቀር ማንኛውም ፈቃድ ሰጭ ሚኒስቴር፣ ማዘጋጃ ቤት፣ የፌዴራል ወይም የክልል መሥሪያ ቤት አዲስ የንግድ ሥራ ፈቃድ መስጠት ወይም ማደስ አይችልም፣

 ለ/ ግብር አሰገቢው ባለሥልጣን ግብር ከፋዩ ያለበትን ግዴታ ስለመፈጸሙ የምስክር ወረቀት የማይሰጥ ቢሆን ስለዚሁ ያለውን ምክንያት በመዘርዘር በጽሑፍ ለጠያቂው ይሰጣል።

 ሐ/ የምስክር ወረቀት አልሰጥም በማለቱ ወይም የንግድሥራ ሥፈታ በመሠረዙ የግብር አሰገቢው ባለሥልጣን በሰጣቸው ምክንያቶች ቅር የተሰኘ ማንኛውም ግብር ከፋይ ቅሬታውን ለአጣሪ ኮሚቴ ሊያቀርብ ይችላል።

## 41. የቢሮ ኃላፊው ስልጣን

• በዚህ አዋጅ በሌሎች አንቀጾች ከተሰጠው ሥልጣን በተጨማሪ ቢሮ ኃላፊው የሚከተለው ሥልጣን ይኖረዋል።

 ሀ/ በተዋዋይ ሀገሮች በሥራ ላይ ባሉ ህጎች ግብር የመክፈል ግዴታ ያለባቸው የንግድ ሥራዎች ተደራራቢ ግብር እንዳይከፈልባቸው ለማድረግ የሚያስችል ስምምነት ከሌሎች መንግሥታት ጋር መዋዋል፣

 ለ/ ማንኛውም ግብር ከፋይ ከፍተኛ የተፈጥሮ ችግር ወይም ሌላ ከባድ አደጋ ወይም ጥፋት ሲደርስበት ወይም በቸልተኝነቱ ምክንያት ሳይሆን ከአቅሙ በላይ በሆኑ ምክንያቶች በዚህ አዋጅ መሠረት ያለበትን ግብር የመክፈል ግዴታ ለመፈፀም የማያስችለው ከአቅም በላይ የሆነ ችግር የደረሰበት ሆኖ ሲያገኘው እስከ ብር 10,000.00 የሚደርሰውን የግብር ዕዳ የመሠረዝ፣

 ሐ/ ከብር 10,000.00 በላይ የሆነ የግብር ዕዳ ቀሪ ሊሆን የሚችለው የክልሉ ስራ አስፈፃሚ ሲፈቅድ ብቻ ይሆናል።

 መ/ ለዚህ አዋጅ እና አዋጁን ተከትሎ ለሚወጣው ደንብ አፈፃፀም አስፈላጊ የሆኑ መመሪያዎች ማውጣት ይችላል።

## 42. የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር አስፈላጊ ስለመሆኑ

 ሀ/ ማንኛውም ግብር የመክፈል ግዴታ ያለበት ሰው የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር የመያዝ ግዴታ አለበት። ይሁን እንጂ በማናቸውም ሁኔታ አንድ ግብር ከፋይ ከአንድ የበለጠ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር እንዲይዝ አይፈቀድለትም።

 ለ/ ማንኛውም ግብር ከፋይ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር ለማግኘት ክፍያ አይጠየቅም።

 ሐ/ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር ለማግኘት የሚደረገው ምዝገባ በግብር አሰገቢው ባለሥልጣን በሚወሰን የጊዜ ሠሌዳ መሠረት ይከናወናል።

## 43. ግብርን ቀንሶ ገቢ የማድረግ ኃላፊነት ለተሰጠው ሰው የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር መስጠት

ከተካፋይ ሂሣብ ላይ ግብር ተቀናሽ የሚደረግበት ማንኛውም ግብር ከፋይ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥሩን ግብርን ቀንሶ ገቢ የማድረግ ግዴታ ላለበት ሰው ማስመዝገብ አለበት። ግብርን ቀንሶ ገቢ የማድረግ ግዴታ ያለበት ሰው የሰበሰበውን ግብር አግባብ ላለው የግብር ባለሥልጣን ገቢ በሚያደርግበት ጊዜ ግብሩ የተቀነሰባቸውን ግብር ከፋዮች መለያ ቁጥር እንዲሁም ከእያንዳንዱ የተቀነሰውን ግብር መጠን የሚያሳይ ዝርዝር አብሮ ማቅረብ አለበት።

## 44. የንግድ ሥራ ፈቃድ

የንግድ ሥራ ለማከናወን የሚያስችል ፈቃድ የተሰጠው ወይም እንዲሰጠው ጥያቄ ያቀረበ ማንኛውም ሰው በፍቃድ ሰጪው ባለሥልጣን ዘንድ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥሩን ማስመዝገብ አለበት።

www.chilot.me

1. የንግድ ሥራ ፈቃድ ወይም የሙያ ፈቃድ የሚሰጥ ወይም የሚያድስ ማናቸውም በክልሉ የሚገኝ የመንግስት መ/ቤት ወይም ተቋም የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር ላላቀረበ ሰው ወይም ድርጅት ፈቃድ አይሰጥም ወይም አያድስም።
2. በንዑስ አንቀጽ/1/ የተነገሩው ቢኖርም ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን ከዚህ በላይ በአንቀጽ42 መሠረት እንዲደርሰው በተደረገው የምዝገባ የጊዜ ሠሌዳ ጠያቂው መመዝገብ ያለበት ቀን ያልደረሰ መሆኑን የሚያመለክት መሆኑን ከተረዳ ግብር ከፋዩን የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር እንዲያቀር አይጠይቀውም።

## 45. መመሪያዎች

የፋይናንስ ቢሮ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር ለማግኘት ግብር ከፋዮች የሚመዘገቡበትን ሥርዓት የሚወስን መመሪያ የማውጣት ሥልጣን ተሰጥቶታል። የሚያወጣውን መመሪያ መሠረት በማድረግ በየምድቡ የሚገኙ ግብር ከፋዮች የሚመዘገቡበትን ቀን ለይቶ የሚያሳይ የምዝገባ ሠሌዳ በማዘጋጀት ይህንንም የጊዜ ሠሌዳ አግባብ ላላቸው ፈቃድ ሰጪ ባለሥልጣናት ያሠራጫል።

## 46. አድራሻ ስለ መለወጥና የንግድ ሥራን ስለ ማቋረጥ

1. የንግድ አድራሻውን የሚለውጥ ማንኛውም ግብር ከፋይ የተደረገውን ለውጥ በ30 ቀናት ውስጥ ለግብር አስገቢው ባለሥልጣን ማስታወቅ አለበት።
2. የንግድ ሥራውን የሚያቋርጥ ማንኛውም ግብር ከፋይ የንግድ ሥራውን ካቋረጠበት ቀን ጀምሮ በ30 ቀናት ውስጥ ለግብር አስገቢው ባለሥልጣን ማስታወቅ አለበት። የንግድ ሥራ እንቅስቃሴ በሚቋረጥበት ጊዜ በዚህ አዋጅ መሠረት ግብር ከፋዩ በዓመቱ መጨረሻ ማቅረብ ያለበትን የገቢ ማስታወቂያ እንቅስቃሴው ከተቋረጠበት ቀን አንስቶ በ60 ቀናት ውስጥ ማቅረብ አለበት። የንግድ ሥራውን እንቅስቃሴ እስካቋረጠበት ጊዜ ድረስ ሊከፈል የሚገባው ግብር በዚህ አንቀጽ መሠረት ገቢውን ለማስታወቅ በተወሰነው ጊዜ ውስጥ ወይም ከዚያ በፊት መከፈል አለበት።
   ሀ/ ከግብር ዘመኑ በፊት ወይም በግብር ዘመኑ ውስጥ ከተቋረጠው የንግድ ሥራ እንቅስቃሴ ኢንቬስትመንት ከማናቸውም የገቢ ምንጭ ግብር ከፋዩ ገቢ ያገኘ እና
   ለ/ የንግድ ሥራው እንቅስቃሴ የኢንቬስትመንቱ ወይም ከማናቸውም ሌላ የገቢ ምንጩ ከመቋረጡ በፊት የተገኘው ገቢ፣ በዚህ አዋጅ መሠረት ግብር የሚከፈልበት ከሆነ ገቢው በተገኘ ጊዜ የንግድ ሥራው እንቅስቃሴ፣ ኢንቬስትመንቱ ወይም ማናቸውም ሌላ የገቢ ምንጭ እንዳልተቋረጠ ተቆጥሮ ይሁ አዋጅ ተፈፃሚ ይደረግበታል።

## 47. መዝገብ የመያዝ ግዴታ

1. ከደረጃ "ሐ" ግብር ከፋዮች በስተቀር በአንቀጽ 2/6/ በተተረጎመው መሠረት በንግድ ሥራ ላይ የተሠማሩ ወይም በሙሉ ወይም በከፊል የሚከራዩ ሕንፃዎች ባለቤት የሆኑ የሂሣብ መዝገብ እና ሰነዶችን የመያዝ ግዴታ አለባቸው።
2. በንዑስ አንቀጽ /1/ መሠረት የሂሳብ መዝገብና ሰነዶችን የመያዝ ግዴታ ያለበት ሰው ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን መረጃዎች እሚልቶ መያዝ አለበት፣
   ሀ/ ቋሚ ንብረቶች የተገዙበትን ቀን፣ የተገዙበትን ዋጋ እና አሁን ያላቸውን የመዝገብ ዋጋ የሚያሳይ የቋሚ ንብረት መዝገብ ጨምሮ የንግድ ሥራውን ሀብትና ዕዳ የሚያሳይ ሰነድ፣
   ለ/ ከንግድ ሥራው እንቅስቃሴ ጋር በተያያዘ በየቀኑ የተገኘውን ገቢ እና የተደረገውን ወጪ በተለይ ከገቢና ወጪው ምክንያት ጋር በማያያዝ፣
   ሐ/ ከንግድ ሥራው ጋር በተያያዘ የተገዙ እና የተሸጡ ዕቃዎችንና አገልግሎቶችን በተመለከተ የሚከተሉትን የሚያሳይ፦
      1/ የተሸጠውን ዕቃና የተሰጠውን አገልግሎት በመለየት፣
      2/ ዕቃውን የገዙ ወይም የሸጡ ወይም አገልግሎቱን የሰጡ ሰዎችን ስም፣ የግብር አስገቢው ባለሥልጣን ለይቶ እንዲያውቃቸው በሚያስችል አኳኋን፣
      3/ የሻጩን የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር የያዙ አስቀድሞ ቁጥር የተሰጣቸው ደረሰኞች በመጠቀም፣
   መ/ በመጋዘን የተከማቹ የንግድ ዕቃዎችን ዓይነት፣ ብዛት እና ለዕቃዎቹ የተደረገውን ወጪ እንዲሁም ዕቃዎቹ የተገመቱበትን ዘዴ ጨምሮ በሂሣብ ዘመኑ መጨረሻ በእጅ ያሉትን ዕቃዎች የሚያሳይ የሰነድ መረጃ፣
   ሠ/ የሚፈለገውን ግብር ለመወሰን የሚያስችሉ ማናቸውም ሌሎች አግባብነት ያላቸውን መረጃዎች፣
3. ግብር ከፋዩ በውጭ አገር ቋንቋ የተዘጋጁ የሂሳብ መዝገቦችና ሰነዶች ያሉት እንደሆነ እነዚህን መዝገቦችና ሰነዶች በራሱ ወጪ በክልሉ ውስጥ በሚሠራባቸው አግባብ ባላቸው የሥራ ቋንቋዎች አስተርጉሞ እንዲያቀርብ የግብር አስገቢው ባለሥልጣን ሊጠይቅ ይችላል።
4. ግብር ከፋዩ በንዑስ አንቀጽ/2/ የተዘረዘሩትን የሂሳብ መዝገቦችና ሰነዶች የያዙት ሂሳብ አግባብነት ካለው የግብር ዘመን አንስቶ ለአሥር ዓመታት ማቆየት አለበት።

## 48. የማኅበር መመሥረቻ ደንብ ስለማቅረብ

ኩባንያዎች የሽርክና ማኅበሮች እና ሌሎች ለንግድ የተቋቋሙ ማኅበራት ሁሉ የተመሠረቱበትን የመተዳደሪያ ደንብና የመመስረቻ ጽሑፍ ትክክል ግልባጭ ለግብር አስገቢው ባለሥልጣን መስጠትና በተከታታይም በዚሁ ላይ የተደረገ ለውጥ ሲኖር ማስታወቅ አለባቸው።

## 49. ኦዲተሮች

1. ማንኛውም ኦዲተር የደንበኛውን ዓመታዊ ሂሣብ መርምሮ የሰጠውን ሪፖርት በግብር አስገቢው ባለሥልጣን በጽሑፍ ሲጠየቅ ማቅረብ አለበት።
2. ጥያቄው በቀረበበት ጽሑፍ በተገለፀው ጊዜ ውስጥ ማንኛውም ኦዲተር ሪፖርቱን ባያቀርብ ግብር አስገቢው ባለሥልጣን የኦዲተሩ ፈቃድ እንዲሰረዝ ለፍቃድ ሰጪው ባለሥልጣን ያስታውቃል።

## ክፍል ሁለት
## ከተከፋይ ሂሳብ ላይ ግብርን ቀንሶ ገቢ የማድረግ ሥርዓት

## 50. ከመቀጠር በሚገኝ ገቢ ላይ የሚከፈለውን ግብር ቀንሶ ገቢ ስለማድረግ

1. በዚህ አዋጅ በግልፅ ከግብር ነፃ እንዲሆን የተደረገ ካልሆነ በስተቀር ማናቸውም ቀጣሪ ለተቀጣሪው ከሚከፍለው ክፍያ ላይ ተገቢውን ግብር ቀንሶ ማስቀረት አለበት።
2. ቀጣሪው በመቀጠር ከሚገኝ ገቢ ላይ ግብር ቀንሶ ገቢ በማድረግ ረገድ ያለበት ግዴታ፣ ለሠራተኛው ከሚፈፀሙ ክፍያዎች ላይ ተቀናሽ መደረግ ካለባቸው ሌሎች ግዴታዎች ቅድሚያ ይኖረዋል።
3. ቀጣሪው ቀንሶ ያስቀረውን ግብር ከእያንዳንዱ ወር መጨረሻ አንስቶ ባሉት /30/ ቀናት ውስጥ ለግብር አስገቢው ባለሥልጣን ገቢ ማድረግ አለበት። በዚህ ዓይነት ተቀንሶ የቀረው ግብር ገቢ በሚደረግበት ጊዜ በወሩ ውስጥ ግብር የሚከፈልበት ገቢ ያገኙትን ሠራተኞች ዝርዝር የሚያሳይ መረጃ ተያይዞ መቅረብ አለበት።
4. ከዚህ በላይ በንዑስ አንቀጽ /3/ መሠረት የሚሰጠው መግለጫ የግብር አስገቢው ባለሥልጣን በሚወስነው ቅርፅና አኳኋን የሚቀርብ ሆኖ የሚከተሉትን መረጃዎች መያዝ አለበት፣
   ሀ/ የእያንዳንዱን ተቀጣሪ ስም፣ አድራሻ እና የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር፣
   ለ/ እያንዳንዱ ተቀጣሪ ከመቀጠር ያገኘውን ግብር የሚከፈልበት ገቢ መጠን፣
   ሐ/ ከዚሁ ገቢ ላይ ተቀንሶ የቀረውን ግብር መጠን፣
   መ/ ከግብር ነፃ የተደረገ ተቀጣሪው ያገኘው ገቢ መጠን፣

## 51. ዕቃዎች ወደ አገር በሚገቡበት ጊዜ ስለሚከፈል የገቢ ግብር

1. ዕቃዎች ለንግድ ወደአገር በሚገቡበት ጊዜ የንግድ ትርፍ ግብር ይከፈልባቸዋል። በዚህ ዓይነት የሚሰበሰበው ግብር፣ ከተከፋይ ሂሳብ ላይ ተቀንሶ እንደቀረ ግብር ተቆጥሮ ግብር ከፋዩ በዓመቱ መጨረሻ መክፈል ከሚገባው የግብር መጠን ላይ እንዲታሰብለት ይደረጋል።

www.chilot.me

2. በዚህ አንቀጽ መሠረት ወደአገር በሚገቡ ዕቃዎች ላይ የሚሰበሰበው የንግድ ትርፍ ግብር አስመጪው ለዕቃው በከፈለው ዋጋ የመድን አረቦን እና የመጓጓዣ ወጪ /ሲ.አይ.ኤፍ/ ላይ የሚታሰብ 3 ፐርሰንት /ሦስት በመቶ/ ይሆናል፡፡
3. ወደ አገር በሚገቡ ዕቃዎች ላይ የተከፈለው ግብር፣ ግብር ከፋዩ ያሰታወቀውን ገቢ መሠረት በማድረግ ከተወሰነው ግብር ያነሰ እንደሆነ፣ ግብር ከፋዩ ልዩነቱን እንዲከፍል ይደረጋል፡፡ ወደአገር በሚገቡ ዕቃዎች ላይ የተከፈለው ግብር በዓመቱ ሊከፈል ከሚገባው ግብር የበለጠ እንደሆነ የግብር አሰገቢው ባለሥልጣን ሂሳቡን አጣርቶ በብልጫ የተከፈለውን ግብር በአንቀጽ /75/ በተገለጸው ጊዜ እና አኳኋን ለግብር ከፋዩ ይመልስለታል፡፡
4. በዚህ አንቀጽ መሠረት የሚሰበሰበው ግብር፣ የግብር ከፋዩን ስም አድራሻ እና የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር በመጠቀም መመዝገብ እና ሂሳቡን በዚሁ መሠረት መያዝ አለበት፡፡ ሆኖም ግብር ከፋዩ የመመዝገቢያው ጊዜ ባለመድረሱ ምክንያት የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር ያልያዘ እንደሆነ፣ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥሩን አግኝቶ ግብሩን ከተከፋይ ሂሳብ ላይ ቀንሶ ገቢ ለሚያደርገው ሰው እስከሚሰጥ ድረስ ምዝገባው የሚከናወነው በግብር ከፋዩ ስምና አድራሻ ብቻ ይሆናል፡፡
5. ፋይናንስ ቢሮ ለዚህ አንቀጽ አፈፃፀም "ለንግድ የሚውሉ ዕቃዎች" የሚለውን ሀረግ ትርጉም በመመሪያ ይወስናል፡፡

## 52. ከተከፋይ ሂሳቦች ላይ ግብርን ቀንሶ ስለማስቀረት

1. በሕግ የሰውነት መብት የተሰጣቸው ድርጅቶች፣ የኢክስዮን ማህበራት የመንግሥት መ/ቤቶች ለትርፍ ያልተቋቋሙ የግል ድርጅቶች እና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች፣ የክልሉ ስራ አስፈፃሚ በሚያወጣው ደንብ ግብር ተቀንሶ ቀሪ እንዲደረግበት ከተወሰነ ማናቸውም ክፍያ ላይ ግብሩን ቀንሰው ማስቀረት አለባቸው፡፡
2. ከተከፋይ ሂሳቦች ላይ ተቀንሶ ቀሪ የሚደረገው ግብር የጠቅላላ ተከፋይ ሂሳብ 2ፐርሰንት /ሁለትበመቶ/ ይሆናል፡፡
3. ግብሩን ቀንሶ ገቢ ማድረግ ያለበት ሰው በወሩ ውስጥ ከተከፈሉ ሂሳቦች ላይ ተቀንሶ ቀሪ መደረግ የሚገባውን አጠቃላይ ሂሳብ ከወሩ የመጨረሻ ቀን ጀምሮ ባሉት አሥር ቀናት ውስጥ ለግብር አሰገቢው ባላሥልጣን ገቢ ማድረግ አለበት፡፡ ከተከፋይ ሂሳቦች ላይ ግብርን ቀንሶ ገቢ የማድረግ ኃላፊነት ያለበት ሰው በወሩ የሰበሰበውን አጠቃላይ ሂሳብ ገቢ በሚያደርግበት ጊዜ ክፍያ የተፈፀመለትን የእያንዳንዱን ሰው ወይም ድርጅት ስም መለያ ቁጥሩን በወሩ ውስጥ ለተጠቀሰው ሰው የተከፈለውን ገንዘብ አጠቃላይ ድምር ተቀናሽ ተደርጎ የቀረበውን ግብር እና በእያንዳንዱ ሰው ስም ለግብር አሰገቢው ባለሥልጣን ገቢ የተደረገውን ሂሳብ የሚያሳይ ዝርዝር ማቀረብ አለበት፡፡
4. ከተከፋይ ሂሳቦች ላይ የተቀነሰው ግብር በዓመቱ መከፈል ከነበረበት ትክክለኛ ግብር ያነሰ ሆኖ የተገኘ እንደሆነ ግብር ከፋዩ ገቢውን በሚያሰታውቅበት ጊዜ በልዩነት የሚፈለገውን ግብር ገቢ ማድረግ አለበት፡፡ ከተከፋይ ሂሳቦች ላይ የተቀነሰው ግብር በዓመቱ መከፈል ከሚገባው በላይ ሆኖ የተገኘ እንደሆነ ግብር አሰገቢው ባለሥልጣን በብልጫ የተከፈለውን ግብር በአንቀጽ 75 በተገለጸው ጊዜ እና አኳኋን ለግብር ከፋዩ ይመልስለታል፣
5. በዚህ አንቀጽ መሠረት ከተከፋይ ሂሳብ ላይ ግብሩን ቀንሶ ገቢ የማድረግ ግዴታ ያለበት ሰው ተቀንሶ ገቢ መደረግ ያለበት ግብር በሙሉ ወይም በከፊል ቀንሶ ገቢ ያላደረገ እንደሆነ ግብሩን ሙሉ በሙሉ ለግብር አሰገቢው ባለሥልጣን ገቢ እንዲያደርግ ይገደዳል፡፡

## 53. የሠንጠረዥ "መ" ገቢ ለባለመብቱ በሚከፈልበት ጊዜ ግብርን ቀንሶ ስለማስቀረት

1. ማናቸውም በሠንጠረዥ "መ" መሠረት ግብር የሚከፈልበትን ገቢ ለባለመብቱ የሚከፍል ሰው በሠንጠረዥ "መ" መሠረት የሚፈለገውን ግብር ከተከፋዩ ሂሣብ ላይ ቀንሶ ማስቀረት አለበት፡፡
2. ከፋዩ ያለበት ግብር ቀንሶ የማስቀረት ግዴታ ከፋዩ ከተከፋዩ ገቢ ላይ ቀንሶ ማስቀረት ካለበት ሌላ ማናቸውም ግዴታ ቀዳሚነት ይኖረዋል፡፡
3. ከፋዩ ቀንሶ ያስቀረውን ግብር ከእያንዳንዱ ወር መጨረሻ አንስቶ ባሉት 15 ቀናት ውስጥ ለግብር አሰገቢው ባለሥልጣን ገቢ ማድረግ አለበት፡፡ ስለሆነም በዚህ ዓይነት ተቀንሶ የቀረው ግብር ገቢ በሚደረግበት ጊዜ በወሩ ውስጥ ግብር የሚከፋልበት ገቢ ያገኙትን ግብር ከፋዮች ዝርዝር የሚያሳይ መረጃ ተያይዞ መቅረብ አለበት፡፡
4. ከዚህ በላይ በንዑስ አንቀጽ /3/ መሠረት የሚሰጠው መግለጫ የግብር አሰገቢው ባለሥልጣን በሚወሰነው ቅርፅና አኳኋን የሚቀርብ ሆኖ የሚከተሉትን መረጃዎች መያዝ አለበት፣
   ሀ/ የእያንዳንዱን ግብር ከፋይ ስም አድራሻ እና የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር
   ለ/ በሠንጠረዥ "መ" መሠረት ግብር የሚከፈልበትን ክፍያ መጠን፡፡
   ሐ/ ከክፍያው ላይ ተቀንሶ የቀረውን ግብር መጠን
5. ለግብር ከፋዩ ክፍያ በሚፈፀምበት ጊዜ ከፋዩ ለእያንዳንዱ ግብር ከፋይ የግብር አሰገቢው ባለእልጣን በሚወሰነው አኳኋን ግብር ተቀንሶ ቀሪ መደረጉን የሚያረጋግጥ የምስክር ወረቀት ይሰጣል፡፡ ይህም የምስክር ወረቀት በንዑስ አንቀጽ /4/ የተዘረዘረውን መረጃ ግብር ካፋዩ ተቀንሶ ቀሪ በተደረገው የግብር መጠን ላይ ቅሬታውን ለማቅረብ የሚችል መሆኑን እና ቅሬታውን ማቅረብ የሚችልበትን አኳኋን የሚገልፅ መሆን አለበት፡፡
6. ግብር ተቀንሶ ቀሪ መደረጉን የሚያረጋግጠው የምስክር ወረቀት በሠንጠረዥ "መ" መሠረት ግብር በሚከፈልበት ገቢ ላይ ተቀንሶ ለቀረው ግብር ማስረጃ ይሆናል፡፡

## 54. የመታወቂያ ወረቀት ስለመስጠት

የግብር አሰገቢው ባለሥልጣን ከተከፋይ ሂሳብ ላይ ግብር ቀንሶ የማስቀረት ኃላፊነት ለተሰጣቸው ሰዎች የመታወቂያ ወረቀት ይሰጣል፡፡

## 55. የተፈፀመውን ክፍያ እና ግብር ተቀንሶ ገቢ መደረጉን የሚያረጋግጥ ሰነድ

1. ግብር ቀንሶ ገቢ የማድረግ ግዴታ ያለበት ሰው በእያንዳንዱ የግብር ዘመን
   ሀ/ የተፈፀሙ ክፍያዎችን፣ እና
   ለ/ ከእነዚህ ክፍያዎች ተቀንሶ የቀረውን ግብር የሚያሳዩ የሂሳብ ሰነዶችን የመያዝ እና የግብር አሰገቢው ባለሥልጣን ምርመራ እንዲያደርግባቸው የማቅረብ ግዴታ አለበት፡፡
2. ግብር ቀንሶ ገቢ የማድረግ ግዴታ ያለበት ሰው ከዚህ በላይ በንዑስ አንቀጽ/1/ የተዘረዘሩትን የሂሳብ ሰነዶች አግባብነት ካላቸው የግብር ዘመን መጨረሻ አንስቶ ለአምስት/5/ የግብር ዓመታት ማቆየት አለበት፡፡
   3. የግብር አሰገቢው ባለሥልጣን ግብር ቀንሶ ገቢ የማድረግ ግዴታ ያለበት ሰው ከዚህ በላይ በንዑን አንቀጽ/1/ የተዘረዘሩትን ሰነዶች ኮፒ እርሱ በሚሰጠው ቅጽ እና ሁኔታ እንዲሁም በሚወሰነው የጊዜ ልዩነት እንዲያቀርብ ሊጠይቅ ይችላል፡፡

## 56. በታክስ ዘመኑ ውስጥ የሚፈለገውን ግብር ስለማስተካከል እና ግብር ቀንሶ ገቢ ማድረግ ያለበት ሰው ስላለበት የመካስ ግዴታ

1. ተቀንሶ ቀሪ የተደረገው ግብር የመጨረሻ የግብር ክፍያ ከሆነበት ሁኔታ በስተቀር ተቀንሶ ቀሪ የተደረገ ግብር ክፍያ /በአንቀጽ 52 ወይም በአንቀጽ 53 መሠረት በየጊዜው የተከፈለ ግብር ወይም በአንቀጽ 51 መሠረት በገቢ ዕቃዎች ላይ የተከፈለ ግብር/ ግብር ከፋዩ በዚያው የታክስ ዘመን ውስጥ ሊከፍል የሚገባው ግብር በሚሰላበት ጊዜ የሚካተት ይሆናል፡፡
2. ግብሩ ተቀንሶ ገቢ የተደረገበት ሰው ተቀንሶ ገቢ የተደረገው ግብር እንዲከፈለው ጥያቄ ያቀረበ እንደሆነ በዚህ አዋጅ መሠረት ከተከፋይ ሂሳብ ላይ ግብር ቀንሶ ያስቀረ እና ለግብር አሰገቢው ባለሥልጣን ገቢ ያደረገ ሰውገቢ የተደረገውን ግብር ለተቀነሰበት ሰው እንደከፈለ ይቆጠራል፡፡

www.chilot.me

## ክፍል ሦስት
## የግብር ሂሳብ አያያዝ መርሆዎች

### 57. የሂሳብ አያያዝ ዘዴ

1. በዚህ አዋጅ በተደነገገው መሠረት በአንድ የግብር ዘመን ውስጥ ግብር ከፋዩ ያገኘል ተብሎ የታሰበውን ወይም ያገኘውን ገቢ ለማረጋገጥ ከዘመኑ በኋላ የሚሰበሰበው ወይም የሚከፈለው ሂሳብ በአጠቃላይ ተቀባይነት ያገኙ የሂሳብ አያያዝ መርሆዎችን መሠረት በማድረግ በዘመኑ እንደተሰበሰበ ወይም እንደተከፈለ ተቆጥሮ እንደአገባብነቱ በገቢነት እንዲያዝ ወይም በወጪ እንዲቀነስ ይደረጋል::
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ እና /3/ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የግብር አስገቢው ባለሥልጣን የተለየ የሂሳብ አያያዝ ሥራ ላይ እንዲውል ካልፈቀደ በስተቀር ማንኛውም ግብር ከፋይ ሂሳቡን በጥሬ ገንዘብ እንቅስቃሴ ላይ በተመሠረት ወይም በተሰበሳቢና ተከፋይ ሂሳብ ላይ በተመሠረት የሂሳብ አያያዝ ዘዴ መያዝ አለበት::
3. ለግብር አከፋፈል ሲባል ኩባንያ ሂሳቡን በተሰብሳቢና ተከፋይ ሂሳብ ላይ በተመሠረተ የሂሳብ አያያዝ ዘዴ መሠረት መያዝ አለበት::
4. ማንኛውም ሰው የሂሳብ አያያዝ ዘዴውን ለመለወጥ እንዲፈቀድለት የግብር አስገቢው ባለሥልጣን በፅሑፍ መጠየቅ ይችላል:: የግብር አስገቢው ባለሥልጣን ተለዋጩ ዘዴ የግብር ከፋዩን ሂሳብ በትክክል የሚያሳይ ነው ብሎ ሳያምንበት ለውጡን መቀበሉን በፅሑፍ ያስታውቃል::
5. የግብር ከፋዩ የሂሳብ አያያዝ ዘዴ እንዲለወጥ ሲፈቀድ የገቢ ርዕሶች ሳይመዘገቡ እንዳይቀሩ ወይም በድጋሚ እንዳይመዘገቡ ለማድረግ የግብር ከፋዩ የገቢ ርዕሶች ተቀናሽ ወይም የታክስ ማካካሻ ሂሳቦች ላይ ለውጡ ከተደረገበት የግብር ዘመን ቀጥሎ ባለው ዓመት ውስጥ ተገቢው ማስተካከያ ሊደረግባቸው ይገባል::

### 58. በጥሬ ገንዘብ እንቅስቃሴ ላይ የተመሠረተ የሂሳብ አያያዝ ዘዴ

1. ለግብር አከፋፈል ሲባል ሂሳቡን በጥሬ ገንዘብ እንቅስቃሴ ላይ በተመሠረተ የሂሳብ አያያዝ ዘዴ የሚይዘውን ግብር ከፋይ ገቢ ለማስላት ግብር ከፋዩ የተቀበለውን ወይም በስሙ የተያዘለትን የገንዘብ መጠን በሂሳቡ ውስጥ ማካተት አለበት::
2. ለግብር አከፋፈል ሲባል ሂሳቡን በጥሬ ገንዘብ እንቅስቃሴ ላይ በተመሠረተ የሂሳብ አያያዝ ዘዴ የሚይዝ ግብር ከፋይ ወጪ አደረገ የሚባለው ግብር ከፋዩ በራሱ የሚፈፅመው ክፍያ ሲሆን ነው::

### 59. በተሰብሳቢና ተከፋይ ሂሳብ ላይ በተመሠረተ የሂሳብ አያያዝ ዘዴ

1. ለግብር አከፋፈል ሲባል ሂሳቡን በተሰብሳቢና ተከፋይ ሂሳብ ላይ በተመሠረተ የሂሳብ አያያዝ ዘዴ የሚይዝ ግብር ከፋይ ገቢውን በሚያሣሳበት ጊዜ በስሙ በተሰብሳቢነት የተያዘውን የገንዘብ መጠን በሂሳቡ ውስጥ ማካተት አለበት::
2. ለግብር አከፋፈል ሲባል ሂሳቡን በተሰብሳቢና ተከፋይ ሂሳብ ላይ የተመሠረተ የሂሳብ አያያዝ ዘዴ የሚይዝ ግብር ከፋይ ወጪ አደረገ የሚባለው በስሙ በተከፋይነት የተያዘ ሲሆን ነው::
3. በዚህ አዋጅ በተደነገገው መሠረት አንድ ሂሳብ በግብር ከፋዩ ተሰብሳቢ ነው የሚባለው የመክፈያው ጊዜ የተላለፈ ወይም ክፍያው የሚፈጸመው በተወሰኑ ክፍያዎች ተከፋፍሎ ቢሆንም ግብር ከፋዩ ሂሳቡን ለመቀበል መብት ባገኘበት ጊዜ ነው::
4. በዚህ አዋጅ በተደነገገው መሠረት አንድ ሂሳብ ተከፋይ ሂሳብ ነው ተብሎ የሚያዘው ምክንያት የሆነው ግዴታ በትክክል የታወቀ ሲሆን ነው::ይሁን እንጂ ግዴታው የታወቀ ቢሆንም ለዚህ ሂሳብ መሠረት የሆነው የኢኮኖሚ ተግባር ከመከናወኑ በፊት እንደተከፋይ ሂሳብ አይያዝም::
5. ለንዑስ አንቀጽ /4/ አፈፃፀም የኢኮኖሚ ተግባር ተከናወነ የሚባለው:
   ሀ/ አገልግሎቶችን እና ንብረቶችን በተመለከተአገልግሎቱ በተሰጠ ወይም ንብረቱ በተገኘ ጊዜ ነው::
   ለ/ በንብረት መጠቀምን በተመለከተ ንብረቱ በጥቅም ላይ ለዋለበት ጊዜ ነው::
   ሐ/ በማናቸውም ሌሎች ሁኔታዎች ግዴታውን ለመወጣት የሚያስችለውን ሙሉ ክፍያ ግብር ከፋዩ በፈፀመበት ጊዜ ነው::

### 60. አስቀድሞ ስለተደረጉ ክፍያዎች

በዚህ አዋጅ አንቀጽ21 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ለመሬት ሊዝ የተፈፀመ ክፍያን ጨምሮ ማናቸውም ከአሥራ ሁለት ወራት በላይ ለሚቆይ አገልግሎት ወይም ማናቸውም ሌላጥቅም የተደረገ ወጪ ተቀናሽ ተፈፃሚ የሚሆነው አገልግሎቱ ወይም ጥቅሙ ሥራ ላይ በሚውልበት የግብር ዘመን ተከፋፍሎ ነው::

### 61. መብትን ስለመጠየቅ

1. ለግብር አከፋፈል ሲባል ሂሳቡን በጥሬ ገንዘብ እንቅስቃሴ ላይ በተመሠረተ የሂሳብ አያያዝ ዘዴ የሚይዝ ግብር ከፋይ ገንዘቡ ለመቀበል የሕግ መብት ያለው ወይም ክፍያ ለመፈፀም ግዴታ ያለበት መሆኑን በመግለፅ የይገባኛል ጥያቄ እስካቀረበ ድረስ ጠያቂው ገንዘቡን የመቀበል መብት ወይም የመክፈል የሕግ ግዴታ የሌለበት ቢሆንም እንዲህ ያለውን ሂሳብ እንደገቢ ወይም እንደወጪ መያዝ አለበት::
2. በንዑስ አንቀጽ/1/ የተነገረው ተፈፃሚ ከሆነ በኋላ ገንዘቡን የተቀበለው ሰው መልሶ የተካ ወይም ወጪ የተደረገ ሂሳብ እንዲመለስ የተደረገ እንደሆነ ገንዘቡ በተተካ ወይም ወጪው በተመለሰበት የግብር ዘመን ውስጥ የተገኘው ገቢ በዚሁ መሠረት መስተካከል አለበት::
3. ለግብር አከፋፈል ሲባል ሂሳቡን በተሰብሳቢና ተከፋይ ሂሳብ ላይ በተመሠረተ የሂሳብ አያያዝ ዘዴ የሚይዝ ግብር ከፋይ ገንዘብ ለመቀበል የሕግ መብት ያለው ወይም ክፍያ ለመፈፀም ግዴታ ያለበት መሆኑን በመግለፅ ጥያቄ እስካቀረበ ድረስ ጠያቂው ገንዘቡን የመቀበል መብት ወይም የመክፈል የሕግ ግዴታ የሌለበት ቢሆንም እንዲህ ያለውን ሂሳብ እንደተሰብሳቢ ወይም እንደተከፋይ ሂሳብ መያዝ አለበት::
4. በንዑስ አንቀጽ/3/ የተነገረው ተፈፃሚ ከሆነ በኋላ ጠያቂው ገንዘቡን ልቀበል ይገባል ወይም ክፍያ የመፈፀም ግዴታ አለብኝ በማለት ያቀረበውን ጥያቄ ያነሳ እንደሆነ ጥያቄውን ባነሳበት የግብር ዘመን ውስጥ ያገኘው ገቢ ተገቢ በሆነ አኳኋን እንዲስተካከል ይደረጋል::

### 62. ለረዥም ጊዜ ስለሚቆዩ ውሎች

1. ለግብር አከፋፈል ሲባል ሂሳቡን በተሰብሳቢና ተከፋይ ሂሳብ ላይ በተመሠረተ የሂሳብ አያያዝ ዘዴ የሚይዝ ግብር ከፋይ ለረዥም ጊዜ ከሚቆይ የንግድ ሥራ ውል ጋር በተያያዘ አንድ ሂሳብ በገቢ ውስጥ መቼ እንደሚካተት ወይም ተቀናሽ እንደሚደረግ የሚወሰነው በአንድ የግብር ዘመን ውስጥ ከውሉ ውስጥ የተጠናቀቀውን በመቶኛ በማስላት ይሆናል::
2. ከረዥም ጊዜ ውል ውስጥ የተጠናቀቀው በመቶኛ የሚወሰነው የውሉን ጠቅላላ ዋጋ እና ከግብር ዘመኑ ማለቂያ ጊዜ በፊት የተደረገውን ወጪ የተደረጉ ማስተካከያዎችን እና የዋጋ ውጣ ውረድን ጨምሮ ከተገመተው ጠቅላላ የውሉ ዋጋ ከሆነው ጋር በማነፃፀር ይሆናል::
3. የንግድ ሥራ የረዥም ጊዜ ውል በሚጠናቀቅበት የግብር ዘመን ውስጥ የንግድ ሥራውን የሚያካሂደው ሰው ለረዥም ጊዜ ከውሉች ጋር በተያያዘ
   ሀ/ የከሰረ ወይም
   ለ/ ያልተካካሰ እና በዚህ አዋጅ አንቀጽ 28 ንዑስ አንቀጽ/1/ መሠረት የሚሸጋገር ኪሣራ ያለው እንደሆነ፡
   ሐ/ የግብር አስገቢው ባለሥልጣን ኪሣራው ወደ አለፉት የግብር ዓመታት እንዲዘዋወር እና
   መ/ ለረዥም ጊዜ ከሚቆይ ውል ጋር በተያያዘ በአንድ የግብር ዘመን ከገቢ ላይ ከሚያዘው ወጪ ድረስ እስካልበለጠ ድረስ ከገቢው ላይ እንዲካካስ ያደርጋል::
4. አንድ ግብር ከፋይ በአንድ የግብር ዘመን ውስጥ በንግድ ሥራው እንቅስቃሴ ዉስጥ የሚያጋጥመው ኪሣራ ከንግድ ሥራው የረዥም ጊዜ ውሎች ጋር እንዲያያዝ ማድረግ የሚቻለው በግብር ዘመኑ ከንግድ ሥራው የረዥም ጊዜ ውሉች የተገኘውን ገቢ ለማስላት የተፈቀደው ወጪ ገቢውን ለመወሰን መሠረት ከተደረጉ ሂሳቦች የበለጠ እንደሆነ ነው::
5. በዚህ አንቀጽ ውስጥ "የንግድ ሥራ የረዥም ጊዜ ውል" ማለት ሥራው ተጀመረበት ጊዜ አንስቶ በ12 ወራት ውስጥ ይጠናቀቃል ተብሎ ከሚገመተው በስተቀር በተጀመረበት የግብር ዘመን ውስጥ ያልተጠናቀቀ የማምረት የመትከል ወይም የግንባታ ሥራ እንዲሁም ከእነዚህ ጋር የተያያዘ አገልግሎት ነው::

www.chilot.me

## ክፍል አራት
## ገቢን ስለማስታወቅ እና ግብርን ስለመወሰን

### 63. የግብር ዓመት

1. በተለየ ሁኔታ እንዲፈፀም ካልተወሰነ በስተቀር ግብር የሚወሰንበት ጊዜ /"የግብር ዓመት"/ ማለት የበጀት ዓመት ሲሆን ይህም ከሀምሌ 1ቀን እስከ ሰኔ 30 ቀን ድረስ ያለው ጊዜ ነው።
2. የግብር ከፋዮች የግብር ዓመት
   ሀ/ ግለሰቦችን እና የሽርክና ማኅበሮችን በሚመለከት የበጀት ዓመቱ
   ለ/ ድርጅቶችን በሚመለከት የድርጅቱ የሂሳብ ዓመት ነው።
3. ማናቸውም ድርጅት በግብር አሰገቢው ባለሥልጣን በቅድሚያ በፅሁፍ ካልተፈቀደለት እና ከፈቃዱ ጋር በተያያዘ የግብር አሰገቢው ባለሥልጣን የዘረጬራቸውን ሁኔታዎች ካላሟላ በስተቀር የሂሳብ ዓመቱን መለወጥ አይችልም።
4. የሂሳብ ዓመቱን እንዲለውጥ የተፈቀደለት ድርጅት ከፈቃዱ ጋር በተያያዘ ከተዘረዘሩት ጉዳታዎች አንዱን ያላሟላ እንደሆነ የግብር አሰገቢው ባለሥልጣን የፅሑፍ ማስታውቂያ በመስጠት ከዚሁ በላይ በንዑስ አንቀጽ/3/ መሠረት ለድርጅቱ የተሰጠውን ፈቃድ መሠረዝ ይችላል።
5. የግብር ከፋይ የሂሳብ ዓመት በንዑስ አንቀጽ /3/ ወይም /4/ መሠረት የተለወጠ እንደሆነ ለውጡ ከመደረጉ በፊት ባለው ሙሉ የግብር ዓመት እና አዲሱ የግብር ዓመት በሚጀመርበት ቀን መካከል ያለው ጊዜ "የመሸጋገሪያ ዓመት" በመባል የሚታወቅ እና በተለየ ሁኔታ የሚታይ ይሆናል።

### 64. የምስክር ወረቀት እና የሠንጠረዥ"ሀ" ገቢን ስለመወሰን

1. ቀጣሪው ለተቀጣሪው የሚሰጠው ግብር ተቀናሽ መደረጉን የሚያረጋግጠው የምስክር ወረቀት ተቀጣሪው ካገኘው የሠንጠረዥ "ሀ" ገቢ ላይ በምስክርወረቀቱ የተመለከተው ግብር ተቀናሽ ለመደረጉ ማረጋገጫ ነው።
2. ተቀጣሪው ካገኘው የሠንጣረዥ "ሀ" ገቢ ላይ ተቀንሶ የቀረውና በአንቀጽ 50 መሠረት ከተጣሪው ከሚቀርብ መግለጫ ጋር ለግብር አስገቢው ባለሥልጣን ገቢ የ. ደረገው ሂሳብ ገንዘቡ ገቢ ከተደረገበት ቀን ጀምሮ የሚፀና በግብር አስገቢው ባለሥልጣን የተወሰነ ግብር እንደሆነ ተደርጎ ይወሰዳል። ሆኖም የግብር አስገቢው ባለሥልጣን ስህተት ወይም ያልተከተተ ገቢ መኖሩን የደረሰበት እንደሆነ ማሻሻያ ለማድረግ ይችላል።
3. አንድ ተቀጣሪ በአንድ የግብር ዓመት ውስጥ ያገኘው ግብር የሚከፈልበት ገቢ የሚያገኝ ወይም የዲፕሎማቲክ መብት ባለቸው ዓለም ዐቀፍ ድርጅቶች የውጭ አገር መንግሥታት እምባሲዎች ሚሲዩናችና በማናቸውም የኮንስለር ተቋሞች የሚሠራ የሠንጠረዥ "ሀ" ገቢ ብቻ የሆነ እንደሆነ ገቢውን የማስታወቅ ግዴታ የለበትም።
4. ከዚሀ በላይ የተነገረው ቢኖርም ከአንድ በላይ ለሆነ ቀጣሪ ተቀጥር ገቢ የሚያገኝ ወይም የዲፕሎማቲክ መብት ባላቸው ዓለም አቀፍ ድርጅቶች የውጭ አገር መንግሥታት እምባሲዎች ሚሲዩኒችና በማናቸውም የኮንስለር ተቋሞች የሚሠራ የሠንጠረዥ"ሀ" ገቢ የሚያገኝ ተቀጣሪ በአንቀጽ 50/3 በተመለከተው ጊዜ ውስጥ ገቢውን ራሱ አስታውቆ ግብሩን መክፈል አለበት።
5. ከአንድ በላይ ለሆነ ቀጣሪ ተቀጥሮ ገቢ የሚያገኝ ሠራተኛን ቀጥሮ የሚያሠራ ሰው ሠራተኛው ከአንድ በላይ ለሆነ ቀጣሪ የሚሠራ መሆኑን ከደረሰበት እና ገቢው በሌላው ቀጣሪ ያልተጣመረ ስለመሆኑ ማስረጃ ሲቀርብለት ገቢውን አጣምሮ ግብሩን ይወስናል።

### 65. የሠንጠረዥ "ለ" እና "ሐ" ገቢን ስለማስታወቅ እና ግብር ስለመወሰን

1. ማንኛውም የሠንጠረዥ "ለ" እና "ሐ" ገቢ የሚያገኝ ግብር ከፋይ የግብር አሰገቢው ባለሥልጣን በሚያወጣው ቅጽ መሠረት።
   ሀ/ የደረጃ "ሀ" ግብር ከፋይ የግብር ዓመቱ በተጠናቀቀ በአራት ወር ጊዜ ውስጥ፣
   ለ/ የደረጃ "ለ" ግብር ከፋይ የግብር ዓመቱ በተጠናቀቀ በሁለት ወር ጊዜ ውስጥ ገቢውን ለግብር አስገቢው ባለሥልጣን ማስታወቅ አለበት።
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ/1/ መሠረት የሚቀርበው ሂሳብ ዓይነት የክልሉ ሥራ አስፈፃሚ በሚያወጣው ደንብ ይወሰናል።
3. በገቢ ማስታወቂያው መሠረት ከተሠላው ግብር ላይ በግብር ዓመቱ ውስጥ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 51 እና 52 መሠረት ከተከፋይ ሂሳብ ላይ ተቀናሽ የተደረገው እና በዚህ አዋጅ አንቀጽ 7 መሠረት እንዲካካስ የተደረገው በውጭ አገር የተከፈለ ታክስ ከተቀነሰ በኋላ ግብር ከፋዩ በልዩነት የሚፈለግበትን ግብር በገቢ ማስታወቂያው ጋር በአንድነት ለግብር አስገቢው ባለሥልጣን ገቢ ማድረግ አለበት።
4. ግብር ከፋዩ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /3/ መሠረት ከተሰላው ግብር የበለጠ ከፍሎ የተገኘ እንደሆነ የግብር አስገቢው ባለሥልጣን በአንቀጽ 75 በተደነገገው መሠረት የገቢውን ማስታወቂያ ትክክለኛነት ባረጋገጠ በ90 /ዘጠና/ ቀናት ውስጥ በብልጫ የተከፈለውን ለግብር ከፋይ መመለስ አለበት።
5. በገቢ ማስታወቂያው ላይ የተመለከተው እና በዘመኑ መከፈል ያለበት ግብር በግብር አሰገቢው ባለሥልጣን የተወሰነ ግብር ሆኖ ይቆጠራል። ሆኖም የግብር አስገቢው ባለሥልጣን ስህተት ወይም ያልተካተተ ገቢ ያለ መሆኑን ያረጋገጠ እንደሆነ ውሣኔውን በዚያው መጠን በማሻሻል የግብር ውሣኔ ማስታወቂያ ይሰጣል።

### 66. የሠንጠረዥ "መ" ገቢን ስለማስታወቅና ግብርን ስለመወሰን

1. የመጨረሻ ታክስ ሆኖ ከተከፋይ ሂሳብ ላይ ተቀንሶ ገቢ በሚደረገው ግብር የማይሸፈን የሠንጠረዥ "መ" ገቢ ያገኘ ማንኛቸውም ግብር ከፋይ የግብር አሰገቢው ባለሥልጣን በሚያወጣው ቅጽ መሠረት ገቢውን ማስታወቅ አለበት። ግብር ከፋዩ የዚህ ዓይነቱ የገቢ ማስታወቂያ ለግብር አስገቢ ባለሥልጣን የሚያቀርበው የኢትዮጵያ የበጀት ዓመት ከተጠናቀቀ ጊዜ ጀምሮ ባለው የሁለት ወር ጊዜ ውስጥ ነው።
2. በገቢ ማስታወቂያው መሠረት ከተሠላው ግብር ላይ በግብር ዓመቱ ውስጥ በአንቀጽ 7 መሠረት እንዲካካስ የተደረገው በውጭ አገር የተከፈለ የሠንጠረዥ "መ" ታክስ ከተቀነሰ በኋላ ቀሪውን ሂሳብ ግብር ከፋዩ ከገቢ ማስታወቂያው ጋር በአንድነት ለግብር አስገቢው ባለሥልጣን ገቢ ማድረግ አለበት።
3. የግብር አሰገቢው ባለሥልጣን ስህተት ወይም ያልተካተተ ገቢ መኖሩን ካላረጋገጠ በስተቀር በገቢ ማስታወቂያው ላይ የተመለከተው በዓመቱ መከፈል የሚገባው ግብር በግብር አሰገቢው ባለሥልጣን የተወሰነ ግብር ሆኖ ይቆጠራል።

### 67. የደረጃ"ሐ" ግብር ከፋዮችን ገቢ በቁርጥ ስለመወሰን

1. የደረጃ "ሐ" ግብር ከፋዮችን የግብር ግዴታ ለመወሰን የቁርጥ ግብር አወሳሰን ዘዴ በሥራ ላይ እንዲውል ይደረጋል።
2. የቁርጥ ግብር የክልሉ ስራ አስፈፃሚ በሚያወጣው ደንብ ውስጥ በተመለከተው በንግድ ሥራው ዓይነት በንግዱ ሥራ ስፋት የንግዱ ሥራ በሚገኝበት ቦታ ያሉትን ልዩነቶች የሚያንፀባርቅ የቁርጥ ግብር አወሳሰን ሠንጠረዥ መሠረት በማድረግ የሚወሰን የግብር መጠን ነው። የክልሉ ስራ አስፈፃሚ በሚፈቅደው መሠረት ግብሩን በየጊዜው ለመክፈል ካልጠየቀና ካልተፈቀደለት በስተቀር ግብር ከፋዩ የቁርጥ ግብሩን በየዓመቱ ከሐምሌ 1ቀን እስከ ሐምሌ 30ቀን ባለው ጊዜ ውስጥ ገቢ ማድረግ አለበት።
3. የቁርጥ ግብር መጠን በሥራ ላይ የሚቆይበት ጊዜ እና ለማሻሻያው መሠረት የሚሆኑ ጉዳዮች የፋይናንስ ቢሮ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል። የተሻሻለውን የቁርጥ ግብር መጠን ፋይናንስ ቢሮ ለገቢዎች መምሪያ ያሠራጫል።

### 68. ግብርን በግምት ስለመወሰን

1. ግብር ከፋዩ ምንም ዓይነት የሂሳብ መዝገብና ሠነድ ያልያዘ እንደሆነ ወይም በማናቸውም ምክንያት የሂሳብ መዝገቡን እና ሠነዱን የግብር አሰገቢው ባለስልጣን ያልተቀበለው እንዲሆን ወይም ግብር ከፋዩ በዚህ ሕግ በተወሰነው ጊዜ ውስጥ ገቢዉን ያላስታወቀ እንደሆነ የግብር አሰገቢው ባለሥልጣን የግብሩን ልክ በግምት ሊወሰን ይችላል።

www.chilot.me

2. ገብር በገምት የሚወሰንበት አኳኋን የፋይናንስ ቢሮ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል።

## 69. ገቢን ማጣመር

ገብር ከፋዩ በአንድ ሠንጠረዥ ሥር ገብር የሚከፈልበት ገቢ ከተለያየ የገቢ ምንጭ የሚያገኝ ሲሆን ገብሩ የሚወሰነው ገቢውን በማጠቃለል ይሆናል።

## 70. ይርጋ

1. ገብር ከፋዩ በዚህ አዋጅ በተመለከተው ጊዜ ውስጥና አኳኋን የገቢ ማስታወቂያውን ያቀረበ ከሆነ የገብር አስገቢው ባለሥልጣን የቀረበውን ማስታወቂያ አስተካክሉ ገብሩን መወሰን የሚችለው በ5/አምስት/ ዓመት ጊዜ ውስጥ ነው። ይህም የ5/አምስት/ ዓመት ጊዜ መቆጠር የሚጀምረው የገቢ ማስታወቂያው መቅረብ ካለበት የመጨረሻ ቀን ጀምሮ ይሆናል።
2. ገብር ከፋዩ በዚህ አዋጅ በተመለከተው አኳኋን የገቢ ማስታወቂያውን ያቀረበ ሆኖ ማስታወቂያው የቀረበው ገቢን ለማስታወቂያ ከተወሰነው ጊዜ በኋላ የሆነ እንደሆነ የገብር አስገቢው ባለሥልጣን በ5 /አምስት/ ዓመት ጊዜ ውስጥ የቀረበውን ማስታወቂያ አስተካክሉ ገብሩን መወሰን ይችላል። ይህም የ5 /አምስት/ ዓመት ጊዜ የሚቆጠር የሚጀምረው የገብር አስገቢው ባለሥልጣን የገቢ ማስታወቂያውን ከተቀበለበት ቀን አንስቶ ነው።
3. ገብር ከፋዩ ገቢውን ያላስታወቀ ወይም የተጭበረበረ የገቢ ማስታወቂያ ያቀረበ እንደሆነ የገብር አስገቢው ባለሥልጣን በማናቸውም ሌላ ሕግ የተደነገገው ይርጋ ሳያግደው ገብሩን በማናቸውም ጊዜ መወሰን ይችላል።

## ክፍል አምስት
## የግብር ውሣኔ ማስታወቂያ

## 71. የግብር ውሣኔ ማስታወቂያ ይዘት

እያንዳንዱ የገብር ውሣኔ ማስታወቂያ የሚከተሉትን አሟልቶ መያዝ አለበት፤

1. ጠቅላላ ገቢን እና በዚህ አዋጅ መሠረት ተቀናሽ የሚሆኑትን ወጪዎች፤
2. ገብር የሚከፈልበትን ገቢ ፤
3. ተፈፃሚነት የሚኖረውን የማስከፈያ ልክ ወይም መጣኝ
4. የተከፈለውንና ቀሪውን ገብር፤
5. ማናቸውንም መቀጮ ወይም ወለድ፤
6. የገብር ከፋዩን ስም አድራሻ የገብር ከፋይ መለያ ቁጥር ፤
7. የገብሩን አወሳሰን ዘዴ እና ገብር ከፋዩ ስላለው መብት አጭር ማብራሪያ ።

## 72. የግብር ውሣኔ ማስታወቂያዎች ስለሚደርሱበት ሁኔታ

1. የገብር አስገቢው ባለሥልጣን ለገብር ከፋዩ የሚሰጣቸው የገብር ውሣኔ ማስታወቂያዎች ወይም ሌሎች ማስታወቂያዎች በሚከተለው ሁኔታ ለገብር ከፋዩ በጽሑፍ ይደርሳሉ።
   ሀ/ ተቀማጭነቱ በኢትዮጵያ ውስጥ ለሆነ ሰው በአደራ ፖስታ ወይም በቀጥታ ለገብር ከፋዩ በእጁ በመስጠት ወይም፣ እሱ የሌለ እንደሆነ ከቤተሰቦቹ ውስጥ ለማንኛውም አካለ መጠን ለደረሰ ወይም በመኖሪያው ወይም የሙያ ወይም የንግድ ሥራ በሚሠራበት ሥፍራ ቀጥሮ ለሚያሰራው ማንኛውም ሰው በመስጠት፤ ሆኖም ማስታወቂያውን የሚቀበል ሰው ካልተገኘ ይኸው ማስታወቂያ በገብር ከፋዩ መኖሪያ ቤት በር ላይ ወይም የመኖሪያ ቤቱ ክፍል በሆነ ወይም በንግድ ሥራ አመቺ ሥፍራ በመለጠፍ፤
   ለ/ ተቀማጭነቱ በኢትዮጵያ ውስጥ ለሆነ ድርጅት በአደራ ፖስታ አማካኝነት በተመዘገበው የድርጅቱ አድራሻ በመላክ ወይም በድርጅቱ የንግድ ሥራ ቦታ ለሚገኘው ማንኛውም የሥራ መሪ ወይም ተቀጣሪ በመስጠት፤
   ሐ/ ተቀማጭነታቸው በኢትዮጵያ ላልሆኑ ሰዎች በኢትዮጵያ ላለው ወኪል ወይም ወኪሎች በእጅ በመስጠት ወይም የማይገኝ ከሆነ ወኪሉ በሚሠራበት የንግድ ሥራ ቦታ ወይም በሌላ አመቺ በሆነ ሥፍራ በመኖሪያ ቤቱ ላይ በመለጠፍ፤

ከእነዚህ አርምጃዎች አንዱም በማንኛውም ምክንያት ካልተሳካ የፍርድ ቤት ማስታወቂያዎች በሚወጡበት ማንኛውም ጋዜጣ ላይ በማሳተም ሊፈፀም ይችላል። ለማሳተሚያ የወጣው ወጪ በገብር ከፋዩ ላይ ይታሰባል።

2. የገብር አስገቢው ባለሥልጣን ለገብር ከፋዩ አግባብ ባለው መንገድ የሰጠው ማንኛውም የገብር ውሣኔ ማስታወቂያ የሚከተሉት ሁኔታዎች ተሟልተው ሲገኙ የመጨረሻና ተፈፃሚነት ያለው ይሆናል።
   ሀ/ ገብር ከፋዩ የገብር ውሳኔ ማስታወቂያ ከደረሰው ወይም የአቤቱታ አጣሪ ኮሚቴ ውሳኔ ከሰጠበት ቀን ጀምሮ ባሉት ሰላሳ /30/ ቀናት ውስጥ የሚፈለግበትን ገብር ካልከፈለ ወይም ለገብር ይግባኝ ጉባዔ ይግባኝ ካላቀረበ ወይም
   ለ/ በዚህ አዋጅ በተጠቀሰው የጊዜ ገደብ ውስጥ የገብር ይግባኝ ጉባዔ የሰጠው ውሳኔ ይግባኝ ያልቀረበበት ከሆነ ወይም
   ሐ/ የይግባኝ ፍርድ ቤቱ የመጨረሻ ውሳኔ ከሰጠ።
3. በንዑስ አንቀጽ /2/ መሠረት የመጨረሻና ተፈፃሚ በሚሆነው የገብር ውሣኔ መሠረት የሚፈለግበትን ገብር ያልከፈለ ገብር ከፋይ ጥፋተኛ ነው።

## ክፍል ስድስት
## ክፍያ

## 73. ገብር በሕግ በተወሰነው ጊዜ መከፈል ያለበት ስለመሆኑ

ማናቸውም በተወሰነ ቀን ለገብር አስገቢው ባለሥልጣን ገቢ መደረግ ያለበት ገብር /ከተከፋይ ሂሳብ ላይ ተቀንሶ የተያዘ ወይም የተሰበሰበ ታክስ ጭምር/ በዚህ በተወሰነው ቀን ገቢ መደረግ አለበት። በተወሰነው ጊዜ ውስጥ ገብርን ያለመክፈል ወለድ እና ገቢው ለዘገየበት መቀጮ የመክፈል ግዴታን ያስከትላል።

## 74. ወለድ

1. ማንኛቸውም ገብር ከፋይ የሚፈለግበትን ገብር በወቅቱ ያልከፈለ እንደሆነ ገብር መከፈል ከነበረበት ጊዜ ጀምሮ እስከተከፈለበት ቀን ድረስ ባልተከፈለው የገብር መጠን ላይ ወለድ የመክፈል ግዴታ አለበት።
2. ከዚህ በላይ በንዑስ አንቀጽ /1/ መሠረት የሚከፈለው ወለድ የማስከፈያ ልክ ባለፈው የሩብ ዓመት በንግድ ባንኮች ሥራ ላይ በዋለው ከፍተኛው የማበደሪያ ወለድ መጣኔ ላይ 25 ፐርሰንት /ሃያ አምስት በመቶ/ ታክሎበት ይሆናል።
3. ወለዱ የሚሰበሰበው ወለድ የሚከፈልበት ገብር በሚሰበሰብበት ዓይነት ነው።

## 75. ማካካሻ እና ተመላሽ ሂሳብ

1. የገብር አስገቢው ባለሥልጣን ከተከፋይ ሂሳብ ላይ ተቀንሶ ገቢ የተደረገው ወይም በየጊዜው የተከፈለው ገብር ወይም በሌላ ማናቸውም ሁኔታ የተከፈለ ገብር ገብር ከፋዩ ሊከፍል ከሚገባው ገብር በላይ መሆኑን ያረጋገጠ እንደሆነ
   ሀ/ ሊከፈል ከሚገባው በላይ የተከፈለ ታክስ ገብር ከፋዩ ለሚፈለግበት፦
      1. በዚህ አዋጅ መሠረት ለሚከፈሉ ሌሎች ገብሮች፤
      2. በዚህ አዋጅ መሠረት ከተከፋይ ሂሳብ ላይ ተቀንሶ ለሚቀረው ገብር፤
      3. በዚህ አዋጅ ወይም በሌሎች የገብርና የቀረጥ ሕጎች መሠረት ገብር ከፋዩ ለሚፈለግበት ሌላ ማናቸውም የገንዘብ መጠን እንዲካካስ ማድረግ፤
   ለ/ የሂሳቡን ትክክለኛነት ባረጋገጠ በዘጠና ቀናት ጊዜ ውስጥ ተራፊውን ሂሳብ ለገብር ከፋዩ መመለስ አለበት።
2. ከዚህ በላይ በንዑስ አንቀጽ 1/ለ/ በተመለከተው ጊዜ ውስጥ ገብር ከፋዩ ተመላሹን ሂሳብ ያላገኘ እንደሆነ ባለፈው ሩብ ዓመት በንግድ ባንኮች ሥራ ላይ በዋለው ከፍተኛው የማበደሪያ ልክ ላይ 25 ፐርሰንት/ሃያ አምስት በመቶ /ታክሎ ወለድ ይከፈለዋል።
3. ከዚህ በላይ በንዑስ አንቀጽ /1/ በተነገረው ሳይወሰን ገብር ከፋዩ በብልጫ የከፈለው ገብር እንዲመለስለት በዚህ አንቀጽ መሠረት ለመጠየቅ ይችላል በብልጫ የተከፈለ ገብር እንዲመለስ የሚቀርብ ጥያቄ ከዚህ በታች ከተዘረዘሩት ዘግይቶ ከተፈፀመው ጀምሮ በሦስት ዓመት ጊዜ

www.chilot.me

ውስጥ ለግብር አሰገቢው ባለሥልጣን በጽሑፍ መቅረብ አለበት

ሀ/ የተመላሽ ጥያቄ ከሚቀርብበት ግብር ጋር በተያያዘ የግብር አሰገቢው ባለሥልጣን ለግብር ከፋዩ የግብር ውሣኔ ማስታወቂያ ከሰጠበት ቀን፤

ለ/ ግብሩ ወይም ወለዱ ከተከፈለበት ቀን።

4. የግብር አሰገቢው ባለሥልጣን በንዑስ አንቀጽ /2/ መሠረት በቀረበ የተመላሽ ጥያቄ ላይ ውሣኔ ከሰጠበት ቀን ጀምሮ በ45 ቀናት ውስጥ የተመላሽ ጥያቄ ላቀረበው ግብር ከፋይ የተሰጠውን ውሣኔ የሚገልጽ ማስታወቂያ በጽሑፍ እንዲደርሰው ማድረግ አለበት።

5. በንዑስ አንቀጽ /4/ መሠረት በተሰጠ ውሣኔ ቅር የተሰኘ ግብር ከፋይ ውሣኔው የግብር ውሣኔ እንደሆነ ተቆጥሮ በይግባኝ ሥርዓት መሠረት በውሣኔው ላይ ይግባኝ የማቅረብ መብት አለው።

## ክፍል ሰባት
## የግብር አሰባሰብ አፈፃፀም

### 76. የግብር ከፋዩን ሀብት ስለመያዝ

1. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /4/ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በማንኛውም በዚህ አዋጅ የተጣለው ግብር የሚፈለግበት ሰው በአንቀጽ 72/3/ በተደነገገው መሠረት ጥፋተኛ ሆኖ የተገኘ እንደሆነ የግብር አሰገቢው ባለሥልጣን የዚህን ግብር ከፋይ ሀብት በመያዝ ለሚፈለግበት ግብር እና ንብረቱን ለመያዝ ለተደረገው ተጨማሪ ወጪ ለመሸፈን እንዲውል ማድረግ ይችላል። የመንግሥት ሠራተኞችን ጨምሮ የማንኛውንም ሠራተኛ ደመወዝ ለሠራተኛው ደመወዝ የመክፈል ኃላፊነት ላለበት ኃላፊ ማስታወቂያ በመስጠት እንዲያዝ ማድረግ ይቻላል።

2. ለዚህ ክፍል አፈፃፀም "መያዝ" በማናቸውም መንገድ መያዝን እንዲሁም የግብር ከፋዩ የሆነ ገንዘብ ወይም ንብረት በእጁ ከሚገኝ ሰው ግብር መሰብሰብን ይጨምራል። በንዑስ አንቀጽ /3/ እና /6/ በተነገረው መሠረት ካልሆነ በስተቀር መያዝ የሚቻለው የመያዙ ትዕዛዝ በተሰጠበት ጊዜ በይዞታ ሥር የሚገኝ ንብረት እና የመያዙ ተግባር በሚከናወንበት ጊዜ ዕንቶ ያለግዴታን በተመለከተ ብቻ ነው። የግብር አሰገቢው ባለሥልጣን የግብር ከፋዩን ሀብት በሚይዝበት ጊዜ የፖሊስ ሠራዊት አባል እንዲገኝ ሊጠይቅ ይችላል። ባለሥልጣኑ ከዚህ በላይ በተመለከተው መሠረት ሀብቱን ከያዘበት ቀን አንስቶ ከሚቆጠር 10 ቀናት ጊዜ በኋላ በሐራጅ ወይም በባለሥልጣኑ ብተፈቀደ በማናቸውም ሌላ ዘዴ የያዘውን ንብረት መሸጥ ይችላል። ሆኖም ንብረቱ የሚበላሽ ከሆነ የንብረቱን ባህርይ ከግንተ ውስጥ በማስገባት ተገቢመስሎ በታየው ጊዜ ሊሸጠው ይችላል።

3. ማናቸውም የተያዘ ንብረት ለመያዙ ምክንያት የሆነውን የግብር ዕዳ ለመሸፈን በቂ ሳይሆን የቀረ እንደሆነ የግብር አሰገቢው ባለስልጣን ከግብር ከፋዩ ላይ የሚፈለገው የግብር ዕዳ እና ከዚህ ጋር የተያያዙ ልዩ ልዩ ወጪዎች ተከፍለው እስከሚጠናቀቁ ድረስ የግብር ዕዳው የሚፈለግበትን ሰው ሌሎች ሀብቶች መያዝ ይችላል።

4. ከዚህ በላይ በንዑስ አንቀጽ /1/ በተደነገገው መሠረት ባልተከፈለ የግብር ዕዳ ምክንያት በመቀጠር የሚገኝን ገቢ ወይም ሌላ ንብረት መያዝ የሚቻለው የግብር አሰገቢው ባለሥልጣን ሀብቱን የመያዝ ሀሳብ እንዳለው አስቀድሞ ለግብር ከፋዩ በጽሑፍ ካስታወቀው በኋላ ይሆናል። በዚህ ዓይነት የሚሰጠው ማስታወቂያ ሀብቱ ከመያዙ ከ30 ቀን በፊት ለግብር ከፋዩ ሊደርሰው ይገባል።

5. የግብር አሰገቢው ባለሥልጣን የግብሩን አሰባሰብ የሚያደናቅፍ ሁኔታ መኖሩን የተረዳ እንደሆነ በንዑስ አንቀጽ1 የተመለከተው የ30 ቀን የጊዜ ገደብ እና በንዑስ አንቀጽ4 የተመለከተው ሳይጠበቅ ግብሩ ወዲያውኑ እንዲከፈል ለማድረግ ጥያቄ ከቀረበና ግብር ከፋዩ ለመክፈል ፈቃደኛ ካልሆነ ንብረትን በመያዝ ግብር የመሰብሰቡ አፈፃፀም ሕጋዊ ይሆናል።

6. ለግብር ከፋዩ የሚከፈለውን ደመወዝ የመያዝ አፈፃፀም ውጤት ደመወዙ እንዲያዝ ከተደረገበት ቀን ጀምሮ የግብሩ ዕዳ ተከፍሉ እስከሚያልቅ ወይም የግብሩ ዕዳ በይርጋ ምክንያት ሊጠየቅ የማይቻል እስከሚሆንበት ጊዜ ድረስ ይቀጥላል።

7. ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ገቢዎች እና ንብረቶች ከመያዝ ነፃ ናቸው።

ሀ/ በሠንጠረዥ "ሀ" ከግብር ነፃ ከተደረገው የገቢ መጠን ሳያልፍ ሠራተኛ የሚያገኘው ደመወዝ ወይም ማናቸውም በተወሰነ ጊዜ የሚገኝ ሌላ ገቢ

ለ/ በማናቸውም የኢትዮጵያ ሕግ እንዳይከበሩ የተደረጉ ገቢዎች ወይም ንብረቶች፡

### 77. የንብረት መያዝ ውጤት

1. በፍርድ ቤት ትዕዛዝ የተከበረ ወይም በአፈፃፀም ላይ ያለ ወይም በአንቀጽ 79 በተመለከተው መሠረት በዋስትና የተያዘ ካልሆነ በስተቀር ማናቸውም በግብር ምክንያት የተያዘ ንብረት በእጁ የሚገኝ ወይም ለግብር ከፋዩ ማናቸውም ግዴታ ያለበት ሰው የግብር አሰገቢው ባለሥልጣን ሲጠይቀዉ የያዘውን ሀብት የማስረከብ ወይም ያለበትን ግዴታ የመፈፀም ኃላፊነት አለበት።

2. ማናቸውም ሰው የግብር አሰገቢው ባለሥልጣን ሲጠይቀው አንድን የተያዘ ንብረት ለማስረከብ ፈቃደኛ ሳይሆን የቀረ እንደሆነ በተያዘው ንብረት መጠን በግል ተጠያ ይሆናል። ሆኖም ተጠያቂነቱ ለንብረቱ መያዝ ምክንያት ከሆነው የግብር ዕዳ መጠን /በግብሩ ዕዳ ላይ የሚታሰበውን ወጪ እና ወለድ ጨምሮ/ ሊያልፍ አይችልም።

3. በንዑስ አንቀጽ 2 ከተመለከተው ይግል ተጠያቂነት በተጨማሪ ንብረቱን የያዘው ሰው ንብረቱን ለማስረከብ ፈቃደኛ ያልሆነው ያለበቂ ምክንያት ከሆነ በንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት የሚፈለገውን የገንዘብ መጠን 50 ፐርሰንት /ሃምሣ በመቶ/ በተጨማሪ እንዲከፍል ይደረጋል።

4. በዚህ አንቀጽ መሠረት በይዞታው ሥር ያለውን ንብረት ያስረከበ ወይም በግብር ከፋዩ የሚፈለግበትን ገንዘብ ከግብር አሰገቢው ባለሥልጣን በተጠየቀው መሠረት ገቢ ካደረገው ገንዘብ ጋር በተያያዘ የግብር ግዴታውን ባልተወጣው ግብር ከፋይ ወይም ማናቸውም ሌላ ሰው ከሚፈለግበት ዕዳ ወይም ካለበት ግዴታ ነፃ ይሆናል።

### 78. የሂሣብ መዝገብ ስለማቅረብ

ማናቸውም ንብረት የተያዘ ወይም እንዲያዝ የታሰበ ከሆነ ስለዚሁ ንብረት ማስረጃ የሚሆን ወይም መግለጫ የያዘ ሰነድ ወይም መዝገብ በእጁ የሚገኝ ወይም በቁጥጥሩ ሥር ያለ ማናቸውም ሰው በግብር አሰገቢው ባለሥልጣን ጥያቄ ሲቀርብለት ሰነዱን ወይም መዝገቡን ለማስረጃነት ማቅረብ አለበት።

### 79. ሀብት ላይ የሚቀርብ የቀደምትነት መብት ጥያቄ

1. ዋስትና የተሰጣቸው የሌሎች አበዳሪዎች የቅድሚያ መብት እንደተጠበቀ ሆኖ በዚህ አዋጅ መሠረት ግብር ተከፋይ ከሚሆንበት ቀን አንሥቶ ተከፍሎ እስካለቀበት ጊዜ ድረስ ግብር የመክፈል ግዴታ ባለበት ሰው ሀብት ላይ ባለሥልጣኑ ከማናቸውም ሌሎች ዕዳዎች የቀደምትነት መብት ይኖረዋል።

2. ማንኛውም ሰው ግብር የመክፈል ግዴታውን ባለመወጣት ጥፋተኛ ሆኖ የተገኘ እንደሆነ የግብር አሰገቢው ባለሥልጣን በጥፋት ምክንያት ያልተከፈለውን ግብር እና ግብሩን ለማስከፈል የሚደረገው እንቅስቃሴ የሚያስከትለውን ወጪ ማስከፈል እንዲቻል የግብሩ ዕዳ የሚፈለግበት ሰው ሀብት በዋስትና ተይዞ እንዲቆ ንብረቱን ለመዘገበው አካል የጽሑፍ ትዕዛዝ የሚሰጥ መሆኑን በመግለጽ ለግብር ከፋዩ ማስጠንቀቂያ ይሰጣል።

3. በንዑስ አንቀጽ/2/ የተገለጸው ማስጠንቀቂያ የደረሰው ግብር ከፋይ ማስጠንቀቂያው በደረሰው በ30 ቀን ውስጥ ግብሩን ያልከፈለ እንደሆነ የግብር አሰገቢው ባለሥልጣን ለመዝጋቢው ባለሥልጣን የግብር ከፋዩ ሀብት ባልተከፈለው የግብር ዕዳ መጠን በዋስትና ተይዞ እንዲቆይ ትዕዛዝ ይሰጣል።

4. በንዑስ አንቀጽ 3 መሠረት የግብር አሰገቢው ባለሥልጣን ግብር የሚፈለግበት ሰው ሀብት በዋስትና ተይዞ እንዲቆይ ትዕዛዝ የሰጠ ሲሆን መዝጋቢው ባለሥልጣን ማናቸውንም ክፍያ ሳይጠይቅ ንብረቱ በዋስትና እንዲያዝ የደረሰውን ትዕዛዝ እንደ ማናቸውም በሀብቱ ላይ እንዳለ የመያዥ ሰነድ ይመዘግባል ቀደም ሲል የተሰጠ የመያዥ መብት እንደተጠበቀ ሆኖ የዋስትናው ምዝገባ የሚፈለገውን ግብር ለማስከፈል በማናቸውም መልኩ በሕግ እንደተሰጠ መያዣ ወይም እንደማናቸውም ሌላ ዕዳ ወይም ክፍያ ሆኖ ይቆጠራል።

www.chilot.me

## 80. የግብር አወሳሰንን ሊያደናቅፍ የሚችል ሁኔታ መኖር

የግብር አሰገቢው ባለሥልጣን የግብሩን አሰባሰብ የሚያደናቅፍ ሁኔታ መኖሩን የሚያሳምን በቂ ምክንያት ያገኘ እንደሆነ እና አስቸኳይ ሁኔታ ሲያጋጥም ትዕዛዙን የሚደግፍ መግለጫ በማያያዝ የግብር ከፋዩ የባንክ ሂሣብ እንዲታገድ እና ስለ ግብር ከፋዩ የፋይናንስ እንቅስቃሴ መረጃ እንዲሰጠው የአስተዳደር ትዕዛዝ ሊሰጥ እና ግብሩንወዲያውኑ መወሰን ይችላል:: ይሁን እንጂ የግብር አሰገቢው ባለሥልጣን ከዚህ በላይ የተመለከተውን አስተዳደራዊ ትዕዛዝ ካስተላለፈበት ቀን ጀምሮ ባሉት አሥር ቀናት ውስጥ ፍ/ቤት ትዕዛዙን እንዲያጸድቅለት ማድረግ አለበት:: የግብር አሰገቢው ባለሥልጣን በዚህ አንቀጽ የተሰጠውን ሥልጣን መጠቀም የሚችለው የግብሩን አወሳሰን ግልጽ ለማድረግ የሚረዳ መረጃ ለማግኘት ብቻ ነው::

## 81. ከተከፋይ ሂሣብ ላይ ተቀንሶ በቀረ ግብር ላይ ስለሚኖር የይገባኛል ቅድሚያ

1. በዚህ አዋጅ መሠረት ከተከፋይ ሂሣብ ላይ ግብር ቀንሶ መያዝ ባለበት ሰው ተቀንሶ የተያዘ ግብር፣
   - ሀ/ የተያዘው ግብር አሰገቢውን ባለሥልጣን በመወከል ይሆናል:
   - ለ/ ግብሩን ቀንሶ የያዘው ሰው ላለበት ዕዳ ወይም ማናቸውም ሌላ ተጠያቂነት እንዲከበር ማድረግ አይቻልም::
   - ሐ/ ግብሩን ቀንሶ የያዘው ሰው የከሰረ ወይም ሂሣቡ በመጣራት ላይ በሚሆንበት ጊዜ ተቀንሶ የቀረው ግብር በመጣራት ላይ ያለው በዕዳ ምክንያት የሚተላለፈው ወይም የከሰረው ድርጅት ሀብት ክፍል ሆኖ አይቆጠርም:: በመሆኑም የግብር አሰገቢው ባለሥልጣን በዚህ ሂሣብ ላይ የሀብት ክፍፍል ከመደረጉ በፊት የይገባኛል ቅድሚያ መብት ይኖረዋል::
2. በዚህ አዋጅ መሠረት ግብርን ቀንሶ ገቢ የማድረግ ግዴታ ያለበት ሰው ከተከፋይ ሂሣብ ላይ ቀንሶ የሚያስቀረው ግብር:
   - ሀ/ ከከፍያው ላይ በመጀመሪያ የሚቀነስ ይሆናል::
   - ለ/ ግብርን ቀንሶ ገቢ የማድረግ ግዴታ ያለበት ሰው በፍ/ቤት ትዕዛዝ ወይም በማናቸውም ሕግ መሠረት ከተከፋይ ሂሣብ ላይ መቀነስ ካለበት ሌላ ሂሳብ በፊት ቅድሚያ ይኖረዋል::

## 82. ግብር ከፋዩ ስላለው ጥበቃ

በዚህ ክፍል መሠረት የተያዘ ማናቸውም ንብረት የሚያዘው፣ የሚጠበቀው፣ እና የሚመዘገበው በግብር አሰገቢው ባለሥልጣን ብቻ ይሆናል:: ማናቸውም ሌላ የመንግሥት አካል በዚህ ክፍል መሠረት የተያዘውን ንብረት ማናቸውንም ሌላ ምክንያት መሠረት በማድረግ እንዲሰጠው ወይም እንዲተላለፍለት መጠየቅ አይችልም:: በዚህ ክፍል መሠረት የተያዘ ንብረት የተሸጠ እንደሆነ ከሽያጩ ከተገኘው ገንዘብ ውስጥ ግብር ከፋዩ ከሚፈለግበት ዕዳ በላይ የሆነው ገንዘብ ለንብረቱ ባለቤት ወዲያውኑ ይመለሳል::

# ክፍል ስምንት

# ሽልማቶች እና አስተዳደራዊ መቀጫዎች

## 83. ለተረጋገጠ መረጃ ስለሚሰጥ ሽልማት

1. ግብር የሚከፈልበትን ገቢ በሚደብቅ አሳንሶ በሚያስታውቅ በሚያጭበረብር ወይም በሌላ በማናቸውም መንገድ ሳይከፍል በሚቀር ግብር ከፋይ ላይ በተጨባጭ መረጃ በመደገፍ ሪፖርት የሚያቀርብ ሰው የተደበቀውን ግብር እስከ ሃያ በመቶ /20 ፐርሰንት/ ድረስ ግብሩ ሲሰበሰብ እንዲያገኝ ይደረጋል::
2. ይሁን እንጂ መረጃ አቅራቢው
   - ሀ/ የግብር አለመከፈሉ ድርጊት ተካፋይ ከሆነ ወይም
   - ለ/ ይህን ማድረግ የሥራው አንድ አካል ከሆነ ለዚህ ሽልማት ተጠቃሚ ሊሆን አይችልም::
3. ዝርዝሩ የፋይናንስ ቢሮ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል::

## 84. ለከፍተኛ የሥራ ውጤት ስለሚሰጥ ሽልማት

1. የግብሩ ባለሥስልጣን እርእያንት ባለው ሁኔታ የግብር መክፈል ግዴታቸውን ለሚፈጡ ግብር ከፋዮች እና ከፍተኛ የሥራ ብቃቱ ለሚያሣዩ የግብር ባለሥልጣኑ ሠራተኞች ሽልማት ይሰጣል::
2. ዝርዝር የፋይናንስ ቢሮ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል::

## 85. ገቢን ባለማስታወቅ ወይም ዘግይቶ በማስታወቅ የሚከፈል መቀጫ

ማንኛውም ግብር ከፋይ በሕግ በተወሰነው ጊዜ ውስጥ ገቢውን ያላስታወቀ እንደሆነ የሚከተለውን መቀጫ ይከፍላል:

- ሀ/ ገቢውን ሳያስታውቅ ለዘገየበት ለመጀመሪያው 30 ቀን ወይም የዚህ ክፍል ለሆነው ጊዜ ብር 1 ሺህ /አንድ ሺህ/
- ለ/ ገቢውን ሳያስተውቅ ለዘገየበት ለተጨማሪው 30 ቀን ወይም የዚሁ ክፍል ለሆነው ጊዜ ብር 2 ሺህ /ሁለት ሺህ/
- ሐ/ ከዚህ በላይ ላለው ገቢውን ሳያስታውቅ ለዘገየበት ለእያንዳንዱ 30 ቀን ብር 1,500 /አንድ ሺህ አምስት መቶ/::

## 86. ግብርን አሳንሶ በማስታወቅ የሚከፈል መቀጫ

1. ማናቸውም ግብር ከፋይ በገቢ ማስታወቂያው ላይ ሊከፍል የሚገባውን ግብር አሳንሶ ያስታወቀ እንደሆነ ያሳነሰውን ግብር መጠን አሥር በመቶ /10ፐርሰንት/ ወይም በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 እንደተመለከተው የተቀነሰው ገቢ ከፍተኛ የሆነ እንደሆነ አሳንሶ ያስታወቀውን ግብር ሃምሳ በመቶ /50ፐርሰንት/ መቀጫ ይከፍላል::
2. ግብር ከፋዩ አሳንሶ ያስታወቀው ግብር ከፍተኛ ነው የሚባለው ከዚህ በታች ከተመለከቱት ከአነስተኛው የበለጠ እንደሆነ ነው:
   - ሀ/ በገቢ ማስታወቂያ መታየት ካለበት ግብር 25 ፐርሰንት /ከሃያ አምስት በመቶ/:
3. ግብር ከፋዩ ይግባኝ ያቀረበ ቢሆንም ይግባኙን የሚመረምረው የይግባኝ ሰሚ ጉባዔ ወይም ፍርድ ቤት የመጨረሻውን ውሣኔ እስከሚሰጥ ድረስ የመቀጫው ተፈጻሚነት ይቀጥላል::

## 87. አዘግይቶ በመክፈል የሚጣል መቀጫ

ማናቸውም ግብር ከፋይ የሚፈለግበትን ግብር በሕግ በተወሰነው ጊዜ ውስጥ ያልከፈለ እንደሆነ የሚከተለው መቀጫ ይጣልበታል:

- ሀ/ ግብሩ ሊከፈል ከሚገባው ቀን ለአንድ ቀን ከዘገየ ያልተከፈለውን ግብር 5 ፐርሰንት /አምስት በመቶ /
- ለ/ ከዚህ በኋላ ላለው ለእያንዳንዱ ወር የመጀመሪያ ቀን ሳይከፈል የቀረውን ግብር ሁለት በመቶ /2 ፐርሰንት/

## 88. ተገቢን የሂሣብ መዝገብ ባለመያዝ የሚጣል መቀጫ

1. ማናቸውም ግብር ከፋይ ለአንድ የተወሰነ የግብር ዘመን መያዝ የሚገባውን ተገቢ የሂሣብ ሰነድ የሂሳብ መዝገብ እና መግለጫ ያልያዘ እንደሆነ የተወሰነበትን ግብር 20 ፐርሰንት መቀጫ ይከፍላል:
2. የግብር አሰገቢው ባለሥልጣን ግብር ከፋዩ ተገቢውን የሂሣብ መዝገብ ሰነድ እና ሉሎችንም መረጃዎች ለሁለት ተከታታይ ዓመታት ሳይዝ የቀረ መሆኑን ሲደርስበት:
   - ሀ/ የግብር አሰገቢው ባሥልጣን ይህንኑ የሚገልጽ ማስታወቂያ ሲልክለት ፈቃድ ሰጪው ቢሮ የግብር ከፋዩን የንግድ ሥራ ፈቃድ ወዲያውኑ ያግዳል::
   - ለ/ ግብር ከፋዩ ተገቢውን የሂሣብ መዝገብ ሰነድ እና ሌሎችንም መረጃዎች በሦስተኛው ዓመትም ያላቀረበ እንደሆነ ይህንኑ የሚገልጽ ማስታወቂያ ሲደርሰው ፈቃድ ሰጪው መ/ቤት የግብር ከፋዩን የንግድ ሥራ ፈቃድ ይሠርዛል::
   - ሐ/ የግብር አሰገቢው ባለሥልጣን ግብር ከፋዩ መዝገብ የመያዝ ግዴታውን ያልተወጣ መሆኑን ሲደርስበት ከዚህ በላይ በተደነገገው መሠረት የግብር ከፋዩ የንግድ ሥራ ፈቃድ እንዲታገድ ወይም እንዲሠረዝ ለፍቃድ ሰጪው ባለሥልጣን የሚልከው ማስታወቂያ በዚህ አዋጅ መሠረት እንደተሰጠ የግብር ውሣኔ ማስታወቂያ ሆኖ ይቆጣጠራል:: ስለሆነም የግብር አሰገቢው ባለሥልጣን ግብር ከፋዩ ግዴታውን ያልተወጣ ለመሆኑ የመጨረሻ ማረጋገጫ ከማግኘቱ በፊት ማስታወቂያውን መላክ የለበትም::

www.chilot.me

## 89. ከተከፋይ ሂሣብ ላይ ግብር ቀንሶ ገቢ ባለማድረግ የሚጣል መቀጫ

1. በዚህ አዋጅ መሠረት ከተከፋይ ሂሣብ ላይ ግብር ቀንሶ ገቢ የማድረግ ግዴታ ያለበት ሰው ቀንሶ ገቢ ያላደረገውን የግብር መጠን ለግብር አሰገቢው ባለሥልጣን ገቢ የማድረግ ግዴታ አለበት። ይሁን እንጂ በዚህ ዓይነት የከፈለውን ሂሣብ ከግብር ከፋዩ መልሶ የማግኘት መብት ይኖረዋል።
2. ከተከፋይ ሂሣብ ላይ ግብር ቀንሶ የማስቀረት ኃላፊነት ያለበት ሰው በዚህ አዋጅ መሠረት ማንኛውም ግብር ከፋይ ያለበት ኃላፊነት ይኖርበታል። በመሆኑም ገቢ እንዲያደርግ የተጠየቀውን የግብር መጠን የመቃወም ወይም ተደም ሲል የከፈለው ታክስ እንዲመለስለት የመጠየቅ መብት አለው።
3. በዚህ አዋጅ በተደነገገው መሠረት ከተከፋይ ሂሣብ ላይ ግብር ቀንሶ ገቢ ያላደረገ ሰው በንዑስ አንቀጽ /1/ ከተደነገገው በተጨማሪ ለእያንዳንዱ ተገቢውን ግብር ቀንሶ ገቢ ሳያደርግ ለፈፀመው ክፍያ ብር1 ሺ መቀጫ ይከፍላል።
4. ከዚህ በላይ ከተደነገገው መቀጫ በተጨማሪ የሚከተሉት ግለሰቦች ከዚህ በታች የተወሰነውን መቀጫ እንዲከፍሉ ይደረጋል፣
   ሀ/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ/1/ እንደ ተመለከተው ከተከፋይ ሂሣብ ላይ ግብር ቀንሶ ገቢ ያለመደረጉን ያወቀ ወይም ማወቅ ያለበት ሥራ አስኪያጅ፣
   ለ/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ/1/ እንደተመለከተው ከተከፋይ ሂሣብ ላይ ግብር ቀንሶ ገቢ ያለመደረጉን ያወቀ ወይም ማወቅ የነበረበት እና ከተከፋይ ሂሣብ ላይ ግብር ቀንሶ ገቢ የማድረጉን ሥርዓት የመከታተል ወይም የመቆጣጠር ኃላፊነት ያለበት ሆኖ ክትትሉን ወይም ቁጥጥሩን በተገቢው መንገድ ባለማከናወኑ ግብሩ ተቀንሶ ገቢ ላለመደረጉ ምክንያት የሆነ የሂሣብ ኃላፊ ወይም ማንኛውም ሌላ ኃላፊ ብር1 ሺህ መቀጫ ይከፍላሉ።

## 90. የግብር ከፋይ መለያ ቁጥርን ባለመጠቀም የሚጣል መቀጫ

1. ግብር ከፋዩ ከተከፋይ ሂሣብ ላይ ግብር ቀንሶ ለሚያስቀረው ሰው የግብር ከፋይ መለያ ቁጥሩን ያላቀረበ እንደሆነ ግብር ቀንሶ የሚያስቀረው ሰው ከተከፋዩ ሂሣብ ላይ 30 ፐርሰንት /ሠላሳ በመቶ /ቀንሶ ገቢ ያደርጋል።
2. ከተከፋይ ሂሣብ ላይ ግብሩን ቀንሶ ገቢ ማድረግ ለሚገባው ሰው የግብር ከፋይ መለያ ቁጥሩን ያላቀረበ ግብር ከፋይ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ/1/ ከተደነገገው በተጨማሪ ብር 5000 /አምስት ሺ ብር/ ወይም ሊከፈለው የሚገባውን ሂሣብ ከሁለቱ አነስተኛውን በመቀጫ መልክ ለግብር አሰገቢው ባለሥልጣን እንዲከፍል ይደረጋል።

## 91. መቀጫን ስለመሰብሰብ እና በመቀጫ ላይ ስለሚቀርብ ይግባኝ

አስተዳደራዊ መቀጫ ከግብር አሰገቢው ባለሥልጣን በሚሰጥ ማስታወቂያ እና የክፍያ ጥያቄ ወዲያውኑ መከፈል አለበት።ስለሆነም የመቀጫ አወሳሰን እና አሰባሰብ ግብር በሚወሰንበት እና በሚሰበሰብበት አፈፃፀም ይመራል።በዚህ አዋጅ ውስጥ "የተወሰነ ግብር" በሚል የተጠቀሰ አስተዳደራዊ መቀጫን ይጨምራል።

## 92. ግብር ከፋዩን ከመቀጫ ነፃ ስለማድረግ

የገቢ ማስታወቂያው ከመመርመሩ በፊት ግብር ከፋዩ በራሱ ተነሳሽነት ወደ ተሳሳተ የግብር ውሣኔ እና አፈፃፀም ሊያመሩ የሚችሉ ስህተቶችን ያረመ እንደሆነ ከግብር እና ከወለድ በስተቀር በዚህ አዋጅ የተጣለውን መቀጫ ከመክፈል ነፃ ይደረጋል።

### ክፍል ዘጠኝ
### የወንጀል ጥፋቶች

## 93. በግብር ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች ስለሚመሩበት ሥነ-ሥርዓት

በግብር ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች የወንጀለኛ መቅጫ ሕጉን በመተላለፍ የሚፈፀሙ በመሆኑ ክሱ የሚመሠረተው የሚታየው እና ይግባኝ የሚቀርበው በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ሥነ-ሥርዓት መሠረት ይሆናል።

## 94. በግብር ከፋይ መለያ ቁጥር ላይ ስለሚፈፀም ጥፋት

ማንኛውም ግብር ከፋይ ከአንድ የበለጠ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር ይዞ የተገኘ እንደሆነ በዚያው በእያንዳንዱ ተጨማሪ መለያ ቁጥር ልክ ከብር 20ሺ /ሃያ ሺ ብር/ በማያንስና ከብር 50 ሺህ /ሃምሣ ሺ ብር/ በማይበልጥ የገንዘብ መቀጫ እና በእያንዳንዱ ተጨማሪ መለያ ቁጥር ልክ በአምስት ዓመት እሥራት ይቀጣል።

## 95. ሕግን በመጣስ ግብር ስላለመክፈል

ማንኛውም ግብር ከፋይ ሕግን በመጣስ ገቢውን ያላስታወቀ ወይም የሚፈለግበትን ግብር ያልከፈለ እንደሆነ ወንጀል እንደፈፀመ ይቆጠራል። ስለሆነም በዚህ አዋጅ አንቀጽ 85 መሠረት ገቢውን አሳንሶ በማስታወቁ ምክንያት ከሚጣልበት መቀጫ በተጨማሪ ጥፋተኛ መሆኑ በፍርድ ቤት ሲረጋገጥ ከ5 ዓመት በማያንስ እሥራት ይቀጣል።

## 96. የሀሰት ወይም አሳሳች መረጃ ስለማቅረብ

1. ማናኛውም ግብር ከፋይ:-
   ሀ/ ለግብር አሰገቢው ባለሥልጣን ሠራተኛ አንድን ነጥብ ከተመለከተ የሀሰት ወይም አሳሳች መረጃ ያቀረበ ወይም
   ለ/ ለግብር አሰገቢው ባለሥልጣን ሠራተኛ ሊቀርብ ከሚገባው መግለጫ ውስጥ መግለጫውን አሳሳች ሊያደርግ በሚችል አኳኋን መካተት የሚገባቸውን ነጥቦች ያስቀረ እንደሆነ፤ የወንጀል ክስ ይመሠረትበታል።
2. የሐሰት መግለጫው የተሰጠው ወይም መካተት የሚገባው ነጥብ የተተወው ያለበቂ ምክንያት የሆነ እንደሆነ:
   ሀ/ የመግለጫው ትክክለኛ ያለመሆን ሊደረስበት ያለመቻሉ ሊከፈል የሚገባው ግብር ከብር 1ሺህ በማይበልጥ እንሶ እንዲከፈል የሚያደርግ ከሆነ ግብር ከፋዩ ከብር 10,000 /አሥር ሺህ/ በማያንስ እና ከብር 20 ሺህ በማይበልጥ የገንዘብ መቀጫ እና ከአንድ ዓመት በማያንስ እና ከሦስት ዓመት በማይበልጥ እሥራት ይቀጣል።
   ለ/ አንሶ እንዲከፈል የሚደረገው ግብር ከብር 1000 የሚበልጥ ከሆነ ከብር 20ሺህ በማያንስ እና ከብር 100.000 በማይበልጥ የገንዘብ መቀጫ እና ከሦስት ዓመት በማያንስ እና ከአምስት ዓመት በማይበልጥ እሥራት ይቀጣል።
3. የሐሰት መግለጫ የተሰጠው ወይም መካተት የሚገባው ነጥብ እንዲካተት ያልተደረገው ሆን ተብሉ ወይም በከባድ ቸልተኝነት የሆነ እንደሆነ:
   ሀ/ የመግለጫው ትክክለኛ ያለመሆን ሊደረስበት ያለመቻሉ ሊከፈል የሚገባው ግብር ከብር 1000 በማይበልጥ እንሶ እንዲከፈል የሚያደርግ ከሆነ ግብር ከፋዩ ከብር 50,000 በማያንስ እና ከብር 100,000 በማያበልጥ የገንዘብ መቀጫ እና ከአምስት አመት በማያንስ እና ከ10 አመት በማይበል አስራት ይቀጣል።
   ለ/ አንሶ እንዲከፈል የሚደረገው ግብር ከብር 1000 የሚበልጥ ከሆነ ከብር 75.000 በማያንስ እና ከብር 200.000 በማይበልጥ የገንዘብ መቀጫ እና ከ10 ዓመት በማያንስ እና ከ15 ዓመት በማይበልጥ እሥራት ይቀጣል።

## 97. የግብር አሰገቢውን ባለሥልጣን ሥራ ስለማሰናከል

1. ማናቸውም ሰው:-
   ሀ/ በዚህ አዋጅ መሠረት ሥራውን በማከናወን ላይ ያለን የግብር አሰገቢ ባለሥልጣን ሠራተኛ ተግባር ያሰናከለ ወይም ለማሰናከል የሞከረ ወይም
   ለ/ የአዋጁን አፈፃፀም በማናቸውም ሌላ አኳኋን ያሰናከለ ወይም ለማሰናከል የሞከረ እንደሆነ ወንጀል መፈፀሙ ተረጋግጦ ሲፈረድበት ከብር 10,000 /አሥር ሺህ/ በማያንስ እና ከብር 100.000 /መቶ ሺህ/ በማይበልጥ የገንዘብ መቀጫ እና በሁለት ዓመት እሥራት ይቀጣል።
2. የሚከተሉት እና እነዚህን የመሳሰሉ ሌሎች ተግባሮች የግብር አሰገቢውን ባለሥልጣን ሥራ የማሰናከል ተግባራት ሆነው ይወሰዳሉ:

ሠ/ የግብር ከፋዩን ገቢ እስገኚ የሥራ እንቅስቃሴዎች የሚመለከቱ ሠነዶችን ሪፖርቶችን ወይም ሌሎች ማናቸውንም መረጃዎች ለመመርመር የግብር አስገቢው ባለሥልጣን ሲጠይቅ ፈቃደኛ ሆኖ ያለመገኘት፣

ለ/ የግብር አስገቢው ባለሥልጣን ለጥያቄ እንዲቀርብ ሲያዝ ፈቃደኛ ሆኖ ያለመገኘት፣

ሐ/ የግብር አስገቢው ባለሥልጣን ሠራተኛ ወደ ግብር ከፋዩ የንግድ ሥራ ቦታ ለመግባት ያለውን መብት መገደብ፡፡

መ/ የሚሰጠውን የግብር ውሳኔ ማስታወቂያና ሌሎች ሰነዶችን የሚመለከቱ ደብዳቤዎች ለመቀበል ፍቃደኛአለመሆን፡፡

## 98. በግብር አስገቢው ባለሥልጣን ሠራተኞች የሚፈፀሙ ጥፋቶች

የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎች ለማስፈጸም በግብር አስገቢው ባለሥልጣን የተቀጠረ ማንኛውም ሰው፡-

ሀ/ በሕግ መሠረት ሊያገኘው ከሚገባ ክፍያ ወይም ሽልማት ውጪ ከተቀጠረበት ተግባር ጋር በተያያዘ በቀጥታ ወይም ቀጥተኛ ባልሆነ መንገድ የገንዘብ ወይም ሌላ ዓይነት ክፍያ ወይም ስጦታ እንዲደረግለት የጠየቀ ወይም የተቀበለ ለክፍያው ወይም ለስጦታው ተስፋ ወይም መያዣ የጠየቀ ወይም የተቀበለ ወይም

ለ/ ከግብር በሚገነው ገቢ ላይ ማጭበርበር ወይም ከዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች ጋር ወይም ከተሰጠው ኃላፊነት መልካም አፈፃፀም ጋር የሚቃረን ተግባር ለመፈፀም ማድረግ የሚገባውን ከማድረግ ለመታቀብ ተገቢ ያልሆነን ነገር ለመፍቀድ በግብር ላይ የሚፈፀምን የማጭበርበር ተግባር ለመደበቅ ወይም በሚሥጢር ለመተግበር ውል የገባ ወይም በሚገበው ማናቸውም ውል ውስጥ በዚህ ተግባር መተባበሩን የሚያሳይ ስምምነት የሰጠ ወይም

ሐ/ በዚህ አዋጅ ለግብር አስገቢው ባለሥልጣን ከተሰጠው ሥልጣን በላይ የሠራ ወይም በተሰጠው ሥልጣን ያለአግባብ የተጠቀመ ጥፋተኛ መሆኑ በፍርድ ቤት ሲረጋገጥ ከብር 50ሺህ በማይበልጥ የገንዘብ መቀጫ እና ከ10ዓመት በማያንስ ከ20 ዓመት በማይበልጥ እሥራት ይቀጣል፡፡

## 99. ሳይፈቀድ ግብር ስለመሰብሰብ

ማንኛውም ሰው በዚህ አዋጅ መሠረት ሳይፈቀድለት ግብር ወይም እንደ ግብር የሚታይ ሌላ ክፍያ የሰበሰበ ወይም ለመሰብሰብ የሞከረ ወንጀል የፈፀመ ሆኖ ጥፋተኛ መሆኑ በፍርድ ቤት ሲረጋገጥ ከብር 50.000 በማያንስ የገንዘብ መቀጫ እና ከ5 ዓመት በማያንስ ከ10 ዓመት በማይበልጥ እሥራት ይቀጣል፡፡

## 100. መርዳት ወይም ማበራታታት

ማንኛውም ሰው የዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች እንዲጣሱ የረዳ ያበረታታ ያነሳሳ ወይም በምስጢር የተባባረ እንደሆነ እንደዋንኛው ጥፋተኛ የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎች በመጣስ ጥፋት ይፈፅማል፡፡ ከዚህ በላይ የተዘረዘሩትን የፈፀመ ሰው ጥፋተኛ መሆኑ በፍርድ ቤት ሲረጋገጥ ዕርዳታውን ወይም ትብብሩን ለሰጠበት ጥፋት ከተወሰነው የገንዘብ እና የእሥራት ቅጣት ባልበለጠ በገንዘብ እና በእሥራት ይቀጣል፡፡

## 101. በድርጅቶች የሚፈፀም ጥፋት

1. በንዑስ አንቀጽ/3/ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ አንድ ድርጅት ይህንን አዋጅ በመተላለፍ ጥፋት የፈፀመ እንደሆነ ጥፋቱ በተፈፀመ ጊዜ የድርጅቱ ሥራ አስኪያጅ የሆነ ማንኛውም ሰው በድርጅቱ የተፈፀመውን ጥፋት እንደፈጸመ ተቆጥሮ በዚህ አዋጅ የተጣለው ቅጣት ተፈፃሚ ይሆንበታል፡፡
2. በንዑስ አንቀጽ/3/ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ማናቸውም ድርጅት በዚህ አዋጅ መሠረት ሊከፈል የሚገባውን ወይም አዋጁ እንደሚገብር የሚቀጥረውን ማናቸውንም ሌላ ክፍያ ገቢ ሳያደርግ የቀረ እንደሆነ ጥፋቱ በተፈፀመበት ጊዜ ወይም ጥፋቱ ከተፈፀመበት ጊዜ አስቀድሞ በነበሩት ስድስት ወራት ውስጥ የድርጅቱ ሥራ አስኪያጅ የነበሩ ሰዎች ከድርጅቱ እና ከሌላው ሰው ጋር በአንድነትና በተናጠል የግብር አስገቢው ባለሥልጣን ለሚፈልገው ግብር እና ሌሎች ክፍያዎች ተጠያቂ ይሆናሉ፡፡
3. በንዑስ አንቀጽ /1/እና /2/ የተደነገጉት፡-

ሀ/ ጥፋቱ የተፈፀመው ግለሰቡ ሳያውቅ ወይም ሳይስማማበት ከሆነ፣

ለ/ እንድ ነገሮችን በጥንቃቄ የሚያይ ሰው በተመሳሳይ ሁኔታ ውስጥ የጥፋቱን መፈፀም ለመከላከል ይወስዳቸዋል ተብሎ የሚገመቱ ጥንቃቄዎችን ተገቢውን ትጋት እና የአሠራር ጥበብ የተሞላበት እርምጃ ግለሰቡ ወስዶ የተገኘ እንደሆነ፣ ተፈፃሚ አይሆኑበትም፡፡

4. ከተከፋይ ሂሳብ ላይ ግብር ቀንሶ ገቢ የማድረግ ኃላፊነት ለተሰጠው ሰው ግብሩን ቀንሶ በማስቀረቱ ምክንያት ዕቃ ለማቅረብ ወይም አገልግሎት ለመስጠት እምቢተኝነት ያሳየ ማናቸውም ሰው ከብር 5ሺህ በማያንስ እና ከብር 10 ሺህ በማይበልጥ የገንዘብ ቅጣትና ከአንድ ዓመት በማያንስና ከሁለት ዓመት በማይበልጥ እሥራት ይቀጣል፡፡
5. ለንዑስ አንቀጽ /1/እና /2/ አፈፃፀም "ሥራ አስኪያጅ" ማለት፡

ሀ/ የሽርክና ማኅበርን በሚመለከት የሽርክናው ማኅበር አባል ወይም የማኅበሩ ሥራ ስኪያጅ ወይም ከሁለቱ ኃላፊነቶች በአንዱ እንደሚሠራ ሆኖ የሚታይ፣

ለ/ ድርጅትን በሚመለከት የኩባንያው የሥራ መሪ ሥራ አሥኪያጅ ወይም ማናቸውም ሌላ ሹም ወይም ከእነዚህ ኃላፊነቶች በአንዱ እንደሚሠራ ሆኖ የሚታይ፣

ሐ/ የሰዎችን ኅብረት በሚመለከት የኅብረቱ ሥራ አሥኪያጅ ወይም በዚህ ኃላፊነት እንደሚሠራ ሆኖ የሚታይ ነው፡፡

## 102/ የጥፋተኞችን ስም በጋዜጣ አትሞ ስለማውጣት

1. የግብር አስገቢው ባለሥልጣን በዚህ አዋጅ ከአንቀጽ 92-100 የተደነገጉትን የወንጀል ጥፋቶች በመፈፀም የተፈረደባቸው ሰዎች ስም ዝርዝር በየጊዜው በዕለታዊ ጋዜጦች ታትሞ እንዲወጣ ያደርጋል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ/1/ መሠረት ታትሞ የሚወጣው ዝርዝር

ሀ/ የድርጅቱን ወይም የግለሰቡን ስም እና አድራሻ፣

ለ/ ባለሥልጣኑ ተገቢ ነው ብሎ የሚያምንበትን የወንጀሉን አፈፃፀም ዝርዝር፣

ሐ/ ጥፋቱ የተፈጸመበትን የግብር ዘመን ወይም ዘመናት፡

መ/ ሳይከፈል የቀረውን ግብር መጠን፡

ሠ/ በተጨማሪ እንዲከፈል የተወሰነበት ግብር ካለ ይሆናል፡፡

## ክፍል አሥር
## የይግባኝ አቀራረብ ሥርዓት

## 103. የአቤቱታ አጣሪ ኮሚቴ

የአቤቱታ አጣሪ ኮሚቴ አባላት በፋይናንስ ቢሮ የገቢዎች መምሪያ ኃላፊ አቅራቢነት በቢሮ ኃላፊው ይሰየማሉ ፡

## 104. ኮሚቴው ስለሚኖረው ሥልጣንና ተግባር

1. ኮሚቴው ተጠሪነቱ በፋይናንስ ቢሮ የገቢዎች መምሪያ ሀላፊ ሆኖ:

ሀ/ በግብር ከፋዮች መቀጫ እንዲነሳ ወለድ ቀሪ እንዲደረግ ወይም የግብር ግዴታ እንዲሻሻል የሚቀርቡ ማመልከቻዎችን ለመመርመርና ውሣኔ ለመስጠት፣

ለ/ ከቀረቡት አቤቱታዎች ጋር ግንኙነት ያላቸውን ማናቸውም የጽሑፍ ማስረጃዎች ወይም መረጃዎች መሰብሰብ፣

ሐ/ በምርመራ ላይ የሚገኘውን ጉዳይ በሚመለከት ረገድ ቀርቦ የሚጠየቀውን ጥያቄ እንዲመልስ ከግብሩ አወሳሰን ጋር በቀጥታ ወይም ቀጥታ ባልሆነ መንገድ ግንኙነት ያለውን ማንኛውንም ሰው የመጥራት፡ እና ቃል የመቀብል፣

መ/ የግብር አስገቢው ባለሥልጣን የሰጠው የግብር ውሣኔ ትክክለኛ የተሟላ እና ይህንን አዋጅ ጠብቆ የተሰጠ መሆኑን የማረጋገጥ ሥልጣን ይኖረዋል ፡፡

2. የአቤቱታ አጣሪ ኮሚቴው ከግብር ከፋዩች የሚቀርበውን አቤቱታ ሊያይ የሚችለው ግብር ከፋዩ የግብር ውሣኔ ማስታወቂያ በደረሰው በ10 ቀናት ውስጥ አቤቱታውን ካቀረበ ነው፡፡
3. በፋይናንስ ቢሮ የገቢዎች መምሪያ ሀላፊ የኮሚቴውን የውሣኔ ሀሳብ ሊያፀድቅ ወይም በውሳኔ ሀሳቡ ካልተስማማ ምክንያቱን በመግለፅ ጉዳዩ እንደገና እንዲታይ ለኮሚቴው ሊመልሰው ይችላል፡፡

## 105. መቀጫን ስለማንሳት

የአቤቱታ አጣሪ ኮሚቴ ፋይናንስ ቢሮ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት በግብር ከፋዩ ላይ የተጣለው አስተዳደራዊ መቀጫ በሙሉ ወይም በከፊል እንዲነሳ ማድረግ ይችላል::

## 106. የግብር ውሣኔን በመቃወም ይግባኝ ስለማቅረብ መብት

1. በማንኛውም ግብር አወሳሰን ቅር የተሰኘ ማንኛውም ግብር ከፋይ ከዚህ በታች ባለው ንዑስ አንቀጽ ሥር የተዘረዘሩትን ግዴታዎች ካሟላ ለግብር ይግባኝ ጉባዔ /ከዚህ በኋላ "የይግባኝ ጉባዔ ተብሎ ለሚጠቀሰው/ ይግባኝ ማቅረብ ይችላል::
2. ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ያላሟላ ይግባኝ በይግባኝ ጉባዔ ተቀባይነት አይኖረውም፤
   ሀ/ ግብር ከፋዩ አከራካሪ የሆነውን የግብር መጠን አምሳ በመቶ /50ፐርሰንት ለግብር አሰገቢው ባለሥልጣን ካላስያዘ
   ለ/ የግብር ውሣኔ ማስታወቂያ ለግብር ከፋዩ በደረሰው ወይም በአቤቱታ ኮሚቴ ውሣኔ በተሰጠ በ30 ቀን ውስጥ ይግባኝ ካለቀረበ::

## 107. ይግባኝ የቀረበበት ቀን

ይግባኙ የቀረበበት ቀን ነው የሚባለው:-

ሀ/ በቀጥታ ለይግባኝ ጉባዔው የቀረበ ሲሆን ይግባኙ በመዝገብ ቤት የተመዘገበበት ቀን ይሆናል ወይም

ለ/ በሪኮማንዴ የተላከ ሲሆን በፖስታ ቤት የተመዘገበበት ቀን ይሆናል:

## 108. የይግባኝ ማመልከቻ ይዘት

1. የይግባኙ ማመልከቻ በሁለት ቅጂ ተዘጋጅቶ የሚከተሉትን የያዘ ይሆናል::
   ሀ/ ግልጽ በሆነ ሁኔታ የይግባኙን ፍሬ ነገር የይግባኙን ምክንያቶች
   ለ/ የግብር ከፋዩን ስም አድራሻ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር
   ሐ/ ከይግባኝ ማመልከቻው ጋር በአባሪነት ሊቀርቡ የሚገባቸውን አግባብ ያላቸው ደጋፊ ሰነዶች እንዲሁም ለግብር አሰገቢው ባለሥልጣን መያዣ የተከፈለበት ደረሰኝ ፎቶ ኮፒ::
2. ከዚህ በላይ በንዑስ አንቀጽ /1/ ውስጥ ከሀ-ሐ ከተዘረዘሩት መካል አንዱ ቢጎድል የይግባኝ ጉባኤው ይግባኝ ባይ የተባለውን ጉድለት እንዲያሟላ ይጠይቀዋል:: ይግባኝ ባይ በአምስት ቀናች ውስጥ የተባለውን ጉድለት ያላስተካከለ እንደሆነ የቀረበው የይግባኝ ማመልከቻ ወዲያውኑ ውድቅ ይሆናል::

## 109. የይግባኝ ሰነዶችን ስለመስጠት

1. ይግባኙ ለመጀመሪያ ጊዜ ከመሰማቱ አስቀድሞ
   ሀ/ የይግባኙ ማመልከቻ ግልባጭ በይግባኝ ጉባዔው አማካይነት ለግብር አሰገቢው ባለሥልጣን እንዲደርሰው ይደረጋል
   ለ/ የግብር አሰገቢው ባለሥልጣን መልሱን ለይግባኝ ጉባዔው ሲያቀርብ ግልባጩን ለይግባኝ ባዩ ይሰጣል፤
2. አቤቱታው ተቀባይነት እንዲኖረው ለማድረግ የማስረዳት ኃላፊነት የይግባኝ ባይ ይሆናል::

## 110. የይግባኝ ጉባዔ ውሣኔ

1. የይግባኝ ጉባዔው የቀረበውን ይግባኝ ከመረመረ በኋላ የይግባኝ ባዩን የከፋይ መለያ ቁጥር ውሣኔው የተሰጠበትን ቀን በጉባዔው ስብሰባ የተገኙትን አባላት ዝርዝር የሊቀመንበሩን ስም አግባብ ኖሯቸው የተወሰዱት አንቀጾች የሚገኙበትን ሕግ የሚያብራራ ውሣኔ በጽሑፍ መስጠት አለበት::
2. የይግባኝ ሰሚ ጉባዔውን ውሣኔ የያዘው መግለጫ የሚከተሉትን ማካተት ይኖርበታል፤
   ሀ/ የተደረሰበትን ድምዳሜ /የይግባኝ ባዩ አቤቱታ ድጋፍ ያለው መሆን ያለመሆኑን ተቀባይነት ያገኘው በሙሉ ወይም በከፊል መሆኑን ተቀባይነት ያገኙ ከመመሪያ ጋር ወደ ግብር አሰገቢው ባለሥልጣን የተመለሰ መሆኑን ይግባኝ ባዩ የሚጠየቅባቸውን ሌሎች ጉዳዩች ዝርዝር/፤
   ለ/ የተረጋገጡትን ፍሬ ነገሮችና በይግባኙ ውስጥ የተጠቀሱትን ሕጎች ትርጉም ይግባኙ በተሰማበት ወቅት በሙሉ በተነሱት አግባብ ባላቸው በእያንዳንዱ ጭብጥ ላይ የተሰጠውን አልባት ውሣኔውን በሚመለከት ረገድ የተሰጠ የሃሳብ ልዩነት ካለ፤
   ሐ/ የይግባኝ ባዩን ይግባኝ የማቅረብ መብቶች::
3. ውሣኔው የተገኙት የጉባዔው አባላት ፊርማና የጉባዔው ማኅተም ያርፍበታል::
4. የይባኝ ጉባዔ :
   ሀ/ ይግባኝ ባይ በሁለት የቀጠሮ ጊዜዎች ሳይገኝ የቀረ እንደሆነ ወይም ይግባኙን ካቀረበ በኋላ የመልስ መልስ ሳያቀርብ ሲቀር:
   ለ/ የግብር አሰገቢው ባለሥልጣን የይግባኙ ማመልካቻ ከደረሰው በኋላ በሁለት የቀጠሮ ጊዜዎች ሳይገኝ የቀረ እንደሆነ ወይም ለይግባኙ መልስ ሳይሰጥ ሲቀር ተከራካሪው ወገን በሌለበት ውሣኔ ይሰጣል::

## 111. የይግባኝ ጉባዔን ውሣኔ በመቃውም ስለሚቀርብ ይግባኝ

1. የይግባኝ ጉባዔ የሰጠው ውሣኔ በሕግ ረገድ ስህተት ነው በማለት ያልተስማማ ማንኛውም ተከራካሪ ወገን የይግባኝ ጉባኤው ውሣኔ በተሰጠ በ30 ቀን ውስጥ ጉዳዩን ሥልጣን ላለው ፍ/ቤት አቅርቦ ስለሕጉ ስህተት ፍርድ ሊጠይቅ ይችላል::
2. ሥልጣን የተሰጠው ፍርድ ቤት በሕግ ረገድ የተነሳውን ክርክር ብቻ ተመልክቶ ውሣኔ ከሰጠ በኋላ ጉዳዩን ወደ ጉባዔው ይመልሳል::
3. ሥልጣን በተሰጠው ፍ/ቤት በሕግ ጥያቄ ላይ በተሰጠው ውሣኔ ቅር የተሰኘ ተከራካሪ ወገን ውሣኔው በተሰጠ በ30 ቀን ውስጥ ለይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ይግባኝ ለማለት ይችላል:: ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤትም ሊያይ የሚችለው የመጀመሪያው ፍርድ ቤት በይግባኝ የሚያየውን የሕግ ጉዳይ ብቻ ነው::
4. ግብር ከፋዩ በግብር ይግባኝ ጉባዔ የተወሰነበት ሙሉ ግብር ካልከፈለ በስተቀር የይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ይግባኙን መቀበል የለበትም::

## 112. የይግባኝ ጉባዔ መቋቋም

1. የክልሉ የግብር ይግባኝ ጉባኤ በክልሉ ዋና ከተማ ይቋቋማል::
2. በንዑስ አንቀጽ/1/ የተደነገገው ቢኖርም የክልሉ መንግሥት በማንኛውም ደረጃ ላይ ለሚገኙት አካባቢዎች የተለየ የይግባኝ ጉባዔ ማቋቋም አስፈላጊ መሆኑን ሲረዳ ለእነዚህ ቦታዎች በአቅራቢያቸው የግብር ይግባኝ ጉባዔ ይቋቋማል::
3. የክልሉ የግብር ይግባኝ ጉባዔ ተጠሪነቱ ለክልሉ ሥራ አስፈፃሚ አካል ይሆናል::

## 113. የይግባኝ ጉባዔ አባሉችን ስለመሰየም

1. በማናቸውም ደረጃ የሚገኝ የይግባኝ ሰሚ ጉባዔ አባለት በሕዝብ ዘንድ ባላቸው ታማኝነት ባላቸው ጠቅላላ እና ልዩ ዕውቀት እንዲሁም ከግብር ጋር በተገናኘ ጥፋት ካልፈፀሙ ሰዎች መካከል ተመርጠው ይሰየማሉ::
2. የክልሉ ስራ አስፈፃሚ አካል የግብር ይግባኝ ሰሚ አባለት የሚመረጡበትን መመዘኛ እና ስብጥር የሚወሰን መመሪያ ያወጣል::
3. ይህንን መመሪያ በመከተል የግብር ይግባኝ ጉባዔ አባላት የሚሆኑት እንደ አግባብነቱ በክልሉ ሥራ አስፈፃሚ ተመርጠው ይሾማሉ::
4. የይግባኝ ሰሚ ጉባዔ ፕሬዚዳንት በክልሉ ፕሬዝዳንት ይሾማል::
5. በእያንዳንዱ የይግባኝ ጉባዔ ከአንድ የበለጡ ጉባዔዎች ሊኖሩ ይችላሉ:: በዚህ ዓይነቱም ሁኔታ እያንዳንዱ ጉባዔ አምስት አባላት የሚኖሩት ሲሆን የራሱን ሊቀመንበር ከአባሉቹ መካከል ይመርጣል::
6. የማንኛውም የይግባኝ ጉባዔ አባል የአገልግሉት ዘመን ለሁለት ዓመታት ጊዜ ይሆናል:: በይግባኝ ጉባዔ ወይም በእያንዳንዱ ጉባዔ በሊቀመንበርነት እንዲያገለግል የተመረጠ ሰው የሥራ ዘመን ሁለት ዓመት ወይም በምትክነት የተመረጠ ሲሆን የተካው ሰው የቀረው የሥራ ጊዜ ይሆናል::
7. የግብር ይግባኝ ጉባዔ ሊቀመንበር እና የቀሩትም ሌሎች አባሉች የክልሉ ሥራ አስፈጻሚ በየጊዜው በሚያወጣው ደንብ መሠረት በጉባዔው ላይ እየተገኙ ለሠሩበት ጊዜ አበል ይከፈላቸዋል::

## 114. የይግባኝ ጉባዔ እና ሊቀመንበሩ ስለሚኖራቸው ተግባርና ሥልጣን:

1. የይግባኝ ሰሚ ጉባዔ ፣
   - ሀ/ በማስረጃ የተረጋገጡ ፍሬ ነገሮችንና ሕግን መሠረት በማድረግ ይግባኝ የተመሠረተበትን የግብር ውሣኔ የማፅናት፣ የመቀነስ ወይም የመሠረዝ ሥልጣንና ለጉዳዩ የመጨረሻ ውጤት ለማስገኘት ትክክልና፣ አስፈላጊ መስሎ የታየውን ማናቸውንም ተመጣሪ ትዕዛዝ የመስጠት ሥልጣን ይኖረዋል።
   - ለ/ የግብር አስገቢውን ባለሥልጣን ወይም ግብር ከፋዩን እንደነገሩ ሁኔታ ተጨማሪ ፍሬ ነገሮች ካሉ እነዚህኑ እንዲያቀርቡ መመሪያ ይሰጣል እንዲሁም
   - ሐ/ እንደሁኔታው አስፈላጊነት ግብር ከፋዩንም ሆነ ግብር አስገቢውን ባለሥልጣን ወይም ማንኛውንም ሌላ ሰው ማኅበር መንግሥታዊ መሥሪያ ቤት ወይም ድርጅት ግብር ከፋዩ ካቀረበው አቤቱታ አግባብ ያላቸውን ደጋፊ ማስረጃዎች እንዲያቀርብ ያዛል።
2. እያንዳንዱ የይግባኝ ሰሚ ጉባዔ ሊቀመንበር
   - ሀ/ የይግባኙን ፍሬ ነገር የያዘውን ጽሑፍ የመጀመሪያ ደረጃ ምርመራ ያደርግበታል፣
   - ለ/ የጉባዔውን አጀንዳ ያዘጋጃል፣
   - ሐ/ የይግባኝ ክርክሩ በሚሰማበት ወቅት ጉባዔው ላይ ይቀመጣል እንዲሁም ሥነ ሥርዓቱን ይመራል፣
   - መ/ በቃለ ጉባዔ የተያዙ ወይም በውሣኔ ውስጥ የተመዘገቡ የቃል ወይም የፅሑፍ ክርክሮች ሁሉ በሚገባ መመዝገባቸውንና ሕግ በሚያዘው ፎርም ዓይነት መዘጋጀታቸውን ያረጋግጣል፣
   - ሠ/ በሊቀመንበነት የሚመራው ጉባዔ ስላከናወናቸው ተግባሮች ዓመታዊ ሪፖርት አዘጋጅቶ ያቀርባል።

## 115. የማስረጻት ኃላፊነት

የተወሰነው ግብር በዝቷል ወይም የግብር አስገቢው ባለሥልጣን የሰጠው ውሣኔ ትክክል አይደለም በሚል በሚቀርብ ክርክር የማስረዳቱ ኃላፊነቱ የተወሰነውን ግብር ወይም የባለሥልጣኑን ውሣኔ የሚቃወመው ሰው ይሆናል።

## 116. ደንብ የማውጣት ሥልጣን

የክልሉ ሥራ አስፈፃሚ ለዚህ አዋጅ ትክክለኛ አተረጓጎምና አፈፃፀም የሚያገለ ደንቦችን ያወጣል።

## ክፍል አሥራ አንድ
## የመሸጋገሪያ ድንጋጌዎች

## 117. የመሸጋገሪያ ድንጋጌ

1. ይህ አዋጅ በሥራ ላይ በሚውልበት ወቅት መክፈል ያለባቸውና በመክፈል ላይ ያሉ የግብር ከፍያዎች ወይም ከማናቸውም ንግድ ሥራ የሞያ ሥራ የቬኬሽን ሥራና ከማናቸውም ሌሎች ሥራዎች የተገኘን ገቢ ወይም በገቢነት የተመዘገበን በሚመለከት በኢትዮጵያ በሥራ ላይ ያለ አግባብነት ያለው የገቢ ግብር ህግ ወይም በዚህ አዋጅ ተፈፃሚነት የማይኖራቸው ሕጎች ሁሉ ተፈፃሚነት አላቸው።
2. በዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች መሠረት የይግባኝ ሰሚ ጉባዔዎች እስከ ሚቋቋሙ ድረስ በአሁኑ ጊዜ በሥራ ላይ ያሉት የይግባኝ ሰሚ ኮሚሲዮኖች ሁሉ ሥራቸውን እንደተለመደው በማካሄድ ይቀጥላሉ።

## 118. ተፈፃሚነት የማይኖራቸው ሕጎች

ቀደም ሲል በሥራ ላይ የነበሩ

1. ከማናቸውም ገቢ ግብር ስለማስከፈል የወጣው አዋጅ ቁጥር 173/1953 ከነማሻሻያዎቹ:
2. ከካፒታል ዋጋ ዕድገት ጥቅም ላይ ግብር ለማስከፈል የወጣው አዋጅ ቁጥር 108/1987
3. የክልሉ የግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባዔን ለማቋቋም የወጣው ደንብ ቁጥር 6/1994 በዚህ አዋጅ ተሽሯል።
4. ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረኑ ማናቸውም ሌሎች ሕጎች በዚህ አዋጅ ውስጥ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖራቸውም።

## 119. አዋጁ የሚፀናበት ቀን

ይህ አዋጅ ከመጋቢት 1 ቀን 1996 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል:

*ሐረር መጋቢት 1 ቀን 1996 ዓ.ም*
*አቶ ፉአድ ኢብራሒም*
*የሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት*
*ፕሬዝዳንት*

www.chilot.me

የሐረሪ ህዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት

# ሐረር ነጋሪ ጋዜጣ

# HARAR NEGARI GAZETA

OF THE HARARI PEOPLE NATIONAL REGIONAL STATE

| | | |
|---|---|---|
| ፰ኛ ዓመት ቁጥር 12<br>8 th Year No 12 | | ሐረር - ግንቦት 24 ቀን 1996<br>HARAR -12 th June,2004 |

| | | |
|---|---|---|
| ያንዱ ዋጋ ብር<br>unit price Br 1:00 | በሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ | የፖስታ ሣጥን ቁጥር<br>P.O Box 272 |



ማውጫ

አዋጅ ቁጥር 43/1996 ዓ.ም

የሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ለ1996 በጀት ዓመት ከእስም ባንክ ለጤና ሴክተር ልማት ፕሮግራም ማስፍጸሚያ የታወጀ የተጨማሪ በጀት አዋጅ - - - - - - - - - - - - - - - - ገጽ358


## አዋጅ ቁጥር 43/ 1996

## የሓረሪ ህዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ለ1996 በጀት ዓ.ም ከእስም ባንክ ለጤና ሴክተር ልማት ፕሮግራም ማስፍጸሚያ የታወጀ የተጨማሪ በጀት አዋጅ

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገ- መንግስት አንቀጽ 52 ንዑስ አንቀጽ 2/ሠ/ መሠረት ክልሉ የራሱን በጀት የማጽድቅና ሥራ ላይ የማዋሉ ስልጣን የተሰጠው በመሆኑ፤-

የሐረሪ ህዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ህገ-መንግስት አንቅጽ 21፤ አንቀጽ 2/ሀ/ እና በክልሉ የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 9/1991 አንቀጽ 21 መሠረት የሚከተለው የተጨማሪ የበጀት አዋጅ ታውጇል።

### 1. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ በ1996 በጀት ዓመት ለመንግስት ሥራዎች ማስፈጸሚያ የታወጀ የተጨማሪ በጀት አዋጅ ቁጥር 43/1996 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

### 2. ስለ ተጨማሪ የገቢ ምንጭ

ከእስም ባንክ ለጤና ሴክተር ፕሮግራም ማስፈጸሚያ ድጎማ

### 3. ስለ ወጭ ምደባ

ከእስም ባንክ ለጤና ሴክተር ፕሮግራም ማስፈጸሚያ ለተጀመሩ ፕሮጀክቶች የሚውል የህክምና መገልገያ መሣሪያ ግዢ ፕሮጀክት ለማከናወን ብር 221000 / ሁለት መቶ ሃያ አንድ ሺ ብር/ ወጪ ሆኖ እንዲከፈል በዚህ አዋጅ ተፈቅዷል።

### 4. ክፍያ ስለመፈጸም

ጉዳዩ ለሚመለከተው የክልሉ መንግስት ጤና ቢሮ ክፍያውን ሲጠይቅ የክልሉ ፋይናንስ ቢሮ ወጪ በማድረግ እንዲከፈል ታዟል።

### 5. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ ግንቦት 24 ቀን 1996 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል።

ሐረር ግንቦት 24/1996

ፉአድ ኢብራሂም

የሐረሪ ሕዝብ ብ/ክ/መንግሥት

ፕሬዝዳንት


www.chilot.me

የሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት

# ሐ ረ ር ነ ጋ ሪ ጋ ዜ ጣ

# HARAR NEGARI GAZETA

OF THE HARARI PEOPLE NATIONAL REGIONAL STATE

| | | |
|---|---|---|
| 8ኛ ዓመት ቁጥር 13<br>8th Year N° 13 | | ሐረር ግንቦት 24 ቀን 1996 ዓ.ም<br>HARAR 2nd JUNE, 2004 |
| ያንዱ ዋጋ<br>unit price 2.00 | በሐረሪ ህዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት<br>ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ | የፖስታ ሳጥን ቁጥር<br>P.O.BOX<br>272 |


## ማውጫ

አዋጅ ቁጥር 44/1996 ዓ.ም
የሐረሪ ህዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የቀበሌዎችን አስተዳደር ለማቋቋም የወጣ አዋጅ....................ገጽ359

## በሐረሪ ህዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የቀበሌዎችን አስተዳደር ለማቋቋም የወጣ አዋጅ::

በሐረሪ ህዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የተጀመረዉ ምቹ የዲሞክራሲያዊ ስርአት ግንባታን ለማጠናከርና ህዝቡን በልማቱ እንቅስቃሴ በቀጥታ በማሳተፍ ፈጣን ልማት ለማምጣት፣ ሰላምና የተሻለ የፍትህ ስርአት እንዲሁም መልካም አስተዳደር እንዲጎለብት ለማድረግ የቀበሌ አስተዳደር የሚጫወተው ሚና ከፍተኛ በመሆኑ:-

የቀበሌ አስተዳደር ለህዝቡ በሚሰጠዉ አገልግሎት ቀልጣፋ ዉጤታማ የአሰራር ግልጽነትና ተጠያቂነት ያለዉ የልማት አጋዥ እንዲሆን ለማስቻል በአግባቡ ማደራጀት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ:

እንዲሁም ህዝቡ በትንሽ በትልቁ ጉዳይ ፍርድ ቤት በመመላለስ ጊዜዉንና ገንዘቡን እንዳያባክን በመደበኛ ፍርድ ቤት የሚፈጥረዉንም የስራ ጫና መቀነስ በማስፈለጉ:

በክልሉ ህገ-መንግስት መሠረት ያልተማከለ የአስተዳደር ስርአትን እዉን ለማድረግና ምቹ ሁኔታዎችን ከወዲሁ ለማመቻቸት እንዲያስችል የቀበሌ አስተዳደርን ማቋቋም በማስፈለጉ:

በሐረሪ ህዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ህገ መንግስት አንቀጽ 26 /2/ሀ/ መሰረት የሚከተለው ታውጇል::

## ምዕራፍ አንድ
## ጠቅላላ ድንጋጌ

1. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "የቀበሌን አስተዳደር ለማቋቋም የወጣ አዋጅ ቁጥር "44/1996 " ተብሎ ሊጠራ ይችላል::

2 .ትርጉም

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጥ ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ዉስጥ፤

ሀ/"ህገ-መንግስት" ማለት የሐረሪ ህዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ህገ-መንግስት ማለት ነዉ::

ለ/ "ቀበሌ" ማለት በታችኛው እርከን ደረጃ ያለዉ የከተማና የገጠር ቀበሌ አስተዳደር ማለት ነዉ::

ሐ/"ሰው" ማለት የተፈጥሮ ወይም የህግ ሰውነት የተሰጠዉ አካል ማለት ነዉ::

መ/"ፍርድ ቤት" ማለት በዚህ አዋጅ መሰረት የተቋቋመ ማህበራዊ ፍርድ ቤት ነዉ::

3. መቋቋም

በሐረሪ ህዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ክልል ውስጥ በሚገኙ በማንኛዉም የከተማና የገጠር ቀበሌ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 10 ሥር የተመለከተው ስልጣንና ተግባር የሚኖረው የቀበሌ አስተዳደር ተቋቁሟል::

www.chilot.me

**4.የአዋጁ ተፈጻሚነት**

ይህ አዋጅ በሐረሪ ህዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ውስጥ ባሉት የከተማና የገጠር ቀበሌዎች ላይ ተፈጻሚ ይሆናል።

**5.የጾታ አገላለጽ**

በዚህ አዋጅ ውስጥ በወንድ ጾታ የተገለጸው የሴት ጾታን ያጠቃልላል።

## ምዕራፍ ሁለት
## የቀበሌ አስተዳደር አደረጃጀት፣ ስልጣንና ተግባር

**6.የቀበሌ አስተዳደር አደረጃጀት**

የቀበሌዎች አስተዳደር የሚከተሉት አካላት ይኖሯቸዋል።

ሀ/ ጠቅላላ ጉባኤ

ለ/ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ

ሐ/ ማህበራዊ ፍርድ ቤት

**7.የቀበሌ ጠቅላላ ጉባኤ**

ማንኛዉም በዜግነት ኢትዮጵያዊ የሆነ እድሜው 18 አመትና ከዚያ በላይ የሆነ የቀበሌው ነዋሪዎች በሙሉ ወይም አብዛኛው የሚገኙበት ጠቅላላ ጉባኤ ነው።

**8.የቀበሌ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ**

በጠቅላላ ጉባኤው የሚመረጡ ሦስት አባላትን ያቀፈ ኮሚቴ ይሆናል።

**9.የቀበሌ ማህበራዊ ፍርድ ቤት**

በማንኛውም የከተማና የገጠር ቀበሌ አስተዳደር ውስጥ የሚገኝ የዳኝነት አካል ነው።

**10.የቀበሌ አስተዳደር ስልጣንና ተግባር**

1. የፌዴራልና የክልሉን መንግስት ህጎች፣ ደንቦችና መመሪያዎች ተግባራዊ ያደርጋል።
2. የቀበለውን ሰላምና ጸጥታ ይጠብቃል።
3. መንግስታዊ አገልግሎቶችን ለቀበሌው ህዝብ የልማት፣ የማህበራዊና የፍትህ አገልግሎቶች በጥራትና በፍጥነት እንዲያገኙ ያደርጋል።
4. በቀበሌ ነዋሪዎች መካከል መግባባትና በሰላም አብሮ የመኖር የዲሞክራሲ ባህል እንዲጎለብት ያደርጋል።
5. በቀበሌው ክልል ማህበራዊ ጠንቆች እንዲወገዱ የቀበሌውን ነዋሪ ህዝብ ያስተምራል፣ ያነቃል፣ ያደራጃል።
6. የቀበሌው ነዋሪ ህዝብ በአካባቢው የልማት ስራዎች እንዲሳተፍ ያንሳሳል፣ ያደራጃል፣ ይመራል።
7. በቀበሌ ህዝብ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ልማትን ለማፋጠን ሰላማዊና ዲሞክራሲያዊ ባህል እንዲጎለብት መንግስታዊና መንግስታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች ጋር በመተባበር ይሰራል።
8. ቀበሌው የሚያስተዳድራቸው የመንግስት ይዞታ ቤቶች ህግና ደንብ በሚፈቅደው መሰረት ማስተዳደር፣ የቤት እበል ለሚከፈላቸው ህግና ደንብ በሚፈቅደው መሰረት እንዲከፈል ያደርጋል።
9. የቀበሌዉን ፀጥታ ህዝቡን በማስተባበር እንዲጠበቅ ያደርጋል፣ ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል።
10. በቀበሌው የሚገኘውን የመንግስትና የህዝብ ንብረት እንዲጠበቅ ያደርጋል።
11. በቀበሌ ክልል ውስጥ ሕገ-ወጥ ንግድና ሕገ-ወጥ ግንባታን ከጅምሩ ይከላከላል፣ ይቆጣጠራል።
12. በቀበሌ ክልል ውስጥ የሚገኙትን ታሪካዊ ቦታና ቅርሶችን በሕጉ መሰረት እንዲጠበቁ ያደርጋል።

**11.የጠቅላላ ጉባኤ ስልጣንና ተግባር**

1. ጠቅላላ ጉባኤው የቀበሌው ከፍተኛ የአመራር አካል ነዉ።
2. የቀበሌ ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴንና የማህበራዊ ፍርድ ቤት ዳኞችን ይመርጣል፣ ይሽራል፣ ዝርዝሩ በሕግ ይወሰናል።
3. የፌዴራልና የክልል ህጎች ደንቦችና መመሪያዎች ተግባራዊ መሆናቸውን ያረጋግጣል።
4. በቀበሌው ውስጥ መልካም አስተዳደርና የዲሞክራሲ ስርአት መከበሩን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል።
5. በቀበሌው ውስጥ የሚካሄዱ ማንኛውም የኢኮኖሚና ማህበራዊ እቅዶች በስራ ላይ መዋላቸዉን ይከታተላል ይቆጣጠራል።
6. የቀበሌ ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ የስራ እንቅስቃሴ ሪፖርት ዉጤቱን ይገመግማል ይቆጣጠራል።

**12.የቀበሌ ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ስልጣንና ተግባር**

የቀበሌ የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ የቀበሌው ከፍተኛ አስፈጻሚ አካል ሆኖ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፣

1. የቀበሌ ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ተጠሪነቱ ለጠቅላላ ጉባኤና ለክልሉ ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ይሆናል።
2. የፌዴራልና የክልል መንግስት ህጎች፣ ደንቦችና መመሪያዎች ስራ ላይ እንዲውሉ ያደርጋል።
3. የቀበሌውን ስራ እንቅስቃሴ እቅድና በጀት ያዘጋጃል፣ በክልሉ ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ሲጸድቅም ተግባራዊ ያደርጋል።
4. የጠቅላላ ጉባኤ እንዲሁም የክልሉ ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ መመሪያዎችንና ዉሳኔዎችን ተግባራዊ ያደርጋል።
5. ቀበሌው የሚያስተዳድራቸውን ቤቶች ያከራያል፣ የኪራይ ገቢ ይሰበስባል እንዲሁም ደንብና መመሪያ ለመከተል ተገቢዉን እድሳት ያደርጋል።
6. የቤት እበል ለሚከፈላቸዉ በህጉ መሰረት እበል ይከፍላል።
7. የቀበሌ ሰላምና ጸጥታ እንዲጠበቅ ያደርጋል።
8. የቀበሌውን የተፈጥሮ ሀብትና አካባቢ ይጠብቃል፣ ይንከባከባል።
9. በቀበሌው ክልል ውስጥ የሚፈፀሙ ህገ.ወጥ የቤት ግንባታዎችንና በሕገ ወጥ ንግድ በህጉ መሰረት ይከላከላል፣ ይቆጣጠራል።
10. የቀበሌው ኢኮኖሚያዊ ማህበራዊ ልማትና ሰላም ለማስገኘት ልዩ ልዩ ኮሚቴዎች ያቋቁማል ፤ የስራ እንቅስቃሴን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል ፤ ይገመግማል፣
11. የቀበሌው ጽዳት ህዝቡን በማስተባበር እንዲጠበቅ ያደርጋል ፤ ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል።
12. ስለ ቀበሌዉ ነዋሪዎች አስፈላጊዉን መረጃ መዝገቦ ይይዛል ሲጠየቅም ለሚመለከተዉ የመንግስት መስሪያ ቤት ወይም አካል መረጃ ይሰጣል።
13. በቀበሌው ክልል ዉስጥ የሚገኙ ቅርሶችን በወጡ ህጎች መሰረት ይንከባከባል፣ ይቆጣጠራል።
14. የቀበሌውን ነዋሪ ህዝብ ለልማት ስራ ያነሳሳል።
15. ከጠቅላላ ጉባኤና ከክልሉ ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ የሚሰጡትን ሌሎች ተመሳሳይ ተግባራት ያከናዉናል።

www.chilot.me

## 13-የቀበሌ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አደረጃጀት

የቀበሌዉ አስተዳደር ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ሊቀመንበር፣ ም/ሊቀመንበርና ፀሐፊ እንዲሁም አስፈላጊ የሆኑ ሰራተኞች ይኖሩታል።

## 14-የቀበሌ ሊቀመንበር፣ ም/ሊቀመንበርና ፀሐፊ ስልጣንና ተግባር።

### ሀ/የቀበሌ ሊቀመንበር ስልጣንና ተግባር

1. የቀበሌዉ አስተዳደር ኃላፊና ተጠሪ ነዉ።
2. የጠቅላላ ጉባኤና ስራ የአስፈጻሚ ኮሚቴ ስብሰባዎችን በሰብሳቢነት ይመራል።
3. የቀበሌዉን ፀጥታና ሰላም ጉዳዮችን በበላይነት ይመራል።
4. የመንግስት ህጎች፣ ፖሊሲዎች፣ ፕሮግራሞችና መመሪያዎች በትክክል ስራ ላይ እንዲዉሉ ያደርጋል።
5. በፋይናንስ ደንብና መመሪያ መሰረት የገንዘብ ወጪን ያዛል።
6. ከፀሐፊዉ ጋር በመሆን በገንዘብ ወጪ ሰነድ ላይ ይፈርማል።
7. በቀበሌዉ ክልል ዉስጥ ለሚከናወኑ ህገ-ወጥ ግንባታዎችና ሕገ ወጥ ንግዶች መከላከልን እንዲሁም የቀበሌዉን ጽዳት በበላይነት ይመራል።
8. በቀበሌዉ ክልል ዉስጥ ለሚከናወኑ ህገ-ወጥ ግንባታዎች እንቅስቃሴ መገታት የበላይ ኃላፊ ነዉ።
9. በቀበሌዉ ለሚከናወን ፀረ-ኤድስ እንቅስቃሴ በበላይነት ይመራል።
10. ከጠቅላላ ጉባኤ፣ ከቀበሌ ስራ አስፈጻሚና ከክልል ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ የሚሰጠዉን ሌሎች ተግባሮች ያከናዉናል።
11. ለጠቅላላ ጉባኤና ለክልሉ ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ሪፖርት ያቀርባል።

### ለ/ የቀበሌ ም/ሊቀመንበር ስልጣንና ተግባር

1. የቀበሌዉን ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች በበላይነት ይመራል።
2. በቀበሌዉ ዉስጥ የህዝብ ግንኙነት ስራን በበላይነት ይመራል።
3. የህዝብ መፅሐፍት ቤቶች እንዲስፋፉ ያደርጋል።
4. በቀበሌዉ ዉስጥ ያሉት ታሪካዊ ቦታና ቅርሶች አስፈላጊዉን ጥበቃና እንክብካቤ እንዲያገኙ ያደርጋል።
5. የህዝብ ዉይይት መድረኮችን ያዘጋጃል።
6. ስፖርታዊ እንቅስቃሴዎች እንዲዘወተሩ ያደርጋል።
7. የቀበሌ ወጣቶችን በማደራጀት በስራ ፍቅርና በጥሩ ስነ-ምግባር እንዲገነቡ ያደርጋል።
8. ወጣቶች እቅማቸዉን በልማት ስራ ላይ እንዲያዉሉ፡ ጤናማና አምራች ኃይል እንዲሆኑ እንድሁም ፍላጎታቸዉን መሰረት ባደረገ በተለያዩ የገቢ ማስገኛ ፕሮግራም ዉስጥ እንዲታቀፉ ድጋፍ ይሰጣል።
9. የህዝቡ የስራ ባህል እንዲዳብር የተለያዩ ስልቶችን በማዉጣት ይንቀሳቀሳል።
10. በቀበሌዉ ህዝባዊ ማህበራት እንዲጠናከርና የልማት ተሳትፎአቸዉ እንዲጎለብት ያደርጋል።
11. የሴቶች ህገ-መንግስታዊ መብቶች በቀበሌዉ መከበሩን ያረጋግጣል፣ በዚሁ መሰረት ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ተሳትፎአቸዉ እንዲያድግ ያደርጋል።
12. የህብረት ስራ ማህበራት እንዲቋቋሙና ህዝቡ የቁጠባ ባህልን እንዲያጎለብት ጥረት ያደርጋል።
13. ጎጂ ባህል፣ አስገድዶ መድፈርና የጎዳና ተዳዳሪዎች ህጋዊ ጥበቃ እንዲደረግላቸዉ ስልት በመቀየስ ስራ ላይ እንዲዉል ያደርጋል።
14. የቀበሌዉ ህዝብ በጋራ በልማት ስራ ላይ እንዲሳተፍ ያደርጋል።
15. የህዝቡ ባህልና ቋንቋ እንዲያድግ ጥረት ያደርጋል።
16. ከሊቀመንበሩ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራትን ያከናዉናል።
17. የስራ አፈጻጸሙን ለቀበሌዉ ሊቀመንበር ያቀርባል።
18. ሊቀመንበሩ በሌለበት ጊዜ ተክቶ ይሰራል።

### ሐ/ የቀበሌ ፀሐፊ ስልጣንና ተግባር

1. የቀበሌዉ አስተዳደር ጽ/ቤት ያደራጃል፣ ይመራል።
2. የቀበሌዉ አስተዳደር ሰነዶችና ማህተም በአግባቡ ይይዛል።
3. የቀበሌዉ ገቢ በአግባቡ እንዲሰበሰብ ያደርጋል።
4. የቀበሌዉን ጠቅላላ ጉባኤና ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ቃለ ጉባኤ ይይዛል።
5. የቀበሌዉን አስተዳደር ጽ/ቤት ንብረት ያስተዳድራል።
6. ከሊቀመንበሩ ጋር በመሆን በገንዘብ ወጪ ሰነዶች ላይ ይፈርማል።
7. የጽህፈት ስራዎችን በሃላፊነት ያስተዳድራል።
8. የቀበሌዉን አስተዳደር ሰራተኞች በኃላፊነት ያስተዳድራል፣ ይመራል፣ ይቆጣጠራል።
9. የቀበሌዉን ሒሳብ ሹም ስራ ይሰራል።
10. ከቀበሌዉ ሊቀመንበር ጋር በመሆን የተለያዩ አጀንዳዎችን ያዘጋጃል።
11. የስራ እንቅስቃሴዉን በየጊዜዉ ለቀበሌዉ ሊቀመንበር ሪፖርት ያደርጋል።
12. ሌሎች በቀበሌ ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ወይም በኮሚቴ አባላት የሚሰጡትን ተግባራት ያከናዉናል።

## ምዕራፍ ሦስት
## ስለ ምርጫና የሥራ ዘመን

## 15-ስለ ምርጫ

### 1. ስለ ምርጫ አፈጻጸም

ሀ- አብዛኛዉ የቀበሌዉ ህዝብ ነዋሪ በተገኙበት ስብሰባ በሚጠቆሙ ዕጩዎች መካከል በአብላጫ ድምጽ የቀበሌዉ ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላትና ማህበ ራዊ ፍ/ቤት ዳኞችን ይመርጣል።

ለ- የምርጫዉ አፈጻጸም ዝርዝር መመሪያ በክልሉ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ያወጣል።

## 16.የቀበሌ ሥራ አስፈጻሚ የሥራ ዘመን

ሀ- የቀበሌ አስተዳደር የስራ ዘመን መደበኛ የቀበሌ አስተዳደር ምርጫ እስኪካሔድ ድረስ ነዉ።

ለ- ከላይ የተጠቀሰዉ የቀበሌ የሥራ አስፈጻሚ የስራ ዘመን እንደተጠበቀ ሆኖ ነገር ግን ሐላፊነታቸዉን በተገቢዉ መንገድ መወጣት ባልቻሉበት ጊዜ በነዋሪ ህዝብ ላይ የሚያስከትለዉ ጉዳት ከፍተኛ ሲሆን የክልሉ ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ የቀበሌዉ አስተዳደር ማገድ ያችላል።

ሐ- በክልሉ ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ የቀበሌዉ ስራ አስፈጻሚ ሲታገድ በአንድ ወር ዉስጥ ጠቅላላ ጉባኤ ተሰብስቦ ሌሎች ስራ አስፈጻሚዎች ይመርጣል። ሆኖም ምርጫዉ እስኪካሔድ ድረስ የቀበሌዉ ጊዜያዊ ስራ አስፈጻሚዎች ይወከላል።

## ምዕራፍ አራት
## ስለ ሥራ ሁኔታ

**17.የስራ ሰአት**

የቀበሌ ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላትና የማህበራዊ ፍርድ ቤት ዳኞች በክልሉ መንግስት በመደበኛ የስራ ሰአት ለነዋሪዉ ህዝብ አገልግሉት ይሰጣሉ።

**18-ክፍያ**

የቀበሌ ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላትና የማህበራዊ ፍርድ ቤት ዳኞች በየወሩ ደመወዝ እየተከፈላቸዉ የሚሰሩ ይሆናሉ። ዝርዝር መመሪያዉ የክልሉ ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ በሚያወጣዉ መመሪያ መሰረት ይወሰናል።

**19.ግልጽና ተጠያቂነት**

ሀ- የቀበሌ ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላት በሰሩት ስራ ወይም በሰጡት ዉሳኔ በጋራም ሆነ በተናጠል ተጠያቂ ይሆናሉ።

ለ- የቀበሌ ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላት ስለ መንግስት የወጡትን ህጎች ደንቦችና መመሪያዎች እንዲሁም ፖሊሲዎች ለነዋሪዉ ህዝብ መድረኮችን በማዘጋጀት ገለጻ በማድረግ የማሳወቅ ግዴታ አለባቸዉ።

ሐ-የቀበሌ ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላት አስፈላጊዉን መረጃዎች ለሚመለከተዉ አካላት የመስጠት ግዴታ አለባቸዉ።

መ- የቀበሌ ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ለሚመለከተዉ አካል የሚሰጠዉ መረጃ ትክክለኛና የነዋሪዉን ህዝብ ጸጥታና ሰላም የማያናጋ መሆኑን የማረጋገጥ ኃላፊነት አለበት።

**20-ስለ ስብሰባ**

ሀ- የቀበሌ ጠቅላላ ጉባኤ በዓመት ሁለት ጊዜ በየስድስት ወሩ ይሰበሰባሉ።

ለ- የቀበሌ አስተዳደር አመራር አካላት በወር አንድ ጊዜ ይሰበሰባሉ።

ሐ- የቀበሌ ሥራ አስፈጻሚ አባላት በሳምንት አንድ ጊዜ ስብሰባ ያደርጋል።

መ- ከላይ "ሀ" እና "ለ" ላይ የተመለከተዉ ግዴታ እንደተጠበቀ ሆኖ አስፈላጊ ሲሆን ጠቅላላ ጉባኤና ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አስቸኳይ ስብሰባ ሊጠራ ይችላል።

ሰ- ከዚህ በላይ በተራ ቁጥር ከ"ሀ" እስከ "ሐ" ያሉት እንደተጠበቁ ሆነዉ የራሳቸዉ ስነ ስርአት ዉስጠ ደንብ ሊያወጡ ይችላሉ።

**21-ስለዉሳኔ አሰጣጥ**

የጠቅላላ ጉባኤና የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ዉሳኔ የሚተላለፈዉ ምን ጊዜም በአብላጫ ድምጽ ሲደገፍ ይሆናል።

## ምእራፍ አምስት
## ስለቀበሌዎች ማህበራዊ ፍርድ ቤት

**22-ስለፍርድ ቤት አደረጃጀትና ተጠሪነት**

1. ማንኛዉም ማህበራዊ ፍርድ ቤት
   ሀ/ አንድ ሰብሳቢ ዳኛ፡ ሁለት ዳኞች እና ሁለት ተጠባባቂ ዳኞች ያሉት አንድ ችሎት እና
   ለ/ አንድ ሬጅስትራር ይኖሩታል።
2. ተጠሪነቱ ፍርድ ቤቱ ለሚገኝበት ቀበሌ ጠቅላላ ጉባኤ ይሆናል።

**23-የሰብሳቢ ዳኛ ስልጣንና ተግባር**

የማህበራዊ ፍርድ ቤት ሰብሳቢ ዳኛ ተጠሪነቱ ለቀበሌዉ ጠቅላላ ጉባኤና ለመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ይሆናል።

1. ፍርድ ቤተን ይወክላል፡
2. ችሎቱን በሰብሳቢነት ይመራል፡
3. ፍርድ ቤቱ ስላከናወናቸዉ ስራዎችና ስላጋጠሙት ችግሮች በ6 ወር አንድ ጊዜ ለቀበሌ ጠቅላላ ጉባኤ እና ለመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ፕሬዝዳንት ዘገባ ያቀርባል።

**24-የማህበራዊ ፍርድ ቤት ሬጂስትራር ስልጣንና ተግባር**

የማህበራዊ ፍርድ ቤት ሬጂስትራር ፍርድ ቤቱ በሚገኝበት የቀበሌ አስተዳደር ጽህፈት ቤት ተቀጣሪነት የሚመደብ ሆኖ፦

ሀ- የክስ አቤቱታ እየተቀበለ መዝገብ ከፍቶ ለችሎት ያቀርባል።

ለ- የይግባኝና የዉሳኔ ግልባጭ ለባለጉዳይ ይሰጣል።

ሐ- የዉሳኔ ግልባጭና በችሎት የሚሰጡ ትዕዛዞችን ወጪ ያደርጋል።

መ- የፍርድ ቤቱን አስተዳደርና የእለት ስራ በቅርብ ይመራል።

ሠ- በችሎት የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናዉናል።

**25-ስለማህበራዊ ፍርድ ቤት የክልል የዳኝነት ስልጣን**

1. ማንኛዉም የማህበራዊ ፍርድ ቤት አንድን ጉዳይ ለማየት በዚሁ አዋጅ ሥልጣን የሚኖረው፡
   ሀ.አመልካቹ ወይም ተከሳሹ የሚኖረው ወይም
   ለ. ክርክር ያስነሳው ጉዳይ የሚገኘው ወይም
   ሐ. ጥፋቱ የተፈጸመው የማህበራዊ ፍርድ ቤቱ በተቋቋመበት የቀበሌ ክልል የሆነ እንደሆነ ነው።
2. አንድ ክስ ከአንድ በላይ በሆኑ ማህበራዊ ፍርድ ቤት የቀረበ እንደሆነ የክሱ ማመልከቻ በቀደምትነት የቀረበለት ማህበራዊ ፍርድ ቤት የዳኝነት ስልጣን እንዳለው ተቆጥሮ ዉሳኔ ይሰጣል።

**26-በፍትሐብሔር ጉዳዮች የሚኖረው የዳኝነት ሥልጣን**

1. ማንኛዉም ማህበራዊ ፍርድ ቤት ፡
   ሀ. ግምቱ ከ1000 ብር የማይበልጥ የገንዘብ ወይም የንብረት ክርክር
   ለ. በቀበሌው አስተዳደር ክልል ዉስጥ ቤቶችና ቦታዎች የኪራይና የአገልግሎት ክፍያ በመጠየቅ የሚነሱ ክርክሮች፣
   ሐ-በፍትሃብሔር ህግ ስለ ቅርንጫፎችና ዛፎች ስሮች (1212) አጥር ወይም ቤት ስለማሳደስ (1218) ስለ ጠፉ ነገሮች ወይም እንስሶች (1219) ስለመተላለፊያ ቦዮችና ቧንቧዎች

www.chilot.me

(1220) ስለመተላለፍ መብት (1221) ስለዝናብ ዉሃ (1245) እና ከወደታች ስለሚገኝ መሬት ግዴታዎች (1246) የሚነሱ ክርክሮችን የማየት ስልጣን ይኖረዋል፡፡

2- ማናቸዉም የማህበራዊ ፍርድ ቤት በመንግሥት አካላት ለሚሰጥ ነጻ አገልግሎት የአመልካችን የኑሮ ሁኔታ አረጋግጦ ማስረጃ ሊሰጥ ይችላል፡፡

## 27-በወንጀል ጉዳዮች የሥረ ነገር ሥልጣን

ሀ. ማናቸዉም ማህበራዊ ፍርድ ቤት የማህበራዊ ፍርድ ቤቶችን ለማቋቋም በወጣዉ አዋጅ ቁጥር 37/82 አንቀጽ 15 ስር ከተደነገጉ የወንጀለኛ መቅጫ ህግ አንቀጽ፡- 734 እስከ 737፣745፣ 757፣760 እስከ 764፣768-775፣777 እስከ 782፣784፣785፣792 እስከ 816 ስር የሚነሱ የደንብ መተላለፍ ክሶች፤

ለ- በክልሉ ፍትህ ቢሮ ሲመራለት በወንጀለኛ መቅጫ ህግ ሌሎች ድንጋጌዎች ስር የሚነሱ የደንብ መተላለፍ ክሶችን፤ በመጀመሪያ ደረጃ አይቶ የመወሰንስልጣን ይኖረዋል፡፡

## 28-ስለ ቅጣት

1- ማናቸዉም ማህበራዊ ፍርድ ቤት ተከሳሹ ጥፋተኛ መሆኑ በሚገባ ካልተረጋገጠ በነፃ ያሰናብታል፡፡

2- ተከሳሹ ጥፋተኛ መሆኑ በሚገባ ሲረጋገጥ ከዚህ በታች ከተዘረዘሩት ቅጣቶች መካከል እንደጥፋቱ ክብደት በአንዱ ሊቀጣው ይችላል፡፡

ሀ. ማስጠንቀቂያ መስጠት ወይም

ለ. ጥፋተኛው ተበዳዩን ሰው ይቅርታ እንዲጠይቅ ማድረግ፤ወይም

ሐ. የጥፋተኛው ድርጊት አሳፋሪ መሆኑን ማሳወቅ ወይም

መ. እንደ ተከሳሹ የመክፈል አቅም በአንድ ጊዜ ወይም በየጊዜው ተከፍሎ የሚያልቅ ከብር አንድ እስከ ብር ሦስት መቶ በሚደርስ መቀጮ መቅጣት ወይም

ሠ. ከመደበኛ የሥራ ሰዓት ዉጭ ከአሥራ አምስት ቀን ያልበለጠ ለህብረተሰቡ ጠቃሚ የሆነ ከሙያው ጋር ተመሳሳይነት ያለው ማህበራዊ ሥራ ማሠራት ወይም

ረ. እስከ ሁለት ወር ለመድረስ በሚችል የማረፊያ ቤት እሥራት መቅጣት ወይም

ሰ. ጥፋቱ የተፈጸመው በንብረት ወይም በአካል ላይ ጉዳት ማድረስ ከሆነ በከሳሽ ጠያቂነት ከብር አምስት መቶ የማይበልጥ ካሳ ማስከፈል፡፡

3. ተደጋጋሚ ወይም ከአንድ በላይ የሆኑ ጥፋቶች ፈጽሞ በተገኘ ተከሳሽ ላይ ማህበራዊ ፍርድ ቤቱ በንዑስ አንቀጽ (2) ከተመለከቱት ከአንድ በላይ የሆኑ ቅጣቶች ሊወስን ይችላል፡፡

4. አስፈላጊ መሆኑን ካመነበት ማህበራዊ ፍርድ ቤቱ በንኡስ አንቀጽ 2 ከተገለጸው ቅጣት በተጨማሪ ተከሳሹ የደንብ መተላለፍ ጥፋት የፈጸመበት መሣሪያ በዉርስ ለመንግሥት ገቢ እንዲሆን ለማዘዝ ይችላል፡

5. ተከሳሹ ጥፋቱን የፈጸመው በሕዝብ መዝናኛ ሥፍራዎች በመጠጥ ቤቶች ወይም በሌሎች ተመሳሳይ ሥፍራዎች ከሆነ ማህበራዊ ፍርድ ቤቱ ካመነበት ከአንድ ወር ለማይበልጥ ጊዜ በሥፍራው እንዳይገኝ በማገድ ተጨማሪ ቅጣት ሊወስንበት ይችላል፡፡

6. ማህበራዊ ፍርድ ቤቱ ቅጣቱን የሚወስነው የጥፋቱን ክብደት የአጥፊዉን የኑሮ ሁኔታ የገቢ መጠን እና ስለቤተሰቡ አስተዳደር ያለበትን ኃላፊነት በማመዛዘን ይሆናል፡፡

## 29. ማህበራዊ ፍርድ ቤትን ስለመድፈር

ማናቸዉም ማህበራዊ ፍርድ ቤት በችሎት ላይ እንዳለ የስድብ ዛቻ የፌዝ ወይም ሌላ ተመሳሳይ የሁከት ድርጊት የፈጸመን ሰው ቀጠሮ ሳያደርግ ወዲያዉኑ ዝርዝር ሁኔታዉን በመመዝገብ

1- ከብር ሀምሳ የማይበልጥ መቀጫ ወይም

2- እስከ 10 ቀን ለመድረስ በሚችል በማረፊያ ቤት የሚቆይ እሥራት ለመቅጣት ይችላል፡፡

# ምዕራፍ ስድስት

# ስለ ማህበራዊ ፍርድ ቤቶች የዳኝነት ሥነሥርአት

## 30-መሠረቱ

1. ማናቸዉም ማህበራዊ ፍርድ ቤት የሚከተለው የዳኝነት ሥነ ሥርአት በዚህ አዋጅ የተደነገገው ይሆናል፡፡

2. ማንኛዉም ሰው በችሎት በመገኘት በቀረበው ጉዳይ ላይ የችሎቱን ሰብሳቢ አስፈቅዶ ትችት የማቅረብ መብት ይኖረዋል፡፡ ሆኖም ፍርድ ቤቱ ዉሳኔ የሚሰጠው ህግን ተከትሎ ይሆናል፡፡

## 31-ስለዳኝነት ነፃነት

የማህበራዊ ፍርድ ቤት ዳኞች የዳኝነት ሥራቸዉን በሙሉ ነፃነት ከሕግ በስተቀር በሌላ ስልጣን አይመሩም፡፡

## 32-በግልጽ ችሎት ስለማየት

ለሕዝብ መልካም ጠባይ ወይም ደህንነት አስፈላጊ ሆኖ ካላገኘው በስተቀር የማህበራዊ ፍርድ ቤት ማናቸዉንም ጉዳይ የሚያየው በዝግ ሳይሆን በግልጽ ችሎት ነው።

## 33- ስለ ማስቻያ ስፍራ

በቀበሌው ክልል መደበኛ ችሎት ስፍራ ያስችላል።

## 34- በችሎት ስለመነሳት

1- ማንኛዉም የማህበራዊ ፍርድ ቤት አባል /ዳኛ/

ሀ/ከተከራካሪ ወገኖች ከአንደኛዉ ጋር የቅርብ የሥጋ /የጋብቻ/ ዝምድና /ያለው ወይም

ለ.ከተከራካሪ ወገኖች ከአንደኛው ጋር ጠብ ያለው ወይም

ሐ.ክርክር የተነሳበትን ነገር አስቀድሞ በእርቅ ወይም በዳኝነት ያየው ከሆነከችሎት ይነሳል።

2- ተቃዉሞ የቀረበበት ማህበራዊ ፍርድ ቤት አባል ሁኔታዉን ተረድቶ በራሱ ፍቃድ ካልተነሳ የቀሩት ዳኞች ተቃዉሞዉን መርምረው ዉሳኔ ይሰጣሉ። በተሰጠው ዉሳኔ ይግባኝ ማቅረብ አይችልም።

3- በተቀነሰው ዳኛ ምትክ ተጠባባቂ ዳኛ ይሰየማል።

## 35- ስለ ክስ አመሰራረት

ማንኛዉም ማህበራዊ ፍርድ ቤት የቀረበለትን ክስ ወይም አቤቱታ ተቀብሎ ከመረመረ በኋላ ተከራካሪ ወገኖች ምስክሮችና ሌሎችም ጉዳዩን ለማጣራት አስፈላጊ የሆኑ ሰዎች እንዲቀርቡ መጥሪያ እንዲደርሳቸው ያደርጋል።

## 36- ስለ መጥሪያ አሰጣጥ

ማህበራዊ ፍርድ ቤት ተከሶ የሚቀርብ ማንኛውም ሰው የተከሰሰበትን ጉዳይ አስቀድሞ እንዲያውቀውና ተዘጋጅቶ እንዲቀርብ ጉዳዩ የሚሰማበትን ቀን ሰዓትና ስፍራ የከሳሹን ስምና የክስ አይነት ባጭሩ ተገልጾ መጥሪያ ይላክለታል፤ ለሚፈለጉ ሌሎች ሰዎች የሚተላለፈውም መጥሪያ በጽሁፍ ይሆናል።

## 37- ስለ ክስ መስማት አጀማመር

1. የማህበራዊ ፍርድ ቤት ክሱ እንዲሰማ በቀጠረበት ቀንና ሰዓት ያስችላል

2. ክሱን መስማት ከመጀመሩ በፊት በመዝገብ ዉስጥ የተጠቀሱትን ተከራካሪ ወገኖች በችሎት መገኘታቸዉን ያረጋግጣል።

3. ክሱ የደንብ መተላለፍን የሚመለከት ከሆነ እንዲሰማና መከላከል እንዲችል ተከሳሹ እራሱ በችሎት መገኘት ይኖርበታል።

## 38- ክስን ስለማንሳት

1. አንድ ከሳሽ የማህበራዊ ፍርድ ቤት በጉዳዩ ላይ የፍርድ ዉሳኔ ከመስጠቱ አስቀድሞ በማንኛዉም ጊዜ ያቀረበዉን ክስ ማንሳት ይችላል።

2. አንድ ከሳሽ ክሱን ከተወ በኋላ በዚያው ጉዳይ ለሁለተኛ ጊዜ ክስ ማቅረብ አይችልም።

## 39- ማስረጃ እንዲቀርብ ስለመጠየቅ

1. ማንኛዉም የማህበራዊ ፍርድ ቤት የቀረበለትን ጉዳይ ለመወሰን የሚያስፈልጉትን ምስክሮች ለመጥራትና የጽሑፍ ማስረጃዎችን አስቀርቦ ለማየት ይችላል።

2. ማንኛዉም ሰው ወይም መሥሪያ ቤት ወይም ድርጅት የማህበራዊ ፍርድ ቤት ሲጠራው መቅረብ ወይም የተጠየቀዉን ማስረጃ በተገለው ጊዜ ዉስጥ የማቅረብ ግዴታ አለበት፡

## 40- በቀነቀጠሮው ከሳሽና ተከሳሽ ወይም ከሳሽ ስለመቅረብ

1. ክሱ እንዲሰማ በተቀጠረበት ቀን ከሳሽናተከሳሽ ሳይቀርቡ ቢቀሩ የክሱ መዝገብ ይዘጋል።

2. ከሳሽ ያልቀረበና ተከሳሽ ግን ቀርቦ ክስ የቀረበበትን ነገር ካመነ የቀረበዉም ክስ ፍትሐ-ብሐርን በሚመለከት ጉዳይ ከሆነ በእምነቱ መሠረት ለከሳሽ ይፈረዳል።

3. ከሳሽ ሳይቀርብ ቀርቶ ተከሳሽ ግን ቀጠሮዉን አክብሮ በመቅረቡ ምክንያት ለተከሳሽ በቂ የሆነ ኪሳራ እንዲያገኝ ይታዘዛል። ተከሳሽ የካደ እነደሆነ ግን የክሱ መዝገብ ይዘጋል።

## 41- ጥሪን ማክበር

1. በደንብ መተላለፍ ጉዳይ አንድ ተከሳሽ በችሎት ተገኝቶ መልስ እንዲሰጥ መጥሪያ ደርሶት ሳይቀርብ የቀረ እንደሆነ በሚቀጥለው ቀጠሮ በቀበሌው ፀጥታ ኮሚቴ ወይም ፖሊስ አማካኝነት ተይዞ እንዲቀርብ ፍርድ ቤቱ ትዕዛዝ ይሰጣል።

www.chilot.me

2. በፍትሐ-ብሔር ጉዳይ ተከሳሽ መጥሪያ ደርሶት ሳይቀርብ የቀረ እንደሆነ የማህበራዊ ፍርድ ቤት ጉዳዩን በሌለበት አይቶ ሊወስን ይችላል::

3. በዉሳኔ አፈጻጸም ጉዳይ መጥሪያ ደርሶት ጥሪዉን ያላከበረ እንደሆነ እና መቅረቡም አስፈላጊ ካልሆነ ዉሳኔው በንብረት ላይ እንዲፈጸም ያዛል:: የተከሳሹ መቅረብ አስፈላጊ ከሆነ ግን በጉኡስ ቁጥር1 ሥር የተደነገገው ተፈጻሚ ይሆናል::

4 በቀነ ቀጠሮው ቀርቦ የምስክርነት ቃሉን እንዲሰጥ ወይም የጽሑፍ ማስረጃ ይዞ እንዲቀርብ መጥሪያ ደርሶት ሳይቀርብ የቀረ ሰው በቀበሌው የፀጥታ ኮሚቴ ወይም በክልሉ ፖሊስ አማካኝነት ተይዞ እንዲቀርብ ፍርድ ቤቱ ትዕዛዝ ይሰጣል::

5. የተላከለትን የማህበራዊ ፍርድ ቤት መጥሪያ ተቀብሎ ደረሰኝ ለመስጠት እንቢተኛነቱን በ2 ምስክር ካረጋገጠ በኋላ ተገቢ የሆነዉን ትእዛዝ መስጠት አለበት::

## 42 የተዘጋዉን መዝገብ ስለማንቀሳቀስ

1. ክሱ እንዲሰማ በተቀጠረበት ቀን ከሳሽ ሳይቀርብ የቀረው ከአልጋ ለመነሳት በማያስችል ህመም የቅርብ ዘመድ ሞቶ ወይም ከቦታ ቦታ ለመዘዋወር በማያስችሉ ወይም ሌሎች ተመሳሳይ ከአቅም በላይ የሆኑ ሁኔታዎች መኖር ምክንያት ከሆነ እክሉ በተወገደ በ30 ቀን ዉስጥ አቤቱታዉን በጽሑፍ አብራርቶ ሊቀርብ ይችላል:: በዚህ የጊዜ ገደብ ካልቀረበ የማህበራዊ ፍርድ ቤት ጥያቄዉን ውድቅ ያደርጋል::

2. የማህበራዊ ፍርድ ቤት የቀረበዉን አቤቱታ ከመረመረ በኋላ ካመነበት የተዘጋዉን መዝገብ እንደገና ከፍቶ እንዲታይ ለማድረግ ይችላል::

3. ተከሳሽ በሌለበት የተሰጠዉን ዉሳኔ እንዲነሳለት በተመሳሳይ ካመለከተ የማህበራዊ ፍርድ ቤት ተከሳሽ ያቀረበዉን አቤቱታ ተቀብሎ ከመረመረ በኋላ ካመነበት በሌለበት የተሰጠዉን ዉሳኔ እንደገና እንዲታይ ለማድረግ ይቻላል::

4. ፍርድ ወይም ዉሳኔ በንባብ በሚሰማበት ቀን አልነበርኩም ብሎ የዚህ አይነት አቤቱታ ሊያቀርብ ተከሳሽ ግን ዉሳኔዉን እንዲነሳለት የማመልከት መብት አይኖረዉም::

## 43 ስለ ዉሳኔ አሰጣጥ

1. የቀረበው ክርክር ከተጠናቀቀ በኋላ ፍርድ ቤቱ በጉዳዩ ላይ በአጭር ጊዜ ዉስጥ ዉሳኔ ይሰጣል:: ሆኖም 15 ቀናት መብለጥ የለበትም::

2. የማህበራዊ ፍርድ ቤቱ በሚሰጠው ዉሳኔ በተቻለ መጠን በሙሉ ድምጽ ይሆናል:: ሙሉ ድምጽ ካልተገኘ ዉሳኔው በድምጽ ብልጫ ይሰጣል፤ አነስተኛ አስተያየትም በዉሳኔው ላይ ይመዘግባል::

3. የማህበራዊ ፍርድ ቤት ዉሳኔዉን በሚሰጥበት ጊዜ በክርክሩ ሂደት የቀረቡትን ነጥቦችና ማስረጃዎች በመግለጽ በዉሳኔው መሠረት ያደረጋቸዉን ምክንያቶች በአጭሩ በፍርዱ ላይ ያሰፍራል::

## 44 ስለ ዉሳኔው አፈጻጸም

1. በማህበራዊ ፍርድ ቤት የተሰጠ ዉሳኔ በይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ካልታገደ በስተቀር ዉሳኔ ከተሰጠበት ቀን በኋላ አፈጻጸሙ ይቀጥላል::

2. ፍርድ ቤቱ የሰጠዉን ዉሳኔ እራሱ ለማስፈጸም ወይም አግባብ ላለው ለሌላ ፍርድ ቤት እንዲያስፈጽም ለመወከል ይችላል::

3. በማህበራዊ ፍርድ ቤት የሚወሰን መቀጫ ለመንግሥት ገቢ ይሆናል::

4. የማረፊያ ቤት እስራት ቅጣት በወንጀለኛ መቅጫ ህግ መሠረት በቅጣት አፈጻጸም ሕግ በተወሰነው ቦታና ሁኔታ ይፈጸማል::

5. የማህበራዊ ፍርድ ቤት ዉሳኔ ለማስፈጸም የተላለፈዉን ትእዛዝ የሚመለከተው አካል ይፈጽማል::

## 45. ስለ ወጪ

ለማሕበራዊ ፍርድ ቤቱ በሚቀርብ ጉዳይ ላይ እያንዳንዱ ተከራካሪ ወገን የራሱን ወጪ ይችላል፤ ሆኖም ከሳሽ ክስ ያቀረበው ሆን ብሎ እያወቀ ተከሳሽን ለማጉላላት መሆኑን ፍርድ ቤቱ ካመነበት ለተከሳሹ እስከ አንድ መቶ ብር የሚደርስ ኪሳራ ሊቆርጥ ይችላል::

## 46 ስለ ይግባኝ

1. ማህበራዊ ፍርድ ቤቱ በሰጠው ዉሳኔ ቅሬታ ያለው ተከራካሪ ወገን ዉሳኔ በተሰጠበት በ30 ቀን ዉስጥ ይግባኙን ለመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ያቀርባል::

2. ይግባኝ ባዩ የመዝገቡ ግልባጭ እንዲሰጠው ሲጠይቅ በአንድ ሳምንት ዉስጥ ተገልብጦ በሬጅስትራሩ አማካኝነት ይሰጠዋል

## 47-ስለ ዳኝነት ክፍያ

የማህበራዊ ፍርድ ቤት በሚሰጠዉ የዳኝነት አገልግሎት ከማንኛዉም ክፍያ ነፃ ይሆናል::

www.chilot.me

## ምዕራፍ ሰባት

## ስለዳኞች ምርጫና የሥራ ዘመን

### 48-በዳኝነት ለመመረጥ ስለሚያበቁ መመዘኛዎች

ሀ/ እድሜዉ 21 ዓመት በላይ የሆነ፡

ለ/ ማንበብና መጻፍ የሚችል

ሐ/ በመልካም አርአያነቱ፡ በታታሪነቱና በታማኝነቱ የአካባቢዉን ህዝብ አክብሮት ያተረፈ የቀበሌው ነዋሪ የማህበራዊ ፍርድ ቤት ዳኛ ሆኖ የመመረጥ መብት አለው፡፡

### 49 የማህበራዊ ፍርድ ቤት ዳኞች የሥራ ዘመን

1. የማህበራዊ ፍርድ ቤት ዳኞች የሥራ ዘመን መደበኛ የቀበሌዎች አስተዳደር ምርጫ እስኪካሄድ ድረስ ይሆናል፡፡

2. የማህበራዊ ፍርድ ቤት ዳኞች የተጣለባቸዉን ኃላፊነት በሚገባ መወጣት ባልቻሉበት ወቅት በጠቅላላ ጉባኤ ዉሳኔ መሠረት በማናቸዉም ጊዜ ከሥራ ሊያሰናብታቸው ይችላል፡፡

## ምዕራፍ ስምንት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### 50/ የሥልጣን ዉክልና

ይህን አዋጅ ለማስፈጸም ይረዳ ዘንድ የክልሉ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ደንቦችና መመሪያዎችን የማውጣት ስልጣን አለው፡፡

### 51 የመተባበር ግዴታ

የቀበሌ አስተዳደሮች ከዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች ጋር የሚቃረን ካልሆነ በስተቀር ከሐረር ከተማ ማዘጋጃ ቤትና ከሌሎች የመንግሥት አካላት ጋር ያላቸዉን ግንኙነት በመቀጠል የመተባበር ግዴታ ይኖርባቸዋል፡፡

### 52 ከፍትህ ቢሮ ጋር የሚኖረው ግንኙነት

የክልሉ ፍትህ ቢሮ የማህበራዊ ፍርድ ቤቶችን አሠራር ቀልጣፋ ለማድረግ የሚያግዙ የህግ ማብራሪያዎችን አዘጋጅቶ ያሰራጫል፡ ትምህርታዊ ሴሚናሮችን ይሰጣል፡፡

### 53 ተፈጻሚነት የሌላቸው ህጎች

ይህን አዋጅ የሚቃረን ማንኛዉም ህግ፡ ደንብ፡ መመሪያና ተለምዶአዊ አሠራር በዚህ አዋጅ የተሸፈኑ ጉዳችን በተመለከተ ተፈጻሚነት አይኖራቸዉም፡፡

### 54 አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ ከዛሬ ግንቦት 24 ቀን 1996 ዓ/ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

ሐረር ግንቦት 24 ቀን 1996 ዓ.ም

ፉአድ ኢብራሂም

የሐረሪ ሕዝብ/ብ/ክ/መንግሥት

ፕሬዝዳንት



www.chilot.me

የሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት

# ሐ ረ ር ነ ጋ ሪ ጋ ዜ ጣ

# HARAR NEGARI GAZETA

OF THE HARARI PEOPLE NATIONAL REGIONAL STATE

| | |
|---|---|
| 8ኛ ዓመት ቁጥር 14<br>8th Year N° 14 | ሐረር ነሐሴ 15 ቀን 1996 ዓ.ም<br>HARAR. Aug 22th, 2004. |

| | | |
|---|---|---|
| ያንዱ ዋጋ<br>unit price 2.00 | በሐረሪ ህዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት<br>ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ | የፖስታ ሳጥን ቁጥር 272<br>P.O.BOX |

## ማዉጫ

አዋጅ ቁጥር 45/1996 ዓ.ም
የሐረሪ ህዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ለ1997 የበጀት ዓመት ሥራዎች የታወጀ የበጀት አዋጅ-----ገጽ 367

## አዋጅ ቁጥር 45/1997 ዓ.ም
## የሐረሪ ህዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ለ1997 የበጀት ዓመት ሥራዎች የታወጀ የበጀት አዋጅ

በ1997 የበጀት ዓመት በክልሉ ዉስጥ ለሚከናወኑ ሥራዎችና አገልግሎቶች የሚያስፈልገዉን በጀት በበጀት ዓመቱ መጀመሪያ ላይ አጽድቆ ሥራ ላይ ማዋል አስፈላጊ በመሆኑ:

የብሔራዊ ክልላዊ መንግስቱ የ1997 በጀት ዓመት በጀት አጠቃሎ ማጽደቅና ሥራ ላይ ማዋል አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ:

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ሪፑብሊክ ህገ መንግስት አንቀጽ 52 ንዑስ አንቀጽ 2/ሠ መሠረት ክልሉ የራሱን በጀት/ የማጽደቅና ሥራ ላይ የማዋል ሥልጣን የተሰጠዉ በመሆኑ ይህ አዋጅ ታዉጇል::

## ክፍል 1
## ጠቅላላ

### አንቀጽ 1

ይህ አዋጅ የ1997 በጀት ዓመት አዋጅ ቁጥር 45/1997 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል::

### አንቀጽ 2

ከሐምሌ 1/1996 ጀምሮ እስከ ሰኔ 30/1997 በሚፈጸመዉ በአንድ የበጀት ዓመት ጊዜ ዉስጥ በክልሉ የሚገኘዉ ገቢ እና ከሌላ ገንዘብ ላይ ከዚህ ጋር በተያያዘዉ ሠንጠረዥ ዉስጥ ለተጠቀሱት ሥራዎችና አገልግሎቶች ቀጥሎ እንደተመለከተዉ:-

ሀ. ለመደበኛ ወጪዎች ብር 57273700
ለ. ለካፒታል ወጪዎች ብር 39316400
ሐ. መጠባበቂያ በጀት ብር 5989900

ድምር ብር 102580000 /አንድ መቶ ሁለት ሚልየን አምስት መቶ ሰማኒያ ሺህ ብር/ ለክልሉ መንግስት ወጪ ሆኖ እንዲከፈል በዚህ አዋጅ ተፈቅዷል::

### አንቀጽ 3

ለፕሮፌሽናል፣ ለልዩ ልዩ አገልግሎቶች እንደዚሁም ለሥራ ማስኪጃ የተፈቀደዉ መደበኛ በጀት ወደ ደመወዝና አበል ማዛወር አይቻልም::



www.chilot.me

## አንቀጽ 4

ለካፒታል በጀት ከተፈቀደዉ ወደ መደበኛ በጀት ማዛወር አይቻልም።

## አንቀጽ 5

በየወሩ ሳይቋረጥ እየተከፈለ የሚያልቅ ሆኖ ለቋሚ የመንግስት ሠራተኞች አስፈላጊ ለሆኑ ጉዳዮች መመሪያ በማዉጣት የደመወዝ ቅድሚያ ክፍያ ለመስጠት የክፍያዉን ጊዜ ለመወሰንና በዚህ አኳኃን በሚሰጠዉ ብድር ላይ ባንክ በሚያስከፍለዉ ዉል መሠረት ለዓመቱ ወለድ እንዲያስከፍል ለክልሉ ፋይናንስ ቢሮ ሥልጣን ተሰጥቶታል።

# ክፍል ሁለት
# የበጀት አስተዳደር

## አንቀጽ 6

### የሐረሪ ህዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት አካላት ሥልጣን

1. ክልላዊ መንግስት አካላት የበላይ ኃላፊዎች ለየቢሮዎቻቸዉ ሥራና አገልግሎት በዚህ አዋጅ የተፈቀደላቸዉን በጀት በሚጠይቁበት ጊዜ የፋይናንስ ቢሮ ኃላፊ ከብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ገቢና ከሌላ ምንጭ እንዲከፍል ታዟል።
2. የበጀት ዝዉዉር ሥልጣን ለሚከተሉት አካላት ተሰጥቶአል።

### ሀ. የሐረሪ ህዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ

1- በጀት ተፈቅዶለት በመከናወን ላይ ካለ የካፒታል በጀት በበጀት አመቱ በጀት ላልተፈቀደለት አዲስ የካፒታል በጀት፡
2- መደበኛ በጀት ከተፈቀደለት አርዕስት /ንዑስ አርዕስት በበጀት አመቱ መደበኛ በጀት ላልተፈቀደለት አዲስ አርዕስት /ንዑስ አርዕስት /
3- ለመደበኛ በጀት ከተፈቀደዉ ወደ ካፒታል በጀት፡
4- ለመደበኛ በጀት ከተፈቀደዉ ደመዉዝና አበል ወደ ሥራ ማስኬጃ
5- ለመጠባበቂያ ከተያዘዉ በጀት ወደ ሌሎች ወጪዎች
6- ለክልሉ ለመደበኛም ሆነ ለካፒታል ወጪ ተፈቅዶ በሥራ ላይ ያልዋለዉን ተራፊ በጀት ወደ ሌሎች ወጪዎች

### ለ. ፋይናንስ ቢሮ

1- ከላይ በአንቀጽ 6ሀ ከ1-2 ከተጠቀሰዉ በስተቀር ጉዳዩ የሚመለከታቸዉ አካላት ሲጠይቁ በአንዱ መደበኛ በጀት አርዕስት ዉስጥ ከአንድ ንዑስ አርዕስት ዉስጥ ከአንድ ንዑስ አርዕስት ወደ ሌላዉ ንዑስ አርእስት በየሂሳብ መደቡ፡

1.1. ጉዳዩ የሚመለከተዉ የክልሉ መንግስት አካልና የፕላንና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ ሲስማሙበት በአንድ የክልሉ መንግስት አካል ሥር ለአንድ አርዕስት ንዑስ አርዕስት ፕሮጀክት በሂሳብ መደቡ፣
1.2 በሥራ አስፈጻሚ ሲፈቀድ በክልለ መደበኛ በጀት ዉስጥ ለመጠባበቂያ ከተያዘዉ ወደ ሌሎች ወጪዎች፣
1.3 በሥራ አስፈጻሚ ሲፈቀድ ለክልሉ ለመደበኛም ሆነ ለካፒታል ወጪ ተፈቅዶ በሥራ ላይ ያልዋለዉን ተራፊ በጀት ወደ ሌሎች ወጪዎች።

ነሐሴ 15/ቀን 1996 ዓ.ም
ክቡር አቶ ፉአድ ኢብራሂም
የሐረሪ ሀ/ብ/ክ/መንግስት
ፕሬዝዳንት



www.chilot.me

የሐረሪ ሕዝብ ክልላዊ መንግስት

# ሐረር ነጋሪ ጋዜጣ

# HARAR NEGARI GAZETA

OF THE HARARI PEOPLE REGIONAL STATE

| | |
|---|---|
| ፱ኛ ዓመት ቁጥር 1<br>9th year No 1 | ሐረር መስከረም 30 ቀን 1997 ዓ.ም<br>HARAR Oct, 10 Th, 2004 |

| | | |
|---|---|---|
| ያንዱ ዋጋ ብር<br>Unit Price Br 5.00 | በሐረሪ ሕዝብ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ | የፖስታ ሣጥን ቁጥር<br>P.O.Box 272 |



ማውጫ

አዋጅ ቁጥር 46/1997 ዓ.ም

የሐረሪ ሕዝብ ክልል ሕገ-መንግስትን ለማሻሻል የወጣ አዋጅ ---------------------------------- ገጽ 369


## የሐረሪ ሕዝብ ክልል ሀገ- መንግሥት ማሻሻያ አዋጅ

### 1. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ «የሐረሪ ሕዝብ ክልል የተሻሻለው ሕገ-መንግስት ማፅደቂያ አዋጅ» ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል::

### 2. ሀገ-መንግሥቱን ስለማሻሻል

ጳጉሜ 6 ቀን 1987 የፀደቀዉ የክልሉ ሕገ-መንግሥት ድንጋጌዎች ይዘትና አቀማመጥ ከታየ በኋላ የሐረሪ ሕዝብ ክልል የተሻሻለው ሕገ-መንግስት በዚህ አዋጅ ፀድቋል::

### 3. ስለ ነባር ሀጎች ተፈጻሚነት

በስራ ላይ ያሉ ሀጎች ከተሻሻለው ሀገ-መንግሥት ጋር እስካልተቃረኑ ድረስ ተፈጻሚነት ይኖራቸዋል::

### 4. ሕገ-መንግሥቱ በስራ ላይ ስለሚውልበት ጊዜ

የሐረሪ ሕዝብ ክልል የተሻሻለዉ ሀገ-መንግሥት ከመስከረም 30/1997 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል::

ሐረር መስከረም 30 ቀን 1997 ዓ.ም

ፋአድ ኢብራሂም

የሐረሪ ሕዝብ ክልል መንግስት ፕሬዝዳንት

## መግቢያ

እኛ የሐረሪ ህዝብ ክልል ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች የኢትዮጵያ ብሔሮች ብሔረሰቦችና ህዝቦች ሲደርስባቸው የነበረውን ኢኮኖሚያዊ ፖለቲካዊ ባህላዊ ኃይማኖታዊ ጭቆና ጫናና ተጽእኖ በተለያየ ስልት መልክና ቦታ ሲታገሉ ቆይተዉ በመጨረሻ በግንቦት ወር 1983 ለዚሁ ሁሉ ምክንያት የሆነውን ሥርዓት በማያዳግም ሁኔታ ለመጣል በመቻሉ በተለይ ጭቁን ብሔሮች ብሔረሰቦችና ህዝቦች ራሳቸውን በራሳቸው ለማስተዳደር ታሪካቸው ባህላቸውና ቋንቋቸውን ለማዳበር ዉስጣቸዉ ብሔራዊ ሀልውናቸዉን ለመጠበቅ የሚያስችላቸውን ምቹ ሁኔታ መፈጠሩንና ይህም ህዳር 29 ቀን 1987 በኢትዮጵያ ህዝቦች በጸደቀው የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሀገ መንግሥት መረጋገጡን በመገንዘብ፤

የሐረሪ ህዝብ ምንም እንኳ በምዕተ ዓመታት ለሚቆጠር ዘመን ራሱን በራሱ ያስተዳድር፤ በራሱ ታሪክ ወግና ባህል ይኮራ የነበረ ቢሆንም በ1886 ዓ.ም በተደረገበት ወረራ በነፍጠኛው ሥርዓት ሥር ከመውደቁም በላይ ይህንን ስርዓት ለማስወገድ በተለያዩ ጊዜያት ባደረገው ንቅናቄና ትግል ምክንያት ለግርፋት ለእስራትና ብሎም ለስደት በመዳረጉ በራሱ ክልል በቁጥር አናሳ መሆኑ የተነሳ ልዩ አወካከል ስልት ማስፈለጉን በመረዳት፤

የሐረሪ ሕዝብ ሲደርስበት የነበረዉን ግፍና ጭቆና ሲካፈሉ ከነበሩት ከአካባቢዉ የኦሮሞ ህዝብ እና ከሌሎች የክልሉ ነዋሪ ህዝቦች በመሆን የክልሉን አስተዳደር በጋራ ማቋቋምና መምራት ያለባቸው መሆኑን በማጤን፤

በክልላችን ውስጥ ዘላቂ ሰላምና ዋስትና ያለው ዲሞክራሲ እንዲሰፍን የግለሰብና የብሔር ብሔረሰብ መሠረታዊ መብቶች የተከበሩበትና ከታሪካችን የወረስነውን የተዛባ አመለካከትና ግንኙነት በማረምና


www.chilot.me

በማስተካከል መልካም አስተዳደርና የህግ የበላይነት የሰፈነበት ሥርዓት መገንባት አስፈላጊ በመሆኑ፣

በተለይም እኛ የሐረሪ፣ የኦሮሞና ሌሎች ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች የተፋጠነ የኢኮኖሚ ዕድገት ለማምጣት ፍትሐዊ የሥልጣን ክፍፍል እንዲኖር በተለይም ሦስቱን የመንግሥት አካላት የሥልጣን ክፍፍልና በመካከላቸው የሚኖረውን ግንኙነት በግልፅ ማስቀመጥና ተጠያቂነታቸውንም በግልጽ መደንገግ አስፈላጊ በመሆኑ፣

በዚሁ መሰረት እኛ የሐረሪ ክልል ምክር ቤት አባላት የመረጠንን ህዝብ በመወከል ከዚህ በፊት ተመክሮበት የጸደቀውንና በስራ ላይ ያለውን የክልሉን ህገ መንግሥት በጥልቀት ተመልክተን ከክልላችን ተወባጭ ሁኔታ ጋር በተገናዘበ መልኩ ተሻሽሎ የቀረበውን ህገ መንግሥት መክረንበትና ተወያይተንበት ዛሬ መስከረም 30 ቀን 1997 ዓ.ም በሙሉ ድምፅ አጽድቀነዋል።

## ምዕራፍ 1

## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

### አንቀጽ 1

### የክልሉ መንግሥት ስያሜ

የሐረሪ ሕዝብ ክልላዊ መንግሥት ተብሎ የሚጠራ ዲሞክራሲያዊ መዋቅር ያለው መንግሥት በዚህ ህገ-መንግሥት ተመስርቷል።

### አንቀጽ 2

### የሐረሪ ሕዝብ ክልል ግዛት ወሰን

የሐረሪ ሕዝብ ክልል በሰሜን በኮምቦልቻና በጃርሶ ወረዳዎች በምስራቅ በጉርሱምና በባቢሌ ወረዳዎች በደቡብ በፈዲስ ወረዳና በምእራብ በአለማያ ወረዳ የሚዋሰን ነው።

### አንቀጽ 3

### ሰንደቅ ዓላማና አርማ

1- የሐረሪ ህዝብ ክልል ሰንደቅ ዓላማና ዓርማ ይኖረዋል። ሰንደቅ አላማውም መደቡ ነጭ ሆኖ ከላይኛው ጠርዝ ገባ ብሎ ወደ አግድም የሚዘልቅ ቀይ መስመር ሲኖረው ከታችኛው ጠርዝ ከፍ ብሎ ወደ አግድም የሚዘልቅ አረንጓዴ መስመር ይኖረዋል።በቀዩና በአረንጎዴው መስመር መካከል ዓርማ ይኖረዋል።

2- የሰንደቅ ዓላማው ቀለማት የሚያስተላልፉት መልዕክት፣

ሀ. ነጩ መደብ የክልሉ ሕዝብ በፍትህና በእኩልነት ላይ ለተመሰረተ ሰላም ያለውን ስሜትና ፍላጎትያመለክታል፣

ለ. ቀዩ መስመር ሕዝቡ ለመብቱና ለነጻነቱ ያደረገውን ትግልና የከፈለውን መስዋዕትነት ያመለክታል፣

ሐ. አረንጓዴው መስመር ሕዝቡ ለልማትና ለዕድገት ቆርጦ መነሳቱንና የወደፊቱን ብሩህ ተስፋ ያመለክታል።

### አንቀጽ 4

### የክልሉ መዝሙር

የሐረሪ ክልል ሕዝብ የረጅም ዘመን የጀግንነትና የፍትሕ ታሪክ እንዲሁም የተገኘውን ድል የሚያሳይና ለተሻለ ኑሮ ያለውን ምኞት የሚያንጸባርቅ የራሱ መዝሙር ይኖረዋል። ዝርዝሩን በህግ ይወሰናል።

### አንቀጽ 5

### ርዕሰ ከተማ

የሐረሪ ሕዝብ ክልል ርዕሰ ከተማ ሐረር ነው።

### አንቀጽ 6

### የስራ ቋንቋ

የሐረሪ ሕዝብ ክልል የስራ ቋንቋ ሐረሪ እና ኦሮምኛ ናቸው።

### አንቀጽ 7

### የፆታ አገላለጽ

በዚህ ሕገ-መንግሥት ውስጥ በወንድፆታ የተደነገገው የሴትንም ፆታ ያካትታል።

## ምዕራፍ ሁለት

## የህገ-መንግሥቱ መሠረታዊ መርሆዎች

### አንቀጽ 8

### የህዝቡ የስልጣን ባለቤትነት

የሐረሪ ሕዝብ የክልሉ የበላይ ሥልጣን ባለቤት ሲሆን፣ የህዝቡ የበላይነትም የሚገለጸው በዚህ ህገ-መንግሥት መሰረት በሚመርጣቸዉ ተወካዮችና ራሱ በሚያደርገው ዴሞክራሲያዊ ተሳትፎ ነው።

### አንቀጽ 9

### የሕገ-መንግሥት የበላይነት

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገ-መንግሥት የበላይነት እንደተጠበቀ ሆኖ:-

1- ይህ ህገ-መንግሥት የክልሉ የበላይ ህግ ነው። ማንኛውም ሕግ ልማዳዊ አሠራር ወይም የመንግሥት አካል ወይም ባለስልጣን ውሳኔ ከዚህ ህገ መንግሥት ጋር የሚቃረን ከሆነ ተፈጻሚነት አይኖረውም።

2- ማንኛውም የክልሉ ነዋሪ የመንግሥት አካል የፖለቲካ ድርጅቶችና ሌሎች ማህበራት እንዲሁም ባለሥልጣኖቻቸው ይህን ህገ-መንግሥት የማክበርና ለሕገ መንግስቱ ተገዢ የመሆን ኃላፊነት አለባቸው።

3- በዚህ ህገ-መንግሥት ከተደነገገው ውጪ በማናቸዉም አኳኋን የመንግሥት ስልጣን መያዝ የተከለከለ ነው።

### አንቀጽ 10

### ሰብዓዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶች

1- ሰብዓዊ መብቶችና ነጻነቶች ከሰው ልጅ ተፈጥሮ የሚመነጩ የማይጣሱና የማይገፈፉ ናቸው።

2- በክልሉ ውስጥ የግለሰቦችና የሕዝቦች ሰብዓዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶች የተከበሩ ናቸው።

www.chilot.me

## አንቀጽ 11

## የመንግሥትና የሀይማኖት መለያየት

1- መንግሥትና ሃይማኖት የተለያዩ ናቸው::

2- መንግሥታዊ ሃይማኖት አይኖርም::

3- መንግሥት በሃይማኖት ጉዳይ ጣልቃ አይገባም:: ኃይማኖትም በመንግሥት ጉዳይ ጣልቃ አይገባም::

## አንቀጽ 12

## የመንግሥት አሠራርና ተጠያቂነት

1- የክልሉ መንግሥት አሠራር ለህዝቡ ግልጽ በሆነ መንገድ መከናወን አለበት::

2- ሕዝቡ በመረጠው ተወካይ ላይ እምነት ባጣ ጊዜ ከቦታው ሊያነሳው ይችላል ዝርዝሩ በህግ ይወሰናል::

3- ማንኛውም የሥራ ኃላፊ ወይም የህዝቡ ተመራጭ ኃላፊነቱን ሲያጓድል ተጠያቂ ይሆናል::

## ምዕራፍ ሦስት

## መሠረታዊ መብቶችና ነጻነቶች

## አንቀጽ 13

## ተፈጻሚነትና አተረጓጎም

1- በማንኛውም ደረጃ የሚገኙ የክልሉ መንግሥት የሕግ አውጪ, የሕግ አስፈጻሚና የዳኝነት አካሉች በዚህ ምዕራፍ የተካተቱ ድንጋጌዎች የማክበርና የማስከበር ኃላፊነትና ግዴታ አለባቸው::

2- በዚህ ምዕራፍ የተዘረዘሩት መሠረታዊ መብቶችና ነጻነቶች ኢትዮጵያ ከተቀበለቻቸዉ ዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብት ሕጋጋት፣ ከዓለም አቀፍ የሰብዓዊ ብቶች ስምምነቶችና ከሌሉች ዓለም አቀፍ ሰነዶች መርሆዎች ጋር በተመጣጣመ መንገድ ይተረጎማሉ::

## ክፍል አንድ

## ሰብዓዊ መብቶች

## አንቀጽ 14

## የሕይወት የአካል ደህንነትና የነጻነት መብት

ማንኛውም ሰው ሰብዓዊ በመሆኑ የማይደፈርና የማይገሰስ በሕይወት የመኖር፣ የአካል ደህንነት መብትና፣ ነጻነት አለው::

## አንቀጽ 15

## በሕይወት የመኖር መብት

ማንኛውም ሰው በሕይወት የመኖር መብት አለው:: ማንኛውም ሰው በሕግ በተደነገገ ከባድ የወንጀል ቅጣት ካልሆነ በስተቀር ሕይወቱን አያጣም::

## አንቀጽ 16

## የአካል ደህንነት መብት

ማንኛውም ሰው በአካሉ ላይ ጉዳት እንዳይደርስበት የመጠበቅ መብት አለው::

## አንቀጽ 17

## የነጻነት መብት

1- በሕግ ከተደነገገው ሥርዓት ውጭ ማንኛውም ሰው ነጻነቱን አያጣም::

2- ማንኛውም ሰው በሕግ ከተደነገገው ሥርዓት ውጭ ሊያዝ፣ ክስ ሳይቀርብበት ወይም ሳይፈረድበት ሊታሰር አይችልም::

## አንቀጽ 18

## ኢ-ሰብዓዊ አያያዝ ስለመከልከሉ

1- ማንኛውም ሰው ጭካኔ ከተሞላበት ኢ-ሰብአዊ ከሆነ ወይም ክብሩን ከሚያዋርድ አያያዝ ወይም ቅጣት የመጠበቅ መብት አለው::

2- ማንኛውም ሰው በባርነት ወይም በግዴታ አገልጋይነት ሊያዝ አይችልም:: በማንኛዉም ዓላማና ሁኔታ በሰው የመነገድ ተግባር የተከለከለ ነው::

3- ማንኛውም ሰው በኃይል ተገዶ ወይም ግዴታን ለማሟላት ማንኛውም ሥራ እንዲሰሩ ማድረግ የተከለከለ ነው::

4- በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 "በኃይል ተገዶ ወይም ግዴታን ማሟላት የሚለው" ሀረግ የሚከተሉትን ሁኔታዎች አያካትትም:-

ሀ. ማንኛውም እስረኛ በእስር ባለበት ጊዜ በሕግ መሠረት እንዲሰራ የተወሰነውን ወይም በገደብ ከእስር በተለቀቀበት ጊዜ የሚሰራውን ማንኛውም ሥራ፣

ለ. ማንኛውም ወታደራዊ አገልግሉት ለመስጠት ሕሊናው የማይፈቅድለት ሰው በምትኩ የሚሰጠው አገልግሉት፣

ሐ. የማህበረሰቡን ሕይወት ወይም ደህንነት የሚያሰጋ የአስቸኳይ ጊዜ ሁኔታ ወይም አደጋ የሚያጋጥምበት ጊዜ የሚሰጥ ማንኛውም አገልግሉት፣

መ. በሚመለከተው ሕዝብ ፈቃድ በአካባቢው የሚፈፀምን ማንኛውም የኢኮኖሚና የማህበራዊ ልማት ሥራ፣

## አንቀጽ 19

## የተያዘ ሰው መብት

1- ማንኛውም ሰው ወንጀል ፈፅሚል ተብሉ በሚያዝበት ጊዜ የቀረበበት ክስና የተያዘበት ምክንያት በሚገባዉ ቋንቋ እንዲነገረዉ መብት አለው::

2- የተያዘ ሰው የተከሰሰበትን ጉዳይ በተመልከተ ያለመናገር መብት ያለው መሆኑ፣ ለመናገር ከመረጠ ደግሞ የሚሰጠው ቃል በፍርድ ቤት በራሱ ላይ በማስረጃነት ሊቀርብበት እንደሚችል መረዳት በሚችለው ቋንቋ እንደተያዘ ወዲያውኑ ማስገንዘቢያ እንዲሰጠው መብት አለው::

3- ማንኛውም የተያዘ ሰው በተያዘ በአርባ ስምንት ሰዓት ውስጥ ፍርድ ቤት የመቅረብ መብት አለው:: ይህም ጊዜ ሰውየው ከተያዘበት ቦታ ወደ ፍርድ ቤት ለማምጣት አግባብ ባለው ግምት የሚጠይቀውን ጊዜ አይጨምርም:: ወዲያውኑ ፍርድ ቤት እንደቀረበ በተጠረጠረበት ወንጀል ለመታሰር የሚያበቃ ምክንያት ያለ መሆኑ ተለይቶ እንዲገለጽለት መብት አለው::

www.chilot.me

4- የያዘው አካል ወይም የሕግ አስከባሪ በጊዜ ገደቡ መሠረት ፍርድ ቤት በማቅረብ የተያዘበትን ምክንያት ካላስረዳ ፍርድ ቤቱ የአካል ነጻነቱን እንዲያስከብርለት የመጠየቅ ሊጣስ የማይችል መብት አለው:: ሆኖም ፍትህ እንዳይጓደል ሁኔታው የሚጠይቅ ከሆነ ፍርድ ቤቱ የተያዘው ሰዉ በጥበቃ ሥር እንዲቆይ ለማዘዝ ወይም ምርመራ ለማካሄድ ተጨማሪ ጊዜ ሲጠይቅ አስፈላጊ በሆነ መጠን ብቻ ሊፈቅድ ይችላል:: ፍርድ ቤቱ የሚያስፈልገውን ተጨማሪ የምርመራ ጊዜ የሚወስነው ኃላፊ የሆኑት ሕግ አስከባሪ ባለስልጣኖች ምርመራውን አጣርተው የተያዘው ሰው በተቻለ ፍጥነት ፍርድ ቤት እንዲቀርብ ያለውን መብት በሚያስከብር መልኩ መሆን አለበት::

5- ማንኛውም ሰው በራሱ ላይ በማስረጃነት ሊቀርብ የሚችል የእምነት ቃል እንዲሰጥ ወይም ማናቸውንም ማስረጃ እንዲያምኑ አይገደድም:: በማስገደድ የተገኘ ማስረጃ ተቀባይነት አይኖረውም::

6- የተያዘ ሰው በዋስ የመፈታት መብት አለው:: ሆኖም በሕግ በተደነገጉ ልዩ ሁኔታዎች መሰረት ፍርድ ቤቱ ዋስትና ባለመቀበል ወይም በገደብ መፈታትን ጨምር በቂ የሆነ የዋስትና ማረጋገጫ እንዲቀርብ ለማዘዝ ይችላል::

## አንቀጽ 20

## የተከሰሰ ሰው መብት

1- የተከሰሰ ሰው ክስ ከቀረበበት በኋላ ተገቢ በሆነ አጭር ጊዜ በመደበኛ ፍርድ ቤት ለሕዝቡ ግልጽ በሆነ ችሎት የመሰማት መብት አለው:: ሆኖም የተከራካሪዎችን የግል ሕይወት፣ የህዝቡን የሞራል ሁኔታ ወይም የአገሪቱን ወይም የክልሉን ደህንነት ለመጠበቅ ሲባል ብቻ ክርክር በዝግ ችሎት ሊሰማ ይችላል:

2- የተከሰሰ ሰው ክሱ በቂ በሆነ ዝርዝር እንዲነገረውና ክሱን በጽሁፍ የማግኘት መብት አለው::

3- ማንኛውም ተከሳሽ በፍርድ ሂደት ጊዜ በተከሰሰበት ወንጀል እንደጥፋተኛ ያለመቆጠር መብት አለው:: በምስክርነት እንዲቀርብም ያለመገደድ መብት አለው::

4- የተከሰሰ ሰው የቀረበበትን ማንኛውም ማስረጃ የመመልከት፣ የቀረቡበትን ምስክሮች የመጠየቅ፣ ለመከላከል የሚያስችለውን ማስረጃ የማቅረብ ወይም የማስቀረብ እንዲሁም ምስክሮቹ ቀርበዉ እንዲሰሙለት የመጠየቅ መብት አለዉ::

5- የተከሰሰ ሰዉ በመረጠዉ የሕግ ጠበቃ የመወከል ወይም ጠበቃ ለማቆም አቅም ከሌለዉና ፍትህ ሊጓደል የሚችልበት ሁኔታ ካጋጠመ ከመንግሥት ጠበቃ የማግኘት መብት አለዉ::

6- ክርክሩ በሚታይበት ፍርድ ቤት በተሰጠበት ትዕዛዝ ወይም ፍርድ ላይ ተከሳሽ ቅሬታ ካለዉ ሥልጣን ላለዉ ፍርድ ቤት ይግባኝ ለማቅረብ ይችላል::

7- ተከሳሽ የፍርዱ ሂደት በማይገባዉ ቋንቋ በሚካሄድበት ጊዜ በመንግሥት ወጪ ክርክሩ እንዲተረጎምለት የመጠየቅ መብት አለው::

## አንቀጽ 21

## በጥበቃ ሥር ያለና በፍርድ የታሰረ ሰው መብት

1- በጥበቃ ሥር ያለና በፍርድ የታሰረ ሰዉ ሰብዓዊ ክብሩን በሚጠብቁ ሁኔታዎች የመያዝ መብት አለው::

2- ማንኛውም የታሰረ ሰው ከትዳር ጓደኛው፣ ከቅርብ ዘመዶቹ፣ ከጓደኞቹ ከኃይማኖት አማካሪዎቹ፣ ከሐኪሞቹና ከሕግ አማካሪዎቹ ጋር ለመገናኘትና እንዲጎበኙት እድል የማግኘት መብት አለው::

## አንቀጽ 22

## የወንጀል ህግ ወደ ኋላ ተመልሶ የማይሰራ ስለመሆኑ

1- ማንኛውም ሰው የወንጀል ክስ ሲቀርብበት የተከሰሰበት ድርጊት በተፈጸመበት ጊዜ ድርጊቱን መፈጸሙ ወይም አለመፈጸሙ ወንጀል መሆኑ በሕግ የተደነገገ ካልሆነ በስተቀር ሊቀጣ አይችልም:: እንዲሁም ወንጀሉ በተፈጸመበት ጊዜ ለወንጀሉ ተፈጻሚ በነበረበው የቅጣት ጣሪያ በላይ የከበደ ቅጣት በማንኛውም ሰው ላይ አይወሰንም::

2- የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ ቢኖርም ድርጊቱ ከተፈጸመ በኃላ የወጣ ሕግ ለተከሳሹ ወይም ለተቀጣው ሰው ጠቃሚ ሆኖ ከተገኘ ከድርጊቱ በኋላ የወጣው ሕግ ተፈጻሚነት ይኖረዋል::

## አንቀጽ 23

## በአንድ ወንጀል ድጋሚ ቅጣት ስለመከልከሉ

ማንኛውም ሰው በወንጀለኛ መቅጫ ህግና ሥነ-ሥርዓት ወይም አግባብ ባላው ሌሎች ህጎች መሠረት ተከሶ የመጨረሻ በሆነ ውሳኔ ጥፋተኛነቱ በተረጋገጠበት ወይም በነጻ በተለቀቀበት ወንጀል እንደገና አይከሰስም ወይም አይቀጣም::

## አንቀጽ 24

## የክብርና የመልካም ስም መብት

1- ማንኛውም ሰው በማንኛውም ሥፍራ በሰብዓዊ ፍጡርነቱ እውቅና የማግኘት መብት አለው::

2- ማንኛውም ሰው ሰብዓዊ ክብሩና መልካም ስሙ የመከበር መብት አለው::

3- ማንኛውም ሰው የራሱን ስብእና ከሌሎች ዜጎች መብቶች ጋር በተጣጣመ ሁኔታ በነጻ የማሳደግ መብት አለው::

## አንቀጽ 25

## የእኩልነት መብት

ሁሉም ሰዎች በህግ ፊት እኩል ናቸው፣ በመካከላቸው ማንኛውም ዓይነት ልዩነት ሳይደረግ በሕግ እኩል ጥበቃ ይደረግላቸዋል:: በዚህ ረገድ በዘር፣ በብሔር፣ ብሔረሰብ፣ በቀለም፣ በጾታ፣ በቋንቋና በኃይማኖት፣ በፖለቲካ አመለካከት፣ በማህበራዊ አመጣጥ፣ በሀብት፣ በትውልድ ወይም በሌላ በማንኛውም አቋም ምክንያት ልዩነት ሳይደረግ ዜጎች ሁሉ እኩልና ተጨባጭ የሕግ ዋስትና የማግኘት መብት አላቸው::

www.chilot.me

## አንቀጽ 26

## የግል ሕይወት የመከበርና የመጠበቅ መብት

1- ማንኛውም ሰው የግል ሕይወቱና ገላዊነቱ የመከበር መብት አለው። ይህ መብት መኖሪያ ቤቱ፣ ሰዉነቱና ንብረቱ ከመበርበር እንዲሁም በግል ይዞታው ያለ ንብረት ከመያዝ የመጠበቅ መብትን ያካትታል።

2- ማንኛውም ሰው በግል የሚጽፋቸውና የሚጻጻፍባቸው፣ በፖስታ የሚልካቸው ደብዳቤዎች፣ እንዲሁም በቴሌፎን፣ በቴሌኮሙኒኬሽንና በኤሌክትሮኒክስ መሳሪያዎች የሚያደርጋቸው ግንኙነቶች አይደፈሩም።

3- የመንግሥት ባለስልጣኖች እነዚህን መብቶች የማክበርና የማስከበር ግዴታ አለባቸው። አስገዳጅ ሁኔታዎች ሲፈጠሩና ብሔራዊ ደህንነት፣ የሕዝቡን ሰላም ለመጠበቅ፣ ወንጀል ለመከላከል፣ ጤናንና የሕዝቡን የሞራል ሁኔታ ለመጠበቅ ወይም የሌሎችን መብትና ነፃነት ለማስከበር ዓላማዎች በወጡ ሕጎች መሠረት ካልሆነ በስተቀር የነዚህ መብቶች አጠቃቀም ሊገደብ አይችልም።

## አንቀጽ 27

## የኃይማኖት የሕሊናና የእምነት ነፃነት

1- ማንኛውም ሰው የማሰብ፣ የህሊናና የኃይማኖት ነፃነት አለው። ይህ መብት ማንኛውም ሰው የመረጠውን ኃይማኖት ወይም ዕምነት የመያዝ ወይም የመቀበል እና የኃይማኖቱን ወይም እምነቱን በግልም ሆነ ከሌሎች ጋር በይፋ ወይም በግል የማምለክ፣ የመከተል፣ የመተግበር፣ ወይም የመግለፅ፣ መብትን ያካትታል።

2- በፌዴራል ሕገ-መንግሥት አንቀፅ 90/2/ የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ የኃይማኖት ተከታዮች ኃይማኖታቸውን ለማስፋፋትና ለማደራጀት የሚያስችሏቸዉ የኃይማኖት ትምህርትና የአስተዳደር ተቋማት ማቋቋም ይችላሉ።

3- ማንኛውም ሰው የሚፈልገውን እምነት ለመያዝ ያለውን ነፃነት በኃይል ወይም በሌላው ሁኔታ በማስገደድ መገደብ ወይም መከልከል አይቻልም።

4- ወላጆችና ሌሎች ሕጋዊ ሞግዚቶች በእምነታቸው መሠረት የኃይማኖታቸውንና የመልካም ሥነ-ምግባር ትምህርት በመስጠት ልጆቻቸውን የማሳደግ መብት አላቸው።

5- ኃይማኖትንና እምነትን የመግለፅ መብት ሊገደብ የሚችለው የሕዝብን ደኅንነት፣ ሰላምን፣ ትምህርትን፣ የሕዝቡን የሞራል ሁኔታ፣ የሌሎች ዜጎችን መሠረታዊ መብቶች ነፃነቶችና መንግሥት ከኃይማኖት ነፃ መሆኑን ለማረጋገጥ በሚወጡ ሕጎች ይሆናል።

## አንቀጽ 28

## በሰብአና ላይ ስለሚፈፀሙ ወንጀሎች

ኢትዮጵያ ባፀደቀቻቸው ዓለም አቀፍ ስምምነቶችና በሌሎች የአገሪቱ ሕጎች በሰው ልጆች ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎች ተብለው የተወሰኑትን ወንጀሎች በተለይ የሰው ዘር የማጥፋት፣ ያለፍርድ የሞት ቅጣት እርምጃ የመዉሰድ በአስገዳጅ ሰውን የመሰወር ወይም ኢ-ሰብአዊ የድብደባ ድርጊቶችን በፈፀሙት ሰዎች ላይ ክስ ማቅረብ በይርጋ አይታገድም። በሕግ አውጭው ክፍልም ሆነ በማንኛውም የመንግስት አካል ውሳኔዎች በምህረት ወይም በይቅርታ አይታለፍም።

## ክፍል ሁለት

## ዴሞክራሲያዊ መብቶች

## አንቀጽ 29

## የአመለካከት ሐሳብን በነፃ የመያዝና የመግለፅ መብት

1- ማንኛውም ሰው ያለማንኛዉም ጣልቃ ገብነት የመሰለውን አመለካከት ለመያዝ ይችላል።

2- ማንኛውም ሰው ያለማንም ጣልቃ ገብነት ሐሳቡን የመግለፅ ነፃነት አለው። ይህ ነፃነት በሀገር ውስጥም ሆነ ከሀገር ውጭ ወሰን ሣይደረግበት በቃልም ሆነ በጽሁፍ ወይም በኅትመት በሥነ-ጥበብ መልክ ወይም በመረጠው በማንኛውም የማሠራጫ ዘዴ ማንኛውንም ዓይነት መረጃና ሀሣብ የመሰብሰብ የመቀበልና የማሰራጨት ነፃነቶችን ያካትታል።

3- የፕሬስንና የሌሎችን መገናኛ ብዙኃን እንዲሁም የሥነ-ጥበብ ፈጠራ ነፃነት ተረጋግጧል። የፕሬስ ነፃነት በተለይ የሚከተሉትን መብቶች ያጠቃልላል።

ሀ. የቅድሚያ ምርመራ በማንኛውም መልኩ የተከለከለ መሆኑን።

ለ. የሕዝብን ጥቅም የሚመለከት መረጃ የማግኘት እድልን።

4- ለዴሞክራሲያዊ ሥርዓት አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎች ሀሳቦችና አመለካከቶች በነፃ መንሸራሸራቸዉን ለማረጋገጥ ሲባል ፕሬስ በተቋምነቱ የአሠራር ነፃነትና የተለያዩ አስተያየቶች የማስተናገድ ችሎታ እንዲኖረው የሕግ ጥበቃ ይደረግለታል።

5- በመንግስት ገንዘብ የሚካሄድ ወይም በመንግሥት ቁጥጥር ሥር ያለ መገናኛ ብዙኃን የተለያዩ የአስተያየቶችን ለማስተናገድ የሚያስችል ሁኔታ እንዲመራ ይደረጋል።

6- እነዚህ መብቶች ገደብ ሊጣልባቸው የሚችለው የሀሳብና መረጃ የማግኘት ነፃነት በአስተሳሰባዊ ይዘቱና ሊያስከትል በሚችለዉ የአስተሳሰባዊ ውጤት ሊገታ አይገባውም በሚል መርህ ላይ ተመስርተው በሚወጡ ሕጎች ብቻ ይሆናል። የወጣቶችን ደኅንነት የሰዉን ክብርና መልካም ስም ለመጠበቅ ሲባል ሕጋዊ ገደቦች በነዚህ መብቶች ላይ ሊደነገጉ ይችላሉ። የጦርነት ቅስቀሳዎች እንዲሁም ሰብዓዊ ክብርን የሚነኩ የአደባባይ መግለጫዎች በሕግ የሚከለከሉ ይሆናል።

## አንቀጽ 30

## የመሰብሰብ፣ ሠላማዊ ሠልፍ የማድረግ ነፃነትና አቤቱታ የማቅረብ መብት

1. ማንኛውም ሰው ከሌሎች ጋር በመሆን መሣሪያ ሳይዝ በሰላም የመሰብሰብ፣ ሠላማዊ ሠልፍ የማድረግ ነፃነትና አቤቱታ የማቅረብ መብት አለው። ከቤት ውጭ የሚደረጉ ስብሰባዎችና ሠላማዊ ሰልፎች በሚንቀሳቀሱባቸው ቦታዎች በሕዝብ እንቅስቃሴ ላይ ችግር እንዳይፈጥሩ ለማድረግ ወይም በመካሔድ ላይ ያለ ስብሰባ ወይም ሠላማዊ ሰልፍ ሠላምን ዲሞክራሲያዊ

www.chilot.me

መብቶችንና የሕዝቡን የሞራል ሁኔታ እንዳይጥሱ ለማስጠበቅ አግባብ ያላቸው ስርዓቶች ሊደነገጉ ይችላሉ::

2. ይህ መብት የወጣቶችን ደህንነት፣ የሰዉን ክብርና መልካም ስምን ለመጠበቅ የጦርነት ቅስቀሳዎች እንዲሁም ሰብአዊ ክብርን የሚነኩ የአደባባይ መግለጫዎችን ለመከላከል ሲባል በሚወጡ ሕጎች መሠረት ተጠያቂ ከመሆን አያድንም::

## አንቀጽ 31

## የመደራጀት መብት

ማንኛውም ሰው ለማንኛውም ዓላማ በማኅበር የመደራጀት መብት አለው:: ሆኖም አግባብ ያለውን ሕግ በመጣስ ወይም ሕገ-መንግሥታዊ ሥርዓቱን በሕገ ወጥ መንገድ ለማፍረስ የተመሠረቱ ወይም የተጠቀሱትን ተግባራት የሚያራምዱ ድርጅቶች የተከለከሉ ይሆናሉ::

## አንቀጽ 32

## የመዘዋወር ነፃነት

በፌደራል ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 32 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም የክልሉ ነዋሪ ወይም በሕጋዊ መንገድ በክልሉ ዉስጥ የሚገኝ ሰዉ በፈለገው የክልሉ አካባቢ የመዘዋወር፣ የመኖር፣ ሐብት የማፍራትና የመያዝ እንዲሁም በፈለገዉ ጊዜ ከክልሉ የመዉጣት ነፃነት አለው::

## አንቀጽ 33

## በመንግሥታዊና ህዝባዊ ሥራዎች የመሳተፍ መብት

በክልሉ ውስጥ ነዋሪ የሆነና የክልሉን የሥራ ቋንቋ የሚያውቅ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ በፌዴራሉና በዚህ ህገ መንግስት መሰረት በማንኛውም የክልሉ መንግሥታዊ ወይም ህዝባዊ ሥራ ተቀጥሮ ወይም ተመርጦ የመስራት መብት አለው::

## አንቀጽ 34

## የጋብቻ የግልና የቤተሰብ መብቶች

1. በሕግ ከተወሰነ የጋብቻ ዕድሜ የደረሱ ወንዶችና ሴቶች በዘር፣ በብሔር፣ በብሔረሰብ ወይም በኃይማኖት ልዩነት ሳይደረግባቸዉ የማግባትና ቤተሰብ የመመስረት መብት አላቸው:: በጋብቻ አፈፃፀም በጋብቻው ዘመንና በፍቺ ጊዜ እኩል መብት አላቸው:: በፍቺም ጊዜ የልጆች መብትና ጥቅም እንዲከበር የሚያደርጉ ድንጋጌዎች ይደነገጋሉ::
2. ጋብቻ በተጋቢዎች ነፃና ሙሉ ፈቃድ ላይ ብቻ ይመሠረታል::
3. ቤተሰብ ከኅብረተሰብና ከመንግሥት ጥበቃ የማግኘት መብት አለው::
4. በሕግ በተለይ በሚዘረዘረዉ መሠረት በኃይማኖት በባህል ሥርዓቶች ላይ ተመሥርተው ለሚፈፀሙ ጋብቻዎች እውቅና የሚሰጥ ሕግ ሊወጣ ይችላል::
5. ይህ ሕገ-መንግሥት የግልና የቤተሰብ ሕግን በተመለከተ በተከራካሪዎች ፍቃድ በኃይማኖቶች ወይም በባህሎች ሕጎች መሠረት መዳኘትን አይከለክልም:: ዝርዝሩ በሕግ ይወሰናል::

## አንቀጽ 35

## የሴቶች መብት

1. ሴቶች ይህ ሕገ-መንግሥት በአረጋገጣቸው መብቶችና ጥበቃዎች በመጠቀም ረገድ ከወንዶች እኩል መብት አላቸው::
2. ሴቶች በዚህ ሕገ-መንግሥት በተደነገገው መሠረት ከወንዶች ጋር እኩል መብት አላቸው::
3. ሴቶች በበታችነትና በልዩነት በመታየታቸው የደረሰባቸውን የታሪክ ቅርስ ከግምት ውስጥ በማስገባት ይህ ቅርስ እንዲታረምላቸዉ በተጠማሪ የድጋፍ እርምጃዎች ተጠቃሚ የመሆን መብት አላቸው:: በዚህ በኩል የሚወሰዱት እርምጃዎች ዓላማ በፖለቲካዊ፣ በማኅበራዊና በኢኮኖሚያዊ መስኮች እንዲሁም በመንግሥት እና በግል ተቋሞች ውስጥ ሴቶች ከወንዶች ጋር በእኩልነት ተወዳዳሪ ተሳታፊ እንዲሆኑ ለማድረግ እንዲቻል ልዩ ትኩረት ለመስጠት ነው::
4. ሴቶች ከጎጂ ባህል ተፅዕና የመላቀቅ መብታቸው መንግሥት ማስከበር አለበት:: ሴቶችን የሚጨቁኑ ወይም በአካላቸው ወይም በአእምሮአቸው ላይ ጉዳት የሚያስከትሉ ሕጎች ወጎችና ልማዶች የተከለከሉ ናቸው::
5. በመንግስት መስሪያ ቤቶች ወይም በግል ድርጅቶች ተቀጥረው የሚሰሩ ሴቶች:-
   ሀ/ የወሊድ ፍቃድ ከሙሉ የደመወዝ ክፍያ ጋር የማግኘት መብት አላቸው፣ የወሊድ ፈቃድ ርዝመት ሴቷ የምትሰራውን ሥራ ሁኔታ፣ የሴቷን ጤንነት የሕፃኑንና የቤተሰቡን ደህንነት ከግምት ውስጥ በማስገባት በሕግ ይወሰናል::
   ለ/ የወሊድ ፍቃድ በሕግ በሚወሰነው መሠረት፤ ከሙሉ የደሞዝ ክፍያ ጋር የሚሰጥ የእርግዝና ፈቃድን ሊጨምር ይችላል::
6. ሴቶች በክልሉ የልማት ፖሊሲዎች አቅድና በፕሮጀክት ዝግጅትና አፈፃፀም በተለይ የሴቶችን ጥቅም በሚነኩ ፕሮጀክቶች ሀሳባቸውን በተሟላ ሁኔታ እንዲሰጡ የመጠየቅ መብት አላቸው::
7. ሴቶች ንብረት የማፍራት፣ የማስተዳደር፣ የመቆጣጠር፣ የመጠቀምና የማስተላለፍ መብት አላቸው:: በተለይ መሬትን በመጠቀም፣ በማስተላለፍ፣ ማስተዳደርና በመቆጣጠር ረገድ ከወንዶች ጋር እኩል መብት አላቸው:: እንዲሁም ውርሱን በሚመለከት በእኩልነት የመታየት መብት አላቸው::
8. ሴቶች የቅጥር፣ የሥራ ዕድገት፣ የእኩል ክፍያና ጡረታን የማስተላለፍ እኩል መብት አላቸው::
9. ሴቶች በእርግዝናና በወሊድ ምክንያት የሚደርስባቸውን ጉዳት ለመከላከልና ጤንነታቸውን ለማስጠበቅ የሚያስችል የቤተሰብ ምጣኔ ትምህርት፣ መረጃ እና አቅም የማግኘት መብት አላቸው::

## አንቀጽ 36

## የሕፃናት መብት

1. ማንኛውም ሕፃን የሚከተሉት መብቶች አሉት
   - ሀ/ በሕይወት የመኖር፤
   - ለ/ ስምና ዜግነት የማግኘት፤
   - ሐ/ወላጆቹን ወይም በሕግ የማሳደግ መብት ያላቸውን ሰዎች የማወቅና የእነሱንም እንክብካቤ የማግኘት፤
   - መ/ጉልበቱን ከሚበዘብዙ ልማዶች የመጠበቅ፣ በትምህርት በጤናውና በደህንነቱ ላይ ጉዳት የሚያደርሱ ሥራዎች እንዲሠሩ ያለመገደድ ወይም ከመሥራት የመጠበቅ፤
   - ሠ/በትምህርት ቤቶች ወይም በሕፃናት ማሳደጊያ ተቋሞች ውስጥ በአካሉ ላይ ከሚፈፀም ወይም ከጭካኔና ኢ-ሰብአዊ ከሆነ ቅጣት ነፃ የመሆን።
2. ሕፃናትን የሚመለከቱ እርምጃዎች በሚወሰዱበት ጊዜ በመንግሥታዊ ወይም በግል የበጎ አድራጎት ተቋማት፣ በፍርድ ቤቶች በአስተዳደር ባለስልጣናት ወይም በሕግ አውጭ አካላት የሕፃናት ደህንነት በቀደምትነት መታሰብ አለበት።
3. ወጣት አጥፊዎች በማረሚያ ወይም በመቋቋሚያ ተቋሞች የሚገኙ በመንግስት እርዳታ የሚያድጉ ወጣቶች ከአዋቂዎች ተለይተው መያዝ አለባቸው።
4. ከጋብቻ ውጭ የተወለዱ ሕፃናት በጋብቻ ውስጥ ከተወለዱ ህጻናት ጋር እኩል መብት አላቸው።
5. መንግሥት <u>ለአሳዳጊ ለሌላቸው</u> ልዩ ጥበቃ ያደርግላቸዋል። በጉዲፈቻ የሚያድጉበትን ሥርዓት የሚያመቻቹና የሚያስፋፉ እንዲሁም ደህንነታቸውንና ትምህርታቸውን የሚያራምዱ ተቋሞች እንዲመሠረቱ ያበረታታል።

## አንቀጽ 37

## ፍትህ የማግኘት መብት

1. ማንኛውም ሰው በፍርድ ሊወሰን የሚገባውን ጉዳይ ለፍርድ ቤት ወይም ለሌላ በሕግ የዳኝነት ሥልጣን ለተሰጠዉ አካል የማቅረብና ውሣኔ ወይም ፍርድ የማግኘት መብት አለው።
2. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀጽ 1 የተመለከተውን ውሳኔ ወይም ፍርድ፤
   - ሀ/ ማንኛውም ማኅበር የአባላቱን የጋራ ወይም የግል ጥቅም በመወከል፤
   - ለ/ ማንኛውንም ቡድን ወይም ተመሳሳይ ጥቅም ያላቸውን ሰዎች የሚወክል ግለሰብ ወይም የቡድን አባል የመጠየቅና የማግኘት መብት አለው።

## አንቀጽ 38

## የመምረጥና የመመረጥ መብት

1. ማናቸውም የክልሉ ሕዝብ በቀለም፣ በዘር፣ በብሔር፣ በብሔረሰብ፣ በፆታ፣ በቋንቋ በኃይማኖት፣ በፖለቲካ ወይም በሌላ አመለካከት ወይም እጿም ላይ የተመሰረተ ልዩነት ሳይደረግበት የሚከተሉት መብቶች አሉት።
   - ሀ/ በቀጥታ እና በነፃነት በመረጣቸው ተወካዮች አማካኝነት በሕዝብ ጉዳይ አስተዳደር የመሳተፍ፤
   - ለ/ ዕድሜ ው 18 ዓመት ሲሞላ በሕግ መሠረት የመምረጥ፤
   - ሐ/ በዚሕ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 33 የተገለፀው እንደተጠበቀ ሆኖ ዕድሜያቸው ከ21 ዓመት ሲሞላው መመረጥ፤
   - መ/ ምርጫው ሁሉ አቀፍ፤ በእኩልነት ላይ የተመሠረተና በሚስጥር ድምፅ አሰጣጥ መራጩ ፈቃዱን በነፃነት የሚገልፅበት ዋስትና የሚሰጥ ሆኖ በሐገራችን ሕገ-መንግሥትና በምርጫ ሕግ መሠረት መሆን አለበት።
2. ማንኛውም ሰው በፖለቲካ ድርጅቶች፣ በሠራተኞች፣ በንግድ፣ በአሠሪዎችና በሙያ ማኅበራት ለተሳትፎ ድርጅቱ የሚጠይቀውን ጠቅላላና ልዩ የአባልነት መስፈርት የሚያሟላ ከሆነ በፍላጎቱ አባል የመሆን መብቱ የተከበረ መሆን አለበት።
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 በተመለከቱት ድርጅቶችውስጥ ለኃላፊነት ቦታዎች የሚካሄዱ ምርጫዎች ነፃና ዴሞክራሲያዊ በሆነ መንገድ ይፈፀማሉ።
4. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 እና 3 ድንጋጌዎች የሕዝብን ጥቅም በሰፊ ባለ ሁኔታ የሚነኩ እስከሆነ ድረስ በሕዝባዊ ድርጅቶች ላይ ተፈፃሚ ይሆናል።

## አንቀጽ 39

## የሐረሪ ህዝብ ብሔራዊ መብቶች

የሐረሪ ሕዝብ በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግሥት የራሱን ዕድል በራሱ የመወሰን እስከ መገንጠል ድረስ ያለዉ መብት በማናቸውም መልኩ ያለገደብ የተጠበቀ ነው። በዚሁ መሠረት የሐረሪ ሕዝብ፤

1. የራሱን ብሔራዊ ማንነት የመጠበቅና የማስከበር፣ ቅርሱንና ታሪኩን የመንከባከብ የማበልፀግ እንዲሁም በቋንቋው የመጠቀም፣ ቋንቋውን የማሳደግና ባህሉን የመግለጽ መብት አለው።
2. በራሱ መልክአ ምድራዊ ክልል ውስጥ የራሱን ጉዳይ በራሱ የማከናወን ራሱን የመስተዳደር እንዲሁም በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ መንግሥት ውስጥ በነፃነትና አድልዎ በሌለበት ተገቢ፣ ፍትሃዊ በሆነ አግባብ ዉጤታማ ተግቶር ለማድረግ መብት አለው፤
3. ራሱን በራሱ የማስተዳደር መብት፣ በራሱ መልክአ ምድር ራሱን የሚያስተዳድርበት መንግሥታዊ ተቋማት የማቋቋምና በፌዴራል አስተዳደሮች ውስጥ ሚዛናዊ ውክልና የማግኘት መብት አለው።
4. በዚህ አንቀጽ በተራ ቁጥር /1/ /2/ እና /3/ የተጠቀሱት መብቶች ታግዱ፣ ተረገጡ፣ ወይም ተሸራረፉ ብሎ ባመነበትና እነኚህም መብቶች በኢፌዴሪ መንግስት አንድነት ጥላ ሥር ሆኖ ሊያስተካክላቸው ባልቻለበት ጊዜ እስከ መገንጠል ድረስ የራሱን እድል በራሱ የመወሰን መብቱን ተግባራዊ ያደርጋል፤
5. የራሱን እድል በራሱ የመወሰን እስከ መገንጠል ያለው መብት በሥራ ላይ የሚውለው፤
   - ሀ/ የመገንጠሉ ጥያቄ በሐረሪ ብሔራዊ ጉባኤ በሁለት ሶስተኛ ድምፅ ተቀባይነት ማግኘቱ ሲረጋገጥ፤

www.chilot.me

ለ/ የጉባኤው የመገንጠል ውሳኔ በደረሰው በሶስት ዓመት ጊዜ ውስጥ የፌዴራሉ መንግሥት ሕዝብ ውሳኔ ሲያደራጅ፣

ሐ/የመገንጠሉ ተያቄ በሕዝበ ውሳኔ በአብላጭ ድምጽ ሲደገፍ፣

መ/ የፌደራሉ መንግሥት መገንጠሉን ለጠየቀው ለሐረሪ ሕዝብ ስልጣኑን ሲያስረክብና፣

ሠ/ በሕግ በሚወሰነው መሠረት የንብረት ክፍፍል ሲደረግ ነው።

6. በዚህ ህገ መንግሥት ውስጥ «የሐረሪ ህዝብ» ማለት ሰፋ ያለ የጋራ ጠባይ የሚያንጸባርቅ ባህል ወይም ተመሳሳይ ልምዶች ያላቸው ሊግባቡበት የሚችሉበት የጋራ ቋንቋ ያላቸው የጋራ ወይም የተዛመደ ህልውና አለን ብለው የሚያምኑና የስነ ልቦና አንድነት ያላቸው በተያያዘ መልክአ ምድር የሚኖር ህብረተሰብ ማለት ነው።

## አንቀጽ 40

## የንብረት መብት

1. ማንኛውም ሰው የግል ንብረት ባለቤት መሆኑ/መሆኗ ይከበርለታል/ይከበርላታል። ይህ መብት የሕዝብን ጥቅም ለመጠበቅ በሌላ ሁኔታ በሕግ እስካልተወሰነ ድረስ ንብረት የመያዝና በንብረት የመጠቀም ወይም የሌሎችን ዜጎች መብቶች እስካልተቃረነ ድረስ ንብረትን የመሸጥ/የማውረስ ወይም በሌላ መንገድ የማስተላለፍ መብቶችን ያካትታል።

2. ለዚህ አንቀጽ አላማ «የግል ንብረት» ማለት ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ዜጋ ወይም ሕጋዊ ሰዉነት በሕግ የተሰጣቸዉ ማኅበራት ወይም አግባብ በአላቸው ሁኔታዎች በሕግ በተለየ በጋራ የንብረት ባለቤት እንዲሆኑ የተፈቀደላቸው ማኅበረሰቦች በጉልበታቸው፣ ፈጠራ ችሎታቸው ወይም በካፒታላቸው ያፈሩት ተጨባጭ የሆነና ተጨባጭነት ጠባይ ሳይኖረው ዋጋ ያለው ዉጤት ነው።

3. የገጠርም ሆነ የከተማ መሬትና የተፈጥሮ ሀብት ባለቤትነት መብት የመንግሥትና የሕዝብ ብቻ ነው። መሬት የማይሸጥ የማይለወጥ የሕዝቦች የጋራ ንብረት ነው።

4. የክልሉ አርሶ አደሮች መሬት በነጻ የማግኘትና ከመሬታቸው ያለመነቀል መብታቸዉ የተከበረ ነው። አፈጻጸሙን በተመለከተ ዝርዝር ሕግ ይወጣል።

5. የመሬት ባለቤትነት የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ መንግሥት ለግል ባለሀብቶች በሕግ በሚወሰን ክፍያ በመሬት የመጠቀም መብታቸውን ያስከብርላቸዋል። ዝርዝሩ በሕግ ይወሰናል።

6. ማንም ኢትዮጵያዊ በጉልበቱ፣ ወይም በገንዘቡ በመሬት ላይ ለሚገነባው ቋሚ ንብረት ወይም ለሚያደርገው ቋሚ መሻሻል ሙሉ መብት አለው። ይህ መብት የመሸጥ፣ የመለወጥ፣ የማውረስ፣ የመሬት ተጠቃሚነቱ ሲቋረጥ ንብረቱን የማንሳት፣ ባለቤትነቱን የማዛወር ወይም የካሳ ክፍያ የመጠየቅ መብትን ያካትታል። ዝርዝር አፈጻጸሙ በሕግ ይወሰናል።

7. የግል ንብረት ባለቤትነት መብት እንደተጠበቀ ሆኖ መንግሥት ለሕዝብ ጥቅም አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ተመጣጣኝ ካሳ በቅድሚያ በመክፈል የግል ንብረትን ለመውሰድ ይችላል።

## አንቀጽ 41

## የኢኮኖሚ የማህበራዊና የባህል መብቶች

1. ማንኛውም የክልሉ ነዋሪ ወይም በክልሉ ውስጥ ለመኖር የሚፈልግ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ በማንኛውም የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ የመሰማራት ለመተዳደሪያዉ የመረጠዉን ሥራ የመስራት መብት አለው።

2. ማንኛውም የክልሉ ነዋሪ መተዳደሪያውን፣ ሥራውንና ሙያውን የመምረጥ መብት አለው።

3. የክልሉ ነዋሪዎች ሁሉ በመንግሥት ገንዘብ በሚካሄዱ ማህበራዊ አገልግሎቶች በእኩልነት የመጠቀም መብት አላቸው።

4. የክልሉ መንግሥት የጤና፣ የትምህርትና ሌሎች ማህበራዊ አገልግሎቶችን ለሕዝቡ ለማቅረብ በየጊዜው እየጨመረ የሚሄድ ሀብት ይመድባል።

5. የክልሉ መንግሥት አካልና የአእምሮ ጉዳተኞችን፣ አረጋውያንና ያለወላጅ ወይም ያለአሳዳጊ የቀሩ ሕጻናትን ለማቋቋምና ለመርዳት የክልሉ ኢኮኖሚ አቅም በፈቀደዉ ደረጃ እንክብካቤ ያደርጋል።

6. የክልሉ መንግሥት ለስራ አጦችና ለችግረኞች ሥራ ለመፍጠር የሚያስችል ፖሊሲ ይከታተላል፣ እንዲሁም በሚካሄደው የሥራ ዘርፍ ውስጥ የስራ ዕድል ለመፍጠር የሥራ ፕሮግራሞችን ያወጣል፣ ፕሮጀክቶችን ያካሂዳል።

7. የክልሉ መንግሥት የክልሉ ነዋሪዎች ጠቃሚ ሥራ የማግኘት እድላቸው እየሰፋ እንዲሄድ ለማድረግ አስፈላጊ እርምጃዎችን ይወስዳል።

8. መንግሥት የባህልና የታሪክ ቅርሶችን የመንከባከብና ለሥነ ጥበብና ለስፖርት መስፋፋት አስተዋጽኦ የማድረግ ኃላፊነት አለበት።

## አንቀጽ 42

## የሠራተኞች መብት

1- ሀ/ የፋብሪካ፣ የጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማትና የአገልግሎት ሠራተኞች፣ ገበሬዎች፣ የእርሻ ሠራተኞች፣ ሌሎች የገጠር ሠራተኞች ከተወሰነ የኃላፊነት ደረጃ በታች ያሉና የሥራ ጠባያቸው የሚፈቅድላቸው የመንግሥት ሠራተኞች የሥራና የኢኮኖሚ ሁኔታዎችን ለማሻሻል በማህበር የመደራጀት መብት አላቸው። ይህ መብት የሠራተኛ ማህበራትንና ሌሎች ማህበራትን የማደራጀት፣ ከአሠሪዎችና ጥቅማቸውን ከሚነኩ ሌሎች ድርጅቶች ጋር የመደራደር መብትን ያካትታል።

ለ/ በንዑስ አንቀጽ /ሀ/ የተመለከቱት የሠራተኛ ክፍሎች ሥራ ማቆምን ወምር ቅሬታቸዉን የማሰማት መብት አላቸው።

ሐ/ በንዑስ አንቀጽ /ሀ/ እና /ለ/ መሠረት እውቅና ባገኙ መብቶች ለመጠቀም የሚችሉት የመንግሥት ሠራተኞች በሕግ ይወሰናሉ።

መ/ ሴቶች ሠራተኞች ለተመሳሳይ ሥራ ተመሳሳይ ክፍያ የማግኘት መብታቸው የተጠበቀ ነው።

www.chilot.me

2. ሠራተኞች በአግባቡ የተወሰነ የሥራ ሰዓት እረፍት፣ የመዝናኛ ጊዜ፣ በየጊዜው ከክፍያ ጋር የሚሰጡ የእረፍት ቀናችን፣ ደመወዝ የሚከፈልባቸው የሕዝብ በዓላት እንዲሁም ጤናማና አደጋ የማያደርስ የሥራ አካባቢ የማግኘት መብት አላቸው::

3. እነዚህ መብቶች ተግባራዊ ለማድረግ የሚወጡ ሕጎች በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት እውቅና ያገኙትን መብቶች ሳይቀንሱ የተጠቀሱት ዓይነት ሠራተኛ ማህበራት ስለሚቋቋምበትና የጋራ ድርድር ስለሚካሄድበት ሥርዓት ይደነግጋሉ::

## አንቀጽ 43

## የልማት መብት

1. የክልሉ ነዋሪዎች የኑሮ ሁኔታቸውን የማሻሻልና የማያቋርጥ እድገት የማግኘት መብታቸው የተጠበቀ ነው::

2. ዜጎች በብሔራዊ ልማት የመሳተፍ በተለይም አባል የሆኑበትንም ማህበረሰብ የሚመለከቱ ፖሊሲዎችና ፕሮጀክቶች ላይ ሀሳባቸውን እንዲሰጡ የመጠየቅ መብት አላቸው::

3. የልማት እንቅስቃሴ ዋና ዓላማ የክልሉን ነዋሪዎች እድገትና መሠረታዊ ፍላጎት ማሟላት ይሆናል::

## አንቀጽ 44

## የአካባቢ ደህንነት መብት

1. የክልሉ ነዋሪዎች ንጹህና ጤናማ በሆነ አካባቢ የመኖር መብት አላቸው::

2. የክልሉ መንግሥት በሚያካሄዳቸው ፕሮግራሞች ምክንያት የተፈናቀሉ ወይም ኑሮአቸዉ የተነካባቸው ሰዎች ሁሉ በመንግሥት በቂ እርዳታ ወደ ሌላ አካባቢ መዛዋወርን ጨምሮ ተመጣጣኝ የሆነ የገንዘብ ወይም ሌላ አማራጭ ማካካሻ የማግኘት መብት አላቸው::

## ምዕራፍ አራት

## የክልሉ መንግሥት አደረጃጀትና የሥልጣን ክፍፍል

## አንቀጽ 45

## የክልሉ አስተዳደር እርከኖች

1- የሐረሪ ሕዝብ ክልል መንግስት በክልል እና በቀበሌ የተዋቀረ ነው:: ይሁን እንጂ የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ሌሎች የአስተዳደር መዋቅሮች ሊያዋቅርና ሥልጣንና ተግባራቸውን ሊወስን ይችላል::

2- ሐረር ከተማ የራሱ አስተዳደር ይኖረዋል:: ዝርዝሩ በሕግ ይወሰናል::

## አንቀጽ 46

## የክልሉ መንግሥት የሥልጣን አካላት

1. የክልሉ ከፍተኛ የሕግ አውጪ አካል የሐረሪ ክልል ምክር ቤት ሲሆን ተጠሪነቱም ለወከለው ሕዝብ ነው::

2. የክልሉ ከፍተኛ የሕግ አስፈጻሚ አካል የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ሲሆን ተጠሪነቱም ለክልሉ ምክር ቤት ነው::

3. የክልሉ የዳኝነት ሥልጣን የክልሉ ፍርድ ቤቶች ብቻ ነው::

## አንቀጽ 47

## የክልሉ መንግሥት ሥልጣንና ተግባር

1. በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግሥት ውስጥ በግልጽ ተለይተው ለፌደራሉ መንግሥት ወይም ለፌደራሉ መንግሥትና ለክልሉ መንግሥት በጋራ ከተሰጡት ሥልጣንና ተግባራት ውጪ ያሉ ማናቸውም ሥልጣንና ተግባር የክልሉ መንግሥት ይሆናል::

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የሰፈረው አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ የሐረሪ ህዝብ ክልላዊ መንግሥት:-

   2.1. የክልሉን የኢኮኖሚና ማህበራዊ ልማት ፖሊሲ ስትራቴጂና ዕቅድ ያወጣል፣ ያስፈጽማል::

   2.2. የክልሉን ህገ መንግሥትና ሌሎች ህጎችን ያወጣል፣ ያስፈጽማል::

   2.3. የፌደራል መንግሥት በሚያወጣው ህግ መሰረት መሬትንና የተፈጥሮ ሀብትን ያስተዳድራል::

   2.4. ራስን በራስ ማስተዳደርን ዓላማ ያደረገ ክልላዊ መስተዳድር ያዋቅራል:: የህግ የበላይነት የሰፈነበት ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ይገነባል የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገ መንግሥትና ይህንን ህገ መንግሥት ይጠብቃል፣ ይከላከላል::

   2.5. የክልሉን መስተዳድር ሠራተኞች አስተዳደርና የሥራ ሁኔታዎች በተመለከተ ህግ ያወጣል፣ ያስፈጽማል፣ ይህን በሚያስፈጽምበት ጊዜ የህገሪቱን የትምህርት፣ የሥልጠናና የልምድ መመዘኛዎች ግምት ዉስጥ ማስገባት ይኖርበታል::

   2.6. ክልሉን ፖሊሲ ሀይል ያደራጃል፣ ይመራል፣ የክልሉን ሠላምና ፀጥታ ይጠብቃል::

   2.7. የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገ መንግሥት አንቀጽ 28 ድንጋጌ እንደተጠበቁ ሆነው በህግ መሰረት ምህረት ወይም ይቅርታ ያደርጋል::

   2.8. ለክልሉ በተወሰነው የገቢ ምንጭ ግብርና ሌሎች ታክሶችን ይጥላል::

   2.9. በክልሉ መስተዳድርና በድርጅት ተቀጣሪዎች ላይ የሥራ ግብር ይጥላል::

   2.10. የመሬት መጠቀሚያ ክፍያ ይወስናል፣ ይሰበስባል::

   2.11. የእርሻ ሥራ ገቢ ግብር ይጥላል፣ ይሰበስባል::

   2.12. በክልሉ በግል ባለቤትነት ስር ካሉ ቤቶችና ሌሎች ንብረቶች በሚገኝ ገቢ ላይ ግብር ይጥላል፣ ይሰበስባል፣ በክልል መስተዳድሩ ባለቤትነት ሥር ባሉ ቤቶችና ሌሎች ንብረቶች ላይ ኪራይ ያስከፍላል::

www.chilot.me

2.13. በክልል መስተዳድር ባለቤትነት ከሚገኙ ድርጅቶች ላይ የንግድ ትርፍ የስራ ግብርና የሽያጭና ኤክሳይዝ ታክስ ይሰበስባል::

2.14. ከፌደራሉ መንግሥት ጋር

ሀ/ በጋራ ከሚያቋቁሟቸው የልማት ድርጅቶች የሚገኘውን የንግድ ትርፍ ግብር፣ ሥራ ግብር፣ የሽያጭና የኤክሳይዝ ታክስ በህጉ መሰረት ይካፈላል::

ለ/ ከድርጅቶች የንግድ ትርፍና ከባለ አክስዮኖች የትርፍ ድርሻ ላይ ግብርና የሽያጭ ታክስ በህጉ መሰረት ይካፈላል::

ሐ/ ከከፍተኛ የማዕድን ሥራዎችና ከማንኛዉም የፔትሮሊየምና የጋዝ ሥራዎች የሚገኘውን የገቢ ግብርና የሮያሊቲ ክፍያዎች በህጉ መሰረት ይካፈላል::

2.15. በክልሉ መስተዳድር አካላት ከሚሰጡ ፍቃዶችና አገልግሎቶች የሚመነጩ ክፍያዎችን ይወስናል ይሰበስባል::

2.16. ከደን የሚገኝ የሮያሊቲ ክፍያን ይወስናል፣ ይሰበስባል::

2.17. በክልሉ ውስጥ ማናቸውም የተፈጥሮ አደጋ ሲያጋጥም ወይም የህዝብን ጤንነት አደጋ ላይ የሚጥል በሽታ ሲከሰት የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ያወጣል::

## ምዕራፍ ስምስት

## የክልሉ ም/ቤት አወቃቀርና፣ አወካከል ሥልጣንና ተግባር

### አንቀጽ 48

### የሐረሪ ህዝብ ክልል ምክር ቤት

የሐረሪ ሕዝብ ክልል ም/ቤት 36 አባላት ያሉትና በሁለት ጉባኤዎች የተዋቀረ የክልል ም/ቤት ነው::

### አንቀጽ 49

### የም/ቤቱ ጉባኤዎች

1. የሐረሪ ሕዝብ ክልል ም/ቤት ሁለት ጉባኤዎች:-

ሀ/ የሕዝብ ተወካዮች ጉባኤና

ለ/ የሐረሪ ብሔራዊ ጉባኤ ናቸው::

2. የሕዝብ ተወካዮች ጉባኤ በዚህ ህገ-መንግሥት አንቀጽ 50/1/ እንደተመለከተው የሚወከሉ ሃያ ሁለት አባላት ይኖሩታል::

3. የሐረሪ ብሔራዊ ጉባኤ በዚህ ሕገ-መንግስት አንቀጽ 50 /2/ እንደተመለከተው የሚወከሉ 14 የሐረሪ ብሔረሰብ አባለት ይኖሩታል::

### አንቀጽ 50

### የጉባኤዎች አከፋፈል አወካከልና አመራረጥ

1. የሕዝብ ተወካዮች ጉባኤ አባላት በሁለት የምርጫ ክልሎች የሚወከሉ አባላት ያሉት ጉባኤ ነው:: አወካከሉ:-

ሀ/ ከጀጎል ምርጫ ክልል 4 አባላትና

ለ/ ከጀጎል ውጭ ካሉት የከተማ ቀበሌዎችና የገጠር ቀበሌ ገበሬ ማህበራትን የሚያጠቃልል የምርጫ ክልል 18 አባላት ይመረጣል::

2. የሐረሪ ብሔራዊ ጉባኤ አባላት በክልሉ ውስጥና ከክልሉ ውጭ በሌላ በኢትዮጵያ ክልሎችና ከተሞች ከሚኖሩ የሐረሪ ብሔረሰብ አባላት ይመረጣል::

3. የጉባኤው አባላት ምርጫ ነፃና ቀጥተኛ በሆነ ድምፅ በሚስጥር በመስጠት ስርዓት ይፈጸማል::

## ክፍል አንድ

## ስለ ክልሉ ምክር ቤት

### አንቀጽ 51

### የሐረሪ ሕዝብ ክልል ም/ቤት ሥልጣንና ተግባር

1. የሐረሪ ሕዝብ ክልል ም/ቤት የሕዝብ ተወካዮች ጉባኤና የሐረሪ ብሔራዊ ጉባኤ በጋራ የሚሰበሰቡበት ም/ቤት ነው:: በዚህ ህገ መንግሥት መሠረት የክልሉ ህግ አውጪና በክልሉ የውስጥ ጉዳዮች ላይ የበላይ የፖለቲካ ስልጣን ባለቤት ነው::

2. የሐረሪ ሕዝብ ክልል ም/ቤት የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል::

ሀ/ የክልሉን ሕገ-መንግስትና ሌሎች ሕጎችን ያወጣል::

ለ/ በዚህ ሕገ-መንግስት አንቀጽ 79 በተደነገገው መሠረት የክልሉን ሕገ-መንግስት ያሻሽላል::

ሐ/ የፌዴራል ሕገ-መንግስት ለክልሉች የተሰጠውን ስልጣን በክልሉ ተግባራዊ ያደርጋል::

መ/ ለክልሉ ፕሬዝደንትነት በሐረሪ ብሔራዊ ጉባኤ ጠቋሚነት የሚቀርበውን እጩ በ2/3ኛ ድምጽ መርምር ይመርጣል::

ሠ/ የክልሉን የውስጥ አስተዳደር ያዋቅራል ያደራጃል::

ረ/ የክልሉን የሕዝብ ደህንነትና ፀጥታን በሚመለከት ሕጎች ደንቦችና መመሪያዎች ያወጣል::

ሰ/ የሕዝብ ተወካዮች ጉባኤና በክልሉ መስተዳደር ም/ቤት የሚቀርቡለትን አዋጆች ደንቦች መመሪያዎችና ፖሊሲዎች መርምር ያፀድቃል::

ሸ/ በክልሉ ፕሬዝዳንት የቀረቡትን ም/ፕሬዝዳንት፣ የክልል አስፈፃሚ/ካብኔ/ አባል የሆኑ የቢሮ ኃላፊዎችና ሌሎች ተመሳሳይ ስልጣን ያላቸውን ኃላፊዎች ሹመት ያፀድቃል::

ቀ/ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ፕሬዝደንት ምክትል ፕሬዝደንትና ዋና ኦዲተር እና የፖሊስ ኮሚሽነር ይሾማል::

በ/ በክልሉ ዳኞች አስተዳደር ጉባኤ የሚቀርቡትን ዳኞች ሹመት ያፀድቃል::

www.chilot.me

ተ/ የክልሉን የመሬት አጠቃቀም ፖሊሲ፣ ደንብና መመሪያ ያወጣል::

ቸ/ ለክልሉ በተሰጠው የገቢ ምንጭ ወሰን ግብርና ታክስ ይጥላል::

ነ/ የክልሉን አመታዊ በጀት ያፀድቃል::

ኘ/ በክልሉ ውስጥ ማናቸውም ድንገተኛ የተፈጥሮ አደጋ ሲያጋጥም ወይም የሕዝብን ጤንነት አደጋ ላይ የሚጥል በሽታ ሲከሰት የአስቸካይ ጊዜ አዋጅ ያውጃል::

አ/ የክልሉን መንግሥት የገቢ ምንጮች የሚመለከቱ ህጎች ያወጣል::

ወ/ በህጉ መሰረት ምህረት ያደርጋል፣ የክልሉን ሠላምና ፀጥታ ለመጠበቅ የሚያስፈልጉ መመሪያዎችን ያወጣል:: የፀጥታና የፖሊስ ሃይሉን ያቋቁማል::

የ/ የክልሉ ርዕሰ መስተዳድርና ሌሎች የክልሉን መንግሥት ባለሥልጣናት ለጥያቄ ይጠራል፣ የአስፈጻሚውን አካል አሠራር ይመረምራል::

## አንቀጽ 52

## የም/ቤቱ አመራርና አሠራር

1. ም/ቤቱ የራሱ አፈ-ጉባኤና ምክትል አፈ-ጉባኤ ይኖሩታል::
2. እንደአስፈላጊነቱ ቋሚና ጊዜያዊ ኮሚቴዎች ይኖሩታል::
3. አፈ-ጉባኤው በህዝብ ተወካዮች ጉባኤ በኩል እንዲሁም ምክትል አፈ-ጉባኤ በሐረሪ ብሔራዊ ጉባኤ በኩል ቀርበው በምክር ቤቱ በ2/3ኛ ድምፅ ይመረጣሉ::

## አንቀጽ 53

## የአፈ-ጉባኤው ስልጣንና ተግባር

1. የም/ቤቱን መደበኛና አስቸኳይ ስብሰባዎች ይጠራል፣ ይመራል::
2. የም/ቤቱን ጠቅላላ ሥራዎች ያስተዳድራል::
3. በም/ቤቱ አባላት ላይ የሚወሰኑ የዲሲፒሊን እርምጃዎችን ያስፈጽማል::
4. የአፈ-ጉባኤው ሌሎች ሥራዎች በዝርዝር የሚወጣ ሌላ ሕግ ይወሰናል::

## አንቀጽ 54

## የምክትል አፈ-ጉባኤው ሥልጣንና ተግባር

1. በአፈ-ጉባኤ ተለይቶ የሚሰጡትን ተግባራት ያከናውናል::
2. አፈ-ጉባኤው በማይኖርበት ጊዜ ተክቶ ይሰራል::

## አንቀጽ 55

## የም/ቤቱ አባላት መብትና ግዴታ

1. ማንኛውም የም/ቤቱ አባል በም/ቤቱ በሚሰጠው ድምጽ ወይም አስተያየት ምክንያት አይከሰስም አስተዳደራዊ እርምጃ አይወሰድበትም::
2. ማንኛውም የም/ቤቱ አባል ከባድ ወንጀል ሲፈጽም እጅ ከፈንጅ ካልተያዘ በስተቀር ያለ ም/ቤቱ ፍቃድ አይያዝም በወንጀልም አይከሰስም::
3. ማንኛውም የም/ቤቱ አባል የመረጠው ሕዝብ አመኔታ ባጣበት ጊዜ ከም/ቤት አባልነት ይወገዳል:: ዝርዝሩ በሕግ ይወሰናል::

## አንቀጽ 56

## የም/ቤቱ የስብሰባ ጊዜና የሥራ ዘመን

1. ም/ቤቱ በዓመት ሁለት ጊዜ መደበኛ ስብሰባ ያደርጋል::
2. የም/ቤቱ አባላት የሥራ ዘመን ለአምስት አመት ነው:: የሥራ ዘመኑ ከማብቃቱ ከአንድ ወር በፊት አዲስ ምርጫ ተካሄዶ ይጠናቀቃል:: የቀድሞው ም/ቤት የሥራ ዘመን በተጠናቀቀ በአስራ አምስት ቀናት ውስጥ አዲሱ ም/ቤት ሥራውን ይጀምራል::
3. የም/ቤቱ መደበኛ ስብሰባ በማይኖርበት ወቅት አፈ-ጉባኤዉ አስቸኳይ ስብሰባ ሊጠራ ይችላል:: የክልሉ ርዕሰ መስተዳድር ወይም ከምክር ቤት አባላት መካከል ከ1/3ኛ በላይ የሚሆኑት አስቸኳይ ስብሰባ እንዲጠሩ ከጠየቁ አፈ-ጉባኤው ስብሰባ የመጥራት ግዴታ አለበት::
4. የም/ቤቱ ስብሰባ በግልፅ ይካሄዳል:: ሆኖም ስብሰባዉ በዝግ እንዲካሄድ በአባላቱ ወይም በክልሉ መስተዳደር ም/ቤት ከተጠየቀና ከም/ቤት አባላት መካከል ከግማሽ በላይ የሚሆኑት ጥያቄውን ከደገፉት ዝግ ስብሰባ ሊደረግ ይችላል::

## አንቀጽ 57

## የውሳኔ አሰጣጥና የአሰራር ሥነ-ሥርዓቶች

1. ከም/ቤት አባላት መካከል ከ2/3ኛ የሚሆኑት ከተገኙ ምልዓተ ጉባኤ ይሆናል::
2. ማንኛውም ውሳኔ የሚተላለፈዉ በም/ቤቱ ስብሰባ ላይ በተገኙት አባላት አብላጭ ድምጽ ይሆናል::
3. ምክር ቤቱ አሰራሩንና የሕግ አወጣጥ ሂደቱን አስመልክቶ ዝርዝር ሕጎችን ሊያወጣ ይችላል::

## ክፍል ሁለት

## የጉባኤዎች ስልጣንና ተግባር

## አንቀጽ 58

## የሕዝብ ተወካዮች ጉባኤ ስልጣንና ተግባር

የሕዝብ ተወካዮች ጉባኤ በክልሉ ም/ቤት ከሚኖረው ስልጣንና ተግባር በተወማሪ የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል::

1. ማንኛውም የኢኮኖሚ ልማትና የማህበራዊ ልማት ፖሊሲ ስትራቴጂ በተመለከተ ረቂቅ ሕግ ያመነጫል፣ ለክልሉ ም/ቤት አቅርቦ ያጸድቃል::
2. የግብርና ታክስ አዋጆችን ያመነጫል፣ ለክልሉ ም/ቤት በማቅረብ ያጸድቃል::
3. የክልሉን በጀት ገምግሞ ለክልሉ ም/ቤት ያቀርባል:

www.chilot.me

4. በክልሉ የም/ቤት አባላት መካከል አፈ-ጉባኤነት አንድ አባል ይጠቁማል፡፡
5. የጉባኤውን ስብሰባ የሚመሩ አፈ ጉባኤ፣ ምክትል አፈ ጉባኤና
6. ቃለ ጉባኤ የሚይዝ አንድ ፀሐፊ ይመርጣል፡፡

## አንቀጽ 59

## የሐረሪ ብሔራዊ ጉባኤ ሥልጣንና ተግባር

1. የሐረሪ ብሔረሰብ ቋንቋና ባሕል በሚመለከት ፖሊሲና ሕግ ያወጣል፡፡
2. በክልሉ ውስጥ የሐረሪ ብሔረሰብ ታሪክና ባሕል የሚያንጸባርቁ ቅርፃቅርፆች የመቃብር ቦታዎች የመስኪድና የአድባራት አጠባበቅን በሚመለከት መመሪያ ያወጣል፡፡
3. የሐረሪ ብሔረሰብ በፌዴራል መንግስት የፌድሬሽን ም/ቤት በሚወከሉ ወይም የሚወከሉ አባል ወይም አባላትን ይመርጣል፡፡
4. የክልሉን ፕሬዝዳንትና የም/ቤቱን ምክትል አፈ-ጉባኤ ይጠቁማል፡፡
5. የጉባኤውን ስብሰባ የሚመሩ አፈ ጉባኤ፣ ምክትል ጉባኤና
6. የጉባኤውን ቃለ ጉባኤ የሚይዝ አንድ ፀሐፊ ይመርጣል፡፡
7. የራስን እድል በራስ የመወሰን መብትን በዚህ ህገ መንግስት አንቀጽ 39 መሰረት ተግባራዊ ያደርጋል፡፡

## ምዕራፍ ሰድስት

## የክልሉ መስተዳደር ምክር ቤት

## አንቀጽ 60

## ስለ አስፈፃሚነት ሥልጣን

1. የክልላዊ መንግስቱ ከፍተኛ የአስፈፃሚነት ስልጣን የተሰጠው ለክልሉ መስተዳደር ምክር ቤት እና ለክልሉ ፕሬዝዳንት ነው፡፡
2. የመስተዳደሩ ም/ቤት አባላት በመንግስት ተግባራቸዉ በጋራ ለሚሰጡት ውሳኔ የጋራ ኃላፊነት አለባቸው፡፡

## አንቀጽ 61

## የክልሉ መስተዳደር ም/ቤት አባላት

1. የክልሉ መስተዳደር ም/ቤት ፕሬዝዳንቱ፣ ምክትል ፕሬዝዳንቱ፣ የቢሮ ኃላፊዎችና የክልሉ መስተዳደር ምክር ቤት በሚወስናቸዉ ሌሎች አባላት የሚገኙበት አካል ነው፡፡
2. ፕሬዝደንቱና የክልሉ አስፈፃሚ አካላት በዚህ ህገ-መንግስትና በሌሎች ህጎች የሚሰጣቸው ተግባርና ኃላፊነት ይኖራቸዋል፡፡
3. የክልሉ መስተዳደር ምክር ቤት ሰብሳቢ ፕሬዝደንቱ ይሆናሉ፡፡
4. የክልሉ መስተዳደር ምክር ቤት ተጠሪነቱ ለክልሉ ምክር ቤት እና ለክልሉ ፕሬዝዳንት ይሆናል፡፡

## አንቀጽ 62

## የክልሉ መስተዳደር ምክር ቤት ስልጣንና ተግባር

በፌዴራል ሕገ-መንግስት የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የክልሉ መስተዳደር ምክር ቤት ከዚህ በታች የተመለከቱት ሥልጣንና ተግባር ይኖሩታል፡፡

1. በፌዴራል መንግስት፣ በክልሉ ምክር ቤት እና በሐረሪ ጉባኤ የወጡት ፖሊሲዎች፣ አዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎች ተግባራዊ መሆናቸውን ይከታተላል፤ ያረጋግጣል፡፡
2. የክልሉን የመስተዳደር አካላትና ሥራን ይመራል፣ ያስተባብራል፣ ይቆጣጠራል፡፡
3. የክልሉን ማሕበራዊ ዕድገትና ኢኮኖሚያዊ ልማት ለማፋጠን የሚያስችሉ ዕቅዶችና ፐሮግራሞችን ያዘጋጃል፤ ለክልሉ ምክር ቤት ቀርቦ ሲፀድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፡፡
4. የክልሉን መስተዳደር ዓመታዊ በጀት በማዘጋጀት ለምክር ቤቱ ያቀርባል፤ ሲፀድቅ ተግባራዊ ያደርጋል፡፡
5. የክልሉን ቢሮዎችና አስፈፃሚ አካላት ያስተባብራል፤ ይመራል፤ ይቆጣጠራል፡፡
6. ህግና ስርአት በክልሉ መከበሩን ያረጋግጣል፡፡
7. የልማት፣ የማህበራዊ ጉዳይ ጸጥታና ደህንነትን በሚመለከት የህግና የፖሊሲ ረቂቆችን ለክልሉ ም/ቤት ያቀርባል፤ ሲጸድቅም በስራ ላይ ያውላል፤
8. በክልሉ ም/ቤት በሚሰጠዉ ስልጣን መሰረት ደንቦችና መመሪያዎችን ያወጣል፡፡
9. ስለ ስራዉ እንቅስቃሴ ለክልሉ ም/ቤት ሪፖርት ያቀርባል፡፡
10. በምክር ቤት የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል፡፡
11. በዚህ ሕገ-መንግስት መሰረት የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ያውጃል፡፡
12. በክልሉ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ልማት ለማፋጠን አስፈላጊ የሆኑ ተቋማትን በሕግ ሊያዋቅር ይችላል፡፡

## አንቀጽ 63

## የፕሬዝዳንቱ አሰያየም

1. ፕሬዝዳንቱ በሀረሪ ጉባኤ አቅራቢነት በክልሉ ም/ቤት የሚመረጥ ይሆናል፡፡
2. የፕሬዝዳንቱ የስራ ዘመን የክልሉ ምክር ቤት የስራ ዘመን ይሆናል፡፡
3. ፕሬዝዳንቱ በምክር ቤቱ ፊትለፊት ቃለመሀላ መፈጸም ይኖርበታል፡፡ የቃለመሀላው ይዘት እንደሚከተለው ይሆናል፡፡

«እኔ ______ በዛሬው ዕለት የሐረሪ ህዝብ ክልል ፕሬዝዳንት በመሆን ሥራዬን ስጀምር የተጣለብኝን ከፍተኛ ሃላፊነት በታማኝነት ለመፈጸም ቃል እገባለሁኝ»

www.chilot.me

## አንቀጽ 64

## የፕሬዚዳንቱ ስልጣንና ተግባር

1. ፕሬዝዳንቱ ተጠሪነቱ ለክልሉ ምክር ቤት ሆኖ የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡፡

   ሀ/ የክልሉን መስተዳድር ምክር ቤት ይመራል፣ ያስተባብራል፣ ይወክላል፡፡

   ለ/ የክልሉ ም/ቤት የሐረሪ ጉባኤ እና የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት የሚያወጡአቸውን ህጎች፣ ደንቦች፣ ፖሊሲዎች፣ መመሪያዎችና ውሳኔዎች ተፈጻሚነት ይከታተላል፤ ያስፈፅማል፡፡

   ሐ/ የክልሉን ም/ፕሬዝዳንት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት እና ምክትል ፕሬዚዳንቱን፣ ዋና ኦዲተር፣ ም/ዋና ኦዲተር እና የፖሊስ ኮሚሽነር፣ የክልሉን መስተዳድር ምክር ቤት አባላትና ሌሎች የክልሉ መስሪያ ቤቶች ሀላፊዎችን ለክልሉ ም/ቤት አቅርቦ ያሾማል፡፡

   መ/ በንዑስ አንቀጽ /ሐ/ ሥር የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ የክልሉ ም/ቤት ሊሰበሰብ ባልቻለበት ጊዜ ከፍ ብሎ የተጠቀሱትን ሃላፊዎች በጊዜያዊነት መድቦ ያሰራል፡፡

   ሠ/ ከክልል መስተዳድር ምክር ቤት አባላት ውጪ የሆኑ ሃላፊዎች ም/ቢሮ ሃላፊዎች ኮሚሽነሮችና ሌሎች የሥራ ሃላፊዎችን ይሾማል፡፡

   ረ/ የካቢኔ አባላት፣ የቢሮ ሃላፊዎች ወይም የጽ/ቤት ሃላፊዎች ችግር ስኖርባቸዉ በማገድና ለክልሉ ም/ቤት በማቅረብ ያስወግዳል፡፡

   ሰ/ የብሔራዊ ክልሉን ደህንነት ለማስጠበቅና ህግና ሥርዓትን ለማስከበር የተቋቋሙትን ክልል አቀፍ የፀጥታና የፖሊሲ ሀይሎች በበላይነት ይመራል፣ ይቆጣጠራል፡፡

   ሸ/በክልሉ የሚገኙትን የበታች የአስተዳደር እርከኖችን ሥራ ይመራል፣ ያስተባብራል፣ ይቆጣጠራል፡፡

## አንቀጽ 65

## የሐረሪ ህዝብ ክልል ፕሬዝዳንት ጽ/ቤት

ፕሬዝዳንቱ በዚህ ህገ መንግስትና በሌሎች ሕጎች የተጣለበትን ሃላፊነት ለመወጣት ይቻለው ዘንድ የራሱ ጽ/ቤት ይኖረዋል፡፡ ዝርዝሩ በሕግ ይወሰናል፡፡

## አንቀጽ 66

## የምክትል ፕሬዝዳንቱ ስልጣንና ተግባር

1. ምክትል ፕሬዝዳንቱ ተጠሪነቱ ለፕሬዝዳንቱ ሆኖ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባር ይኖረዋል፡፡

   ሀ. በክልሉ ፕሬዝዳንትና በክልል መስተዳድር ም/ቤት የሚሰጡት ተግባራትን ያከናውናል፡፡

   ለ/ ፕሬዝዳንቱ በማይኖርበት ወይም ሥራዉን ለማከናወን በማይችልበት ጊዜ ተክቶ ይሰራል፡፡

## ምዕራፍ ስባት

## ስለ ፍርድ ቤቶች አወቃቀርና የዳኝነት ስልጣን

## አንቀጽ 67

## ስለ ነጻ የዳኝነት አካል መቋቋም

1. በክልሉ ነጻ የዳኝነት አካል በዚህ ህገ-መንግስት ተቋቁሟል፡፡
2. የዳኝነት ስልጣንን ከመደበኛ ፍርድ ቤት ወይም በህግ የመዳኘት ስልጣን ከተሰጠዉ ተቋም ዉጭ የሚያደርግና በህግ የተደነገገውን የዳኝነት ስርዓት የማይከተል ልዩ ወይም ጊዜያዊ ፍርድ ቤት አይቋቋምም፡፡

## አንቀጽ 68

## ስለ ባህላዊና ኃይማኖታዊ ዳኝነት

1. የሀይማኖትና የባህል ፍርድ ቤቶች በሚወጣ ዝርዝር ህግ መሰረት ሊቋቋሙ ወይም ዕውቅና ሊሰጣቸው ይችላል፡፡
2. ይህ ህገ መንግሥት ከመጽደቁ በፊት በመንግሥት ዕዉቅና አግኝተው ሲሰራባቸዉ የነበሩ ሀይማኖታዊና ባህላዊ የዳኝነት አካላት በዚህ ህገ መንግሥት እውቅና አግኝተው ይደራጃሉ፡፡

## አንቀጽ 69

## የዳኝነት ስልጣን

1. የክልሉ የዳኝነት ስልጣን የፍርድ ቤቶች ብቻ ነው፡፡
2. በየትኛዉም ደረጃ የሚገኝ የዳኝነት አካል ከማናቸውም የመንግስት አካል ባለስልጣን ወይም ሌላ ተጽእኖ ነጻ ነው፡፡
3. ዳኞች የዳኝነት ተግባራቸውን በሙሉ ነፃነት ያከናዉናሉ፤ ከህግ በስተቀር በሌላ ሁኔታ አይመሩም፡፡
4. ማንኛውም ዳኛ ከዚህ በታች በተጠቀሱት ሁኔታዎች ካልሆነ በስተቀር በህግ የተወሰነው የጡረታ ዕድሜ ከመድረሱ በፊት ከፈቃዱ ውጭ ከዳኝነት ስራው አይነሳም፡፡

   ሀ/የዳኞች አስተዳደር ጉባኤ በዳኞች የዲሲፒሊን ህግ መሰረት ጥፋት ፈፅሟል ወይም ጉልህ የሆነ የስራ ችሎታና ቅልጥፍና አንሶታል ብሎ ሲወስን ወይም፤

   ለ/በህመም ምክንያት ዳኛው ተግባሩን በተገቢው ሁኔታ ማከናወን አይችልም ብሎ ሲወስንና፤

   ሐ/የጉባኤው ውሳኔ ለክልሉ ምክር ቤት ቀርቦ በአባላቱ አብላጫ ድምጽ ተደግፎ ሲጸድቅ፡፡

5. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 4 መሰረት አንድን ዳኛ ከዳኝነት ስራው የሚያስነሳው ጥፋት ፈፅሟል ብሎ ጉባኤው ካመነበት ጉዳዩ በክልሉ ም/ቤት እስኪወሰን ድረስ ከዳኝነት ስራው ይታገዳል፡፡
6. የማንኛውም ዳኛ የጡረታ መውጫ ጊዜ አይራዘምም፡፡

www.chilot.me

## አንቀጽ 70

## የፍርድ ቤቶች አደረጃጀትና ስልጣን

1. የክልሉ የዳኝነት አካል በጠቅላይ ፍርድ ቤት፣ በከፍተኛ ፍርድ ቤትና በመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ይደራጃል።
2. የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት
   ሀ/ ክልላዊ ጉዳዮችን በተመለከተ ከፍተኛውና የመጨረሻው የዳኝነት ስልጣን፤
   ለ/ በፌዴራል ጉዳዮች ላይ የፌዴራል መንግስት ከፍተኛ ፍርድ ቤት የዳኝነት ስልጣንና፤
   ሐ/ ማንኛውም ክልላዊ ፍርድ ቤት የሰጠው የመጨረሻ ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ሲኖርበት በሰበር የማየት ስልጣን ይኖረዋል። ዝርዝሩ በህግ ይወሰናል።
3. የክልሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ከክልላዊ ስልጣኑ በተጨማሪ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የዳኝነት ስልጣን ይኖረዋል።
4. የክልሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በፌዴራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤት የዳኝነት ስልጣኑ መሰረት በሚሰጠው ውሳኔ ላይ የሚቀርበው ይግባኝ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይታያል።
5. የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ባለው በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የዳኝነት ስልጣኑ መሰረት በሚሰጠዉ ውሳኔ ላይ የሚቀርበው ይግባኝ በፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይታያል።
6. የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት የዳኝነት አካላቱን የሚያስተዳድርበትን በጀት ለክልሉ ም/ቤት አቅርቦ ያስወስናል፤ ሲፈቀድም በጀቱን ያስተዳድራል።
7. የክልሉ ጠቅላይና ከፍተኛ ፍ/ቤቶች በውክልና ለሚሰሩት ፌዴራላዊ የዳኝነት ተግባር ከፌዴራል መንግስት የበጀት ማካካሻ ይሰጣቸዋል።

## አንቀጽ 71

## የዳኞች አሿሿም

1. የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሮዝዳንትና ምክትል ፕሬዝዳንት በክልሉ ፕሬዝዳንት አቅራቢነት በክልሉ ምክር ቤት ይሾማሉ።
2. የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት፣ የከፍተኛ ፍ/ቤት እና የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ዳኞች በክልሉ የዳኞች አስተዳደር ጉባኤ አቅራቢነት በክልሉ ምክር ቤት ይሾማሉ።
3. የክልሉ ዳኞች አስተዳደር ጉባኤ የክልሉን ጠቅላይ ፍርድ ቤትና ከፍተኛ ፍርድ ቤት ዳኞች ሹመት ለክልሉ ምክር ቤት ከማቅረቡ በፊት የፌደራሉ ዳኞች አስተዳደር ጉባኤ በዕጩዎቹ ላይ ያለውን አስተያየት ከራሱ መግለጫ ጋር ለክልሉ ምክር ቤት የማቅረብ ኃላፊነት አለበት። ሆኖም የፌደራል ዳኞች አስተዳደር ጉባኤ የተጠየቀውን አስተያየት በሦስት ወራት ጊዜ ውስጥ ካላቀረበ የክልሉ ምክር ቤት የዕጩ ዳኞች ሹመት ያፀድቃል።

## አንቀጽ 72

## ስለ ክልሉ ዳኞች አስተዳደር ጉባኤ መቋቋም

1. በክልሉ ውስጥ ዳኞች በአብላጫ ድምጽ የሚወከሉበት የዳኞች አስተዳደር ጉባኤ ይቋቋማል።
2. የክልሉ የጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዝዳንት የጉባኤው ሰብሳቢ ይሆናል።
3. የጉባኤው አባላት ዝርዝር እንዲሁም ሥልጣንና ተግባር በሕግ ይወሰናል።

## አንቀጽ 73

## ህገ መንግሥቱን ስለመተርጎም

1. የህገ መንግሥታዊ ክርክር ጉዳይ ሲነሳ በህገ መንግሥት ተርጓሚ ኮሚስዮን ውሳኔ ያገኛል።
2. የህገ መንግሥት ተርጓሚ ኮሚስዮን የህገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ በሚያቀርብለት ህገ መንግሥታዊ ጉዳይ ላይ በሰላሳ ቀናት ውስጥ ውሳኔ ይሰጣል።
3. የህገ መንግሥት ተርጓሚ ኮሚሲዮን የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል።
   ሀ/ በኢፌድሪ የፌደሬሽን ምክር ቤት የሐረሪ ተወካይ ሰብሳቢ
   ለ/ በኢፌድሪ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የሐረሪ ክልል ተወካዮች መካከል አንደኛውም ምክትል ሰብሳቢ ሁለተኛው ፀሐፊ ሆነው በኮሚሲዮኑ ይመረጣሉ።
   ሐ/ በሐረሪ ህዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት በሐረሪ ጉባኤና በሐረሪ ህዝብ ተወካዮች ጉባኤ ከእያንዳንዱ ጉባኤ የሚወከሉ ሁለት ሁለት ተወካዮች አባላት።
   መ/ በሐረሪ ህዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የቀድሞ ፕሬዝዳንት/ፕሬዝዳንቶች/ ድምጽ ሳይሰጡ የሚሳተፉበት።

## አንቀጽ 74

## የሕገ-መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ

1. የክልሉ ሕገ-መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ በዚህ ሕገ-መንግሥት ተቋቁሟል።
2. የክልሉ ሕገ-መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ አስራ አንድ አባላት ይኖሩታል፣
3. አባላቱም የሚከተሉት ናቸው።
   ሀ/ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዝዳንት ..........ሰብሳቢ፣
   ለ/ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ምክትል ፕሬዝዳንት ..........ምክትል ሰብሳቢ፣
   ሐ/ በክልሉ መስተዳድር ፕሬዝዳንት አቅራቢነት በክልሉ ምክር ቤት የሚሾሙ በሙያ ብቃታቸውና በሥነ-ምግባራቸው የተመሰከረላቸው ስድስት የሕግ ባለሙያዎች፣
   መ/ በአፈ-ጉባኤው አቅራቢነት ከክልሉ ምክር ቤት አባላት መካከል የሚሰየሙ 3 ተወካዮች፣

www.chilot.me

4. የህገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ ሥልጣንና ተግባር

ሀ/ የህገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ ህገ መንግሥታዊ ጉዳዮችን የማጣራት ሥልጣን ይኖረዋል:: በሚያደርገው ማጣራት መሰረት ህገ መንግሥቱን መተርጎም አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ለህገ መንግሥት ተርጓሚ ኮሚሲዮን በጉዳይ ላይ የውሳኔ ሐሳብ ያቀርባል::

ለ/ በክልሉ ህግ አውጪ አካል የሚወጡ ህጎች ከዚህ ህገ መንግሥት ጋር ይቃረናሉ የሚል ጥያቄ ሲነሳና ጉዳዩም በሚመለከተው ፍርድ ቤት ወይም በባለ ጉዳዩ ሲቀርብለት መርምሮ ለመጨረሻ ውሳኔ ለህገ መንግሥት ተርጓሚው ኮሚሲዮን ያቀርባል::

ሐ/ በፍርድ ቤቶች የህገ መንግሥት ትርጉም ጥያቄ ሲነሳ

1. ህገ መንግሥቱን መተርጎም አስፈላጊ ሆኖ ሳያገኘው ሲቀር ጉዳዩን ለሚመለከተው ፍርድ ቤት ይመልሳል በአጣሪዉ ጉባኤ ውሳኔ ቅር የተሰኘ ባለጉዳይ ቅሬታውን ለህገ መንግሥት ተርጓሚ ኮሚሲዮን በይግባኝ ማቅረብ ይችላል::

2. የትርጉም ጥያቄ መኖሩን ያመነበት እንደሆነ በጉዳዩ ላይ የሚሰጠዉን ሕገ መንግሥታዊ ትርጉም ለህገ መንግሥት ተርጓሚ ኮሚሲዮን ለመጨረሻ ውሳኔ ያቀርባል::

መ/ የሚመራበትን ሥነ ሥርዓት አርቅቆ ለህገ መንግሥት ተርጓሚ ኮሚሲዮን ያቀርባል ሲፈቀድም ተግባራዊ ያደርጋል::

## ምዕራፍ ስምንት

## አንቀጽ 75

## ስለቀበሌ አስተዳደር መቋቋም

1. የቀበሌ አስተዳደር የክልሉ የመጨረሻው መንግሥታዊ የአስተዳደር እርከን ነው::

2. የቀበሌ አስተዳደር የሚከተሉት አበይት አካላት ይኖሩታል

ሀ/ የቀበሌ ምክር ቤት፣

ለ/ የቀበሌ አስተዳደር ምክር ቤት፣

ሐ/ የማህበራዊ ፍርድ ቤት ናቸው::

3. የቀበሌ መስተዳድር አካላት አደረጃጀትና ሥልጣንና ሃላፊነታቸውን በተመለከተ በዝርዝር ህግ ይወጣል::

## ምዕራፍ ዘጠኝ

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

## አንቀጽ 76

## የአስቸኳይ ጊዜ ድንጋጌ

1. ማናቸውም የተፈጥሮ አደጋ ሲያጋጥም ወይም የህዝብን ጤንነት አደጋ ላይ የሚጥል በሽታ ሲከሰት እና ምክር ቤት በማይሰበሰብበት ጊዜ የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት በዚህ ህገ-መንግስት አንቀጽ 55 ንዑስ ቁጥር 11 በተሰጠው ስልጣን መሰረት የአስቸኳይ ጊዜ ድንጋጌ ያወጣል::

2. የመስተዳድር ምክር ቤቱ የአስቸኳይ ጊዜ ድንጋጌውን አውጥቶ በስራ ላይ ባዋለ በአስራ አምስት ቀን ውስጥ አፈ-ጉባኤው ምክር ቤቱን አስቸኳይ ስብሰባ ጠርቶ ማስጸደቅ አለበት::

3. የመስተዳድር ምክር ቤት ያወጣው የአስቸኳይ ጊዜ ድንጋጌ በምክር ቤቱ ተቀባይነት ካገኘ ሊቆይ የሚችለው ለስድስት ወራት ብቻ ይሆናል:: ሆኖም የክልሉ ምክር ቤት በሁለት ሶስተኛ ድምጽ ሲወስን የአስቸኳይ ጊዜ ድንጋጌው በየአራት ወሩ ሊታደስ ይችላል::

4. የመስተዳደሩ ምክር ቤት እና ም/ቤቱ በአስቸኳይ ጊዜ ድንጋጌ የሚያወጣቸው ድንጋጌዎችና የሚወስዳቸው እርምጃዎች በማናቸውም ረገድ በዚህ ህገ-መንግስት አንቀጽ 14፣ 16፣ 18//1/ እና 2፣ 21/1/፣ 24፣ 1/25፣ 27/1/ እና 39 የተቀመጡትን መብቶች የሚገድቡ መሆን የለባቸውም::

5. በክልሉ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ በሚታወጅበት ወቅት የክልሉ ምክር ቤት ከአባላቱና ከሕግ ባለሙያዎች መርጦ የሚመድባቸው ሰባት አባላት ያሉት የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ አፈፃፀም መርማሪ ቦርድ ያቋቁማል:: ቦርዱ በፌደራሉ ህገ መንግስት አንቀፅ 93 /6/ የተጠቀሱት ስልጣንና ኃላፊነቶች ይኖሩታል::

## አንቀጽ 77

## የክልሉ ፖሊሲ ዓላማዎች

ማንኛውም የመንግሥት አካል የፌደራሉንና የክልሉን ሕገ-መንግሥት፣ ሌሎች ሕጎችና ፖሊሲዎች በስራ ላይ ሲያውል በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ መንግስት ምዕራፍ 10 አንቀጽ 85 እስከ አንቀጽ 92 የተመለከቱትን ብሔራዊ ፖሊሲ መርሆዎችና ዓላማዎች መሰረት በማድረግ ነው::

## አንቀጽ 78

## የክልሉ ዋና ኦዲተር

1. የክልሉ ዋና ኦዲተር በመስተዳድሩ ፕሬዝዳንት አቅራቢነት በምክር ቤቱ ይሾማል::

2. የክልሉ ዋና ኦዲተር የክልሉን ቢሮዎችና የሌሎች መስሪያ ቤቶች ሂሳቦችን በመቆጣጠር በክልሉ መንግሥት የተመደበው ገንዘብ በጀት በበጀት ዓመቱ እንዲሰሩ ለተወሰኑ ሥራዎች በሚገባ መዋሉን ለክልል ምክር ቤቱ ሪፖርት ያቀርባል::

3. የክልሉ ዋና ኦዲተር የመስሪያ ቤቱን በጀት በቀጥታ ለክልሉ ምክር ቤት አቅርቦ ያፀድቃል::

## አንቀጽ 79

## የሕገ-መንግሥት ማሻሻያ ሃሳብን ስለማመንጨትና ስለማሻሻል

1. የዚህ ሕገ-መንግሥት ምዕራፍ 3 ድንጋጌዎች በፌደራል ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 105 ከተደነገገው ውጭ ሊሻሻሉ አይችልም::

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ ከተዘረዘሩት ውጭ ያሉት የሕገ-መንግሥቱ ድንጋጌዎች ሊሻሻሉ የሚችሉት:-

ሀ/ የህገ መንግሥቱ የማሻሻያ ሐሳብ ከሁለቱ ጉባኤዎች ቢያንስ በአንዱ ሲነሳ

www.chilot.me

የሐረሪ ሕዝብ ክልላዊ መንግስት

# ሐረር ነጋሪ ጋዜጣ

# HARAR NEGARI GAZETA

OF THE HARARI PEOPLE REGION STATE

9ኛ ዓመት ቁጥር 2
9th year No. 2

ሐረር መስከረም 30 ቀን 1997 ዓ.ም
HARAR October 10th 2004

| | | |
|---|---|---|
| ያንዱ ዋጋ ብር<br>Unit Price B. 2.00 | በሐረሪ ሕዝብ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ | የፖስታ ሣጥን ቁጥር<br>P.O.Box 272 |

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር 47/1997 ዓ.ም
የሐረሪ ሕዝብ ክልላዊ መንግስት አስፈጻሚ አካላትን አደረጃጀት በማሻሻልና ሥልጣንና ተግባራቸውን ለመወሰን የወጣ አዋጅ————ገፅ 385

## የሐረሪ ህዝብ ክልላዊ መንግስት አስፈጻሚ አካላትን አደረጃጀት ለማሻሻልና ሥልጣንና ተግባራቸውን ለመወሰን የወጣ አዋጅ::

የሐረሪ ህዝብ ክልል መንግስት ክልላዊና ሀገራዊ ፖሊሲዎችንና ስትራቴጂዎችን በተቀናጀ መንገድ ተግባራዊ በማድረግ ቀልጣፋና ውጤታማ፣ ግልፅነትንና ተጠያቂነትን በሚያሰፍን እና ውስን ሀብትን በቁጠባ ለመጠቀም በሚያስችል ሁኔታ አደረጃጀቱን በማስተካከል መልካም አስተዳደርና ልማትን ማረጋገጥ እንደሚቻል በመታመኑ፤

ቀደም ሲል የተቋቋሙና በአዲስ የተዋቀሩ ተመሳሳይና ተቀራራቢ ተግባርና ኃላፊነት ያላቸው አስፈጻሚ አካላትን በማሰባሰብና በማዋሃድ በተናጠል እና በመስተዳድሩ ምክር ቤት አባልነት፤ ኃላፊነት እንዲኖራቸው በማድረግ እና የክልሉን ዋና ዋና የፖሊሲ አስፈጻሚ ቢሮዎችን አደረጃጀት በማሻሻል እንደገና ሥልጣንና ተግባራቸውን መወሰን በማስፈለጉ፤

በሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልል መንግስት ምክር ቤት በ1997 ተሻሽሎ በወጣው ህገ-መንግስት አንቀጽ51(2) (ሀ) መሠረት የሚከተለው ታውጇል::

## ምዕራፍ አንድ
## ጠቅላላ

### 1. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ «የሐረሪ ህዝብ ክልል መንግስት አስፈጻሚ አካላት አደረጃጀት ማሻሻያ አዋጅ ቁጥር 47 /1997 » ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል::

### 2. ትርጓሜ

በዚህ አዋጅ ውስጥ:-

1. "ክልል ምክር ቤት" ማለት በሐረሪ ህዝብ ክልል መንግስት ህገ-መንግስት አንቀጽ_46/1/ የተመለከተው የክልሉ መንግስት ከፍተኛ የሕግ አውጪ አካል ነው::
2. " መስተዳድር ምክር ቤት" ማለት በሕገ-መንግስቱ አንቀጽ 46/2/ መሠረት የተመለከተው የክልሉ መንግስት ከፍተኛ የህግ አስፈጻሚ አካል ነው::
3. "ቢሮ ወይም መ/ቤት" ማለት በዚህ አዋጅና በሌሎች ህጎች መሠረት የተቋቋመ የክልሉ መንግስት ቢሮዎችን፣ ኮሚሽኖችን ፣ባለሥልጣኖችን ፣ኢንስቲትዩቶችን፣ ተቋማትንና ሌሎች መሰል አስፈጻሚ አካላትን ይጨምራል::
4. "የቢሮ ኃላፊ ወይም ምክትል ኃላፊው" ማለት በዚህ አዋጅ አንቀጽ 4 ከንዑስ አንቀጽ (1)-(9) ከተመለከቱት ቢሮዎችና ሌሎች መሥሪያ ቤቶች መካከል አንዱን የሚመራና የመስተዳድሩ ምክር ቤት /ካቢኔ/ አባል የሆነ ወይም ምክትሉ ማለት ነው::

## ምዕራፍ ሁለት
## ስለ ክልል መስተዳድር ምክር ቤት

### 3. የክልል መስተዳድር ምክር ቤት አወቃቀርና አደረጃጀት

1. የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት /ካቢኔ/ የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል:-
   ሀ/ ርዕሰ መስተዳድር፣
   ለ/ ምክትል ርዕሰ መስተዳድር፤ እና
   ሐ/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 4 ውስጥ የተመለከቱትን ቢሮዎች የሚመሩ ኃላፊዎች::
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1(ሐ) የተመከለተው ማንኛውም ቢሮ ኃላፊ በመስተዳድሩ ምክር ቤቱ ስብሰባ ላይ ሊገኝ በማይችልበት ጊዜ ምክትሉ ወይም ከአንድ በላይ ምክትሎች ካሉ በግልጽ ተለይቶ ውክልና የተሰጠው ምክትል በምክር ቤቱ ስብሰባ ላይ በምትክ አባልነት ይሳተፋል::

www.chilot.me

4. **የመስተዳድር ምክር ቤት አባል ቢሮዎች፡-**

የሚከተሉት የመስተዳድር ምክር ቤት አባል የሆኑ ቢሮዎች በዚህ አዋጅ ተቋቁመዋል፡-

1. የትምህርትና አቅም ግንባታ ቢሮ፤
2. የሕዝብ አደረጃጀት ባህልና ማኅበራዊ ጉዳይ ቢሮ፤
3. የግብርናና የገጠር ልማት ቢሮ፤
4. የፍትህና ፀጥታ ጉዳይ ቢሮ፤
5. የንግድ ኢንዱስትሪና ከተማ ልማት ቢሮ፤
6. የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ፤
7. የማስታወቂያና ህዝብ ግንኙነት ቢሮ፤
8. የጤና ጥበቃ ቢሮ፣ እና
9. የሐረር ከተማ ማዘጋጃ ቤት።

5 **የቢሮዎች ተጠያቂነት**

1. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 4 ከንዑስ አንቀጽ (1) እስከ (9) የተጠቀሱት ቢሮዎች በክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ለሚያሳልፉት ውሳኔ የጋራ ኃላፊነትና ተጠያቂነት አለባቸው፤
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የሠፈረው አጠቃላይ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ እያንዳንዱ መሥሪያ ቤት የተቋቋመበትን ዓላማ መሠረት በማድረግ በዚህ አዋጅ ተለይተው የተሰጡትን ተግባርና ኃላፊነቶች የመወጣት ግዴታ አለበት።

6. **የኃላፊዎች ተጠሪነት**

1. የቢሮ ኃላፊዎችና የሐረር ከተማ ማዘጋጃ ቤት ሹም ተጠሪነት ለርዕሰ መስተዳድሩና ለመስተዳድሩ ምክር ቤት ይሆናል፤
2. የሴቶች ጉዳይ ጽ/ቤት ኃላፊ ፤እና የኤች አይ ቪ/ኤድስ/ መከላከያና መቆጣጠሪያ ሴክሬተሪያት ጽህፈት ቤት ኃላፊ፤ ተጠሪነት ለርዕሰ መስተዳድሩ ይሆናል።
3. ከዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) እና (2) ከተመለከቱት ውጭ ያሉ ቢሮዎችና ሌሎች መሥሪያ ቤቶች ኃላፊዎች ተጠሪነት እንደ አግባብነቱ ለሚመለከተው ቢሮ ኃላፊ ወይም አካል ይሆናል።

7. **የአስፈጻሚ አካላት ተጠሪነት**

1. የሚከተሉት አስፈጻሚ አካላት ተጠሪነት ለትምህርትና አቅም ግንባታ ቢሮ ይሆናል፡-
   ሀ/ የሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን፤ እና
   ለ/ የሥራ አመራር ኢንስቲትዩት።
2. የሚከተለው አስፈጻሚ አካል ተጠሪነት ለሕዝብ አደረጃጀት ባህልና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮ ይሆናል፡-
   ሀ/ የኅብረት ሥራ ማኅበራት ማደራጃና ማስፋፊያ ጽህፈት ቤት።
3. የሚከተለው አስፈጻሚ አካል ተጠሪነት ለግብርናና ገጠር ልማት ቢሮ ይሆናል፡-
   ሀ/ አደጋ መከላከልና ምግብ ዋስትና ጽህፈት ቤት።
4. የሚከተሉት አስፈጻሚ አካላት ተጠሪነት ለፍትህና ፀጥታ ጉዳይ ቢሮ ይሆናል፡-
   ሀ/ የሚሊሺያ ጉዳይ ጽ/ቤት፣
   ለ/ የፖሊስ ኮሚሽን ፣ እና
   ሐ/ የማረሚያ ኮሚሽን።
5. የሚከተለው አስፈጻሚ አካል ተጠሪነት ለንግድ ኢንድስትሪና ከተማ ልማት ቢሮ ይሆናል፤
   ሀ/የጥቃቅንና አነስተኛ ንግድ ሥራዎች ማስፋፊያ ጽህፈት ቤት።
6. በዚህ አዋጅ በግልፅ ያልተመለከቱት ሌሎች መሥሪያ ቤቶች በሙሉ ተጠሪነት ለክልሉ ፕሬዝዳንትና /ወይም/ ለመስተዳደሩ ምክር ቤት ወይም በማቋቋሚያ አዋጆቻቸው ለተገለጹት አካላት ሆኖ አደረጃጀትና ዝላቂ ተጠሪነታቸው በመስተዳደሩ ምክር ቤት የሚወሰን ይሆናል።
7. እያንዳንዱ የቢሮና የሌላ አስፈጻሚ አካል ኃላፊ የሚመራውን አስፈጻሚ አካል ለሚመለከቱ ሥራዎች ፕሮግራሞችና ህጎች አፈጻጸም ተጠሪነቱ በዚሁ አዋጅ አንቀጽ 6 እና አንቀጽ 7 ከንዑስ አንቀጽ/1/ እስከ/6/ እንደተመለከተው ሆኖ፡-
   ሀ/ ቢሮውን ወይም መሥሪያ ቤቱን የመምራትና የመወከል ኃላፊነት ይኖረዋል፤
   ለ/ የቢሮውን ወይም የመሥሪያ ቤቱን ሥልጣንናና ተግባር ሥራ ላይ የማዋል ኃላፊነት ይኖረዋል፤
   ሐ/ ሥልጣንና ተግባሩን በከፊል ለሥራ ቅልጥፍ እና ውጤታማነት አስፈላጊ በሆነ መጠን ለበታች ኃላፊዎች መስጠት ይችላል።
8. የቢሮ ወይም የሌላ መሥሪያ ቤት ምክትል ኃላፊ ፣ ኃላፊው በማይኖርበት ጊዜ ተክቶ ይሠራል፤ እንደዚሁም በመደበኛ ሁኔታ ደግሞ በመዋቅራዊ የሥራ ዝርዝር በተመለከተው መሠረት የኃላፊው የቅርብ ረዳት ሆኖ ይሠራል።

## ምዕራፍ ሦስት
## የቢሮዎችና የሌሎች መሥሪያ ቤቶች ሥልጣንና ተግባር

8. **የትምህርትና አቅም ግንባታ ቢሮ**

ቢሮው የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖረዋል፡-

1. በህጉ መሠረት በክልሉ ውስጥ በቴክኒክ ሙያ ሥልጠና ለተሰማሩ ተቋማት እውቅና ይሰጣል፣ደረጃቸውን ጠብቀው ላልተገኙት የሰጠውን ዕውቅና ያነሳል፣
2. የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ማስረጃ ለመስጠት የሚችሉ ተቋማትን ያቋቁማል ያደራጃል ይቆጣጠራል፣
3. መደበኛ ወይም መደበኛ ባልሆኑ አጫጭር ሥልጠናዎች የትምህርቱን ካሪኩለም በማዘጋጀት በሥራ ላይ እንዲውል ያደርጋል፣
4. የክልሉን የቴክኒክና ሙያ ሥልጠና ክልሉ ከሚሻው የዕድገትና የሰው ኃይል ፍላጎት ጋር ተጣጥሞ እየተካሄደ መሆኑን ጥናትና ክትትል ያደርጋል አስፈላጊውን እርምጃ ይወስዳል፣
5. የክልሉ የቴክኒክና ሙያ ሥልጠና በአገሪቱ በአጠቃላይ ያለውን ደረጃ የጠበቀ መሆኑን ያረጋግጣል፣
6. በተሟላ ጥናት ላይ በመመስረት አስፈላጊው ማሻሻያዎችን ያደርጋል አዳዲስ ሥልጠናዎች ይከፍታል አላስፈላጊ የሆኑትን ያጥፋል፣
7. የድህረ ሥልጠና ክትትል ጥናት በክልሉ ውስጥ እንዲካሄድ ያደርጋል፤
8. ሰልጣኞች ሥራ ፈጣሪ እንዲሆኑ ከሚያግዙ መንግስታዊና መንግስታዊ ካልሆኑ ተቋማት ጋር ግንኙነት ይፈጥራል፣ የጋራ ጥናትና ምክክር በየጊዜው ያካሄዳል፤
9. የግል ባለሀብቶች፣ ማኅበረሰቡ፣ መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማት በቴክኒክና ሙያ ትምህርት ሥልጠና ውስጥ ሊሳተፉ የሚችሉበትን ሁኔታ ያመቻቻል ስልቶች ይቀይሳል፣ ያዘጋጃል፣
10. የክልሉ የቴክኒክና ሙያ ትምህርት ሥልጠና ካውንስል እንዲቋቋም ያደርጋል የካውንስሉን ሴክቴሪያትም ያደራጃል፣
11. የአቅም ግንባታ ፖሊሲን ያመነጫል፣ ዕቅድና በጀት ያዘጋጃል፣ ሲፈቀድም በስራ ላይ ያውላል፤
12. የክልሉን አቅም ግንባታ ፕሮግራሞችና ሥራዎችን በበላይነት ያስተባብራል፣ ይመራል ያስፈጽማል ይከታተላል፣

www.chilot.me

13. ለአቅም ግንባታ አስፈላጊ የሆኑ ተቋማት እንዲቋቋሙና እንዲጠናከሩ ያደርጋል፣
14. በቢሮዎችና በሌሎች መንግስት መስሪያ ቤቶችና አስፈላጊ ተቋማት ለሚካሄዱ የአቅም ግንባታ ሥራዎች አስፈላጊውን ድጋፍ ይሰጣል፣
15. የሴቶችን አቅም ለመገንባት የተለየ አትኩሮት ይሰጣል፣ እንዲሰጥም ክትትል ያደርጋል፣
16. በክልሉ የሰለጠነ የሰው ኃይል አስተዳደር አደረጃጀትና አሰራር ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችል ስትራቴጂና ስልት ይቀይሳል፣
17. በክልሉ በልማት ወደኋላ ለቀሩ ቀበሌዎችና አካባቢዎች የተለየ የአቅም ግንባታ ፕሮግራሞችን ይቀይሳል፣
18. ቢሮው በክልሉ መንግስት አስፈጻሚ አካላት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 2/1988 አንቀጽ 14 እና በሌሎች ሕጎች ትምህርትን በሚመለከት የተሰጡ ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፣
19. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 7 ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከቱትን አስፈጻሚ አካላት በበላይነት ይመራል ያስተባብራል፤
20. ሌሎች በክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት የሚሰጡትን ትምህርትንና አቅም ግንባታን ለማስፋፋትና ለማጠናከር የሚያስፈልጉ ተግባራትን ያከናውናል።

9. **የሕዝብ አደረጃጀት ባህልና ማኅበራዊ ጉዳይ ቢሮ**

ቢሮው የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. የተለያዩ የሕብረተሰብ ክፍሎች በሙያ በዕድሜና በሌሎች ሲቪክ ማህበራት ተደራጅተው መብትና ጥቅማቸውን በማስጠበቅ ለሀገሪቱ ልማትና እድገት አስተዋጽኦ የሚያደርጉበትን ሁኔታ ያመቻቻል ሲፈቀድም በሥራ ላይ ያውላል፤
2. ሴቶች ለመብታቸው እንዲታገሉና የጾታ እኩልነት እንዲረጋገጥ ያደራጃል፤
3. የህዝቡን የልማት ቡድኖች አደረጃጀት ይከታተላል፣ በተለይ አርሶ አደሩ በአደረጃጀቱ ተጠቃሚ መሆኑን ያረጋግጣል፤
4. የልማት ቡድኖች ያልተደራጁበት ና ያልተጠናከሩትን አካባቢዎች በመለየት ሕዝቡ በስፋት እንዲደራጅ ያበረታታል ያደራጃል ያጠናክራል፤
5. ሕዝቡ በመደራጀት ሊሳተፍባቸው የሚገባ የልማት መስኮችንና ሕዝቡን ለማደራጀት መከተል ስለሚገባው ስልቶች ያጠናል ተግባራዊ ያደርጋል፤
6. የሕዝብ አደረጃጀትና ተሳትፎን የሚመለከቱ መረጃዎችንና እስታስቲክስ ያሰባስባል፣ያጠናክራል ፣ለሚመለከተው አካል ያቀርባል፤
7. የሕዝቡን አደረጃጀትና ዲሞክራሲያዊ ተሳትፎ ለማጎልበት የሚረዱ ጹሁፎችን በማዘጋጀት ያሰራጫል፤
8. የተደራጁ ሕዝባዊ ማኀበራት እንዲጠናከሩና ራሳቸውን እንዲችሉ ሥልጠና የሚያገኙበትን ሁኔታ ያመቻቻል፤
9. በክልሉ የተደራጁ የሙያ የልማት እና ሕዝባዊ ማህበራት ያሉባቸውን ችግሮች ያጠናል ችግሮቹ መፍትሔ የሚያገኙበትን መንገድ ይቀይሳል፡
10. ሕዝባዊና የሙያ ማኀበራት በልማት ሥራዎች የሚሰማሩበትን ሁኔታ ያጠናል በልማት ሥራዎች ላይ እንዲሰማሩ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፡
11. በክልሉ የሚንቀሳቀሱ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ከሕዝባዊ ማኀበራት ጋር በቅንጅት መሥራት እንዲችሉ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፤
12. ወጣቶች ለክልሉ ልማትና ዲሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ የድርሻቸውን ለመወጣት እንዲችሉ በአካልና በአእምሮ የዳበሩ ኃላፊነት የሚሰማቸው በሥነ-ምግባር የታነጹ ወጣቶች ለማፍራት የሚቻልበትን ስልት ይቀይሳል በሥራ ላይ እንዲውል ያደረጋል፡
13. ወጣቶች ጤንነታቸው ተጠብቆ ከጎጂ ልምዶችና ከወንጀል ድርጊቶች ርቀው አምራች ዜጎች በመሆን እራሳቸውን ችለው ለኅብረተሰቡ ልማት ጠቃሚ ሊሆኑ የሚያስችላቸውን የሙያ፣የቴክኒክ፣የምክርና ሌሎች አገልግሎቶች ያገኙ ዘንድ እንዲመቻች ያደራጃል እንዲደራጁም ያግዛል፡
14. ወጣቱ ትውልድ የሥራ ፍቅርና የሀገር መውደድ ስሜት ኖሮት ለዚህም ራሱን እንዲያዘጋጅና ሁለ-ገብ ስብዕናውን ለማጠናከር የሚረዳ የሥነ-ዜጋ ትምህርት መሰጠቱን ያረጋግጣል፤
15. የወጣቱን የፈጠራና የሥነ-ጥበብ ችሎታ እየዳበረ እንዲሄድ ያበረታታል፣ የተለያዩ ውድድሮች እንዲዘጋጁና ወጣቶች እንዲሳተፉበትም ድጋፍ ያደርጋል የፈጠራ ውጤት ባለቤትነታቸው መከበሩንም ያረጋግጣል፡
16. ባህልና ስፖርትን በተመለከተ በክልሉ መንግስት አስፈጻሚ አካላት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 2/1988 እና ሌሎች ህጎች ለክልሉ ባህልና ስፖርት ቢሮ ተሰጥተው የነበሩት ሥልጣንና ተግባራት በዚህ አዋጅ ለህዝብ አደረጃጀት ባህልና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮ ተሰጥተዋል፤
17. ሠራተኛና ማኀበራዊ ጉዳይን በተመለከተ በክልሉ መንግስት አስፈጻሚ አካላት ማቋቋሚያ አዋጅ 2/1988 እና ሌሎች ሀጎች ለአደጋ መከላከል ሠራተኛና ማኀበራዊ ጉዳይ ቢሮ ተሰጥተው የነበሩት ሥልጣንና ተግባራት በዚህ አዋጅ ለህዝብ አደረጃጀት ባህልና ማኀበራዊ ጉዳይ ቢሮ ተሰጥቷል፤
18. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 7 ንዑስ አንቀጽ (2) የተመለከቱትን አስፈጻሚ አካላት በበላይነት ይመራል፤ያስተባብራል፤
19. ሌሎች በክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት የሚሰጡት የህዝብ አደረጃጀት ባህልና ማህበራዊ ጉዳዮችን ለማዳበርና ለማጠናከር የሚረዱ ተግባራትን ያከናውናል።

10. **የግብርናና ገጠር ልማት ቢሮ**

ቢሮው የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. የክልሉን የገጠር ልማት ስትራተጂና ፖሊሲ ያመነጫል፤ዕቀድናበጀት ያዘጋጃል፣ሲፈቀድም ሥራ ላይ እንዲውል ያድርጋል፣
2. በመንግስት የተነደፈውን በምግብ ሰብል ራስን የመቻልና የምግብ ዋስትናን የሚያረጋግጥ መርሀ-ግብር ሥራ ላይ ለማዋል የግብርና ልማትን እንዲስፋፋ ያደርጋል፣ የሰብልና የእንስሳት ሀብት ልማትን እንደየ ሥነ ምህዳሩ እንዲስፋፋ ያደርጋል፣
3. በገጠሩ ልማትን ለማፋጠን ከሚመለከተው አካል ጋር በመሆን ማዳበሪያ፡ምርጥ ዘር የተለያዩ ከግብርና ጋር የተያያዙ መድኃኒቶች የእርሻ መሳሪያዎችና ሌሎች አስፈላጊ የምርት ማሳደጊያ አቅርቦቶችና የብድር አገልግሎቶች ለአርሶ አደሩ ጊዜውን ጠብቆ እንዲቀርብ አስፈላጊውን ሁሉ ያደርጋል፣
4. ሴቶች የመሬት ባለይዞታነት መብታቸው እንዲረጋገጥና ከመሬቱ የሚገኘውን ምርትና ማናቸውንም ጥቅሞች መቆጣጠርና ማስተዳደር እንዲችሉ ሁኔታዎችን ያመቻቻል ያግዛል፣

www.chilot.me

38. በመሬት ምርታማነትና በተለያዩ አግሮ ኢኮሎጂዎች ባለው ልዩነት ላይ በመመስረት አማካይ የመሬት ይዞታን አጥንቶ ያቀርባል:ሲወሰንም ሥራ ላይ መዋሉን ያረጋግጣል:
39. በክልሉ ተጨባጭ ሁኔታ ላይ የተመሰረተ ጥናት በማካሄድ የአፈርና ውሃ ልማትና ጥበቃ ሥራ ያካሄዳል:
40. የዝናብ እጥረት ባለባቸው አካባቢዎች ውሃ በአፈር ውስጥ እንዲጠራቀም ያደርጋል የውሃ ማቆር ሥራ እንዲከናወን አስፈላጊውን እገዛ ያደርጋል:
41. የመንግስት ደን: ፓርክ: የዱር አራዊት መጠለያና የችግኞች መትከያና የአደን ቦታዎች ይከልላል: ይመዘግባል: ያስተዳድራል:
42. የደን ምርት መርሃ ግብር ያዘጋጃል ስራ ላይ ያውላል በህዝብና ባለሀብቶች መንግስታዊና መንግስታዊ ባልሆኑ ተቋማት ደን እንዲለማ ያበረታታል:የቴክኒክ ድጋፍ ይሰጣል:
43. የመጥፋት አደጋ ለተጋረጠባቸው የዕፅዋት ዘር የዱር እንስሳትና አእዋፋት ልዩ ትኩረት በመስጠት ይጠብቃል ያለማል:
44. በደንና ዱር-አራዊት ውጤቶች፣ በአደንና በዱር አራዊት እርባታ ላይ ለተሰማሩ ነጋዴዎች ፍቃድና ድጋፍ ይሰጣል:ስራቸውን ይቆጣጠራል:
45. መሬትን ያለአግባብ የተጠቀመ ወይም ለማይገባ አገልግሎት ያዋለና በደንና በዱርአራዊት ላይ ከህግ ውጪ ጉዳት ያደረሰ :ማናቸውንም ሰው ለህግ ያቀርባል ወይም ለህግ እንዲቀርብ ያደርጋል:
46. ከተፈጥሮ አካባቢ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ህይወት ያላቸውን የተፈጥሮ ሀብቶች ይጠብቃል ወይም እንዲጠበቁ ያደርጋል አጠቃቀማቸውን ይቆጣጠራል፤
47. የገጠር መሬትና የተፈጥሮ ሀብትን በክልሉ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታ መዝግቦ ይይዛል:
48. አጠቃላይ የክልሉን የመሬት አጠቃቀም ዕቅድ በማጥናት ያጠቃቀሙን ስልት ያወጣል አፈጻጸሙንም ይከታተላል:
49. በገጠር መሬት ላይ የሚነሱ አለመግባባቶችን የሚፈታ አካል ያደራጃል ለአፈጻጸሙም መመሪያ ይሰጣል:
50. የክልሉን አጠቃላይ የልማት ዕቅድ መሠረት በማድረግ የውኃ ሀብት ልማት ዕቅድ ያዘጋጃል:
51. በክልሉ የውኃ ሀብትን የተመለከቱ መረጃዎችን ይሰበስባል ያጠናቅራል:
52. በክልሉ የውኃ ሀብት ጥናትና ዲዛይን ያከናውናል:
53. በክልሉ የሚካሄዱ የውኃ ሀብት ፕሮጀክቶችን ያስፈጽማል:
54. የገጠሩ ኅብረተሰቡ በውኃ ሀብት ልማት ሥራ ላይ እንዲሳተፍ ያደራጃል: ያስተምራል: ለህብረተሰብ የቴክኒክ ድጋፍ ይሰጣል:
55. የመጠጥ ውኃ ኮንስትራክሽንና የመስኖ ልማት ስራዎችን ያካሂዳል:
56. የክልሉ ህዝብ በተመጣጠነ ዋጋ ጥራት ያለው ውኃ እንዲያገኝ የውኃ ታሪፍ ከማዕከላዊ መንግስት የውኃ ፖሊሲ በመነሳት ያወጣል:
57. የመጠጥ ውሃ አቅርቦት ማግኛ የሆኑ የጉድጓድ የወንዝ የከርሰ ምድር ጂኦሎጂካልና ሃይድሮሎጂካል መረጃዎችን ይሰበስባል ጥናት ያካሂዳል:
58. የመጠጥ ውኃ አቅርቦት ጥናትና ዲዛይን ያከናውናል፣
59. የኮንስትራክሽን ሥራዎች በዲዛይናቸው መሠረት መፈጸማቸውን ይቆጣጠራል:
60. ለምህንድስና ስራዎች ዝርዝር የሥራና የዋጋ ተመን ያዘጋጃል፣
61. የመስኖ ልማት ጥናትና ዲዛይን ያከናውናል፣
62. ከመስኖ ልማት ጋር የተያያዙ ፖሊሲዎች እስትራቴጂዎችና ህጎችን ያዘጋጃል ሲጸድቅም ሥራ ላይ ያውላል፣
63. የአነስተኛ መስኖዎች የዲዛይን ጥናት እንዲካሄድ ያደርጋል መካከለኛና ከፍተኛ ፕሮጀክቶች በሌሎች ተቋራጮች እንዲከናወኑ ያደርጋል፣
64. ግንባታቸው የተጠናቀቁ የመስና ግንባታዎችን ተጠቃሚዎች እንዲረከቡ ያመቻቻል ከተጠቃሚዎች ጋር ተገቢውን ስምምነት በመፈጸም ያስረክባል ከሚመለከታቸው በየደረጃው ከሚገኙ የመስተዳድር እና ሌሎች አካላት ጋር በመቀናጀት የመስኖዎች ደህንነት እንዲጠበቅ ያደርጋል ከተጠቃሚዎች አቅም በላይ ሆኖ ሲገኝ የጥገናና የድሳት ሥራ ያከናውናል፣
65. ከመስኖ ግንባታ ጋር የተያያዙ የአፈርና የውሃ ጥበቃ ጥናትና ዲዛይን ሥራ ያካሄዳል ለዚህም ተግባር አፈጻጸም ከመንግስትና ከግል ተቋማት ጋር ይተባበራል፣
66. የክልሉ ህብረተሰብ ስለ መስኖ አጠቃቀም ዘዴ ያለውን ግንዛቤ ከፍ ለማድረግ ያስተምራል ይቀሰቅሳል፣
67. የመስኖ ልማት ተጠቃሚዎች ከመስኖ ኤክስቴንሽን አገልግሎት የሚያገኙትን ጥቅም እንዲያሳድጉ ያደርጋል:ባህላዊ የመስኖ ስራዎችንም ያበረታታል፣
68. የመስኖ ተጠቃሚዎች በማህበር እንዲደራጁ ያደርጋል:ድጋፍና እገዛም ይሰጣል፣
69. ከሚመለከታቸው ክፍሎች ጋር በመተባበር ከውሃ ጋር ተያይዘው የሚመጡ ችግሮችን የውሃ መበከልና የመሳሰሉትን ይቆጣጠራል፣
70. በህግ ላይ በመመስረት በመስኖ ግንባታ ምክንያት በይዞታቸው ላይ ጉዳት ለደረሰባቸው አርሶ አደሮች ወይም ሌሎች ግለሰቦች ካሳ እንዲከፈል ያደርጋል፣
71. ሕብረተሰቡ ውሃን የመሰብሰብ የማቆርና ልማት ላይ የማዋል ልምድ እንዲያዳብር ያደረጋል:በጉዳዩ ላይ ከሚመለከታቸው መንግስታዊና መንግስታዊ ካልሆኑ አካላት ጋር በቅንጅት ይሰራል፣
72. ለሐረር ከተማ ውኃና ፍሳሽ አገልግሎት ባለሥልጣን የቴክኒክ ድጋፍ ይሰጣል::
73. የአካባቢ ጥበቃን በተመለከተ የሚወጡ ፖሊሲዎችንና ስልቶችን ከሚመለከታቸው አካላቶች ጋር በመሆን በስራ ላይ ያውላል:ያስተባብራል:ይቆጣጠራል: አካባቢን በሚበክሉ ነገሮችና አካላት ላይ አስፈላጊውን የማስተካከያ እርምጃ ይወስዳል::
74. ሌሎች በክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት የሚሰጡትን ተዛማጅ ተግባራት ያከናውናል::

## 11. <u>የፍትህና ፀጥታ ጉዳይ ቢሮ</u>

ቢሮው የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል:-

1. በክልሉ ውስጥ ሕግና ሥርዓት መከበሩንና የህብረተሰቡ ሰላምና ደህንነት መጠበቁን ይከታተላል ያረጋግጣል፤
2. በየደረጃው ባሉ የአስተዳደር እርከኖች የፍትህና ፀጥታ ሥራን ይከታተላል ያስተባብራል፤

www.chilot.me

3. ከአጎራባች ክልሎች ጋር በሚዋሰኑ አካባቢዎች የሚነሱ አለመግባባቶች በሰላማዊ መንገድ የሚፈታበትን ምቹ ሁኔታ ይፈጥራል፤
4. በአስተዳደር በህዝብ ደህንነትና በፀጥታ ሥራ ጉዳዮች አግባብነት ካለው የፌደራል መንግስትና የሌሎች ክልሎች አካላት ጋር ግንኙነት በማድረግ በቅንጅት ይሠራል፤
5. በአዋጅ ቁጥር 2/1988 አንቀጽ 18 እና ሌሎች ህጎች ለክልሉ ፍትህ ቢሮ ተሰጥተው የነበሩ ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፤
6. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 7 ንዑስ አንቀጽ (4) የተመለከቱትን አስፈጻሚ አካላት በበላይነት ይመራል ያስተባብራል:
7. ሌሎች በክልል መስተዳድር ምክር ቤት የሚሰጡትን የፍትህና አስተዳደር ሥራዎችን ለማጠናከር የሚረዱ ተግባራትን ያከናውናል::

## 12. ንግድ ኢንዱስትሪና ከተማ ልማት ቢሮ

1. በሐረሪ ህዝብ ክልል መንግስት አስፈጻሚ አካላትን ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 2/1988:-
   - ሀ/ በአንቀጽ 10 እና በሌሎች ህጎች ለክልሉ ኢንዱስትሪ ትራንስፖርት ንግድና ቱሪዝም ቢሮ:
   - ለ/ በአንቀጽ 9 እና በሌሎች ህጎች ለክልሉ ሥራና ከተማ ልማት ቢሮ እና
   - ሐ/ በአንቀጽ 11 እና በሌሎች ህጎች ለክልሉ ውሃ ሀብት ማዕድንና ኢነርጂ ቢሮ ተሰጥተው ከነበሩት ማዕድንና ኢነርጂን በተመለከተ ተሰጥተውት የነበሩት ሥልጣንና ተግባራት በዚህ አዋጅ ለክልሉ ንግድ ኢንዱስትሪና ከተማ ልማት ቢሮ ተሰጥቷል:
2. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 7 ንዑስ አንቀጽ (5) የተመለከቱትን አስፈጻሚ አካላት በበላይነት ይመራል ያስተባብራል::
3. በዚህ አንቀጽ ከንዑስ አንቀጽ (1) እና (2) የተጠቀሱት እንደተጠበቁ ሆኖ በተጨማሪነት
   - ሀ/ የተሽከርካሪዎች ዋጋ ይገምታል:
   - ለ/ የገጠር መንደሮች ለእድገት ከተማነት የሚበቁበትን ሥራዎች ይሰራል እንዲሁም:
   - ሐ/ የመንገድ ትራፊክ ደንብ መከበሩን ያረጋግጣል ደንብ ተላላፊዎችን ይቆጣጠራል: በህግ መሠረት ተገቢውን እርምጃ ይወስዳል ወይም እንዲወሰድ ያደርጋል:
   - መ/ ሌሎች ከክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት የሚሰጡትን የንግድ ኢንዱስትሪና ከተማ ልማት ሥራዎችን ለማስፋፋት የሚረዱ ተግባራትን ያከናውናል::

## 13. የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ

1. በሐረሪ ሕዝብ ክልል መንግስት አስፈጻሚ አካላትን ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 2/1988;
   - ሀ/ በአንቀጽ 12 እና በሌሎች ህጎች ለፕላንና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ ተሰጥተው የነበሩት ሥልጣንና ተግባራት:
   - ለ/ በአንቀጽ 13 እና በሌሎች ህጎች ለክልሉ ፋይናንስ ቢሮ ተሰጥተው የነበሩት ሥልጣንና ተግባራት ፡እና
   - ሐ/ በአንቀጽ 24 እና በሌሎች ህጎች ለክልሉ ስነ ሕዝብ ጽ/ቤት ተሰጥተው የነበሩት ሥልጣንና ተግባራት በዚህ አዋጅ መሠረት ለክልሉ ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ ተሰጥቷል:: በተጨማሪም
2. በክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት የሚሰጡትን የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ተግባራትን ለማጠናከር የሚረዱ ተግባራትን ያከናውናል::

## 14. የጤና ጥበቃ ቢሮ

1. በሐረሪ ሕዝብ ክልል መንግስት አስፈጻሚ አካላትን ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 2/1988 አንቀጽ 15 እና በሌሎች ህጎች ለጤና ቢሮ ተሰጥተው የነበሩ ከሕዝብ ጤና አጠባበቅ ሥራዎች ጋር የተያያዙ ሥልጣንና ተግባራት ለጤና ጥበቃ ቢሮ ተሰጥቷል::

## 15. የማስታወቂያና ሕዝብ ግንኙነት ቢሮ ሥልጣንና ተግባር:

ቢሮው የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል:-

1. የክልሉ መንግስትና ሕዝብ በኢኮኖሚ በፖለቲካና ማህበራዊ ኑሮ መስክ የሚያደርጉትን እንቅስቃሴ በመከታተል በተለያዩ መገናኛ ብዙሃን እንዲሰራጭ ያደርጋል፤
2. ክልላዊ ኢንፎርሜሽንና የሚዲያ ፍቃድ ይሰጣል የዘርፉን አገልግሎት ይከታተላል ይቆጣጠራል:
3. በፖሊሲና ወቅታዊ ጉዳዮች ላይ የመንግስት ቃል አቀባይ ሆኖ ይሰራል የክልሉን መንግስት ፖሊሲና አቋም የሚገልጽ የፕሬስ መግለጫዎችን እያዘጋጀ በሚዲያ ያሰራጫል መጽሔቶችን ጋዜጦችን ብሮሸሮችንና መሰል ሕትመቶችን ያሰራጫል:
4. በክልሉ መንግስት የተቋቋሙ መገናኛ ቡዙሃንን ያደራጃል:ያስፋፋል:የሰው ኃይል የአመራርና የአደረጃጀት ፖሊሲዎቻቸውን ይወስናል:ይመራል፤
5. የክልሉን መንግስታዊ ኢንፎርሜሽንና ኮሚዩኒኬሽን አገልግሎት ተቋም ያደራጃል ይመራል፤
6. በክልሉ የኢንፎርሜሽን ነፃነትና ተደራሽነት መብት እንዲከበር ያደርጋል፤
7. የክልሉን ሕዝብ ንቃተ ህግ እንዲዳብር በልማት ያለውም ተሳትፎ እንዲጨምር የሥራና ቁጠባ ባህል እንዲዳብር ያስተምራል: ያበረታታል፤
8. በህገ-መንግስቱ የተረጋገጡለትን መብቶች በመጠቀም ሕዝቡ በየሥልጣን እርከኑ ያሉትን የመንግስት አካላት በመቆጣጠር ተሳትፎውን እንዲያሳድግ ያበረታታል፤
9. በተለያዩ የመንግስት የሥልጣን መዋቅሮች ውስጥ የሚታዩትን ጥንካሬዎችና ድክመቶች ለህብረተሰቡ ይገልጻል:
10. የሀገር ውስጥና የውጭ መገናኛ ቡዙሃንን በመከታተል መልስ ሊሰጣቸው ለሚገባ ተገቢውን ምላሽ ይሰጣል፤
11. የክልሉን መንግስትና ሕዝብ እንቅስቃሴ በተመለከተ ኤግዚቢሽኖችንና ፕሬስ ኮንፈረንሶችን ያዘጋጃል፤
12. በሕዝብ መገናኛ ቡዙሃን በሴቶች አካልና አዕምሮ ላይ ጉዳት የሚያስከትሉ ጎጂ ልማዳዊ ባህሎች እንዲወገዱ ሴቶች በፖለቲካና ማህበራዊ ጉዳዮች ሊኖራቸው የሚገባውን ተሳትፎና እንዲሁም የፆታ እኩልነት በልማት ውስጥ የሚኖረውን ሚና በማስጨበጥ ላይ ትኩረት በማድረግ ይሰራል፤
13. ማስታወቂያና ፕሬስ ሕዝብና መንግስት በማገናኘት ህብረተሰቡን በማስተማር በመቀስቀስ ረገድ የድርሻውን ለመወጣት የሚያስችሉ ሌሎች በክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት የሚሰጡ ተግባራትን ያከናውናል::

www.chilot.me

16. **የሐረር ከተማ ማዘጋጃ ቤት**
በሐረሪ ህዝብ ክልል መንግስት የሐረር ከተማ ማዘጋጃ ቤት በከተማው ማዘጋጃ ቤት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 7/1990 አንቀጽ 6 እና በሌሎች ህጎች የተሰጡት ከማዘጋጃ ቤት አገልግሎት ጋር ተያያዥ የሆኑ ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል።

17. **ሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን**
የክልሉ ሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን በክልሉ መንግስት አስፈጻሚ አካላትን ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 2/1988፡ በመንግስት ሠራተኞች አዋጅ ቁጥር 34/1996 እና በሌሎች አግባብነት ባላቸው ህጎች የተሰጡት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል።

18. **የፖሊስ ኮሚሽን**
የፖሊስ ኮሚሽን በሐረሪ ህዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የፖሊስ ኮሚሽንን ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 38/1996 አንቀጽ 6 እና በሌሎች ህጎች ለኮሚሽኑ የተሰጡት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል።

19. **ማረሚያ ኮሚሽን**
የማረሚያ ኮሚሽን በሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የማረሚያ ኮሚሽንን ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 39/1996 አንቀጽ 6 እና በሌሎች ህጎች ለክልሉ ማረሚያ ኮሚሽን የተሰጡ ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል።

20. **የሴቶች ጉዳይ ጽህፈት ቤት**
የክልሉ ሴቶች ጉዳይ ጽህፈት ቤት በሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት አስፈጻሚ አካላትን ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 2/1988 አንቀጽ 22 እና በሌሎች ህጎች የተሰጡት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል።

21. **የኅብረት ሥራ ማኅበራት ማደራጃና ማስፋፊያ ጽ/ቤት**
የኅብረት ሥራ ማኅበራት ማደራጃና ማስፋፊያ ጽህፈት ቤት በክልሉ መንግስት የኅብረት ሥራ ማኅበራት ማደራጃና ማስፋፊያ ጽህፈት ቤትን ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 35/1996 አንቀጽ 6 እና በሌሎች ህጎች የተሰጡት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል።

22. **አደጋ መከላከል የምግብ ዋስትና ጽህፈት ቤት**
ጽህፈት ቤቱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡
1. የእርዳታና የምግብ ዋስትና ፕሮግራሞችን በሥራ ላይ ለማዋል የሚያስፈልጉ የልማት ፕሮጀክት ዝግጅቶችንና አፈፃፀሞችን ያስተባብራል፡
2. ለችግር ጊዜ አቅርቦት የሚውል የመጠባበቂያ እህል አማካይ በሆኑ ቦታዎች ያከማቻል ያስተዳድራል በሥርዓት ጠብቆ ለችግር ጊዜ እንዲውል ያደርጋል ይከታተላል፡
3. በክልሉ የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ ጉዳዩ የሚመለከታቸው የተለያዩ የመንግስት አስፈጻሚ አካላት የረጅም መካከለኛና አጭር ጊዜ ዕቅድ እንዲያዘጋጁ ያደርጋል አስፈላጊ ሲሆን ድጋፍ ይሰጣል አፈፃፀሙን ይከታተላል፡
4. በክልሉ ኢኮኖሚያዊ እድገት ለማምጣትና ለሕዝቡ የምግብ ዋስትና ለማረጋገጥ በፈቃደኝነት ላይ የተመሰረተ የህዝብ ማስፈርን ጨምሮ መንግስት የሚያወጣቸውን ፕሮግራሞች ተግባራዊ ያደርጋል፡
5. ውሃን የማሰባሰብና አቁሮ የመጠቀም ሥራዎች እንዲለመዱና በተለይም በድርቅ በተደጋጋሚ በሚጠቁ አካባቢዎች በስፋት እንዲካሄዱ ያደርጋል፡
6. የምግብ ዋስትና ፕሮግራም ፕሮጀክቶች ማስፈጸሚያ ፈንድ ወይም ሌላ የሀብት ምንጭ ያፈላልጋል በመንግስትና መንግስታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች ወይም ሕዝባዊ ማህበራት አማካኝነት በሥራ ላይ እንዲውል ያደርጋል ይቆጣጠራል፤
7. በክልሉ የሚንቀሳቀሱ መንግስታዊ ያልሆኑ የልማትና የዕርዳታ ድርጅቶችን ይቆጣጠራል ስምምነት ያደርጋል ፤ ከሚመለከተው አካል ጋር አስፈላጊውን እርምጃ ይወስዳል፤
8. ቅድመ አደጋ መከላከል ሥራዎችን ያከናውናል፤
9. በክልሉ አስፈጻሚ አካላትን ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 2/1988 አንቀጽ 16 ለአደጋ መከላከል ሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮ ተሰጥተው ከነበሩትና በዚህ አዋጅ አንቀጽ 9 ንዑስ አንቀጽ 17 ከተዘረዘሩት ውጭ ያሉት ሥልጣንና ተግባራት በዚህ አዋጅ መሠረት ለክልሉ አደጋ መከላከል ምግብ ዋስትና ጽ/ቤት ተላልፏል፤

23. **የሚሊሻ ጉዳይ ጽህፈት ቤት**
የሚሊሻ ጉዳይ ጽህፈት ቤት በሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የሚሊሻያ ጉዳይ ጽህፈት ቤትን ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 27/1993 አንቀጽ 8 እና በሌሎች ህጎች ለሚሊሻ ጉዳይ ጽ/ቤት የተሰጡት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል።

24. **የጥቃቅንና አነስተኛ ንግድ ሥራዎች ማስፋፊያ ጽ/ቤት**
ጽህፈት ቤቱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፦
1. በክልሉ ውስጥ አነስተኛና ጥቃቅን የንግድ ተቋማት እንዲስፋፉ ያደርጋል፤
2. በክልሉ ውስጥ ከመንግስታዊና መንግስታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች ጋር ግንኙነት በመፍጠር የጥቃቅንና አነስተኛ ንግድ ሥራ ማሕበራት ድጋፍ እንዲያገኙ ሁኔታዎችን ያመቻቻል። በተለይም የማምረቻና የመሸጫ ቦታዎች፡ የፋይናንስና የብድር አገልግሎቶች ፤ የጥሬ ዕቃና የማምረቻ መሣሪያዎች እንዲሁም የመሠረተ ልማት አውታሮች የሚገኙበትን ሁኔታ ያመቻቻል፡
3. ጥቃቅንና አነስተኛ ንግድ ሥራዎች ማሰልጠኛ ማዕከል እንዲቋቋም ሁኔታዎችን ያመቻቻል፡ በክልሉ ውስጥ በጥቃቅንና አነስተኛ የንግድ ሥራዎች ለተሰማሩ የሕብረተሰብ ክፍሉች ሥልጠናዎች እንዲዘጋጅ ያድርጋል፡ያስተባብራል፤
4. በክልሉ ውስጥ የሚገኙትን ሥራ አጥ የሆኑ ወጣቶችና ሴቶች አምራች ዜጋ ሊያደርጉ የሚችሉ ጥቃቅንና አነስተኛ የንግድ ሥራ ፕሮጀክቶች እንዲጠኑ ያደርጋል፤ተግባራዊ መሆናቸውንና ውጤት ማስገኘታቸው ይከታተላል፤
5. መረጃና የምክር አገልግሎት ለተጠቃሚዎች የሚሰጥበትን ሥርዓት ይዘረጋል፤
6. ጥቃቅንና አነስተኛ ንግድ ሥራዎችን ለማስፋፋት የሚረዱ ሌሎች ከበላይ አካላት የሚሰጡ ተግባራትን ያከናውናል።

25. **የሥራ አመራር ኢንስቲትዩት**
የክልሉ የሥራ አመራር ኢንስቲትዩት በክልሉ መንግስት የሥራ አመራር ኢንስቲትዩት ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 20/1991 አንቀጽ 5 እና በሌሎች ህጎች የተሰጡት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል።

26. **የመንገድ ሥራ ባለሥልጣን**
ባለሥልጣኑ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፦

www.chilot.me

1. የክልሉ መንገድ ኔት ዎርክንና የመንገድ ሥራን እንዲሁም የመንገዶችን አጠባበቅና አጠቃቀም በተመለከተ የፖሊሲ ሀሳቦችና ሕጎችን ያመነጫል፤
2. አግባብነት ካለው አካል ጋር በመተባበር የመንገዶችን ደረጃ እንዲወጣ ያደርጋል ሲፈቀድም ይተገብራል፤
3. የመንገዶችን የአገር አቀፍ እስታንዳርድ ከክልሉ ተጨባጭ ሁኔታ ጋር በማዛመድ ደረጃዎችን ይከታተላል ይተገብራል፤
4. የክልሉ መንገዶች ሥራና ተያያዥ ሥራዎችን በተመለከተ የረጅም፣ የመካከለኛና የአጭር ጊዜ ዕቅዶችንና ፕሮግራሞችን ያዘጋጃል ሲፈቀድም ይተገብራል፤
5. የክልሉ መንገዶችን ፊዚቢሊቲ ጥናት ያካሄዳል እንዲካሄድ ያደርጋል ይተገብራል፤
6. የክልሉ መንገዶች ሥራ ዲዛይን ያዘጋጃል ወይም በብቁ አማካሪዎች አማካኝነት እንዲያዘጋጁ ያደርጋል፤
7. መንገዶችን በራስ ሀይል ይሰራል ወይም በራስ ተቋራጮች አማካኝነት እንዲሰሩ ያደረጋል፤
8. በሌላ አካል ለሚሰሩ መንገዶች አማካሪዎች የሥራ ተቋራጮች የሚመረጡበትን መስፈርቶች ይወስናል፤
9. የሥራና የአማካሪነት አገልግሎት ውሎችን ያዘጋጃል እንዲዘጋጁ ያደርጋል ይመረምራል ያዋውላል፡ ሥራዎችን በተገባው ውል መሠረት መከናወናቸውን ለማረጋገጥ የሚያስችል ስልት እንዲኖር ያደርጋል፡ በበላይነት ይቆጣጠራል፤
10. የክልሉን መንገዶች ደህንነት ለመጠበቅ የሚረዱ ማናቸውንም ተግባራት ያቅዳል፡ያጠናል ፡ሲፈቀድም ይተገብራል፡
11. አግባብ ካላቸው መስተዳድር አካላት ጋር በመተባበር መንገዶች ለታለመላቸው ዓላማ መዋላቸውን ይቆጣጠራል፤
12. የክልሉን መንገዶች በሚመለከት የትራፊክ ምልክቶች ዲዛይን ይሰራል፡ ወይም ያደራጃል፡አግባብ ካላቸው የመንግስት መስሪያ ቤቶች የትራፊክ መረጃዎችን በመሰብሰብ በመንገዶች ላይ የትራፊክ መልከቶችን ያደርጋል፤ተከታትለው እንዲያስፈጽሙ ለሚመለከታቸው መሥሪያ ቤቶች ያሳውቃል፤
13. የክልሉን የመንገዶች ወይም የአደባባዮችን አቅጣጫ ጠቋሚ ምልክቶች ይተክላል ይንከባከባል፤
14. ለህብረተሰቡ በቡድን ፡ በግል ወይም በመንግስታዊና መንግስታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች አማካኝነት ለሚሰሩ መንገዶች በእስታንዳርዱ መሠረት እንዲሰሩ ፍቃድ ይሰጣል ይቆጣጠራል እንደአስፈላጊነቱ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት ተገቢውን የቴክኒክ እና የማቴሪያል ድጋፍ ይሰጣል፤
15. በክልሉ መንገዶች የሚጠቀሙትን ተሽከርካሪዎች ክብደት፡ ዓይነትና የፍጥነቱ ወሰን ይወስናል፤
16. በክልሉ መንገድን በተወሰነ ጊዜ ለመዝጋት ለመቆፈር የመሠረተ ልማት አውታር መንገድ ላይ ለመዘርጋት ወይም መንገዶችን ከታለመላቸው ዓላማ ውጪ ለመጠቀም ለሚቀርቡ ጥያቄዎች ፍቃድ ይሰጣል፤
17. ለተለያዩ የክልሉ መንገድ ተጠቃሚዎች የሚውሉ መንገዶችን ለይቶ ይወስናል ምልክቶችን ይተክላል፡
18. በክልሉ የመንገድ መብራቶች እንዲተከሉ እና እንዲጠበቁ ያደርጋል፤
19. ለእግረኛ መተላለፊያ የሚያስፈልገውን የመሬት ስፋትና የእግረኛ ደረጃዎችን ይወስናል የእግረኛ መተላለፊያ መንገዶችን ይሰራል እንዲሰሩ ያደርጋል ይንከባከባል፤
20. በክልሉ መንገዶች ዳርና ዳር ወይም መካከል የሚተከሉ ዛፎችን አይነትና መጠን ይወስናል አፈጻጸሙን ይቆጣጠራል፡
21. በክልሉ ውስጥ ለሚሰራቸው መንገዶች ድጋፍ ለማግኘት በመንገዱ ተጠቃሚ የሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎችን ያስተባብራል ያሳትፋል፡
22. በመንገዶች ላይ የመኪና ማቆሚያ ቦታዎችን ለይቶ ይወስናል፡
23. በክልሉ የሚከናወኑ የጎርፍ መከላከልና ማስወገድ ሥራዎች በመንገዶች ላይ ጉዳት የማያደርሱ መሆናቸውን ያረጋግጣል፡ ይቆጣጠራል፡
24. መንገዶች አግባብ ባለው አካል እንዲሰየሙ ሀሳብ ያቀርባል ሲፈቀድም ይተገብራል፤
25. ለመንገድ ሥራ የሚውሉ ማቴሪያሎችን በተመለከተ ጥናት ያካሂዳል የተገኙ ጠቃሚ ውጤቶችንም በሥራ ላይ ያውላል፤
26. ባለስልጣኑ የሚያስፈልገውን የሰው ኃይል እንዲሰለጥን ያደርጋል፡
27. ለክልሉ መንገዶች ሥራ የሚያስፈልጉ ማቴሪያሎችን ያመርታል ይጠቀማል እንደአስፈላጊነቱም ይሸጣል፤
28. ለመንገድ ሥራ የሚውሉ ማቴሪያሎችን ማምረቻና የመገልገያ መሣሪያዎች መጠገኛ ተቋማትን ያቋቁማል፡
29. ለሚሰጣቸው ማናቸውም አገልግሎቶች ተገቢውን ክፍያ ይጠይቃል ሌሎች ክፍያዎችን ይሰበስባል፡
30. ውል ይዋዋላል የሚንቀሳቀስና የማይንቀሳቀስ ንብረት ይገዛል ይሸጣል ባለቤት ይሆናል ይከራያል ያከራያል እርዳታ /ስጦታ ይቀበላል ወዘተ... በስሙ ክስ ይከሳል ይከሰሳል፤
31. ሌሎች አግባብነት ካላቸው የበላይ አካላት የሚሰጡ ተዛማጅ ተግባራት ያከናውናል።

## ምዕራፍ አራት
## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### 27. ስለ ሌሎች አስፈጻሚ አካላት

1. በዚህ አዋጅ ውስጥ ሥልጣንና ኃላፊነታቸው ያልተገለጹት የክልሉ ኢች አይ ቪ/ኤድስ/ መከላከያና መቆጣጠሪያ ምክር ቤት ሴክሬተሪያት ጽህፈት ቤት፡ የሐረር ከተማ ውሃና ፍሳሽ አገልግሎት ባለሥልጣን ፡ የጀጎል ቅርስ ተንከባካቢ ባለአደራ ጽ/ቤት፡ የኢንቨስትመንት ጽ/ቤት እና ሌሎች የክልሉ አስፈጻሚ አካላትና ተቋማት በተቋቋሙበት ህግ በተደነገገው መሠረት ይቀጥላሉ፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ስለተገለጹት ተጠሪነትን የሚመለከቱ ጉዳዮች የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት /ካቢኔ/ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናሉ።

### 28. በየደረጃው ስለሚቋቋሙ አስፈጻሚ አካላት

1. በዚህ አዋጅ የተመለከቱት ቢሮችና ሌሎች መሥሪያ ቤቶች እንደስራቸው አይነትና ስፋት በቀበሌው ወይም ከሁለት በላይ የሆኑ ቀበሌዎችን በማማከል ቅርንጫፍ መስሪያ ቤት ሊኖራቸው ይችላል።
2. በየትኛውም ደረጃ የሚገኝ ቅርንጫፍ መስሪያ ቤት የተሰጠውን ስልጣንና ተግባር በዋናነት በክልል ደረጃ ለዋናው መስሪያ ቤት የተሰጠውን ስልጣንና ተግባር ሥራ ላይ ማዋል ይሆናል፤
3. ቅርንጫፍ መስሪያ ቤቶች የተሰጣቸውን ስልጣንና ተግባር አፈጻጸም በተመለከተ ተጠሪነታቸው በየደረጃው ለሚገኝ አስተዳደር ምክር ቤትና ለበላይ መስሪያ ቤቱ ነው።

www.chilot.me

## 29. መብትና ግዴታን ስለማስተላለፍ

1. ከዚህ አዋጅ በፊት ለየብቻ የነበሩና በዚህ አዋጅ እንዲዋሀዱ የተደረጉት ቢሮዎች ወይም መሥሪያ ቤቶች መብትና ግዴታቸውም በዚህ አዋጅ መሠረት በእነርሱ ውህደት ወደተመሠረተው አዲሱ መሥሪያ ቤት ተላልፏል፤
2. ቀድሞ በአንድ ላይ የነበሩና በዚህ አዋጅ እንዲለያዩ የተደረጉ የአስፈጻሚ መስሪያ ቤቶች በዚህ አዋጅ ከተሰጣቸው ስልጣንና ተግባር ጋር ተያያዥነት ያላቸውን መለያየት የሚቻል ከሆነ በዚህ አዋጅ ስልጣንና ተግባራቸው ወደ ተላለፈበት መስሪያ ቤት ተላልፏል፤
3. በዚህ አዋጅ ከመለየታቸው በፊት የጋራ መብትና ግዴታ እያላቸው በመለያየታቸው ምክንያት መብትና ግዴታን ለይቶ ወደ አንዱ አካል ማስተላለፍ አስቸጋሪ ሆኖ ሲገኝ ጉዳዩ ለክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት /ካቢኔ/ ቀርቦ የሚወሰን ይሆናል።

## 30. የተሻሩ ህጎች

1. በዚህ አዋጅ መሠረት ተግባርና ኃላፊነታቸው እንዲቀጥል የተደረጉ አስፈጻሚ አካላት ስልጣንና ተግባራት እንደተጠበቀ ሆኖ ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረኑ የክልሉ መንግስት አስፈጻሚ አካላት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 2/1988 ድንጋጌዎች እና የአዋጅ ቁጥር 27/1993 አንቀጽ 7 በዚህ አዋጅ ተሽሯል፤
2. ሌሎች የክልሉ ሴክተር መስሪያ ቤቶች ማቋቋሚያ አዋጆች ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረኑ ከሆነ በዚህ አዋጅ ውስጥ ለተደነገጉት ጉዳዮች ተፈጻሚነት አይኖራቸውም።

## 31. የመሸጋገሪያ ድንጋጌዎች

1. በዚህ አዋጅ መሠረት አስፈላጊ መዋቅር ተዘርግቶ ሥራ ላይ እስከሚውል ድረስ በሥራ ላይ ያሉ ደንቦችና መመሪያዎች ለስድስት ወራት ጊዜ ብቻ ተፈጻሚነታቸው ይቀጥላል፤
2. ይህ አዋጅ ከመውጣቱ በፊት የተጀመሩት ሥራዎች በዚህ አዋጅ መሠረት በሚመለከተው አካል እንደተጀመሩ ተቀጥረው አፈጻጸማቸው ይቀጥላል።

## 32. ደንብና መመሪያ

1. በዚህ አዋጅ የተቋቋሙትን ቢሮዎችና መስሪያ ቤቶች ስልጣንና ተግባር በሥራ ላይ የሚያውሉ ቦርዶች ኤጀንሲዎች ባለስልጣን መስሪያ ቤቶችንና ሌሎች ተቋማትን የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት /ካቢኔ/ አጥንቶ በደንብ እንዲያቋቁም በዚህ አዋጅ ስልጣን ተሰጥቶታል፤
2. ይህን አዋጅ በሥራ ላይ ለማዋል የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ደንብ ወይም መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡
3. በዚህ አዋጅ የተቋቋመ ማንኛውም ቢሮ ወይም ሌላ መሥሪያ ቤት በዚህ አዋጅ የተሰጡትን ስልጣንና ተግባራት ሥራ ላይ ለማዋል የሥራ መመሪያ ሊያወጣ ይችላል።

## 32. የመተባበር ግዴታ

ጉዳዩ የሚመለከተው ማንኛውም አካል በዚህ አዋጅ የተመለከቱትን ድንጋጌዎች በሥራ ላይ ለማዋል የመተባበር ግዴታ አለበት።

## 33. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ ከመስከረም 30/1997 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል።

ሐረር መስከረም 30/1997 ዓ.ም
ፋአድ ኢብራሂም
የሐረሪ ህዝብ ክልል መንግስት
ርዕሰ መስተዳድር

www.chilot.me

የሐረሪ ሕዝብ ክልላዊ መንግስት

# ሐ ረ ር ነ ጋ ሪ ጋ ዜ ጣ
# HARAR NEGARI GAZETA

OF THE HARARI PEOPLE REGIONAL STATE

9ኛ ዓመት ቁጥር 7
9th year No 7

ሐረር መጋቢት 9 ቀን 1997 ዓ.ም
HARAR March 18th 2005

| ያንዱ ዋጋ ብር 1<br>Unit Price Br. 1 | በሐረሪ ሕዝብ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ | የፖስታ ሣጥን ቁጥር 272<br>P.O.Box |
|---|---|---|

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር 50/1997 ዓ.ም

የታሪካዊ የጁገል ተንቀሳቃሽና የማይንቀሳቀስ ቅርስ ባለአደራ ጽህፈት ቤት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 21/1992 ማሻሻያ አዋጅ——————ገጽ 408

## አዋጅ ቁጥር 50/1997 በሐረሪ ህዝብ ክልላዊ መንግስት የታሪካዊ ጁገል ተንቀሳቃሽና የማይንቀሳቀስ ቅርስ ተንከባካቢ ባለአደራ ጽህፈት ቤት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 21/1992ን ለማሻሻያ የወጣ አዋጅ

ታሪካዊው የጁገል ቅርስ በአለም አቀፍ ደረጃ ልዩ ትኩረት የተሰጠውና በዓለም ቅርስ መዝገብ ተመዝግቦ ተጨባጭ ጥበቃና እንክብካቤ እንዲያገኝ የጁገል ዙሪያ ጥብቅ መሬት (Buffer zone) በስሩ መልኩ ግልጽ ተደርጎ የሕግ ከለላ እንዲያገኝ ማድረግ በማስፈለጉ፡-

የሐረሪ ብሔራዊ ጉባኤ በሐረሪ ህዝብ ክልላዊ መንግስት ሕገ-መንግስት አንቀጽ 59 ንዑስ አንቀጽ (1) በተሰጠው ስልጣን መሠረት ከዚህ የሚከተለው ታውጇል፡፡

### 1. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "የታሪካዊ ጁገል ተንቀሳቃሽና የማይንቀሳቀስ ቅርስ ተንከባካቢ ባለአደራ ጽህፈት ቤት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 21/1992 ማሻሻያ አዋጅ ቁጥር 50/1997" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### 2. ማሻሻያ

የክልሉ መንግስት የታሪካዊ ጁገል ተንቀሳቃሽ ቅርስ ተንከባካቢ ባለአደራ ጽህፈት ቤት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 21/1992 እንደሚከተለው ተሻሽሏል፡፡

የአዋጁ አንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ /1/ ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ እንደ ተተክቷል፡፡

"/1/ " የጁገል ክፍለ ከተማ " ማለት በሐረሪ ህዝብ ክልላዊ መንግስት ርዕሰ ከተማ 3342 ሜትር ርዝማኔ ባለው አጥር ተከልሎ በ48 ሄክታር የመሬት ስፋት የተቀረቀረችው ጥንታዊ የሐረር ከተማ አምብርት ክፍለ ከተማ እና ከጎንቡ ውጭ በሰሜን መቅረዕ ወንዝን ተከትሎ በሰሜን ምስራቅ ሸንኮር ወንዝን ይዞ እስከ አው-አባድር ወንዝ፣ በምሥራቅ በአው-አባድር እስከ ማዊር ድረስ ሲሆን በምዕራብ በኩል ደግሞ ከዱከ በር አካባቢ ሁለቱን የመስተዳድር እና ማዘጋጃ ቤት ሕንጻዎችን አካተ ወደ አስማዕዲን በሪ በመውረድ የአው-መሸሐድ /አይኮካ ዋሻ/ መንገድን ተከትሎ የጅጅጋ መንገድን በመያዝ እና በመታጠፍ ከማዊር ወንዝ ጋር የሚገናኝ ቦታ ድረስ ያለውን ጥብቅ መሬት ያጠቃልላል፡፡

### 3. አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በሐረር ነጋሪ ጋዜጣ ከታተመበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

ሐረር መጋቢት 9 ቀን 1997ዓ.ም
ፉአድ ኢብራሂም
የሐረሪ ሕዝብ ክልላዊ መንግስት
ፕሬዝዳንት

www.chilot.me

የሐረሪ ሕዝብ ክልላዊ መንግስት

# ሐ ረ ር ነ ጋ ሪ ጋ ዜ ጣ
# HARAR NEGARI GAZETA

OF THE HARARI PEOPLE REGIONAL STATE

10ኛ ዓመት ቁጥር 2
10th year No 2

ሐረር መስከረም 23 ቀን 1998 ዓ.ም
HARAR October 3/ 2005

| ያንዱ ዋጋ ብር<br>Unit Price Br. | በሐረሪ ሕዝብ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ | የፖስታ ሣጥን ቁጥር 272<br>P.O.Box |
|---|---|---|

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር 52/ 1998ዓ.ም
የሐረሪ ሕዝብ ክልላዊ መንግስት ህገ-መንግስትን ለማሻሻል የወጣ አዋጅ——————————ገጽ 421

## የሐረሪ ህዝብ ክልላዊ መንግስት ህገ-መንግሥት ለማሻሻል የወጣ አዋጅ

በሐረሪ ህዝብ ክልላዊ መንግሥት ህገ-መንግሥት መሠረት የክልሉን ማኀበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግር ለመፍታት እየተደረገ ያለዉን ጥረት የማያግዙ የህገ-መንግሥት ደንጋጌዎችን ማሻሻል ተገቢ ሆኖ በመገኘቱ፤

በሐረሪ ህዝብ ክልል የተሻሻለው ህገ- መንግሥት አንቀጽ 51/ (2) (ሰ) መሠረት ይህ ህገ-መንግሥታዊ ማሻሻያ ታውጇል፡፡

1. **አጭር ርዕስ፡-**

ይህ አዋጅ የሐረሪ ህዝብ ክልላዊ መንግሥት ህገ-መንግሥት ሁለተኛ ማሻሻያ አዋጅ ቁጥር 52/1998 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ማሻሻያ**

የህገ-መንግሥቱ አንቀጽ 57 ንዑስ አንቀጽ (1) ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (1) ተተክቷል፡፡

" (1) ከሁለቱ ጉባዔዎች ከያንዳንዳቸው ከግማሽ በላይ ከተገኙ ምልዓተ ጉባኤ ይሆናል፡፡ "

3. **አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ አዋጅ ከመስከረም 23 ቀን 1998 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

ሐረር መስከረም 23/1998ዓ.ም

ከቡር ሙራድ አብዱልሃዲ

ፕሬዝዳንት

www.chilot.me

የሐረሪ ህዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት

# ሐረር ነጋሪ ጋዜጣ

# HARAR NEGARI GAZETA

OF THE HARARI PEOPLE NATIONAL REGIONAL STATE

10ኛ ዓመት ቁጥር 4
10th year No 4

ሐረር የካቲት 30/1998
Harar march 9/2006

| ያንዱ ዋጋ ብር<br>Unit Price<br>Br.7 | በሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት<br>ጠባቂነት የወጣ | የፖስታ ሣጥን ቁጥር 272<br>P.O.Box 272 |
| --- | --- | --- |

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር53/1998 ዓ:ም
የሐረሪ ሕዝብ ክልል ምክር ቤት የአሠራር እና የአባላት ሥነ-ምግባር አዋጅ ገጽ422

## አዋጅ ቁጥር 53/1998

## የሐረሪ ሕዝብ ክልል ም/ቤ የአሠራር እና የአባላት ሥነ-ምግባርን ለመወሰን የወጣ አዋጅ

የሐረሪ ሕዝብ ክልል ምክር ቤት በህገ መንግሥቱ መሠረት የክልሉ መንግሥት ከፍተኛው የስልጣን አካልና በክልሉ መንግሥት ሥልጣን ክልል ዉስጥ በሆኑ ጉዳዮች ሁሉ ህግ የማውጣት ሥልጣን ያለው በመሆኑ::

ይህንኑ ህግ የማውጣት ሥልጣኑን መሠረት አድረጎ የክልሉ ምክር ቤት በህገ መንግሥቱ የተሰጡትን ሥልጣንና ተግባራት እንዲሁም በህዝቡ የተጣሉበትን ሃላፊነት በበለጠ ለመወጣት ይቻለው ዘንድ ከህገ መንግሥቱና ከክልሉ አዲሱ የአስፈጻሚ አካላት አደረጃጀት ጋር የተገናዘበና ብቃት ያለው ዉስጣዊ አደረጃጀት፤የኮሚቴ

ዎች አደረጃጀት የተሚላ የስብሰባና የህግ አወጣጥ ሥነ ሥርአት እንዲሁም የአሠራር ስልትና ዝርዝር ሥርአቶች መዘርጋት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ::

የምክር ቤቱን አባላት መብትና ግዴታዎች እንዲሁም የአባላቱ ስነ-ምግባር ከህገ-መንግሥቱና ከፌደራል መንግሥቱ የፓርላማ አሠራር መርሆዎች ጋር . የተጣጣመሆና ዲሞክራሲያዊ ባህሪያትን የሚያጎለብትና ለሕዝብ ግልጽ የሆነ አሠራር መከተል ተገቢ በመሆኑ፤

የሐረሪ ሕዝብ ክልል ምክር ቤት ተሻሽሎ በወጣው የክልሉ ህገ-መንግሥት አንቀጽ 51(2)(ሀ)እና 57(3)በተሰጠው ስልጣን መሠረት የሚከተለዉን አውጇል::

www.chilot.me

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

### 1/ አጭር ርዕስ:-

ይህ አዋጅ «የሐረሪ ሕዝብ ክልል ምክር ቤት የአሠራር እና የአባላት ሥነምግባር መወሰኛ አዋጅ ቁጥር53 /1998» ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል::

### 2/ ትርጓሜ:-

በዚህ አዋጅ ሌላ ትርጉም ካልተሰጠው በስተቀር::

1.«ህገ መንግሥት»ማለት መስከረም 30 ቀን 1997 ዓ.ም ተሸሽሎ የወጣው የሐረሪ ህዝብ ክልል ህገ መንግሥት ነው::

2. «ምክር ቤት» ማለት በሐረሪ ክልል ህገ መንግሥት አንቀጽ 48 እና 49 በተደነገገው መሠረት የተቋቋመ የሐረሪ ክልል ምክር ቤት ነው::

3.« ኮሚቴ» ማለት አንድን ጉዳይ ለማከናወን እንደሁኔታው በም/ቤቱ የሚቋቋም ቁጥራቸው የተወሰነ አካላትን የሚያካትት አካል ነው::

4..« ቋሚ ኮሚቴ» ማለት በዚህ አዋጅ በተሰጠው ሥልጣንና ተግባር ዙሪያ የምክር ቤቱን ተግባር ለማቀላጠፍ ሲባል በምክር ቤቱ የሚቋቋም አካል ነው::

5.« ጊዛዊ ኮሚቴ» ማለት በምክር ቤቱ አስቸኪይ ሁኔታ ሲፈጠር፣ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ እና በቋሚ ኮሚቴዎች በቀጥታ ልከናወን የማይችል ነው ብሎ ስያምን በምክር ቤቱ የሚቋቋም ኮሚቴ ነው::

6.« አስረጂ » ማለት ምክር ቤቱ ወይም የምክር ቤቱ ቋሚ ኮሚቴዎች በተሰጣቸው ተግባር ዙሪያ የበለጠ መረጃ ለማግኘት በተጋጋዥነት የሚገኙ ግለሰቦች ወይም ባለ ሥልጣናት ወይም አካላት ናቸው::

7. « የጋራ ኮሚቴ » ማለት አንድ ጉዳይ በም/ቤቱ ወይም በአፈ ጉባኤው አማካኝነት ከአንድ በላይ በሆኑ ቋሚ ኮሚቴዎች እንዲታይ ሲመራ ጉዳዩን በአንድነት የሚያጠኑ ወይም የሚያከ ናዉኑ ኮሚቴዎች ናቸው::

8. « አፈ ጉባኤ » ወይም ምክትል አፈ ጉባኤ » ማለት እንደቅደም ተከተላቸው የም/ቤቱ አፈ ጉባኤ እና ምክትል አፈ ጉባኤ ነው::

9. « የም/ቤቱ የሥራ ዘመን » ማለት በኢትዮጵያ የምርጫ ህግ መሠረት በሚደረግ ጠቅላላ ምርጫ የተመረጡ የምክር ቤት አባላት ያላቸው የዉክልና ዘመን ነው::

10. « አባል » ማለት በህገ መንግሥቱ አንቀጽ 50 በተመለከተው መሠረት ተመርጦ ለም/ቤት አባልነት መመረጡ አግባብ ባለው አካል የተረጋገጠለት ዜጋ ነው::

11. « ስብሰባ » ማለት በክልሉ ህገ-መንግሥት አንቀጽ 56 ወይም በዚህ አዋጅመሰረት ተገቢው ዉክልና ባላቸው የም/ቤቱ ኃላፊዎች ወይም አባላት ጥሪ የሚሰበሰቡት የምክር ቤቱ ስብሰባ ነው::

www.chilot.me

12/ « የመጀመሪያ ንባብ »ማለት የህግ ረቂቅ ለመጀመሪያ ጊዜ ለምክር ቤቱ ቀርቦ በህጉ መሠረታዊ ይዘት ላ አጠቃላይ ዉይይት ከተደረገበት በኋላ ህጉን የማጽደቅ ወይም ለዝርዝር እይታ ለሚመለከተው ቋሚ ኮሚቴ የመምራት ሂደት ነው::

13/ « ሁለተኛ ንባብ» ማለት ከመጀመሪያውንባብ በኋላ በአፈጉባኤው አማካኝነት ለበለጠ እይታ ወደ ሚመለከታቸው ቋሚ ኮሚቴ ተመርቶ ቋሚ ኮሚቴው ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በሚያደርገው ዉይይት ያጠናከረው የዉሳኔ ሃሳብና አስተያየት ለም/ቤቱ አባላት ቀርቦ የሚደረገው የዉይይት ሁኔታ ነው::

14/ « ሦስተኛ ንባብ » ማለት ከሁለተኛ ንባብ በኋላ ም/ቤቱ በበለጠና በስፋት እንደገና እንዲያይ ለሚመለከተው ቋሚ ኮሚቴ የመራው ረቂቅ ህግ እነደገና ወደ ም/ቤቱ ተመልሶ የሚደረገው የዉይይት ሁኔታ ነው::

15/ «የቴክኒክ እርምት » ማለት የቋንቋና መስል ግድፈት ማስተካከያ ሲሆን በማናቸዉም ረገድ የህጉን ይዘት የማይለዉጥ ማሻሻያ ነው::

16.«አስተባባሪኮሚቴ»ማለት የም/ቤቱ አፈ-ጉባኤና ም/አፈ-ጉባኤ፣የቋሚ ኮሚቴዎች ሰብሳቢ፣እንዲሁም የም/ቤቱን ጽ/ቤት ኃላፊ የያዘ አካል ነው::

17 «መንግሥታዊ አካላት» ማለት ምክር ቤቱ ወይም ኮሚቴዎቹ በቀጥታ የሚከታተ ተሊቸዉና የሚቆጣጠሯቸው በሙሉ ወይም በከፊል በመንግሥት በጀት የሚመደብላቸው ተቋማት ናቸው::

18.«የመንግሥት ረቂቅ ህግ» ማለት በክልሉ መስተዳድር ም/ቤተ ዉሳኔ ተደግፎ ለምክር ቤቱ የሚቀርብ ረቂቅ ህግ ወይም ለም/ቤቱ ተጠሪ በሆኑ የመንግስት አካላት የሚቀርቡ ረቂቅ ህጎች ማለት ነው ::

## ክፍል ሁለት

## ስለ ምክር ቤቱ አደረጃጀትና ዋና ዋና ተግባራት፤

### 3/ የክልል ምክር ቤቱ አጠቃላይ አደረጃጀት

1.የሐረሪ ክልል ም/ቤት አደረጃጀት የሚከተለው ይሆናል::

ሀ. የምክር ቤቱ ጠቅላላ ጉባ፣

ለ..የም/ቤቱ ልዩልዩ ኮሚቴዎች፤

ሐ. የምክር ቤቱ ጽ/ቤት ናቸው

2.በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1)(ሀ)(ለ) ሥር የተገለጹት አካላት ስልጣንና ተግባራት በዚህ አዋጅ የተደነገገ ሲሆን የም/ቤቱ ጽ/ቤት ሥልጣንና ተግባራት በማቋቋሚያ አዋጅ ተደንግጎ ይገኛል::

3.ከላይ በንዑስ አንቀጽ1 የተዘረዘሩት አካላት ቢኖሩም ምክር ቤቱ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ሌሎችአካላትን ሊያቋቁም ይችላል::

### 4/ስለ ምክር ቤቱ ዋና ዋና ተግባራት፤

የሐረሪ ህዝብ ክልል ምክር ቤት በህገ መንግሥቱ አንቀጽ 51 ላይ ከተሰጠው ባለ ብዙ ፈርጅ ስልጣን እንደተጠበቀ ሆኖ የሚከተሉት አጠቃላይ ተግባራትና ኃለፊነቶች ይኖሩታል::

1.ህጎችን ማውጣት፤

2.የክልሉን ርዕሰ መስተዳድርና ሌሎች የክልሉን መንግሥት ባለ ሥልጣት ለጥያቄ መጥራት የሚያቀርቡትን ሪፖርት ማዳመጥ እንዲሁም አስፈላጊ

www.chilot.me

ሆና ሲገኝ ተገቢዉን እርምጃ መውሰድ:-

3.የክልሉን የመንግሥት አካላት አሠራርን መመርመርና መከታተል:-

4.ቋሚ ኮሚቴዎችንና ሌሎች ጊዜያዊ ኮሚቴዎችን ማቋቋም እንዲሁም ሪፖርታቸዉን ማዳመጥ ዉሳኔዎችና መመሪያዎችን መስጠት፤

5.የክልሉ አስፈፃሚ አካል ከፌደራልና ከሌሎች ህጋዊ ከሆኑት ሶስተኛ ወገኖች ጋር የሚያደርገዉን ስምምነቶች በምክር ቤቱ መጽደቅ የሚያስፈልጋቸዉን መርምሮ ማጽደቅ::

6.የተሰያዩ ሹመቶችን ማጽደቅ ወይም እንደአግባብነቱ መስጠት ናቸው::

## ክፍል ሦስት

## የምክር ቤቱ ሥራ አጀማመር እና የም/ቤቱአፈ ጉባኤዎች አመራረጥ፤ሥልጣንና ተግባራቸው እንዲሁም የምክር ቤቱ አሠራርና የአባላት ሥነ ምግባር፤

## ንዑስ ክፍል አንድ

### 5. የምክር ቤቱ ሥራ አጀማመር እና የአፈ ጉባኤዎች አመራረጥ፤

1.የቀድሞው ምክር ቤት ተሰናብቶ የአዲሱ ም/ቤት የሥራ ዘመን በሚጀመርበት ጊዜ የተተኪው ም/ቤት ስብሰባ የሚከፈተው በብሔራዊ ምርጫ ቦርድ የክልሉ ተጠሪ ወይም ቦርዱ በሚወክለው ማናቸዉም ሰውበተገኘበት ይሆናል::

2.በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተጠቀሰው የምርጫ ቦርድ ተወካይ የም/ቤቱን ጊዜያዊ አስመራጭ ኮሚቴ ከም/ቤቱ አባላት መካከል ሦስት ሰዎችን ያስመርጣል::

3.የአስመራጭ ኮሚቴው አንነተኛ ተልኮ እንደቅደም ተከተላቸዉ አፈ-ጉባኤዉንና ምክትሉን ከም/ቤቱ አባላት መካከል በህገ-መንግስቱ አንቀጽ52(3)መሠረት ማስመረጥ ይሆናል::

### 6/የአፈ ጉባኤዉና የም/አፈጉባኤው ስልጣንና ተግባራት፤

#### 1.ስለአፈጉባኤዉ ሥልጣንና ተግባር፤

አፈጉኤው የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባርራት ይኖሩታል:

ሀ. የምክር ቤቱን ስብሰባዎች በሰብሳቢነት ይመራል፤

ለ. ምክር ቤቱ ከሌሎች ጋር በሚያደርጋ ቸው ግንኙነቶች ሁሉ ምክር ቤቱን ይወክላል፤

ሐ.በምክር ቤቱ ስብሰባ ወቅት ሥነ ሥርአት መከበሩን ፤ የስብሰባው ክብርና ሞገስ የተጠበቀ መሆኑን ያረጋግጣል፤

መ.የምክር ቤቱን የስብሰባ አሰተባባሪ፤ የሥነ ስርአትና ጸጥታ አስከባሪን በበላይነት ይመራል፤

ሠ.የም/ቤቱን ዉሳኔዎች ትዕዛዞችና መመሪያዎች ስሚመለከታቸው አካላት ወይም ባለ ስልጣናት ወይም ግለሰቦች ያስተላልፋል::

ረ. የጽ/ቤቱን ተግባሮች በበላይነት ይመራል፤ ይቆጣጠራል፤

ሰ.በምክር ቤቱ የሚቋቋሙትን ቋሚና ጊዜያዊ ኮሚቴዎች ሥራ ያስተባብራል፤

ሸ.ከአስተባባሪ ኮሚቴ አባላት ጋር በመመካከር የምክር ቤቱን አጀንዳ ቅደም ተከተል ይወስናል ይህንንም ለስብሰባው ያሳውቃል ::

www.chilot.me

ቀ. በምክር ቤቱ ዉሳኔ መሠረት በምክር ቤቱ ስበሰባ ላይ ተገኝተው ማብራሪያ እንዲሰጡ የሚፈለጉ የመንግሥት ባለሥልጣኖችና ሌሎች ግለሰቦች በምክር ቤቱ ስበሰባ ላይ እንዲገኙ ቦታ ቀንና ሰአት ወስና በፀሐፊው አማካይነት ጥሪ ያስተላልፋል፡፡

በ. በዉይይት ሂደት የተነሱና ዉሳኔ ሊሰጥባቸው የሚገቡ ጭብጦችን በግልጽ ያስቀምጣል፤ ለድምጽም ያቀርባል፤ የድምጹን ዉጤት ለስብሰባው ይገልጻል፤

ተ. ምክር ቤቱ ባሳለፋቸው ረቂቅ ህጎች ላይ ይፈርማል፤ ለክልሉ ርዕሰ መስተዳድ ሩም እንዲፈርምባቸው በሁለት የሥራ ቀናት በማያንስ ጊዜ ዉስጥ ያስተላልፋል፤

ቸ.በስብሰባው ሂደት ወቅት የተናጋሪዎችን ቅደም ተከተል ይይዛል፤በዚሁ መሠረት የመናገር እድል ይሰጣል፤እያንዳንዱ ተናጋሪ የሚወስደው ጊዜ በቀረበው ሃሳብ መሠረት ይወስናል፡

ነ. በስብሰባወ ሂደት ወቅት የሚነሱ የሥነ-ሥርአት ጥያቄዎች ላይ ዉሳኔ ይሰጣል፤

ኘ. የምክርቤቱን እንግዶች ይቀበላል፤ ስለ መስተንግዷቸው ተገቢዉን መመሪያ ይሰጣል፤ ምክር ቤቱና ክልሉን ዲሞክራሲያዊ ሂደት ያስተዋዉቃል፤ያስተምራል፤

አ.ሥልጣንና ተግባሩን በከፊል ለምክትል አፈጉበአው በጽሑፍ ለመወከል ይችላል፤

ከ.-ም/ቤቱ በውሳኔ የሚሰጠውን ሌሎች ተግባሮች ያከናውናል ፡፡

**2) የምክትል አፈ-ጉባኤው ሥልጣንና ተግባር፤**

ሀ/አፈጉባአው በሌለበት ወይም ሥራዉን ለማከናወን በማይችልበት ወይም በምክር ቤቱ ዉይይት አቋም ይዞ ለመሳተፍ በሚፈልግበት ጊዜና ሁኔታ እሱን ተክቶ ይሠራል፤

ለ. በምክር ቤቱና በአፈጉባአው ተለይተው የሚሰጡትን ሌሎች ተግባሮች ያከናዉናል፤

**ንኡስ ክፍል ሁለት**

**የምክር ቤቱ አሠራርና የአባላት ሥነ ምግባር፤**

**7. የዕለታዊ አጀንዳዎች አቀራረብ**

1.ምክር ቤቱ የሚወያይባቸው አጀንዳዎች የሚመነጩት፤

ሀ.በክልሉ መስተዳድር ም/ቤት፤

ለ.ከሐረሪና ከሕዝብ ተወካዮች ጉባዔዎች፤

ሐ.በአፈ-ጉባዔው፤

መ.በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት፤

ሠ.በምክር ቤቱ ኮሚቴዎች፤

ረ. በምክር ቤት አባላት፤

ሰ. ለምክር ቤቱ በቀጥታ ተጠሪ በሆኑ አካላት፤

2.ከላይ በንዑስ አንቀጽ 1 (ሀ) የሚቀርብ አጀንዳ ቅድሚያ ተሰጥቶት ዉይይት ይደረግበታል፡፡

3.ከላይ በንዑስ አንቀጽ (1) በተዘረዘሩት አካላት የሚመነጩ አጀንዳዎች ለምክር ቤቱ የሚቀርቡት በአፈ-ጉባኤው በኩል ነው::

4.ለም/ቤቱ የሚቀርቡት ማናቸውም አጀንዳ ጉባኤ ከመካሄዱ ከአንድ ወር በፊት ለአፈ-ጉባኤው መቅረብ ይኖርበታል፤

5.በአጀንዳ አቅራቢዎች አስቸኳይ ናቸው ተብለው የሚታመንባቸው ጉዳዮች ጉባዔው ከመካሄዱ ከ48 ሠዓት በፊት ለአፈጉባኤው በማቅረብ እና በም/ቤቱ አባላት ከግማሽ በላይ መደገፍ አለባቸው::

6.በአጀንዳዎች አቀራረብ ቅደም ተከተልና ለዉይይት የሚያስፈልገዉን ጊዜ በተመለከተ አፈ-ጉባኤዉና አስተባባሪ ኮሚቴው አባላት በጋራ በመመካከር ይወስናሉ፡

7.ሊሎች አስገዳጅ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው በአፈጉባኤው በኩል ተቀርጸው በቀረቡ አጀንዳዎች ምክር ቤቱ በእያንዳንዱ ላይ ድምጽ ይሰጣል በአብላጫ ድምጽ ሲደገፍም በአጀንዳነት ይያዛል::

8.ምክር ቤቱ በአጀንዳነት ባፀደቃቸው ጉዳዮች ላይ በቂ ዉይይት በማድረግ ዉሳኔ ያሳልፋል::

9.ምክር ቤቱ የተለየ አቅጣጫ ካላስቀመጠ በስተቀር በምክር ቤቱ ዉድቅ የሆነ አጀንዳ በዚያው ዓመት ተመልሶ ለምክር ቤቱ አይቀርብም::

## 8/የምክር ቤቱ አባላት መብትና ግዴታዎች እንዲሁም የሥነምግባር አሠራሮች

የምክር ቤቱ አባላት ሥልጣንና ተግባራቸውን በአግባቡ መወጣት የሚያስችላቸው መብቶች ይኖሯቸዋል:: በአንጻሩም ህብረተሰቡ የጣለባቸዉን ኃላፊነቶችና የሥነምግባር ግዴታዎች በአግባቡ መወጣት ይኖርባቸዋል:: ዝርዝሩ በህግ ይወሰናል::

## ክፍል አራት

## 9. የህግ አወጣጥ ሥነ-ሥርአት:-

1. ምክር ቤቱ ህግ የሚያወጣው አዳዲስ ህጋጋትን በመደንገግ፤ነበር ህጋጋትን በማሻሻልና፤ በመሻር እንዲሁም የተለያዩ ውሳኔዎችን በማጽደቅና በማሳለፍ ይሆናል::

2.ህግን የማመንጨት ተግባራት በዋነኛነት የክልሉ መስተዳድር ም/ቤት ሆኖ ከዚህ በታች የተመለከቱት አካላት የሄው ስልጣን ይኖራቸዋል::

ሀ. ጠቅላይ ፍርድ ቤት

ለ. የምክር ቤቱ ቋሚ ኮሚቴዎች:

ሐ. የምክር ቤቱ አባላት:

መ. ተጠሪነታቸው ለምክር ቤቱ የሆኑ ሊሎች መንግሥታዉያን አካላት:

ሠ. አፈጉባኤው :

ረ. የህዝብ ተወካዮች ጉባዔ:

ሰ. የሐረሪ ጉባዔ

ሸ.ምክትል አፈ-ጉባዔዉ ናቸው::

3.ከላይ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2/ሐ/በተገለጸው መሠረት የሚቀርብ ማናቸዉም የህግ ረቂቅ በጽሑፍ ሆኖ ቢያንስ የምክር ቤቱን 5 አባላት የድጋፍ ፊርማ ማግኘት አለበት:

www.chilot.me

2.ማናቸዉም የህግ ረቂቅ በአፈ-ጉባዔው በኩል ለምክር ቤቱ ይቀርባል።

## 10/ ስለመጀመሪያ ንባብ፡-

1.የህግ ረቂቅ ሰነዱ በተያዘለት አጀንዳመሠረት በአፈ-ጉባዔው፣ወይም አፈ-ጉባዔው በሚወክለው ሰው የህግ ረቂቅ ይዘቱን ባጭሩ ከቀረበ በኋላ ም/ቤቱ በአጠቃላይ ይዘቱ ላይ እንዲወያይ ይደረጋል።

2. ረቂቅ ህጉ ቢዚህ ደረጃ የሚጸድቅበት ሁኔታ ካልኖረ በስተቀር፣ዉይይቱ እንደተጠናቀቀ በአፈጉባኤው አማካኝነት ቁጥር ተሰጥቶት ለሚመለከተው ቋሚ ኮሚቴ ወይም ኮሚቴዎች ለበለጠ እይታና ጥናት ይመራል።

3. በአስቸኳይነቱ ምክንያቶች ከ48 ሠዓት በፊት ለአባላት ያልተሠራጨ ረቂቂ ከሆነ ሠነዱ በዝርዝር ተነቦ ዉይየት ይደረጋል።

4. ረቂቅ ህጉ የተመራለት ቋሚ ኮሚቴ የሚወጣው ህግ በአስቸኳይነቱ የሚታመን በት ካልሆነ በስተቀር_ ጉዳዩን አጥንቶ የዉሳኔ ሐሳቡን ለም/ቤቱ ለማቅረብ ቢያንስ የአሥራ አምስት የሥራ ቀናት ማግኘት ይገባዋል።

## 11/ ሁለተኛ ንባብ፡-

1.የመጀመሪያው ንባብ ከተጠናቀቀ በኋላ አፈጉባኤው ለሚመለከተው ቋሚ ኮሚቴ በተመራው የህግ ረቂቅ ላይ የተጠናቀረዉን የዉሳኔ ሃሳብና አስተያየት በቋሚ ኮሚቴው አማካኝነት ለምክር ቤቱ እንዲነበብ ይደረጋል።

2.አፈጉባዔው በቀረበው የዉሳኔ ሃሳብ ላይ ዝርዝር ዉይይት እንዲደረግ መድረክ ይከፍታል፤

3.በዚህ ዉይይት የህግ ረቂቁን ሲጠቃለል ካልቻለ ለዳግም እይታ ወደ ሚመለከተው ቋሚ ኮሚቴ ተመልሶሲመራ ይችላል ። ዉይይቱ በበቂ ሁኔታ ከተጠናቀቀ ግን ህግ ሆኖ እንዲወጣ ይወስናል።

## 12/ ሦስተኛ ንባብ፡-

1.ረቂቅ የህግ ሠነዱ ዳግም የተመራለት ቋሚ ኮሚቴ የሚያሻሽለዉን አሻሽሎ የመጨረሻ ዉሳኔ ሃሳቡን ለምክር ቤቱ በንባብ እንዲያሰማ ይደረጋል፤

2.በቀረበው የመጨረሻ ሃሳብ ላይ ምክር ቤቱ በቂ ዉይይት በማካሄድ ህግ ሆኖ እንዲወጣ ይወስናል።

## 13/ ሕጉ በሥራ ላይ ስለሚዉልበት ሁኔታ፡-

1.አፈጉባኤው የህግ ረቂቁን ምክር ቤቱ መክር የተስማማበትና ያፀደቀው መሆኑን በመግለጽ የብሔራዊ ክልሉ ፕሬዝዳንት ይፈርምበት ዘንድ ይልከዋል፡

2.ሠነዱ ለብሔራዊ ክልሉ ፕሬዝዳንት በደረሰ በአስራ አምስት ቀናት ዉስጥ ካልተፈረመ ህግ ሆኖ ይወጣል።ሆኖም ግን ህጉ በሐረሪ ነጋሪ ጋዜጣ ታትሞ ከመውጣቱ በፊት የቴክኒክ እርምት ማድረግ የሚያስፈልገው ሆኖ ሲገኝ እርምቱን አፈ-ጉባዔው ያደርጋል።

3.የፀደቀው ህግ በአፈ- ጉባዔው አማካኝነት ቁጥር ተሰጥቶት በሐረር ነጋሪ ጋዜጣ ይታተማል።

www.chilot.me

4.ህጉ ከመታተሙ በፊት ከቴክኒክ እርማት ባሻገር መሚላት ያለበት ክፍተት ሲገኝበት በሚመለከተው አማካኝነት ክፍተቱን የሚያሚላ ሃሳብ ለም/ቤቱ ቀርቦ ከፀደቀ በኋላ በዚያው ህግ ላይ ተካቶ ይታተማል ስለተካተተው ሃሳብም ከመታተሙ በፊት የክልሉ ፕሬዝዳንት እንዲያውቀው ይደረጋል።

## ክፍል አምስት

## የመንግሥት አካላትን አሠራር ስለ መከታተልና ስለ መቆጣጠር፣ሪፖርት ስለ ማቅረብና ስለመመርመር እንዲሁም ዉሳኔ ስለመስጠት

### 14.መንግሥታ ዊአካላትን ስለመከታተልና ስለመቆጣጠር

1.ምክር ቤቱ የክሉን መንግሥዊ አካላት የሚከታተልበትና የሚቆጣጠርበት ዋና አላማ፣

ሀ. የህዝብና የመንግሥት ሀብትና ንብረት በአግባቡ ሥራ ላይ መዋሉን፣

ለ.ሥራዎችሥርአትን መሠረት አድርገው እየተከናወኑ መሆኑን፣

ሐ.ፍትሃዊና ፈጣን የልማት አቅጣጫ መኖሩን፣

መ.ዲሞክራሲያዊ ሥርዓትንና መልካም አስተዳደር ማስፈኑን፣

ሠ.የዜጎችመብት፣ ሠላምና ደህንነት መከበሩን፣

ረ. በመንግሥት አካላት መካከል የተቀናጀ አሠራር መኖሩን ማረጋገጥ ነው።

2.ምክር ቤቱ በሚከተሉት አካላት ላይ ክትትልና ቁጥጥር ያደርጋል፣

ሀ.የክልሉ መንግሥታዊ አካላት፣

ለ.ለምክር ቤቱ ተጠሪ የሆኑ የራሱ የዉስጥ አካላትን

### 15/ ሪፖርት ስለማቅረብ።

1.የክልሉ ርዕሰ መስተዳድር በበጀት ዓመቱ መጀመሪያ ወራት አጠቃላይ እቅዱን በተመለከተ እንዲሁም በዓመቱ አጋማሽና መጨረሻ ወራት አጠቃላይ የሥራ እንቅስቃሴዉን በተመለከተ ለም/ቤቱ ሪፖርት ያቀርባል።

2.እያንዳንዱ የክልሉ መንግሥት አካል ለሚመለከተው የም/ቤቱ ቋሚ ኮሚቴ በተመደበለት ጊዜ ሪፖርት ማቅረብ አለበት። አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘም እያንዳንዱ የክልሉ መንግሥት አካላት በሚመለከተው ቋሚ ኮሚቴ አማካኝነት ለም/ቤቱ ሪፖርት ያቀርባል።

3.በንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት የሚቀርበው ሪፖርት፣ በዋናነት ዓመታዊ የሥራ ዕቅድና ዉጤቱ፣ አስተዳደራዊ ሂደቱና የበጀት አፈጻጸሙ ፣ ያጋጠሙ ዋና ዋና ችግሮችና አዎንታዊ የሥራ ዉጤቶችን የመሳሰሉትን ማካተት አለበት።

4.ሲባ አስገዳጅ ሁኔታ ካላጋጠመ በስተቀር የሪፖርት አቅራቢው መ/ቤት ኃላፊ ሪፖረቱን ያቀርባል።

5.ሪፖርቱ በኃላፊው ተወካይ ሲቀርብ የሚችለው፣ ኃላፊው ሊቀርብ ያልቻለበት ምክንያትና በተወካዩ የሚቀርብ መሆኑ ለአፈ ጉባኤዉና ለሚመለከተው ቋሚ ኮሚቴ አስቀድሞ በማሳወቅ ይሆናል።

### 16/የቀረበውን ሪፖርት ስለ መመርመርና ዉሳኔ ስለመስጠት።

1.የም/ቤቱ አባላት በአፈ ጉባኤው በሚሰ

www.chilot.me

ጣቸው ቅደም ተከተል መሠረት ለሪፖርት አቅራቢው ጥያቄና አስተያየት ያቀርባሉ::

2.በንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት ለም/ቤቱ በተሰጡት መልሶች ዙሪያ ተጨማሪ ጥያቄዎችና አስተያየቶች እንዲቀርቡ ይደረጋል::

3.ሪፖርቱን አስመልክቶ የማጠቃለያ አስተ ያየት መድረክ ይሰጣል፤አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘም ም/ቤቱ የሚመለከተዉን ቋሚ ኮሚቴ ተጨማሪ ማጣራትና ምርመራ አድረጎ ሪፖርት እንዲያቀርብለት ሊያዝ ይችላል::

4.ም/ቤቱ በንዑስ አንቀጽ 3 መሠረት የቀረበዉን ሪፖርት አዳምጦ መሠረታዊ ችግር ለሆነ ከመሰለ አስፈላጊዉን እርምጃ ይወስዳል::

## 17 የኮሚቴዎችን ሪፖርት ስለ ማዳመጥ፤

1. የም/ቤቱ ቋሚና ሌሎች ኮሚቴዎች አፈጉባኤው በሚያወጣው የጊዜ ሰሌዳ መሰረት በተሰጣቸው ተግባር ዙሪያ አመራሮቻቸው ወይም ተወካዮቻቸው ለም/ቤቱ ሪፖርት ያቀርባሉ::

2.ቋሚ ኮሚቴዎች የሚያቀርቡት ሪፖርት:-

ሀ.ዓመታዊ አጠቃላይ የሥራ አፈጻጸ ማቸውን በተመለከተና

ለ. በየጊዜው በም/ቤቱ የሚመራላቸዉን ጉዳይ በተመለከተ ነው::

3.የጊዜያዊ ኮሚቴዎች ሪፖርት በተሰጣ ቸው የተለየ ተልኮ ላይ የተወሰነ ይሆናል ::

4.የም/ቤቱ አባላት በቀረበው ሪፖርት ዙሪያ ዉይይት ያደርጋሉ፤አስተያየት ይሰጣሉ ዉሳኔዎችን ያሳልፋሉ::

## ክፍል ስድስት

## የምክር ቤቱ ኮሚቴዎች አደረጃጀት፤ሥልጣንና ተግባር እንዲሁም አጠቃላይ አሠራር፤

### ንዑስ ክፍል አንድ

### ስለ ም/ቤቱ የተለያዩ ኮሚቴዎች

### 18.ምክር ቤቱ በዚህ አዋጅመሠረት የሚከተሉት የኮሚቴ አይነቶች ይኖሩታል::

1. አስተባባሪ ኮሚቴ
2. ቋሚ ኮሚቴ
3. ጊዜያዊ ኮሚቴ
4. የጋራ ኮሚቴ፤

### 19.የአስተባባሪ ኮሚቴው አደረጃጀት፤ ሥልጣንና ተግባር እንዲሁም አሠራር፤

#### 1. አስተባባሪ ኮሚቴው፤

ሀ.አፈ-ጉባኤዉ፤ምክትል አፈጉባኤዉን የቋሚ ኮሚቴዎች ሰብሳቢ እና የምክር ቤቱ ጽ/ቤት ኃላፊን በአባልነት የያዘ ነው::

ለ.የሚመራው በአፈ-ጉባኤው ሲሆን ዉሳኔዎችን በአብላጫ ድምጽ ያሳልፋል፤ ከአባላቱ መካከል ከግማሽ በላይ የሚሆኑት በስብሰባው ላይ ከተገኙ ምልዐተ ጉባኤ ይሆናል::

ሐ.ከአባላቱ መካከል የራሱን ፀሐፊ ይመርጣል::

2. የም/ቤቱ አስተባባሪ ኮሚቴ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል:

www.chilot.me

ሀ.የኮሚቴዎችን የሥራ እቅድ ያስተባብራል፤ የምክር ቤቱን አጠቃላይ የሥራ ሂደት ቅንጅትና ስኬታማነት ይከታተላል፤

ለ.በም/ቤቱ ዉስጥ የሚስተዋሉትን ዋና ዋና ችግርችና አዉንታዊ ገናት በሚመለከት በየወቅቱ ይገመግማል፤አጠቃላይ የሥራ አቅጣጫ በመቀየስ ለሚመለከተው ኮሚቴ መመሪያ ይሰጣል፤

ሐ.አፈ-ጉባኢዉ በዚህ ኮሚቴ እንዲታዩ ያመነባቸው ጉዳዮችና እንዲሁም የቋሚ ኮሚቴ አባላት ተወያይተው በአስተባባሪ ኮሚቴው እንዲታዩ የሚወስኗቸውን አጀንዳዎች በተመለከተ ይወያያል

መ. አዳዲስ መንግሥታዊ አካላት ሲደራጁ ወይም የነበሩት እንደ አዲስ ሲዋቀሩ ተገቢዉን ክትትልና ቁጥጥር ይደረግ ዘንድ ጉዳዩን ከሥራ ጠባዩ ጋር ለሚዛመደው ቋሚ ኮሚቴ ይመራል፤ይከታተላል፡

ሠ. በአጀንዳ ቅደም ተከተል ላይ ይወስናል፤

ረ. ከመጀመሪያ ንባብ በፊት በቀረበው ረቂቅ የህግ ሠነድ ላይ ይዘቱን ይመረምራል፤ይገመግማል፤

3/ቋሚ ኮሚቴዎች እንዲከተሏቸው በዚህ አዋጅ አንቀጽ 34 የተዘረዘሩትን አጠቃላይ የአሠራር ስልቶች አስተባባሪ ኮሚቴውም እንደ ሥራ ባህሪው ተግባራዊ ሊያደርጋቸው ወይም ሊጠቀምባቸው ይችላል::

## 20/ የቋሚ ኮሚቴዎች አደረጃጀት፤

1.ምክር ቤቱ የሚከተሉትን ቋሚ ኮሚቴዎች ይኖሩታል ::

ሀ. የአኮኖሚ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ፤

ለ.የማሐበራዊ ጉዳይ ቋሚ ኮሚቴ፤

ሐ.የበጀትና የፋይናንስ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ፤

መ. የህግ፤የአስተዳደር እና የሴቶች ጉዳይ ቋሚ ኮሚቴ ናቸው::

2.ቋሚ ኮሚቴዎች ተጠሪነታቸው ለም/ቤቱና ለአፈ ጉባዔው ይሆናል::

3.እያንዳንዱ ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢዉና ፀሐፊዉን ጨምሮ ከክልል ም/ቤቱ በቀጥታ የሚመረጡ 5 አባላት ይኖሩታል

4.አንድ የም/ቤት አባል በአንድ ጊዜ ከአንድ ቋሚ ኮሚቴ በላይ አባል ሆኖ ሊሠራ አይችልም::

5.የቋሚ ኮሚቴዎች ሰብሳቢዎች ተጠሪነታቸው ለአፈ ጉባኢዉና ለኮሚቴው ይሆናል::

6.እያንዳንዱ ቋሚ ኮሚቴ ለሥራው አስፈላጊ የሆኑ ድጋፍ ሰጪ ሠራተኞችን ከም/ቤቱ ጽ/ቤት እንዲጠቀሙ ይደረጋል::

## 21/የጊዜያዊ ኮሚቴዉ አደረጃጀት፤ ሥልጣንና ተግባር እንዲሁም አሠራር፤

1.ም/ቤቱ በቋሚ ኮሚቴዎች በቀጥታ ሊከናወን የማይችሉ አስቸኳይና አስፈላጊ ናቸው ብሎ ያመነባቸው ሁኔታዎች ሲያጋጥሙት ጊዜያዊ ኮሚቴዎችን ያቋቁማል::

www.chilot.me

2.የጊዜያዊ ኮሚቴው ሥልጣን በሚከሰተው አስቸኳይና አስፈላጊ ጉዳይ ዙሪያ ሆኖ ተልዕኮዉን ለማከናወን አጠቃላይ የአሠራር አቅጣጫ በም/ቤቱ የሚሰጠው ይሆናል::

3.የጊዜያዊ ኮሚቴው አባላት ብዛት እንደሁኔታው በም/ቤቱ የሚወሰን ሆኖ ኮሚቴዉን የሚመሩ ሰቀመንበርና ፀሐፊ ም/ቤቱ ይመድባል::

4.ጊዜያዊ ኮሚቴው በሚሰጠው ሥልጣን ዙሪያ ሥራዉን ካከናወነና ለም/ቤቱ ጥቅል ሪፖርት ካቀረበ በኂላ የሚከስም ይሆናል::

## 22/ ስለ ጋራ ኮሚቴዎች አደረጃጀት

የጋራ ኮሚቴዎችበምክር ቤቱ ወይም በአፈ ጉባኤው አማካኝነት አንድን ጉዳይ አጅግ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ከአንድ በላይ በሆኑ የም/ቤቱ ቋሚ ኮሚቴዎች እንዲታይ ሲመራ ጉዳዩን በአንድነት የሚያጠኑ ወይም የሚያከናዉኑ ኮሚቴዎች ናቸው::

## ንዑስ ክፍል ሁለት

## የቋሚ ኮሚቴዎች፣የሰብሳቢዎች እና የፀሐፊዎች የወል ሥልጣንና ተግባር እንዲሁም የአባላት ግዴታ::

## 23/ የቋሚ ኮሚቴዎች የወል ሥልጣንና ተግባር:

የምክር ቤቱ ቋሚ ኮሚቴዎች የሚከተሉት የወልሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል:

1. በአንቀጽ 11፣12እና 17 ድንጋጌዎች መሠረት በተመራላቸው የህግ ረቂቆች ላይ የዉሳኔ ሃሳቦችና አስተያቶችን ለም/ቤቱ የማቅረብ::

2.በየቋሚ ኮሚቴዎች ሥር እንደየአግባቡ በተደላደሉት መንግሥታዊ አካላት አሥራር ላይ ምርመራና ክትትል የማድረግ::

3.እንደየ አግባቡ በተለያዩ መንገዶችና ሁኔታዎች የሚቀረቡላቸዉን አቤቱታዎች ያስተናግዳሉ:: ዝርዝሩ በህግ ይወሰናል::

4.ኮሚቴዎቹ በተቋቋሙበት አላማ ዙሪያ ጥናቶችን የማካሄድና የክልሉን ፖሊሲዎች ስትራቴጂዎችና ፕሮግራሞች ተግባራዊ መሆናቸዉን የመከታተል::

5.ልዩ ልዩ አውደ ጥናቶችንና የዉይይት መድረኮችን የማዘጋጀትና የልምድ ልዉዉጦች የማድረግ፣

6.ከምክርቤቱና ከአፈ ጉባኤው የሚሰጡቸ ዉን ሌሎች ተዛማች ተግባራት የማከናወን፣

## 24/ የቋሚ ኮሚቴው ስብሳቢዎች ሥልጣንና ተግባር

የቋሚ ኮሚቴዎች ሰብሳቢዎች ከዚህ በታች የተመለከቱት የወል ሥልጣንና ተግባራት ይኖራቸዋል::

1.ኮሚቴዎችን በመወከል ከልዩ ልዩ አባላትና ባለ ሥልጣናት ጋር የሥራ ግንኙነትን የማድረግ፣

2.የየኮሚቴዎቻቸዉን ሥራ በበላይነት የመምራት፣ የማስተባበርና የስብሰባ ሥነ ሥርአቶቻቸዉን የማስጠበቅ፣

3.የኮሚቴዎቻቸዉን መደበኛና አስቸኳይ ስበሰባዎችን ይጠራል::

www.chilot.me

4. ፕሬ የተደረገላቸው ተጋባዥ እንግዶችን እንዲገኙ ቅድመ ሁኔታዎችን የማመቻቸት

5. ለኮሚቴው ሥራ ቅልጥፍና አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው የኮሚቴ ሥራዎች በአንድ አባል ወይም በሁለት አባላት እንዲሠሩና ለኮሚቴው አስተያየት ወይም የዉሳኔ ሐሳቦች እንዲያቀርቡ ያደርጋል::

6. ለምክር ቤቱ የሥራ ዘገባ የማቅረብና፤

7. ከአፈጉባዔዉና ከምክር ቤቱ በተሰይ የሚሠጡትን ሌሎች ተግባራት የማከናወን ፤

## 25/ የቋሚ ኮሚቴው ፀሐፊዎች ሥልጣንና ተግባር፤

የቋሚ ኮሚቴ ፀሐፊዎች ከዚህ በታች የተመለከቱት የወል ሥልጣንና ተግባራት ይኖራቸዋል::

1. ስብሳቢዎቹ በማይገኙበት ጊዜ ተተክተው የመሥራት፤

2. በስብሰባው ወቅት የኮሚቴዉን ቃለ ጉባኤ ይይዛል፡

3. ኮሚቴዎቹን የሚመለከቱ ማናቸዉም ሰነዶች በአግባቡ መያዛቸዉና መጠበቃቸዉን የማረጋገጥ፤

4. በስብሳቢዎቹ የሚሰጣቸዉን ሌሎች ተግባራት የማከናወን፤

## 26/ የቋሚ ኮሚቴው አባላት ግዴታዎች፤

የቋሚ ኮሚቴዎች አባላት የሚከተሉት ዋና ዋና ግዴታዎች አሏቸው ::

1. በቂ በሆነ ምክንያት ካልሆነ በስተቀር በማናቸዉም የኮሚቴው ስብሰባዎች የመገኘት፤

2. የተመደቡላቸዉን ሥራዎች በአግባቡ የመከታተልና የማከናወን፤

3. በክልሉ ዉስጥም ሆነ ከክልሉ ዉጭ በሚደረጉት ጥናቶች ስብሰባዎች እንዲሁም የመስክ ሥራዎች የሚወከል አባል ስለ ሁኔታው የተጠናከረ ሪፖርት ለሚመለከተው ኮሚቴና እንደሁኔታው ለምክር ቤቱ የማቅረብ፤

4. እያንዳንዱ የኮሚቴ አባል በተናጥልም ይሁን በጋራ ለሚያከናዉነው ሥራ ኃላፊነት አለበት ::ኃላፊነቱን በሚያጓድል ወይም አለ አግባብ የሚጠቀም የኮሚቴ አባል በኮሚቴው ተገምግሞ እና ተወስኖ ለምክር ቤቱ ሪፖርት ይቀርባል ::

## ንዑስ ክፍል ሦስት

## የእያንዳንዱ ቋሚ ኮሚቴዎች ሥልጣንና ተግባር

ቋሚ ኮሚቴዎች በዚህ አዋጅ መሠረት በወል የተሠጣቸው ስልጣንና ተግባር እንደተጠበቀ ሆኖ እያንዳንዱ የምክር ቤቱ ቋሚ ኮሚቴዎች የሚከተሉትን ሥልጣንና ተግባር ይኖራቸዋል::

## 27/የኢኮኖሚ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ::

1. የኢኮኖሚ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ የሚከተሉትን መንግሥታዊ መሥሪያ ቤቶች አሠራር ይከታተላል፤ይቆጣጠራል-

ሀ. ግብርናና የገጠር ልማት ቢሮ፤

ለ. የከተማ ልማት፤ንግድ ኢንዱስትሪና ትራንስፖርት ቢሮ፤

ሐ. የሐረር ከተማ ማዘጋጃ ቤት

www.chilot.me

መ.ከዚህ በላይ በፊደል ተራ ሀ ለና ሐ ሥር ለተጠቀሱ ቢሮዎች ተጠሪ የሆኑ መሥሪያ ቤቶችና ድርጅቶች፤

2. ከላይ በንኡስ አንቀት 1 የተዘረዘሩትን አካላት በተመለከተ በማንኛዉም ህጎች ተሰይተው በተሰጢቸው ሥልጣን እና ተግባር ዙሪያ ፤ይቆጣጠራል፤ይከታተላል አስፈላጊ ሆና ሲገኝም ይመረምራል፤

## 28.የማህበራዊ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ

1. የማህበራዊ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ የሚከተሉትን መንግሥታዊ መሥሪያ ቤቶች አሠራር ይከታተላል፤ይቆጣጠራል

ሀ. የትምህርትና የአቅም ግንባታ ቢሮ

ለ. የሕዝብ አደረጃጀት ባህልና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮ፤

ሐ. የጤና ጥበቃ ቢሮ

መ. የአ.ች.አይ.ቪ. (ኤድስ)መከላከያና መቆጣጠሪያ ጽ/ቤት

ሠ. የማስታወቂያና የሕዝብ ግንኙት ቢሮ

ረ. ከዚህ በላይ በፊደል ተራ ቁጥሮች ሀ፤ለ፤እና ሐ ለተጠቀሱት ቢሮዎች ተጠሪ የሆኑ መንግሥታዉያን መሥሪያ ቤቶችና ጽ/ቤቶች፤

2. ከዚህ በላይ በንዑስ አንቀጽ አንድ ሥር የተዘረዘሩትን አካላት በተመለከተ በማናቸዉም ህጎች ተሰይተው በተሰጢቸው ስልጣንና ተግባራት ዙሪያ ይቆጣጠራል፤ይከታተላል አስፈላጊ ሆና ሲገኝም ይመረምራል፤

## 29.የበጀትና የፋይናንስ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ

1. የበጀትና የፋይናንስ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ የሚከተሉትን መንግሥታዊ መሥሪያ ቤቶች አሠራር ይከታተላል ይቆጣጠራል::

ሀ. የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ፤

ለ. ዋና ኦዲተር መ/ቤት

ሐ. የኪራይ ቤቶች አስተዳደር ድርጅት

መ. የሐረር ከተማ ዉሃና ፍሳሽ አገልግሎት

2 ከላይ በንዑስ አንቀጽ 1 የተዘረዘሩትን አካላት በተመለከተ በማንኛውም ህጎች ተሰይተው በተሰጣቸው ሥልጣንና ተግባር ዙሪያ ይቆጣጠራል፤ይከታተላል አስፈላጊ ሆና ሲገ ኝም ይመረምራል ::

## 30.የህግ፤የአስተዳደርና የሴቶች ጉዳይ ቋሚ ኮሚቴ

1. የህግ፤የአስተዳደር እና የሴቶች ጉዳይ ቋሚ ኮሚቴ የሚከተሉትን መንግሥታዊ መ/ቤቶች አሠራር ይከታተላል፤ይቆጣጠራል፤

ሀ. ጠቅላይ ፍርድ ቤት

ለ. የፍትሃና ፀጥታ ጉዳይ ቢሮ፤

ሐ. የዳኞች አስተዳደር ጉባኤ፤

መ. የሴቶች ጉዳይ ጽ/ቤት፤

ሠ. ከዚህ በላይ በፊደል ተራ ቁጥር «ሀና «ለ»ሥር ለተመለከተው መሥሪያ ቤት ተጠሪ የሆነ ·መንግሥታዊ መሥሪያቤቶችና ጽ/ቤቶች ፤

www.chilot.me

2. ከላይ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ሥር የተዘረዘሩትን አካላት በተመለከተ በማናቸዉም ህጎች ተሰደተው በተሰጣቸው ሥልጣንና ተግባራት ዙሪያ ረቂቅ ህጎችን አዘጋጅቶ ያቀርባል፤ ይቆጣጠራል ፤ይከታተላል አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝም ይመረምራል::

3. ከላይ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1ፊደል ተራቁጥር ሀ ሥር የተጠቀሰዉን አካል በተመለከተ በፌደራል ህገ-መንግሥትና በክልሉ ህገ-መንግሥት አንቀጽ 78(1)እና 67(1)መሠረት የነጻ ዳኝነት መርህን በማይጋፋ መልኩ የክትትልና የቁጥጥር ሥራዉን ያከናዉናል::

4. ምክር ቤቱ ወይም አፈ-ጉባዔው ወደ ማናቸዉም ቋሚ ኮሚቴዎች የሚመራዉን ረቂቅ ህጎች ይዞታቸዉን በተመለከተ ይመረምራል፤ አስተያየት ይሰጣል::

5. በህገ-መንግሥቱ አንቀጽ 55(2) የተመለከተዉን የህግ ክለሳ የማንሳት ጥያቄ ሲቀርብ ለምክር ቤቱ የዉሳኔ ሃሳብ ያቀርባል::

6. በህጉ መሠረት የምህረት ጥያቄ ከሚመለከተው አካል ሲቀርብ ለምክር ቤቱ የዉሳኔ ሀሳብ ያቀርባል::

7. ከዚህ በላይ በንዑስ አንቀጽ 1(መ) የተመለከተው መ/ቤት እንደተጠበቀ ሆኖ በክልሉ የሚገኙ መንግሥታዊ አካ ላትና ድርጅቶች ለሴቶች ሁለንተናዊ ጥያቄ ተገቢዉን ትኩረት ለጥተዉና የጾታን ጉዳይ አካተው የተንቀሳቀሱና የሚንቀሳቀሱ ስለመሆኑ ይከታተላል፤ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝም ይመረምራል:: እርምጃ እንዲወሰድ ያደርጋል::

## 31.በቋሚ ኮሚቴዎች ሥር ስላልተደላደሉ የመንግሥት አካላት:-

በዚህ አዋጅ ከአንቀጽ 27 እስከ 30 በተቋቋሙት ቋሚ ኮሚቴዎች ስር ያልተደላደሉ መንግሥታዊ አካላት አሠራር በተመለከተ በየትኛው ቋሚ ኮሚቴ አማካኝነት ምርመራና ክትትል እንደሚደረግባቸው በአስተባባሪው ኮሚቴ እየታየ የሚወሰን ይሆናል ::

## ንዑስ ክፍል አራት

## የኮሚቴዎች አጠቃላይ አሠራርና ሥነ ሥርአት ::

## 32. የቋሚ ኮሚቴዎች አጠቃላይ አሠራር

የምክር ቤቱ ቋሚ ኮሚቴዎች የሚከተሉት ዋና ዋና የአሠራር ሥልቶችና ሥነ ሥርአቶች ይኖሯቸዋል ::

1. ከመጀመሪያ ንባብ በኋላ በአፈ-ጉባዔው በኩል ለቋሚ ኮሚቴዎች የተመራ ረቂቅ ህጎችን እንደየሁኔታው፤-

ሀ. ማስታወቂያ በማውጣት፤

ለ. አስረጂ አካላትን በመጋበዝ፤

ሐ.የሕዝብ አስተያየት መስጫ መድረኮችን በማዘጋጀት አበልጽገው ለምክር ቤቱ ውሳኔ ሀሳብና አስተያየት የማቅረብ

2. ቋማ ኮሚቴዎች የመመርመርና የመከታተል ሥራቸዉን የሚያከናዉኑት:-

ሀ.ከሚመለከታቸው መሥሪያቤቶች አመታዊ እቅድና ክንዉን መግለጫ በመቀበል፤

ለ. ስብሰባዎችንና ኮንፈረንሶችን በመሳተፍ፤

ሐ. የሚመለከታቸዉን አንላት በመጥራትና በማነጋገር አስፈላጊ ከሆነም መግለጫ እንዲሰጡ በማደረግ፤

መ. ለሥራው መደበር አጋዥ የሆኑ የተለያዩ የመስክ ጉብኝቶችን በማድረግ፤

ሠ.ከተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች የሚደርሲቸዉን ጥቆማዎችና አቤቱታ ዎች መነሻ በማድረግ፤

3.ከሲ.ሲ·ች ቋሚ ኮሚቴዎች ወይም አካሉ·ች ጋር ቅንጅት በመፍጠር፣

4. ሪፖርት በማዘጋጀትና ልዩ ልዩ መግለጫዎችን በመስጠት፤

5. በአመታዊ እቅዶች በመመራትና ጠቅላላ አሠራርችን በመገምገም ይሆናል::

## 33.የጋራ ኮሚቴዎች አሠራር፤፤

1.የጋራ ኮሚቴዎች ከአባሉ·ቻቸው·መካከል ሰብሳቢዉንና ፀሐፊዉን ይመርጣል
2. ከያንዳንዱ ቋሚ ኮሚቴ ከግማሽ በላይ የሚሆኑ·ት አባላት በስብሰባው· ከ*ገኙ· የጋራ ኮሚቴው· ምልዐተ ጉ·ባኤ ይሆናል::

3. የጋራ ኮሚቴው· ዉሳኔዎቻቸዉን በአብላጫ ድምጽ ያሳልፋሉ· ሆኖም ድምጹ እኩ·ል ለእኩ·ል የተከፈለ እንደሆነ ሰብሳቢው· የደገፈው· ሃሳብ የጋራ ኮሚቴው· ዉሳኔ ይሆናል::

4. የጋራ ኮሚቴ አባላት በምክር ቤቱ ወይም በአፈ-ጉ·ባኤው· አማካኝነት የተመሩላቸዉን ጉ·ዳዮች በሚመለከቱበት ጊዜ ሁ·ሉ· በዚህ አዋጅ አንቀጽ 34 ሥር በሰፈሩት የአሠራር ስልቶችና ሥነ ሥርአት ይጠቀማሉ·::

## 34. የቋሚ ኮሚቴዎች የስብሰባ ሥነ ሥርአት

1. ከግማሽ በላይ የሚሆኑ·ት የቋሚ ኮሚቴ አባላት በስብሰባው· ከተገኙ· ምልዐተ ጉ·ባኤ ይሆናል ::

2. የቋሚ ኮሚቴው· ው·ሳኔዎች በአብላጫ ድምጽ ያሳልፋሉ· ሆኖም ድምፁ· እኩ·ል በእኩ·ል የተከፈለ እንደሆነ ሰብሳቢው· የደረፈው· ሃሳብ የኮሚቴው· ው·ሳኔ· ይሆናል ::

3. ለምልዐተ ጉ·ባኤ ሳይቆጠሩ አጀንዳ ሳያስይዙ· እና ያለ ድምጽ በቋሚ ኮሚቴው· ስብሰባ የምክር ቤቱ አባላትና ተጋባዥ እንግዶች በዉይይቱ ላይ መሳ ተፍ ይችላሉ·::

4. የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው· እያንዳንዱ ቋሚ ኮሚቴ የስብሰባ ሥነ ስርአቱን በተመለከተ በዝረዝር ህግ የሚወጣ ይሆናል::

## ክፍል ሰባት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

## 35.ደንብ የማው·ጣት ሥልጣን፤

በዚህ አዋጅ ዉስጥ የሰፈሩትን ድንጋጌዎች ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ·ትን ዝርዝር ደንቦች ምክር ቤቱ ያወጣል::

## 36.ይህ አዋጅ ከመው·ጣቱ በፊት ስለተከናወኑ· ጉ·ዳዮች

ህጉ· ከመው·ጣቱ በፊት ለምክር ቤቱ የቀቡ· አጀንዳዎችና ፕሮግራሞች ካሉ·ና ለምክር ቤቱ አባላት ዉይይት እንዲደረግባቸው· ያልቀረቡ· ከሆነ አዲስ በሚወጣው· ህግ መሠረት የሚፈጸሙ· ይሆናሉ·:: ሆኖም ህጉ· ከመው·ጣቱ በፊት ቀደም ሲል በምክር ቤቱ ተሠርተው· እንዲቀርቡ· ያስተላለፋቸው· ትዕዛዝና ዉሳኔዎች ያሳለቁ ከሆነ በቀድሞው· ትእዛዝ መሰረት የሚጠናቀቁና የሚፈፀሙ· ይሆናል ::

## 37.ተፈጻሚነት ስለማይኖራቸው· ህጎች ፡

ይህን አዋጅ የሚቃረን ማናቸዉም ህግ፤ደንብ፤መመሪያ ወይም የተለመደ አሠራር በዚህ አዋጅ በተመለከቱት ጉ·ዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖረዉም::

## 38. አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በክልሉ· ምክር ቤት ከፀደቀበት ከየካቲት 30/1998 ጀምሮ የፀና ይሆናል::

## ሐረር

የካቲት 30 ቀን 1998 ዓ/ም

ሙ·ራድ አብዱልሃዲ

የሐረሪ ክልል ፕሬዝዳንት

www.chilot.me

የሐረሪ ህዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት

# ሐ ረ ር ነ ጋ ሪ ጋ ዜ ጣ

# HARAR NEGARI GAZETA

OF THE HARARI PEOPLE NATIONAL REGIONAL STATE

10ኛ ዓመት ቁጥር 5
10th year No.5

ሐረር መጋቢት 1 ቀን 1998
Harar 10 th March 2006

| | | |
|---|---|---|
| ያንዱ ዋጋ 0.50<br>unit price Br 0.50 | በሐረሪ ህዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት<br>ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ | የፖስታ ሣጥን ቁጥር 272<br>p.o.Box - 272 |

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር 54 /1998 ዓ.ም
በ1998 የበጀት አመት በሲቪል ሰርቪስ ዉስጥ ለሚገኙ ለመንግስት ሰራተኞች የተደረገ አዲስ የደሞዝ እርከን ጭማሪ የታወጀ ተጨማሪ በጀት አዋጅ ቁጥር 54 /1998 ገጽ 437

## አዋጅ ቁጥር 54 /1998

## ለሐረሪ ሕ/ብ/ክ/መንግስት የ1998 በበጀት ዓመት ከፌደራል መንግስት ለደሞዝ ጭማሪ የተመደበዉን የበጀትድጐማ በመደበኛ በተጨማሪ በጀት የታወጀ አዋጅ

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገ መንግስት አንቀጽ 52 ንዑስ አንቀጽ 2/ሠ/መሰረት ክልሉ የራሱን በጀት በማጽደቅና ሥራ ላይ በማዋል ስልጣን የተሰጠዉ በመሆኑ ፤የሐረሪ ሕዝብ ክልል ምክር ቤት ተሻሽሎ በወጣዉ የክልሉ ህገ መንግስት አንቀጽ 51 (2) (1) በተሰጠዉ ስልጣን መሰረት የሚከተሰዉን አዉጇል ።

### 1. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "በ1998 የበጀት ዓመት በሲቪል ሰርቪስ ዉስጥ ለሚገኙ የመንግስት ሰራተኞች የተደረገ አዲስ የደመወዝ እርከን ጭማሪ ለመሸፈን በተሳከ ድጎማ የታወጀ ተጨማሪ ቡጀት አዋጅ ቁጥር 54 /1998" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል ።

### 2. ስለ ተጨማሪ በጀትና የገቢ ምንጭ

ከፌደራል መንግስት ግምጃ ቤት ከተገኘ የበጀት ድጎማ ብር 4469200 ( አራት ሚሊዮን አራት መቶ ስልሣ ዘጠኝ ሺህ ሁለት መቶ ብር ) በዚህ አዋጅ መሰረት የሐረሪ ህዝብ ክልላዊ መንግስት የ1998 ዓ/ም ተጨማሪ በጀት ሆኖ እንዲሰራበት ጸድቋል።

### 3. ለደመወዝ ጭማሪ መደበኛ ወጪ

ሀ/ ከሐምሌ 1/97 - ሰኔ 98 ላለዉ ጊዜ ለደሞዝ ጭማሪ ብር 4212900 እና

ለ/ ከሐምሌ 1/97 - ሰኔ 98 ላለዉ ጊዜ ለጡረታ መዋጮ 6 % ብር 256300 ጠቅላላ ድምር ብር 4469200 ( አራት ሚሊዮን አራት መቶ ስልሣ ዘጠኝ ሺህ ሁለት መቶ ብር ) ወጪ ሆኖ እንዲከፈል በዚህ አዋጅ ተፈቅዷል ።

### 4. ክፍያ ስለመፈፀም

ጉዳዩ የሚመለከታቸዉ የክልሉ መንግስት አካላትና መ/ቤቶች ክፍያ ሲጠየቁ የክልሉ የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ ከላይ ከተጠቀሰዉ የገንዘብ ምንጭ እንዲከፈል ታዟል ።

### 5. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ ከመጋቢት 1 ቀን 1998 ጀምሮ የፀና ይሆናል ።

ሐረር መጋቢት 1/1998
ሙራድ አብዱልሃዲ
የሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት
ፕሬዚዳንት

www.chilot.me

የሐረሪ ህዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት

# ሐ ረ ር ነ ጋ ሪ ጋ ዜ ጣ

# HARAR NEGARI GAZETA

OF THE HARARI PEOPLE NATIONAL REGIONAL STATE

| | |
|---|---|
| 10ኛ አመት ቁጥር 6<br>10th year No 6 | ሐረር መጋቢት 1/1998<br>Harar march 10/2006 |

| | | |
|---|---|---|
| ያንዱ ዋጋ ብር 4:00<br>Unit Price Bir. 4:00 | በሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ | የፖስታ ሣጥን ቁጥር 272<br>P.o .Box 272 |


አዋጅ ቁጥር 55/1998 ዓ.ም
የሐረሪ ክልል የዋና ኦተዲር መሥሪያ ቤትን እንደገና ለማቋቋም የወጣ አዋጅ...............................................ገጽ438

## አዋጅ ቁጥር 55/1998 ዓ/ም

## የሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤትን እንደገና ለማቋቋም የወጣ አዋጅ

የኦዲት ሥርዓትን ማጠናከር የክልሉን ኢኮኖሚ በሚገባ ለመምራትና ለማስተዳደር የሚያስፈልገውን አስተማማኝ መረጃ በማግኘት ረገድ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያለው በመሆኑ፣

በልዩ ልዩ የልማትና አስተዳደር መስኮች የተሰማሩ የመንግስት መሥሪያ ቤቶችና ድርጅቶች የገንዘብ አስተዳደር ተገቢውን የሒሳብ አያያዝ ሥርዓት የተከተለ የገቢ አሰባሰባቸው፣የወጪ አፈቃቀዳቸውና የንብረት አስተዳደራቸው የመንግስት ሕጎችን፣ ደንቦችንና መመሪያዎችን ተከትሎ የተፈጸመ መሆኑንና ዕቅድና ፕሮግራማቸውንም በቅልጥፍና እና ኢካኖሚያዊ በሆነ መንገድ በማከናወን የሚጠበቅባቸውን ግብ ማሟላታቸውን ማረጋገጥ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣

በክልሉ መንግስት አወቃቀር በሚገኙ መሥሪያ ቤቶች ውስጥ ተጠያቂነትን፣ ግልጽነትን እና መልካም አስተዳደርን ለማስፈን ኦዲት አንዱ መሣሪያ በመሆኑ፣ እና የክልሉ ዋና ኦዲተርና የመሥሪያ ቤቱን የሙያ ነፃነት በይበልጥ ማረጋገጥ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣

ለዚሁም ተግባራዊነት የሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤትን እንደገና አጠናክሮ ማቋቋም በማስፈለጉ፣

የሐረሪ ሕዝብ ክልል ምክር ቤት ተሻሽሎ በወጣው የክልሉ ሕገ-መንግስት አንቀጽ 51 ንዑስ አንቀጽ 2 (ሀ) እና (ሠ) በተሰጠው ስልጣን መሰረት የሚከተለውን አውጇል።

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ ድንጋጌ

### 1. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "የሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤት እንደገና ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 55/1998 ዓ.ም" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

www.chilot.me

## 2. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚሰጠው ካልሆነ በስተቀር፣ በዚህ አዋጅ ውስጥ፦

1. "ክልል" ማለት የሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልል ነው ::
2. "ክልል ምክር ቤት" ማለት በሐረሪ ህዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ክልል ህገ-መንግስት አንቀጽ 46(1) የተመለከተው የክልል መንግስት ከፍተኛ የህግ አውጪ አካል ነው::
3. "የመስተዳድር ም/ቤት" ማለት የሐረሪ ህዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የአስፈፃሚ ምክር ቤት ነው::
4. "የክልል መንግስት መ/ቤት" ማለት ቢሮ፣ ዘርፍ፣ ኮሚሽን፣ ጽ/ቤት፣ ባለሥልጣን፣ ተቋም፣ ኤጀንሲ ወይም ማናቸውም ሌላ የክልሉ መንግስት መ/ቤት ነው::
5. "ድርጅት" ማለት ማናቸውም በሙሉ ወይም በከፊል የክልሉ መንግስት የሆነ የማምረቻ፣ የማከፋፈያ፣ የአገልግሎት ሰጭ ወይም ሌላ የንግድ ድርጅት ነው::
6. "ዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤት" ማለት በዚህ አዋጅ ተጠናክሮ የተቋቋመ የክልሉ ዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤት ነው::
7. "ዋና ኦዲተር" ማለት የክልሉ ዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤት የበላይ ኃላፊ ነው::
8. "ኦዲት" ማለት የፋይናንሻል ኦዲት፣ የክዋኔ ኦዲት፣ የሀብት አጠባበቅና ቁጥጥር ኦዲት፣ እንዲሁም የልዩ ኦዲት ሲሆን በመንግስት ፖሊሲ መሠረት ወደፊት በጥናት ተደግፈው የሚወጡ የኦዲት ዓይነቶችን ጭምር ያካትታል::
9. "የተራድኦ ሂሳብ" ማለት ብሔራዊ ክልላዊ መንግስቱ ወይም የዚሁ መንግስት ማናቸውም መ/ቤት ወይም ድርጅት በዓይነት ወይም በጥሬ ገንዘብ ከእርዳታ ሰጪ አካላት የተቀበለው የብድር ወይም የእርዳታ ሂሳብ ነው::

## 3. እንደገና ስለመቋቋም

የሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ዋና ኦዲተር መ/ቤት /ከዚህ በኋላ "መሥሪያ ቤቱ" እየተባለ የሚጠራ/ የሕግ ሰውነት ያለውና ራሱን የቻለ የክልሉ መንግስት አካል ሆኖ በዚህ አዋጅ እንደገና ተቋቁሟል።

## 4. የመሥሪያ ቤቱ ዓላማዎች

መሥሪያ ቤቱ በዚህ አዋጅ መሠረት የሚከተሉት አበይት ዓላማዎች ይኖሩታል።

1. የክልሉን ዕቅድና በጀት በሚገባ ለመምራትና ለማስተዳደር የሚያስፈልገውን አስተማማኝ መረጃ ለማግኘት የሚረዳ የኦዲት ሥርዓት መመሥረትና ማጠናከር፣
2. የክልሉ መንግሥት ገንዘብና ንብረት አግባብ ባላቸው ህጎች፣ ደንቦችና መመሪያዎች መሠረት መሰብሰቡን፣ መጠበቁንና በአግባቡ ሥራ ላይ መዋሉን ማረጋገጥ፣
3. አግባብነት ካላቸው አካላት ጋር በመተባበር በክልሉ ውስጥ የሂሳብ አያያዝና የኦዲት ሙያ እንዲያድግና እንዲዳብር ጥረት ማድረግ፣
4. የክልሉ መንግስት መስሪያ ቤቶችና ድርጅቶች ሂሳብ ኦዲት የሚደረግበትን የኦዲት ደረጃ ማውጣትና ተግባራዊ መሆኑን መከታተል።

## 5. የመ/ቤቱ አቋም

መሥሪያ ቤቱ፦

1. አንድ ዋና ኦዲተር
2. የኦዲት ዳይሬክተሮች /የኦዲት መምሪያ ኃላፊዎች
3. የኦዲት ሥራ አስኪያጆች /የኦዲት ዋና ክፍል ኃላፊዎች
4. በተለያዩ ደረጃ የሚገኙ ኦዲተሮችና
5. ሌሎች አስፈላጊ ባለሞያዎች እና የድጋፍ ሰጭ ሠራተኞች ይኖሩታል።

# ክፍል ሁለት

# የክልሉ ዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤት ሥልጣንና ተግባር

## 6. የመሥሪያ ቤቱ ሥልጣንና ተግባር

1. መሥሪያ ቤቱ በህግ የተሰጠውን ተግባር ለማከናወን የሚያስፈልገው ሥልጣን ሁሉ ይኖረዋል።
2. በዚህ አጠቃላይ አነጋገር ሳይወሰን መሥሪያ ቤቱ፦

ሀ/ የክልሉን መንግስት መሥሪያ ቤቶችና ድርጅቶች ሂሳብ፣ የተራድኦ ሂሳብና ስጦታዎችን ጭምር ኦዲት ያደርጋል፣ ያስደርጋል፣

ለ/ የክልሉ መንግስት መሥሪያ ቤቶችና ድርጅቶች ያስገኙት ውጤት ሕጉን የተከተለ ፣ ኢኮኖሚያዊ በሆነ አሰራር የተፈጸመ መሆኑንና ተፈላጊውን ግብ መምታቱን ለማረጋገጥ እንደአስፈላጊነቱ የክዋኔ ኦዲት ያደርጋል፣ ያስደርጋል።

ሐ/ የክልል መንግስቱ መስሪያ ቤቶችና ድርጅቶች አጠቃላይ የቁጥጥር ሥርዓት በበቂ ሁኔታ መነደፉንና በትክክለኛ መንገድና በብቃት ተግባራዊ መሆኑን ለማረጋገጥ የሀብት አጠባበቅና ቁጥጥር ኦዲት ያደርጋል፣ ያስደርጋል።

መ/ የክልሉ መንግስት ዋጋው ከብር 500,000 (አምስት መቶ ሺህ ብር) በላይ የሆነ ሥራ ለግል የሥራ ተቋራጮች በውል የሰጠ እንደሆነ ይህንኑ መንግስት ነክ የግል ሥራ ተቋራጮች ሂሳብ ኦዲት ያደርጋል፣ ያስደርጋል። ይሁን እንጂ ዋና ኦዲተሩ በጉዳዩ ላይ ወንጀል ተፈጽሟል ብሎ በሚያምንበት ወይም ለመፈጸሙ ጥርጣሬ ወይም በቂ ፍንጭ በሚያገኝበት በማናቸውም ጊዜ ሁሉ ከተጠቀሰው የገንዘብ መጠን በታች የሆነን ሂሳብ ኦዲት ያደርጋል፣ ያስደርጋል።

www.chilot.me

ሠ/ በምክር ቤቱ፣ በክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት እና በክልሉ ፍርድ ቤቶች አግባብ ያለው ጥያቄና ትዕዛዝ ሲቀርብ እንዲሁም የጉዳዩ ክብደት ላይ ተመስርቶ ከመንግስት መ/ቤቶች፣ ከድርጅቶችና ከህብረተሰቡ በሚቀርቡ ጥያቄና ጥቆማ በመነሳት በሂሳቡ ላይ ተንክል በመሠራቱ ፍንጭ ከታየ ወይም ግድፈትና ጉድለት ከተገኘ ከመደበኛው ኦዲት ውጪ ልዩ ኦዲት ያከናውናል፣እንዲከናወን ያደርጋል፣

ረ/ ከዚህ በላይ የሰፈሩት ድንጋጌዎች መሠረት ያከናወነውን የኦዲት ሥራ ውጤት አግባብ ላለው የመንግስት መ/ቤት ወይም ድርጅት የበላይ ኃላፊ ያሳውቃል፣ የኦዲት ውጤቱ ወንጀል መፈጸሙን የሚያሳይ ሆኖ ሲገኝ ወዲያውኑ ለሚመለከተው አካል ሪፖርት ያደርጋል፣

ሰ/ ጉዳዩ ከሚመለከታቸው መሥሪያ ቤቶች እና ድርጅቶች እንዲሁም ከፌዴራልና ከሌሎች ክልላዊ የኦዲት መ/ቤቶች ጋር በመመካከር የኦዲት ደረጃን (ስታንዳርድ) እና የአሠራር ሥርዓት መወሰኛ መመሪያዎችን ያወጣል፣

ሸ/ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ከሚመለከታቸው መሥሪያ ቤቶችና ድርጅቶች ጋር በመተባበር ለውስጥ ኦዲተሮች ተገቢውን ሥልጠናና የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ምስክርነት ይሰጣል፣

ቀ/ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ማናቸውም የውስጥ ኦዲተሮች የቢሮአቸውን፣ የጽህፈት ቤታቸውን ወይም የድርጅታቸውን ሂሳብና ንብረት ኦዲት አድርገው ውጤቱን እንዲገልጹለት ያስደርጋል፣

በ/ አንድ ሂሳብ ወንጀል ባለበት ሁኔታና ታማኝነት በጎደለው አኳኋን መያዙን ለማመን ምክንያት ያለው እንደሆነ ይህንን ሂሳብ በሚያመለክቱ ጽሑፎች፣ መዘክሮች፣ መዝገቦች፣ ሰነዶችና ከእነዚሁ ጋር ግንኙነት ባላቸው ሌሎች መረጃዎች ላይ ያሽጋል፣

ተ/ የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ ስለገንዘብና የሂሳብ አጠባበቅ በሚያዘጋጃቸው የህግና ደንብ ረቂቆች ላይ አስፈላጊውን ምክርና አስተያየት ይሰጣል፣

ቸ/ ከሚመለከታቸው የፌዴራልና የክልል መንግስታት መስሪያ ቤቶች ጋር በመተባበር የሂሳብ አያያዝና የኦዲት ሙያ ትክክለኛውን ፈር ይዞ እንዲዳብር ጥረት ያደርጋል፣

ኀ/ በክልሉ ውስጥ በኦዲት ሙያ ለሚሰሩ ኦዲተሮችና የሂሳብ አያያዝ ሥራ ለሚያከናውኑ የሂሳብ አዋቂዎች በሥራው መስክ ለመሰማራት የሚያስችለውን የምስክር ወረቀት ይሰጣል፣ያድሳል፣ያግዳል፣ይሰርዛል፣

ነ/ ከፌዴራሉ መንግስት ዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤት ጋር በመመካከር የኦዲተሮችንና የሂሳብ አያያዝ ባለሙያዎችን የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ለመስጠት፣ ለማገድና ለመሰረዝ የሚያስችል ወጥነት ያለው መመሪያ ያወጣል፣

ኘ/ የምስክር ወረቀቶችን በሚሰጥበትና በሚታደስበት ጊዜ በዚሁ አዋጅ መሠረት በሚወጣ ደንብ የሚወሰነውን የአገልግሎት ዋጋ ያስከፍላል፣

## ፯· ውክልና ስለመስጠት

1. መሥሪያ ቤቱ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 6 ንዑስ አንቀጽ 2 ከፊደል ተራ ቁጥር ሀ እስከ ሠ በሰፈሩት ድንጋጌዎች ሥር የተመለከቱትን ሥልጣንና ተግባራት እንደ አስፈላጊነቱ ከፌዴራል ዋና ኦዲተር ድጋፍና እገዛ ሊጠይቅ ይችላል። እንዲሁም በስምምነት ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤት፣ ለሌሎች ክልላዊ የኦዲት መሥሪያ ቤቶች ወይም ለግል የኦዲት ሥራ ድርጅቶች በውክልና ሊሰጥ ይችላል።
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ድንጋጌ መሠረት ውክልና የተሰጣቸው የኦዲት አካላት በመስሪያ ቤቱ የወጣውን የኦዲት ደረጃ እና የአሰራር ሥነ ሥርዓት መከተልና የደረሱበትን ውጤት ለመ/ቤቱ የማሳወቅ ኃላፊነት ይኖርባቸዋል።
3. መ/ቤቱ በውክልና ተቀባይ አካል የተደረገው ኦዲት የኦዲት ደረጃውን የተከተለ መሆኑን ያረጋግጣል፣ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝም የኦዲት አገልግሎት ወጪ በኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች እንዲሸፈን ያደርጋል።

# ክፍል ሶስት

# የክልሉ ዋና ኦዲተር የአሿሿም ሥነ ሥርዓት

## ፰· የእጩ አቀራረብና የአሿሿም ሥነ ሥርዓት

1. የክልሉ ዋና ኦዲተር በክልሉ ርዕሰ መስተዳደር አቅራቢነት በምክር ቤቱ ይሾማል።
2. እንደ ክልሉ ተጨባጭ ሁኔታ ተሿሚው በኦዲት ሙያና በፋይናንስ ሥራ አመራር እንዲሁም በመንግስት ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች ረገድ ተገቢውን የትምህርት ዝግጅትና ስልጠና የተካበተ የሥራ ልምድና አስተማማኝ የብቃት ደረጃ እንዲኖረው ያስፈልጋል።
3. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 2 ሥር የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ እጩ ተሿሚው በታታሪነቱ በታማኝነቱ በሥነ ምግባሩ መልካም ስም ያተረፈ መሆን ይገበዋል።

## ፱· ከፖለቲካ ፓርቲ አባልነት ገለልተኛ ስለመሆን

፩· ዋና ኦዲተሩ ከማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ አባልነት ገለልተኛ ይሆናል።

፪· በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ሥር የተደነገገው ቢኖርም ዋና ኦዲተሩ በፖለቲካ ፓርቲ ውስጥ ገብቶ በየትኛውም ደረጃ መሳተፍ ከፈለገ በቅድሚያ ሥራውን መልቀቅ ይኖርበታል።

## 10· ክፍያ

የዋና ኦዲተሩ ደመወዝ፣ አበልና ልዩ ልዩ ጥቅማጥቅሞች በርዕሰ መስተዳድሩ መነሻ አቅራቢነት በክልሉ ምክር ቤት ይወሰናል። ሆኖም ምክር ቤቱ በማይሰበሰብበት ወቅት የፌዴራል እና የክልል ኦዲት መሥሪያ ቤቶችን

www.chilot.me

ተምክሮ በማገናዘብ በመስተዳድሩ ምክር ቤት ሊወሰን ይችላል።

## 11· ተጠሪነት

መሥሪያ ቤቱም ሆነ ዋና ኦዲተሩ ተጠሪነታቸው ለምክር ቤቱ ይሆናል፣

## 12· የሥራ ዘመን

1· የዋና ኦዲተሩ የሥራ ዘመን አስራ ሁለት ዓመት ይሆናል።

2· በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ሥር የተመለከተው የሥራ ዘመን ሲያበቃ ዋና ኦዲተሩ በምክር ቤቱ ከታመነበት እንደገና ሊሾም ይችላል።

## 13· ተሿሚው ከኃላፊነት ስለሚነሳበት ምክንያት

ዋና ኦዲተሩ ከሚከተሉት ምክንያቶች በአንዱ ወይም በሌላው ከኃላፊነት ሊነሳ ወይም ከሥራ ሊሠናበት ይችላል።

1. በህመም ምክንያት ሥራውን በሚገባ ለማከናወን የማይችል መሆኑ ሲረጋገጥ፣
2. ግልጽ የሆነ የሥራ ችሎታ ማነስ የሚታይበት ሆኖ ሲገኝ፣
3. በሥራው ላይ በሚያሳየው ቸልተኝነት ሳቢያ ጥፋተኛ ወይም ምግባረ ብልሹ ሆኖ ሲገኝ፣
4. ሙስና ወይም ሕግን የሚጻረር የወንጀል ድርጊት መፈፀሙ በበቂ ማስረጃ ሲረጋገጥ፣
5. ምክር ቤቱ ካስፈለገው አገልግሎቱን ለማራዘም የሚኖረው ስልጣን እንደተጠበቀ ሆኖ በህግ ከተወሰነው የጡረታ መውጫ እድሜ ሲደርስ፣
6. የሥራ ዘመኑ ሲያበቃ፣
7. በገዛፈቃዱ ሥራውን ለመልቀቅ በጽሁፍ ሲጠይቅ።

## 14· ክፍት የሥራ ቦታን ስለመሙላት

1· የክልሉ ዋና ኦዲተር በዚህ አዋጅ አንቀጽ 13 ሥር በተዘረዘሩት ምክንያቶች፣ ከኃላፊነት የተነሳ፣ ከሥራ የተሰናበተ ወይም ከዚህ ዓለም በሞት የተለየ እንደሆነ የክልሉ ርዕሰ መስተዳድር ከኦዲት ዳይሬክተሮች ወይም በኦዲት ዳይሬክተሮች ቦታ ተመድቦ የሚሰራውን አንዱን በጊዜያዊነት መድቦ ሊያሰራ ይችላል።

## ክፍል አራት

## የክልሉ ዋና ኦዲተር ሥልጣንና ተግባር

## 15· የዋና ኦዲተሩ ሥልጣንና ተግባር

የክልሉ ዋና ኦዲተር የመሥሪያ ቤት የበላይ ኃላፊ በመሆን በዚህ አዋጅ አንቀጽ 6 ሥር ለመሥሪያ ቤቱ የተሠጠውን ሥልጣንና ተግባር በሥራ ላይ ከማዋል በተጨማሪ ከዚህ የሚከተሉት ዝርዝር ስልጣንና ተግባር ይኖሩታል፣

1. የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ አዘጋጅቶ የሚልከውን የክልሉን መንግሥት የተጠቃለለ ሂሳብ በደረሰው ስድስት ወራት ውስጥ ኦዲት አድርጎ የተገኘውን ውጤት ከአስተያየት ጋር ለቢሮው ይመልሣል፣
2. ስለመሥሪያ ቤቱ አጠቃላይ የሥራ እንቅስቃሴ ዓመታዊ ዘገባ ለምክር ቤቱ ያቀርባል፣
3. ለምክር ቤቱ በሚቀርቡ የክልሉ መሥሪያ ቤቶችና ድርጅቶች የኦዲት ሪፖርቶች ላይ የመንግስት በጀትና ፋይናንስ ቋሚ ኮሚቴ ተገቢውን ክትትል እያደረገ ወቅታዊ እርምጃ ስለሚወስድበት ሁኔታ ያማክራል፣
4. ዓመታዊና የተጠቃለለ ዘገባ ለማቅረብ እስከ ተወሰነ ጊዜ ድረስ ሊቆይ በማይችሉ፣ አስፈላጊና አፋጣኝ ናቸው ብሎ ባመነባቸው ጉዳዮች ላይ ልዩ ዘገባ አዘጋጅቶ ለምክር ቤቱ ያቀርባል፣
5. ተግባሩን በሚገባ ለማከናወን ይቻለው ዘንድ መሥሪያ ቤቱን ያደራጃል፣
6. የመሥሪያ ቤቱን የበጀት ግምት አዘጋጅቶ ለምክር ቤቱ ያቀርባል፣ ሲፈቀድም በሥራ ላይ ያውላል፣
7. ለመሥሪያ ቤቱ የተፈቀደው አጠቃላይ በጀት ተግባርና ኃላፊነቱን በተሟላ ሁኔታ ለመወጣት በቂ ሆኖ ባልተገኘ ጊዜ የተጨማሪ በጀት ፈቃድን በሚመለከት ልዩ ጥያቄ ለምክር ቤቱ ወይም ምክር ቤቱ በማይሰበሰብበት ጊዜ እርሱ ለሚወክለው አካል ሊያቀርብ ይችላል፣
8. አስፈላጊ ሆኖ ባገኘው ጊዜ በክልሉ መንግስት መሠረታዊ የፋይናንስ አስተዳደር መርሆዎች መሠረት በመስሪያ ቤቱ የውስጥ በጀት ዝውውር ላይ ይወስናል፣
9. የሠራተኞችን ቅጥርና አስተዳደር በክልሉ መንግስት ሲቪል ሰርቪስ ማስተዳደሪያ ሕግ፣ ደንብና መመሪያ መሠረት ይፈጽማል፣
10. የመሥሪያ ቤቱ ኦዲተሮች ሊከተሉት የሚገባውን ዝርዝር የሙያ ሥነ-ምግባር መመሪያ ያዘጋጃል፣
11. ለመስሪያ ቤቱ ከተፈቀደው የበጀት ወሰን ሳያልፍ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ሙያዊ አገልግሎት ለማግኘት ይቻለው ዘንድ ውሎችን ሊዋዋል ይችላል፣
12. ኃላፊነቱን በተሟላ ሁኔታ ለመወጣት ይቻለው ዘንድ መጽሐፍቶች፣ መዘክሮችን፣ መዝገቦችን፣ ሠነዶችንና ሌሎች መረጃዎችን ለመመልከትና አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ከሕዝብ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት መረጃዎችን፣ ዘገባዎችንና ትንተናዎችን ጠይቆ መቀበል ይችላል፣
13. ለምክር ቤቱ በሚቀርቡ የመንግስት ሂሳብና ኦዲት ሪፖርቶች/ የተጠቃለለ ፈንድ ሂሳብ /የመሥሪያ ቤቱን ሥራዎች የሚገልጹ ዓመታዊ ዘገባና ልዩ ዘገባዎች ላይ መፈረምን ሳይጨምር በዚህ አንቀጽ ሥር የተሰጡትን ስልጣንና ተግባራት በውክልና ሊሰጥ ይችላል።

www.chilot.me

# ክፍል አምስት

# ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

## 16. ስለ መሥሪያ ቤቱ የሂሳብ ምርመራ

የመሥሪያ ቤቱ ሂሳብ በምክር ቤቱ በሚሰየም ብቁ እና ነፃ በሆነ ኦዲተር ተመርምሮ ውጤቱ ለምክር ቤቱ ይቀርባል::

## 17. ስለ ኦዲት ሥርዓት፣ ወሰንና የጊዜ ገደብ

1. መሥሪያ ቤቱ አንድን ሂሳብ ኦዲት ሲያደርግ እንደነገሩ ሁኔታ አንድ በአንድ በዝርዝር ወይም አልፎ አልፎ የኦዲት ዘዴ ሊጠቀም ይችላል:: ቢሆንም በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፯ ንዑስ አንቀጽ ፪ ከፊደል ተራ ቁጥር ሀ እስከ ሠ በሰፈሩት ድንጋጌዎች መሠረት ሂሳቦችን ኦዲት አድርጎ በሚያቀርበው ዘገባ ውስጥ ለእያንዳንዱ ሂሳብ የኦዲት ዘዴውን፣ ሁኔታና ጥልቀት መግለጽ አለበት፣

2. መሥሪያ ቤቱ የሚያከናውናቸው የኦዲት ሥራዎች ኦዲት ከሚደረግበት የበጀት ዓመት ወደኃላ ከሁለት የበጀት ዓመታት ማለፍ የለባቸውም:: ነገር ግን ወንጀል ተፈጽሟል ብሎ ያመነ እንደሆነ ሁለት የበጀት ዓመታት ወደኃላ አልፎም ቢሆን ኦዲት ሊያደርግ ይችላል::

## 18. የኦዲት ተደራጊዎች ግዴታ

1. ማንኛውም ሰው ኦዲተሩ ለኦዲት ሥራ አስፈላጊ ናቸው ያላቸውን ሰነዶች፣ የቃል ማስረጃዎችና ወይም ሌሎች መረጃዎች እንዲያቀርብ በተጠየቀ ጊዜ ወዲያውኑ የማቅረብ ግዴታ አለበት::

2. መስሪያ ቤቱ እንዲቆጣጠራቸው በዚህ አዋጅ ሥልጣን የተሰጠውን አካላት ገንዘብ ወይም ንብረት የተረከበ፣ ወጪ ያደረገ፣ የከፈለ ወይም የሂሳቡ ኃላፊ የሆነ ማንኛውም ሰው ሲጠየቅ ሂሳቡን ኦዲት የማስደረግ ግዴታ አለበት::

3. ኦዲት ተደራጊ መሥሪያ ቤቶች በመሥሪያ ቤቱ በተላኩ ሪፖርቶች ውስጥ የተገለጹ ግኝቶችን አስመልክቶ ተገቢውን የእርምት እርምጃ እንዲወስዱ በተሰጠው የማሻሻያ ሐሳቦችና አስተያየቶች መሠረት ከ 30 ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ እርምጃ የመውሰድና ውጤቱን የማሳወቅ ግዴታ አለባቸው::

4. ማንኛውም ኦዲት ተደራጊ አካል መሥሪያ ቤቱ ተግባርና ኃላፊነቱን ለመወጣት ይቻለው ዘንድ ለመደበው ኦዲተር ሥራውን ለማካሄድ የሚያስችለውን የተሟላ ቢሮ አዘጋጅቶ የመስጠት ግዴታ አለበት::

## 19. የመተባበር ግዴታ

መሥሪያ ቤቱ ሥልጣኑንና ተግባሩን ሥራ ላይ ለማዋል እንዲችል ማንኛውም ሰው አስፈላጊውን ድጋፍ መስጠት ይኖርበታል::

## 20- የማስታወቅ ግዴታ

1. የመሥሪያ ቤቱ:-
የክልሉ ዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤት የኦዲት ሥራ በሚያከናውንበት ጊዜ ወንጀል መፈጸሙን የሚያሳምን በቂ ምክንያት ያገኘ እንደሆነ ይህንኑ አግባብ ላለው የክልሉ ፍትህ አካል እና ለሚመለከታቸው አካላት የማስታወቅ ግዴታ አለበት፣

2. የሌሎች አካላት:-
ዋናዉ ኦዲተር በዚህ አዋጅ የተሰጡትን ተግባር በአግባቡ ለመወጣት ያስችለው ዘንድ በክልሉ ውስጥ ተፈፃሚነት ያላቸው መመሪያዎች እንዲወጡ ሲደረግ የሚመለከተው አካል ለዋናው ኦዲተር የማሳወቅ ግዴታ አለበት::

## 21. ጥፋትና ቅጣት

ማንኛውም ሰው:-

1. መሥሪያ ቤቱ ለምርመራ እንዲቀርቡለት የሚጠይቃቸውንና ተገቢነት ያላቸውን ሠነዶች፣ የቃል ማስረጃዎችና /ወይም ሌሎች መረጃዎችን ያላቀረበ፣
2. ሐሰተኛ መሆኑን እያወቀ ወይም እውነተኛ መሆኑን ለማመን ምክንያት ሳይኖረው ማንኛ ውንም መረጃ ለዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤት ወይም ለወኪሉቹ የሰጠ፣
3. መሥሪያ ቤቱ ሥራውን በሚገባ እንዳያከናውን ያሰናከለ፣
4. ያለበቂ ምክንያት በዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤት በቀረቡ የኦዲት ሪፖርቶች ላይ በተሰጡ የማሻሻያ አስተያየቶችና ሐሳቦች መሠረት ወቅታዊ እና አጥጋቢ እርምጃ ያልወሰደ፣
5. የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎች እንዲፈጽም በተጠየቀ ጊዜ ፍቃደኛ ሆኖ ያልተገኘ እንደሆነ አግባብ ባለው ህግ ይቀጣል::

## 22- ደንብና መመሪያ የማውጣት ሥልጣን

1. ለዚህ አዋጅ ተፈፃሚነት የሚያስፈልገውን ደንብ ምክር ቤቱ ሊያወጣ ይችላል፣
2. መሥሪያ ቤቱ ለዚህ አዋጅና በአዋጁ መሠረት ለሚወጡ ደንቦች ሙሉ ተፈጻሚነት የሚያግዙ ዝርዝር መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል::

## 23. የተሻሩና ተፈፃሚነት የማይኖራቸው ሕጎች

www.chilot.me

1. የሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የዋናው ኦዲተር መሥሪያ ቤትን ለማቋቋም የወጣው አዋጅ ቁጥር 19/1991 ዓ/ም በዚህ አዋጅ ተሽሯል።
2. ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረን ማንኛውም ህግ፣ደንብ፣መመሪያ ወይም የተለመደ አሠራር በዚህ አዋጅ ውስጥ በተጠቀሱ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም፣

## 24. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ ከመጋቢት 1ቀን 1998 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል።

**ሐረር መጋቢት 1 ቀን 1998 ዓ.ም**

**ሙራድ አብዱልሃዲ**

**የሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ**

**መንግስት ኘሬዝዳንት**

www.chilot.me

የሐረሪ ህዝብ ክልላዊ መንግስት

# ሐረር ነጋሪ ጋዜጣ

# HARAR NEGARI GAZETA

OF THE HARARI PEOPLE REGIONAL STATE

| | |
|---|---|
| 11ኛ አመት ቁጥር 4<br>11th year No.4 | ሐረር ነሐሴ 17 ቀን 1998<br>Harar Aug 23/2006 |

| | | |
|---|---|---|
| ያንዱ ዋጋ ብር 3:00<br>Unit Price Bir. 3:00 | በሐረሪ ሕዝብ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ | የፖስታ ሣጥን ቁጥር 272<br>P.o .Box |

## ማውጫ

አዋጅ ቁጥር 56/1998 ዓ.ም
የሐረሪ ህዝብ ክልል ም/ቤት የቤቶች ልማት ፕሮጀክት ጽ/ቤትን ለማቋቋም የወጣ አዋጅ ............ገጽ 444

## አዋጅ ቁጥር 56/1998 ዓ.ም
## የሐረሪ ህዝብ ክልላዊ መንግስት
## የቤቶች ልማት ፕሮጀክት ጽ/ቤትን
## ለማቋቋም የወጣ አዋጅ

በሐረር ከተማ ውስጥ በዋነኛ ችግርነት የሚነሳውን የመኖሪያ ቤቶች ዕጥረት መቅረፍና ደረጃውን ያልጠበቁ ቤቶች በአብዛኛው ፈርሰው መገንባት የቤት ልማት ዕቅዱ አንዱ አካል በመሆኑ፤

የቤት ዕጥረቱን ለመፍታት በከተማው ነባርና ማስፋፊያ አካባቢዎች ወጪ ቆጣቢ የሆኑ ቴክኖሎጂዎችን በመጠቀም ደረጃቸውን የጠበቁ ቤቶች እንዲገነቡ ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

በከተማው ፕላን መሰረት የነዋሪውን የኢኮኖሚ ደረጃ ባገናዘበ፤ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪውን በሚያጠናክርና የሥራ ዕድል በሚፈጥር ሁኔታ ዋጋና የጥራት ደረጃውን በሚያሟላ መልኩ እንዲሰሩ ማድረግ በማስፈለጉ፤

በርካታ የመኖሪያ ቤቶች ግንባታ በአጭር ጊዜ ውስጥ ለማከናወን የሚያስችል የተቀናጀ የቤቶች ልማት ፕሮግራም ዕቅድ አዘጋጅቶ ተግባራዊ ማድረግ ተገቢ በመሆኑ፤

ፍትሃዊ፣ ግልጽ፣ ቀልጣፋና ውጣ ውረድ በሌለው ቀላል በሆነ ስነ-ሥርዓት፣ እዲሁም የተጠቃሚዎች የፆታ ተዋፅኦ በሚያረጋግጥና የገቢ አቅምን ግምት ውስጥ በሚያስገባ የክፍያ መጠንና የአከፋፈል ሁኔታ የተገነቡ ወይም የሚገነቡ ቤቶችን

www.chilot.me

ለከተማው ነዋሪዎች የሚያስተላልፍና ከቤቶች ግንባታ እስከ ኮንስትራክሽን ያሉትን የሥራ ሂደቶችን በበላይነት የሚመራና የሚያስፈጽም የቤቶች ልማት ፕሮጀክት ጽ/ቤትን በህግ ማቋቋም በማስፈለጉ፤

በተሻሻለው የሐረሪ ህዝብ ክልል ህገ-መንግስት አንቀጽ 51 ንዑስ አንቀጽ 2(ሀ) ላይ በተደነገገው መሰረት የክልሉ ምክር ቤት ይህንን አዋጅ አውጥቷል::

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

### 1. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ ''የሐረሪ ህዝብ ክልል የቤቶች ልማት ፕሮጀክት ጽህፈት ቤት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 56/1998'' ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል::

### 2. ትርጓሜ

በዚህ አዋጅ ውስጥ:-

1. ''ክልል'' ማለት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግስት አንቀጽ 47 (1) (9) መሠረት የተቋቋመው የሐረሪ ህዝብ ክልል ነው::
2. '' መስተዳድር ምክር ቤት'' ማለት በክልሉ ህገ-መንግስት ከፍተኛ የአስፈፃሚነት ሥልጣን የተሰጠው አካል ነው::
3. '' ከተማ'' ማለት የሐረር ከተማ ነው::
4. ''ግንባታ'' ማለት ቤትና ከቤት ጋር ተያያዥነት ያለው የግንባታ ሥራ ነው::
5. ''ቦርድ'' ማለት በዚህ አዋጅ መሠረት የተቋቋመ የክልሉ መንግስት የቤቶች ልማት ፕሮጀክት ጽህፈት ቤት ቦርድ ነው::
6. ''ሰው'' ማለት ማንኛውም የተፈጥሮ ወይም በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው::

### 3. መቋቋም

የሐረሪ ህዝብ ክልል የቤቶች ልማት ፕሮጀክት ጽህፈት ቤት ከዚህ በኋላ '' ጽህፈት ቤቱ'' እየተባለ የሚጠራ ራሱን የቻለና ህጋዊ ሰውነት ያለው የሐረሪ ህዝብ ክልላዊ መንግስት መሥሪያ ቤት ሆኖ ተቋቁሟል::

### 4. የጽህፈት ቤቱ ዓላማ

ጽህፈት ቤቱ ከዚህ የሚከተሉት አቢይ ዓላማዎች ይኖሩታል:-

1. ዝቅተኛና መካከለኛ ገቢ ያላቸውን የከተማ ነዋሪዎች የቤት ችግር ለመቅረፍ ወጪ ቆጣቢ የሆኑ ቴክኖሎጂዎችን በመጠቀም ቤት ማቅረብ፣ የከተማውንም ገጽታ መቀየር::
2. ጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማትን በቤት ልማት ፕሮግራም በማሳተፍ መስኩን ማስፋፋትና ማጠናከር::
3. በጽህፈት ቤቱ የሚገነቡትን የጋራ መኖሪያ ቤቶችን ለከተማው ነዋሪዎች ፍትሃዊ፣ ግልጽ፣ ቀልጣፋና ውጣ-ውረድ በሌለው ቀላል በሆነ ሥነ-ስርዓት እንዲሁም የተጠቃሚዎችን የፆታ ተዋጽኦ በሚያረጋግጥና የገቢ አቅምን ግምት ውስጥ በሚያስገባ የክፍያ መጠንና የአከፋፈል ሁኔታ እዲተላለፍ ማድረግ ነው::

## ክፍል ሁለት

## የጽህፈት ቤቱ አደረጃጀት፣ ስልጣንና ተግባር

### 5. የጽህፈት ቤቱ አደረጃጀት

ሀ/ ጽ/ቤቱን በበላይነት የሚመራ አንድ ቦርድ፤
ለ/ ዋና ሥራ አስኪያጅ እና
ሐ/ ለሥራው የሚያስፈልጉ በቂ ሠራተኞች ይኖሩታል::

## 6. የቦርዱ አደረጃጀትና ተጠሪነት

1. ከሚመለከታቸው የባለ ድርሻ አካላት የተውጣጣ አመራር ሰጭ ቦርድ በዚህ አዋጅ መሠረት ተቋቁሟል:: ጽህፈት ቤቱም በዚህ ቦርድ ይመራል::
2. የቦርዱ ተጠሪነት ለክልሉ መስተዳድር ምክር ቤትና ለር/መስተዳድሩ ይሆናል::

## 7. የቦርዱ አባላት

1. የክልሉ ም/ፕሬዝዳንት .................................. ሰብሳቢ
2. የቤቶች ልማት ፕሮጀክት ጽ/ቤት ኃላፊ....አባልና ፀሐፊ
3. የሐረር ከተማ ማዘጋጃ ቤት ሹም.......................አባል
4. የክልሉ ን/ኢ/ከ/ል ቢሮ ኃላፊ ........................ አባል
5. የትምህርትና አቅም ግንባታ ቢሮ ኃላፊ.............. አባል
6. የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ ኃላፊ ............ አባል
7. የህዝብ አ/ማ/ጉ/ቢሮ ኃላፊ .......................... አባል

## 8. የቦርዱ ሥልጣንና ተግባር

ቦርዱ በዚህ አዋጅ መሠረት የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል :-

1. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 10 ለጽ/ቤቱ የተሰጡት ስልጣንና ተግባራት በትክክል ስራ ላይ መዋላቸውን ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል፤
2. ጽህፈት ቤቱ የሚጠናከርበትንና አሰራሩ የሚሻሻልበትን መንገድ ይቀይሳል፤
3. የጽቤቱን ሥራ አስኪያጅ በመምረጥ ለክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት አቅርቦ ያፀድቃል፣ ደመወዙንና ጥቅማ ጥቅሙን ይወስናል፤
4. ተጠሪነታቸው ለሥራ አስኪያጁ የሆኑትን መምሪያ ኃላፊዎች ቅጥርና ስንብት ያፀድቃል፤ ደሞዝና አበላቸውን አስጠንቶ ይወስናል፤
5. የጽህፈት ቤቱን ዓመታዊ የፋይናንስ የስራ አፈፃፀም ሪፖርቶችን ገምግሞ አስፈላጊውን መመሪያ በመስጠት አቅጣጫ ያስቀምጣል፤
6. የክልሉን የቤቶች ልማት መድረክ፣ እስትሪንጅ ኮሚቴና ሌሎች አስፈላጊ የሆኑ ኮሚቴዎችን ያቋቁማል፤ የአሰራር መመሪያዎችን ያወጣል፤ ያስተባብራል፤
7. የጽ/ቤቱን የአሠራር መመሪያዎች ተጠንተው ሲቀርቡለት መርምሮ ያፀድቃል፣ በትክክል ሥራ ላይ መዋላቸውን ይከታተላል፤
8. የጽህፈት ቤቱ የሰው ኃይል ፍላጎትና መዋቅር ተጠንቶ ሲቀርብለት መርምሮ ያፀድቃል፣ ያሻሽላል፣ ተግባራዊነቱን ይከታተላል፤
9. የጽህፈት ቤቱ ዓመታዊ ዕቅድና በጀት ተዘጋጅቶ ሲቀርብለት መርምሮ በካቢኔ ያፀድቃል፣ አፈፃፀሙን ይከታተላል፤
10. የጽህፈት ቤቱን አመራር አካላት ቢያንስ በወር አንድ ጊዜ እየተገናኘ በዕቅዱ መሰረት እየተከናወነ ስለመሆኑ የሥራ ሂደቱን ይከታተላል፣ ይገመግማል፣ አስፈላጊውን የአመራር አቅጣጫ ያስቀምጣል፤
11. የቦርድ አባል የሆኑ መስሪያ ቤቶች ለጽህፈት ቤቱ የሚሰጡት ድጋፍና የሚጫወቱት ድርሻ በአግባቡ እየተከናወነ መሆኑን ይከታተላል፣ አመራር ይሠጣል፤
12. በጽህፈት ቤቱ የጥናትና ምርምር አካል እየተዘጋጁ የሚቀርቡ አዳዲስ የግንባታ ቴክኖሎጂዎችና ማቴሪያሎች በሥራ ላይ መዋላቸውን ይቆጣጠራል፤
13. የቦርዱንና የጽ/ቤቱን አጠቃላይ የሥራ አፈፃጸም እና ፋይናንስን በተመለከተ ወቅታዊ ዘገባዎችን ለመስተዳድሩ ም/ቤት ያቀርባል፤
14. የጽህፈት ቤቱን ዓላማዎች ለማራመድና ለማስፈጸም አስፈላጊ የሆኑ ተግባራትን ይፈጽማል ::

www.chilot.me

9. ስለቦርዱ ስብሰባዎች

1. ቦርዱ በወር አንድ ጊዜ ይሰበሰባል፤ ሆኖም አስቸኳይ ስብሰባዎች በማናቸውም ጊዜ በሰብሳቢው ሊጠራ ይችላል::
2. የቦርዱ አባላት ከግማሽ በላይ በስብሰባው ላይ ከተገኙ ምልዓተ ጉባኤ ይሆናል::
3. የቦርዱ ውሳኔ የሚተላለፈው በአብላጫ ድምጽ ነው፤ እኩሌታ ድምጽ ሲገኝ ሰብሳቢው ድምጹን የሰጠበት ወገን, አብላጫ ድምጽ ይሆናል::
4. የቦርድ አባላትን ድርሻና ሌሎች ተዛማጅ ጉዳዮች ላይ መወሰን የሚያስችል የራሱን መመሪያ በማጽደቅ ተግባራዊ ማድረግ ይችላል::

10. የጽህፈት ቤቱ ስልጣንና ተግባር

1. በከተማው ያለውን የቤት ዕጥረት ለማቃለል መንግስት ሊመድብ የሚገባውን በጀትና ሊያደርገው የሚገባውን ድጋፍ እንደዚሁም ለጽ/ቤቱ የሚያስፈልገውን ዓመታዊ በጀት ያዘጋጃል፣ በቦርድ በኩል ለክልሉ መንግስት ያቀርባል፣ ሲፈቀድም በስራ ላይ እንዲውል ያደርጋል፣ አጠቃቀሙን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፤
2. ከከተማው መሪ ፕላን ጋር የተጣጣሙና ለከተማው ውበት አውንታዊ አስተዋፅኦ የሚያደርጉ የቤት ዲዛይኖችን ወጪ በሚቀንስ ሁኔታ ያዘጋጃል ወይም እንዲዘጋጅ ያደርጋል፤
3. የቤቶች ልማትን ለማከናወን የሚያስፈልገው የፋይናንስ አቅርቦት የሚገኝበትን ሁኔታ ያመቻቻል፣ ከሀገር ውስጥ ምንጮች ቦርዱ ሲፈቅድ ገንዘብ ይበደራል፣ ዝርዝሩ በመስተዳድር ምክር ቤት በሚያወጣው ደንብ ይወሰናል፤
4. ከዲዛይን እስከ ኮንስትራክሽን ያሉት የስራ ሂደቶችን ደረጃ በደረጃ እንዲፈፀሙና የቤት ልማቱ ግንባታ ፕሮግራም በቅልጥፍና እንዲከናወን ተገቢውን ስልት ይቀይሳል፣ በስራ ላይ መዋሉንም ያረጋግጣል፤
5. በገበያ ላይ ዕጥረት ያለባቸውን የቤት ልማቱ ግንባታ ግብአቶች ጥቅል ግዢ በመፈፀም የዋጋና የዕቃ ጥራት ተጠቃሚ መሆን የሚቻልባቸው ሁኔታዎች ሲኖሩ በሃገር ውስጥና ከውጭ አገር ዕቃዎችን ይገዛል፤
6. ወጣት ተኮር የአካባቢ ልማት ፕሮግራም አፈፃፀም አጠቃላይ የግንባታ ስራዎችን ይሰራል፤
7. ለቤቶች ልማት ፕሮግራም በሚመደብ በጀት አስፈላጊ የሆኑ ቁሳቁሶችንና የግንባታ ዕቃዎችን ግዢ ከሀገር ውስጥ ይፈጽማል፤
8. በማዘጋጃ ቤቱና በክልሉ መንግስት ድጋፍ የሚከናወኑ የቤት ልማት ፕሮግራሞች ጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማትን በሰፊው የሚያሳትፉ እንዲሆኑ አመቺ የአሰራር ስርዓቶችን ይዘረጋል፤
9. አነስተኛና ጥቃቅን ተቋማትን በቤት ልማት ፕሮግራሞች በማሳተፍ አቅማቸው እንዲጎለብት ያደርጋል፤
10. በቤት ልማት ዘርፍ የተሰማሩ የጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማት የአቅም ግንባታ ስራዎችን ያስተባብራል፣አስፈላጊ ድጋፎችን እንዲያገኙ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፤
11. በጽህፈት ቤቱ የተገነቡ ወይም የሚገነቡ የኮንዶሚኒየም ህንፃዎች ህጋዊ በሆነ ግልጽ አሰራር መሰረት ለተጠቃሚዎች ያስረክባል፤
12. በከተማ ቁልፍ የሆኑት ችግሮች አንዱ የሆነውን የመኖሪያ ቤት እጥረት ለማቃለል በከተማው ነባርና በማስፋፊያ አካባቢ ወጪ ቆጣቢ የሆነ ቴክኖሎጂ በመጠቀም ደረጃቸውን የጠበቁ ቤቶች በመገንባት የግንባታ ኢንዱስትሪን ያጠናክራል ወይም ኮንትራት በመስጠት እንዲገነቡ ያደርጋል፤

www.chilot.me

13. በከተማው ለሚገነቡ ቤቶች የመሬትና የመሰረተ ልማት አቅርቦት መኖሩን ከሚመለከታቸው ጋር በመቀናጀት ያረጋግጣል፤
14. ለቤቶች ልማት የሚፈለጉ ቦታዎችን ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ቅንጅት በመፍጠር እንዲዘጋጁ ያደርጋል፤
15. ከግንባታ ኢንዱስትሪ ጋር በተያያዘ የሥልጠና ስርዓት በመዘርጋት ብቁ ባለሙያዎችን ለማፍራት ዕገዛ ያደርጋል፤
16. የንብረት ባለቤት መሆን፣ መከራየት፣ ውል መዋዋል፣ ለመሸጥና በስሙ ለመክሰስና ለመከሰስ ይችላል፤
17. ዓላማውን ለማስፈጸም የሚያስችሉ ተዛማጅ ተግባራትን ያከናውናል::

## 11. ስለ ጽህፈት ቤቱ ሥራ አስኪያጅ፣ሌሎች ኃላፊዎችና ሠራተኞች

1. የጽህፈት ቤቱ ስራ አስኪያጅ በቦርዱ አቅራቢነት በክልሉ መስተዳደር ምክር ቤት ይሾማል፣ ተጠሪነቱም ለቦርዱ ይሆናል::
2. የጽህፈት ቤቱ መምሪያ ኃላፊዎች በማኑዋሉ መሰረት በሥራ አስኪያጁ አቅራቢነት በቦርዱ ይመደባሉ::

## 12. የጽህፈት ቤቱ ሥራ አስኪያጅ ሥልጣንና ተግባር

የጽህፈት ቤቱ ሥራ አስኪያጅ ተጠሪነቱ ለቦርዱ ሆኖ ከዚህ ቀጥሎ የተዘረዘሩት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል:-

1. ሥራ አስኪያጁ የፕሮጀክት ጽህፈት ቤቱ ዋና ሥራ አስፈፃሚ ሆኖ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 10 ለጽ/ቤቱ የተሰጡት ሥልጣንና ተግባራትን በሥራ ላይ ያውላል፣ በበላይነት ይመራል፣ ተቋሙን ያስተዳድራል፣ ይቆጣጠራል፤
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተመለከተው አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ ሥራ አስኪያጁ፤
   ሀ. በክልሉ ውስጥ በተቀናጀ የቤት ልማት ፕሮግራም የሚከናወኑ ግንባታ ሥራዎችን ያስተባብራል፣ ይመራል፣ የልምድና የተሞክሮ ልውውጦችን እንዲካሄዱ ያደርጋል፤
   ለ. የጽ/ቤቱን ዓመታዊ የስራ ፕሮግራም በጀት ያዘጋጃል፣ ፕሮግራሙ የሚተገበርበት ስታንዳርድ ያወጣል፣ ሲጸድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፤
   ሐ. ለጽ/ቤቱ የተፈቀደው በጀትና የሥራ ፕሮግራም ተግባራዊ መሆናቸውን ያረጋግጣል፣ የክንውንና የሂሳብ ሪፖርት አዘጋጅቶ ለቦርዱና ለክልሉ የፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ ያቀርባል፤
   መ. በግንባታው ሥራ ላይ የሚሰማሩት የሥራ ተቋራጮችን ለመመልመል የሚያስፈልጉ መመዘኛዎችን እንዲወጣ ያደርጋል፣ ምልመላውና የማጣራቱ ሥራ በአግባቡ መከናወኑን ይቆጣጠራል፤
   ሠ. በከተማው የሚከናወኑ የቤት ልማት ግንባታ ሥራዎች በመርሃ ግብሩ መሠረት መከናወናቸውን ያረጋግጣል፣ አስፈላጊውን የቴክኒክና አስተዳደራዊ ድጋፍ ይሰጣል፤
   ረ. ከውጭና ከሀገር ውስጥ በጅምላ ግዢ የሚገቡ የግንባታ ማቴሪያሎች ክምችትና ሥርጭት በአግባቡ የሚከናወንበትን ሥርዓት በመዘርጋት አፈፃፀሙን ይቆጣጠራል፤
   ሰ. በክልሉ ውስጥ የሚከናወኑ የቤት ልማት የግንባታ ሥራዎች በየጊዜው እየተሻሻሉ በአዳዲስ የግንባታ ቴክኖሎጂዎች፣ በአማራጭ የግንባታ

ማቴሪያሎች እየዳበሩ እንዲሄዱ የምርምር፣ የጥናትና የስልጠና ተግባራት እንዲከናወኑ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፤

ሸ. በአሰሪና ሰራተኞች አዋጅ ቁጥር 377/1996 (እንደ ተሻሻለው) እና በክልሉ ሲቪል ሰርቪስ ህግ መሠረታዊ መርሆዎች መሠረት ተዘጋጅቶ በርዱ በሚያፀድቀው የጽ/ቤቱ የሰራተኛ አስተዳደር ማኑዋል መሠረት ሰራተኞችን ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል፣ ያሰናብታል፤

ቀ. በቦርዱ ማስጸደቁ እንደተጠበቀ ሆኖ ተጠሪነታቸው ለእርሱ የሆኑትን የጽህፈት ቤቱ አላማ አስፈፃሚ የስራ ኃላፊዎች በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2(ሸ) በተገለጸው ማኑዋል መሰረት ያስተዳድራል፣ ይመድባል የስራ ዝርዝራቸውን ይገልፃል፣ የዲሲፕሊን እርምጃ ይወስዳል፣ ከሥራም ያሰናብታል፤

በ. ከሶስተኛ ወገኖች ጋር በሚደረጉ ግንኙነቶች ሁሉ ጽ/ቤቱን ይወክላል፤

ተ. በክልሉ ለሚካሄደው የቤቶች ልማት ፕሮግራም ማስፈጸሚያ የሚሆን ቋሚ የቤቶች ልማት ፈንድ የሚቋቋምበትንና የፋይናንስ ምንጩ በየጊዜው እየሰፋ የሚሄድበትን መንገድ ያጠናል፣ አፈፃፀሙንም ይመራል፣ ይከታተላል፤

3. ሥራ አስኪያጁ ለጽ/ቤቱ የሥራ ቅልጥፍና በሚያስፈልገው መጠን ስልጣንና ተግባሩን በከፊል ወይም በሙሉ ለበታች የሥራ ኃላፊዎች በውክልና መስጠት ይችላል ።

## ክፍል ሦስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

13. በጀት

የጽህፈት ቤቱ የበጀት ምንጮች የሚከተሉት ይሆናሉ:-

1. በክልሉ መንግስት የሚመደብ በጀት፤
2. በቦንድ ሽያጭ ወይም በሀገር ውስጥ ምንጮች በክልሉ መንግስት ወይም በክልሉ መንግስት ስም በብድር የሚገኝ ገንዘብ፤
3. የቤት ልማትን ለማገዝ ከለጋሽ ድርጅቶች እና ግለሰቦች የሚገኝ ድጋፍ፤
4. ከተጠቃሚዎች የሚከፈል ክፍያ።

14. አስተዳደራዊ ጉዳዮች

ጽህፈት ቤቱ በቦርዱ የጸደቀ የራሱ የሆነ መዋቅር፣ የደሞዝ እስኬል፣ ጥቅማ ጥቅም፣ የፋይናንስ እና የንብረት አስተዳደር፣ የዕቃ ግዥ አጠቃቀም መመሪያዎች እንዲሁም ሠራተኞቹ የሚተዳደሩበት የክልሉ መንግስት ሰራተኞችና የአሰሪና ሠራተኛ ጉዳይ ህግጋትን መሰረታዊ መርሆዎች በመከተል የተዘጋጀ መመሪያ ይኖረዋል።

15. የሒሳብ መዛግብት

1. ጽህፈት ቤቱ የተሟሉና ትክክለኛ የሆኑ የሒሳብ መዛግብትን ይይዛል፤
2. በሒሳብ መዛግብቱና በገንዘብም ሆነ ንብረት ነክ ሰነዶች አያያዝና አጠባበቅ ረገድ ተቀባይነት ያላቸውን የድርብ ሒሳብ አሠራር መርሆዎች ይከተላል።

16. የሒሳብ ምርመራ

የጽህፈት ቤቱ የሂሳብ መዛግብትና ገንዘብም ሆነ ንብረት ነክ ሰነዶች በክልሉ ዋና ኦዲተር መስሪያ ቤት ይመረመራል፣ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ካቢኔው በሚሰይማቸው የውጭ ኦዲተሮች የኦዲት ምርመራ ሊያደርግ ይችላል።

www.chilot.me

**17. የመተባበር ግዴታ**

ማንኛውም ሰው ጽህፈት ቤቱ ሥራውን በሚያከናውንበት ጊዜ የመተባበር ግዴታ አለበት::

**18. የጽህፈት ቤቱ የሥራ ዘመን**

1. የፕሮጀክት ጽ/ቤቱ የሥራ ዘመን የተቀናጀ የቤቶች ልማት ፕሮግራም እስከሚያበቃ ጊዜ ድረስ ይሆናል፤ ሆኖም የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት የጽህፈት ቤቱን የሥራ ዘመን ማብቂያ በተለየ ሁኔታ እንዲያጥርም ሆነ እንዲረዝም ማድረግ ይችላል፤
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ድንጋጌ ቢኖርም የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት በጥናት ላይ ተመስርቶ የጽህፈት ቤቱን ሥልጣንና ተግባር በማሻሻል ከሌሎች የክልሉ መንግስት ተቋማት ጋር እንዲዋሃድ በማድረግ የቤት ልማቱን ሥራ ለማስቀጠል ይችላል::

**19. የተፈፃሚነት ወሰን**

ይህ የቤቶች ልማት ፕሮጀክት ጽ/ቤት በዚህ አዋጅ ከመቋቋሙ በፊት በጽ/ቤቱ ስም የተፈጠሩ የተለያዩ መብቶችና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ መሠረት እንደተፈጸሙ ተቆጥሮ ለጽ/ቤቱ መብትና ግዴታዎቹ ተላልፈዋል::

**20. ደንብና መመሪያ የማውጣት ሥልጣን**

1. ይህንን አዋጅ ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ ደንቦችን የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ሊያወጣ ይችላል፤
2. ቦርዱ ለአዋጁና በአዋጁ መሠረት ለሚወጡ ደንቦች ተፈፃሚነት የሚረዱ ዝርዝር ማንዋሎችና መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል::

**21. ተፈፃሚነት ስለማይኖራቸው ህጎች**

ይህንን አዋጅ የሚቃረኑ ማናቸውንም ህግ ወይም የአሠራር ልምድ በዚህ አዋጅ ውስጥ የተደነገጉትን ጉዳዮች በሚመለከት ተፈፃሚነት አይኖራቸውም::

**22. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ አዋጅ ከነሃሴ 17 ቀን 1998 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል::

ሐረር ነሐሴ 17 ቀን 1998 ዓ.ም
ሙራድ አብዱልሃዲ
የሐረሪ ሕዝብ ክልላዊ መንግስት
ፕሬዝዳንት

www.chilot.me

የሐረሪ ሕዝብ ክልላዊ መንግስት

# ሐረር ነጋሪ ጋዜጣ
# HARAR NEGARI GAZETA
OF THE HARARI PEOPLE REGIONAL STATE

11ኛ ዓመት ቁጥር 5
11th year No 5

ሐረር ነሐሴ 18 ቀን 1998 ዓ.ም
HARAR Aug 24/ 2006

ያንዱ ዋጋ ብር 2
Unit Price Br. 2

በሐረሪ ሕዝብ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

የፖስታ ሣጥን ቁጥር 272
P.O.Box

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር 57/1998ዓ.ም
የሐረሪ ሕዝብ ክልላዊ መንግስት ለ1999 በጀት ዓመት ሥራዎች የታወጀ የበጀት አዋጅ ——————————ገጽ 451

## አዋጅ ቁጥር 57/1998 ዓ.ም
## በሐረሪ ሕዝብ ክልላዊ መንግሥት ለ1999 በጀት አመት ሥራዎች የታወጀ የበጀት አዋጅ

ለ1999 የበጀት ዓመት በክልሉ መንግሥት ለሚከናወኑ ሥራዎችና አገልግሎቶች የሚያስፈልገዉን በጀት በበጀት ዓመቱ መጀመሪያ ላይ አጠቃሎ በማጽደቅ ሥራ ላይ ማዋል አስፈላጊ በመሆኑ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገ መንግሥት አንቀጽ 52 (2) (ሠ)መሠረት ክልሉ የራሱን በጀት የማጽደቅና ሥራ ላይ ስማዋል በተሰጠው ስልጣንና በክልላዊ መንግሥቱ ህገ መንግሥት አንቀጽ 51 (2) (ሀ) መሠረት የሚከተሰው ታዉጇል፡፡

### ክፍል 1
### ጠቅላላ

**አንቀጽ 1**

ይህ አዋጅ «የሐረሪ ህዝብ ክልላዊ መንግስት የ1999 በጀት ዓመት በጀት አዋጅ ቁጥር 57/1998»ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**አንቀጽ 2**

ከሐምሌ 1/1998 ጀምሮ እስከ ሰኔ 30/1999 በሚፈጸመው በአንድ የበጀት ዓመት ጊዜ ዉስጥ በክልሉ ከሚገኘው ገቢ እና ከሌላ ገንዘብ ላይ ከዚህ ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ ዉስጥ ለተጠቀሱት ሥራዎችና አገልግሎቶች ቀጥሎ እንደተመለከተው፤

ሀ. ለመደበኛ ወጪዎች ብር 82,093,300

ለ. ለካፒታል ወጪዎች ብር 50,159,700

ሐ. መጠባበቂያ በጀት ብር 16,277,000

ድምር 148,530,000

/አንድ መቶ አርባ ስምንት ሚሊዮን አምስት መቶ ሰላሳ ሺህ ብር /ለክልሉ መንግሥት መስተዳደር ወጪ ሆኖ እንዲከፈል በዚህ አዋጅ ተፈቅዷል፡፡

**አንቀጽ 3**

ለፕሮፌሽናል ለልዩ ልዩ አገልግሎቶች እንደዚሁም ለሥራ ማስኬጃ የተፈቀደው መደበኛ በጀት ወደ ደመወዝና አበል ማዛወር አይቻልም፡፡

**አንቀጽ 4**

ለካፒታል በጀት ከተፈቀደው ወደ መደበኛ በጀት ማዛወር አይቻልም

**አንቀጽ 5**

በየወሩ ሳይቋረጥ እየተከፈለ የሚያልቅሆኖ ለቋሚ የመንግስት ሠራተኞች አስፈላጊ ለሆኑ ጉዳዮች መመሪያ በማውጣት የደመውዝ ቅድሚያ ክፍያ ለመስጠት፤ የክፍያዉንም ጊዜ ለመወሰንና በዚህ አኳኋን በሚሰጠው ብድር ላይ ባንክ በሚያስከፍለው ወለድ መሠረት በዓመቱ እስከ 12% ወለድእንዲያስከፍል ለክልሉ ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ ሥልጣን ተሰጥቶታል፡፡

### ክፍል 2
### የበጀት አስተዳደር

**አንቀጽ 6**

የሐረሪ ህዝብ ክልላዊ መንግሥት አካላት ሥልጣን፤

1. የክልሉ የመንግሥት አካላት የበላይ ኃላፊዎች ለየመሥሪያ ቤቶቻቸው ሥራና አገልግሎት በዚህ አዋጅ የተፈቀዱላቸዉን በጀት በሚጠይቁበት ጊዜ የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ ከክልሉ ገቢና ከሌላ ምንጭ እንዲከፍል ታዚል፡፡

2. የበጀት ዝውውር ስልጣን ለሚከተሉት አካላት ተሰጥቶአል፤

www.chilot.me

ሀ. <u>የሐረሪ ህዝብ ክልላዊ መንግሥት መስተዳድር ምክር ቤት</u>

1- በጀት ተፈቅዶለት በመከናወን ላይ ካለ የካፒታል በጀት በበጀት አመቱ በጀት ሳልተፈቀደለት አዲስ የካፒታል በጀት፣

2- መደበኛ በጀት ከተፈቀደለት አርእስት /ንዑስ አርዕስት/ በበጀት ሽመቱ መደበኛ በጀት ሳልተፈቀደለት አዲስ አርዕ ስት/ንዑስ አርዕስት/፣

3- ለመደበኛ በጀት ከተፈቀደው ወደ ካፒታል በጀት፣

4- ለመጠባበቂያ ከተያዘው በጀት ወደ ሴሎች ወጪዎች

5- ለክልሉ መንግስት ለመደበኛም ሆነ ለካፒታል ወጪ ተፈቅዶ በሥራ ላይ ያልዋለዉን ተራፊ በጀት ወደ ሴሎች ወጪዎች

6- በቀበሌ መስተዳደር የተመደበዉን በጀት በገ/ኢ/ልማት ቢሮ በኩል እንዲደለደሉ ዉክልና ይሰጣል::

ለ. <u>የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ</u>

1- በዚህ አዋጅ አንቀጽ 6(2) (ሀ) ከተሰጠው በስተቀር፤ጉዳዩ የሚመለከታቸው አካላት ሲጠይቁ በአንዱ መደበኛ በጀት አርዕስት ዉስጥ ከአንድ ንዑስ አርዕስት ወደ ሌላ ንዑስ አርዕስት በየሂሳብ መደቡ እና፤

2- በጀት ተፈቅዶለት በመከናወን ላይ ካለ የካፒታል በጀት ጉዳይ የሚመለከታቸው አካላት ሲጠይቁ ከአንድ ንዑስ አርዕስት ወደ ሌላ ንዑስ አርዕስት በየሂሳብ መደቡ የቢሮ ሐላፊ ወይም ውክልና የሚሰጠው አካል ይፈቅዳል::

3- ለመደበኛ በጀት ከተፈቀደው ደመወዝና አበል ወደ ሥራ ማስኬጃ የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ ኃላፊ ሲፈቅድ ብቻ ዝውውር ይፈጸማል::

4- በበጀት ዓመቱ የመንግስት መ/ቤቶች ከተለያዩ ድርጅቶች በአይነት የሚያገኙትን ስጦታ በተጨማሪም በጀት እንዲመዘገቡ ጥያቄ ሲቀርብ የቢሮ ኃላፊ ወይም ውክልና የተሰጠው አካል ይፈቅዳል ::

ሐረር ነሐሴ 18 1998

ሙራድ አብዱልሐዲ

የሐረሪ ህዝብ ክልል መንግሥት

ፕሬዝዳንት

www.chilot.me

# የሐረሪ ሕዝብ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት የ1999 በጀት ዓመት የገቢ የዉጭ ዕርዳታና ብድር ማጠቃለያ

| | ብር |
|---|---|
| ሀ/ **መደበኛ ገቢ** | |
| የታክስ ገቢ | 16 ,000,000 |
| ታክስ ያልሆኑ ገቢ | 4,000,000 |
| ልዩ ልዩ ገቢዎች (ከለፉት አመታት ተመላሽ በጀት) | 8,000,000 |
| **የመደበኛ ገቢ ድምር** | 28,000,000 |
| ለ/ **የፌደራል መንግስት ድጎማ** | |
| ከግምጃ ቤት | 117,120,000 |
| ከውጭ ዕርዳታ | 1,810,000 |
| ከውጭ ብድር | 1,600,000 |
| **የድጎማ ድምር** | 120 ,530, 000 |
| **ጠቅላላ ድምር** | 148,530,000 |

www.chilot.me

# የሐረሪ ህዝብ ክልላዊ መንግስት የ1999 በጀት
# አመት ወጪና የወጪ አሸፋፈን

## 1. ወጪ

### ሀ/ መደበኛ ወጪ

| | በሴክተር መ/ቤት | በቀበሌ መስ/ጽ/ቤት | ጠ/ድምር |
|---|---|---|---|
| አስ/ርና ጠቅላላ አ/ገ ዘርፍ | 20,440,700 | 7,686,900 | 28,127,600 |
| ኢኮኖሚ ልማት ዘርፍ | 8,219,600 | 1,132,200 | 9,351,800 |
| ማህበራዊ አገልግሎት ዘርፍ | 29,167,000 | 15,446,900 | 44,613,900 |
| **የመደበኛ በጀት ድምር** | 57,827,300 | 24,266,000 | 82,093,300 |
| መጠባበቂያ በጀት | | | 16,277,000 |
| *ጠቅላላ ድምር* | | | ***98,370,300*** |

### ለ/ ካፒታል ወጪ

| | | | |
|---|---|---|---|
| ኢኮኖሚ ልማት አገልግሎት | 20,318,400 | 3,700,900 | 24,019,300 |
| ማህበራዊ አገልግሎት | 10,009,000 | 2,836,200 | 12,845,200 |
| ለአስ/ ና ጠቅላላ አገልግሎት | 3,047,600 | 10,247,600 | 13,295,200 |
| **የካፒታል በጀት ጠቅላላ ድምር** | 33,375,000 | 16,784,700 | 50,159,700 |
| **ጠቅላላ ወጪ ድምር** | | | |

## 2. የወጪ አሸፋፈን

### ሀ/ የአገር ውስጥ ገቢ

| | |
|---|---|
| የታክስ ገቢ | 16,000,000 |
| ታክስ ያልሆነ ገቢ | 4,000,000 |
| ልዩ ልዩ ገቢዎች . | 8,000,000 |

**የአገር ውስጥ ገቢ ድምር** ------------------------------------------------ **ብር** 28,000,000

በጀት መርጃ ከመ/ግ/ ቤት ---------------------------------------ብር 117,120,000

**የበጀት መርጃ ድምር**---------------------------------------------- -**ብር** 117,120,000

**ጠቅላላ የገቢ ድምር**---------------------------------------------- -**ብር** 145,120,000

### ለ/ የወጭ እርዳታ

የጥሬ ገንዘብ እርዳታ -----------------------------ብር 1,810,000

**የውጭ እርዳታ ድምር** ----------------------------------------------- -**ብር** 1,810,000

### ሐ/ የውጭ ብድር

ከውጭ ብድር -------------------------------------ብር 1,600,000

**የብድር ድምር** ------------------------------------------------------------ -**ብር** 1,600000

**የገቢ የእርዳታና የብድር ጠቅላላ ድምር** ---------------------------------- **ብር** 148, 530, 000

www.chilot.me

## የሐረሪ ህዝብ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት ገቢ
## የ1999 በጀት ዓመት

| የሂሳብ መደብ | የገቢው አይነት | ብር |
|---|---|---|
| | **ጠቅላላ ገቢ** | **148,530,000** |
| | **የክልሉ ገቢ** | **28,000,000** |
| 1100 | ቀጥታ ታክስ | 14,399,500 |
| 1100-1110 | ከገቢ ከትርፍና ከካፒታል ዋጋ ዕድገት ገቢ ግብር | |
| 1101 | ምንዳና ደሞዉዝ | 5,395,300 |
| 1102 | ከኪራይ ገቢ ግብር | 50,000 |
| 1103 | የግለሰቦች የንግድ ሥራ ትርፍ ግብር | 3,668,200 |
| 1106 | ከካፒታል ዋጋ ዕድገት ጥቅም | 57,600 |
| 1107 | ከግብርና ስራ ገቢ ግብር | 111,500 |
| 1109 | ከገቢ ዕቃዎች የቅድሚያ ገቢ ግብር | |
| 1111 | የወለድ ገቢ ግብር | |
| 1112 | የጫት ገቢ | 5,116,900 |
| 1120-1190 | የተጨማሪ እሴት ታክስ | |
| 1120-1160 | የአገር ውስጥ ከሚመረቱ ዕ/ተ/ዕ/ታ/ | |
| 1169 | ሌሎች ዕቃዎች | |
| 1170-90 | የአገልግሎት ተጨማሪ እሴት ታክስ | |
| 1176 | ስራ ተቋራጭ | |
| 1200 | አገር ዉስጥ የሚመረቱ የዕቃዎች ሽያጭ | 1,927,400 |
| **1220-40** | **ተርን ኦቨር ታክስ** | **592,600** |
| 1224 | ከምግብ | 148,200 |
| 1225 | ከለስላሳ መጠጥ | 12,000 |
| 1227 | ከአልኮልና የአልኮል መጠጥ | 26,000 |
| 1228 | ከቢራ | 17,000 |
| 1231 | ጥጥ፡ድርና ማግ፡ ጨርቃ ጨርቅ ልብሶ | 40,000 |
| 1232 | ከቆዳና የቆዳ ውጤቶች | 8,000 |
| 1234 | ብረትና ቆርቆሮ | 49,400 |
| 1235 | የዕህፈት መሣሪያ | |
| 1237 | እርሻና እርሻ ውጤት | 80,000 |
| 1238 | እንጨትና የእንጨት ዉጤቶች | 22,000 |
| 1249 | ከሌሎች | 190,000 |
| **1250-70** | **የአገልግሎት ተርን ኦቨር ታክስ** | **1,123,300** |
| 1252 | ከጋራዥ | 99,100 |
| 1253 | ከልብስ ንጽህና | 4,300 |
| 1254 | ከልብስ ስፌት | 18,500 |
| 1255 | ጥብቅና | 2,400 |
| 1256 | ከፎቶ ግራፍ ፎቶ ኮፒ ማንሳት | 45,000 |
| 1258 | ከስራ ተቋራጭ | 345,100 |
| 1259 | ከመኝታ ቤት | 350,700 |
| 1263 | ከህዝብ መዝናኛ | 6,900 |
| 1264 | ከጸጉር ማስተካከልና ቁንጅና ሣሎን | 61,300 |

www.chilot.me

| | | |
|---|---|---|
| 1265 | ቱርስት ማስተናገድ | |
| | | |
| 1279 | ከሌሎች አገልግሎት | 190,000 |
| **1290** | **ቴምብር ሽያጭና ቀረጥ** | **211,500** |
| 1291 | ከቴምብር ሽያጭ | 45,100 |
| 1292 | ከቴምብር ቀረጥ | 166,400 |
| 1400 | ታክስ ያልሆኑ ገቢዎች | |
| **1410-1420** | **ከፍቃድና ከሌሎች ክፍያዎች** | **307,300** |
| 1413 | የሥራ ፈቃድ | 24,900 |
| 1414 | የፍርድ ቤት መቀጫ | 33,600 |
| 1415 | ዳኛነት | 106,700 |
| 1417 | የንግድ ድርጅትና የባለሙያ ምዝገባና የንግድ ፍቃድ ክፍያ | 78,300 |
| 1418 | የመጋዘን ኪራይ | |
| 1429 | ሌሎች ፍቃዶችና ክፍያዎች | 63,800 |
| **1430-1450** | **ከመንግስት የዕቃና የአገልግሎት ሽያጭ** | **1,889,200** |
| 1431 | የመንግስት ጋዜጦች መጽሄቶችና ህተመ. | |
| 1433 | የማስታወቂያ | |
| 1434 | የእንስሳትና ህክምና አገልግሎት | 34,700 |
| 1436 | የመድኃኒትና የሕክምና ዕቃዎች ሽያጭ | 94,300 |
| 1437 | የጤና ምርመራና ሕክምና | 711,200 |
| 1439 | የታተሙ ቅጾች | 218,900 |
| 1441 | የወህኒ ቤቶች አስተዳድር | 163,900 |
| 1451 | የመንገድ ትራንስፖርት አገልግሎት | 644,800 |
| 1456 | የደን ውጤቶች ሽያጭ | 21,400 |
| 1459 | ከሌሎች ዕቃዎችና አገልግሎቶች | |
| **1460-1470** | **የመንግስት ኢንቪስትመንት ገቢ** | **1,135,200** |
| 1465 | ለመንግስት ሠራተኞች ከተሰጠ ብድር | 65,000 |
| 1468 | ከገጠር መሬት መጠቀሚያ ክፍያ | 100,000 |
| | መደበኛ ያልሆኑ እና ልዩ ልዩ ገቢዎች | |
| 1489 | ልዩ ልዩ ገቢዎች | 970,200 |
| 4000 | ልዩ ልዩ ገበቢች ከለፉት ዓመታት ተመላሽ በጀት | |
| | **ድጎማ** | **120,530,000** |
| 1610 | የፌደራል መንግስት ድጎማ | 117,120,000 |
| 3000 | ከውጭ ብድር | 1,600,000 |
| 2000 | ከውጭ እርዳታ | 1,810,000 |

www.chilot.me

# የሐረሪ ህዝብ ክልላዊ መንግስት
## የ1999 ዓመት መደበኛ በጀት

መደበኛ በጀት

| አገልግሎት<br>ዘርፍ<br>አርዕስት<br>ን/አርዕስት | | | |
|---|---|---|---|
| | | 09 የሐረሪ ህ/ብ/ክ/መንግስት | |
| | | 100 አስተዳደርና ጠቅላላ አገልግሎት | 20,440,700 |
| | | 110 የመንግስት ልዩ ልዩ ክፍሎች | 4,286,400 |
| | | 111 የክልሉ ምክር ቤት | 1,574,900 |
| | | 01 የክልል ም/ቤት ጽ/ቤት | 1,242,600 |
| | | 02 ሐረሪ ብሄራዊ ጉብኤ | 212,500 |
| | | 03 የህዝብ ተወካዮች ጉባኤ | 119,800 |
| | | 113 ዋና ኦዲት መ/ቤት | 948,400 |
| | | 115 ፕሬዚዳንት ጽ/ቤት | 1,569,400 |
| | | 119 ሴቶች ጉዳይ ጽ/ቤት | 203,700 |
| | | 121 ፍትህና ጸጥታ ጉዳይ ቢሮ | 1,403,000 |
| | | 122 ጠቅላይ ፍርድ ቤት | 2,725,100 |
| | | 127 ፖሊስ ኮሚሽን | 4,998,500 |
| | | 129 ማረሚያ ቤቶች ኮሚሽን | 2,804,500 |
| | | 134 የሚሊሺያ ጉዳይ ጽ/ቤት | 479,200 |
| | | 152 ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ | 2,371,200 |
| | | 01 አስተዳደርና ጠቅላላ አገልግሎት | 2,348,100 |
| | | 04 ግብር ይግባኝ ሰሚ | 23,100 |
| | | 153 ማስታወቂያና ህዝብ ግንኙነት ቢሮ | 598,500 |
| | | 155 ሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን | 764,300 |
| | | 200 ኢኮኖሚ አገልግሎት | 8,219,600 |

www.chilot.me

| | | | |
|---|---|---|---|
| | 210 | ግብርናና የተፈጥሮ ሀብት | |
| | 211 | ግብርና ገጠር ልማት ቢሮ | 3,778,100 |
| | | | |
| | 231 | ንግድ ኢንዱስትሪ ከተማ ልማት ቢሮ | 2,318,600 |
| | 232 | አነስተኛና ጥቃቅን ንግድ ማ/ማ/ጽ/ቤት | 261,000 |
| | 235 | የኢንቬስትመንት ጽ/ቤት | 146,900 |
| | 273 01 | የመንገድ ስራ ባለስልጣን | 772,000 |
| | 275 | ቤቶች ልማት ፕሮጀክት | 943,000 |
| | 300 | ማህበራዊ አገልግሎት | 29,167,000 |
| | 310 | አጠቃላይ ትምህርት | 11,979,900 |
| 311 | 01 | ትምህርትና አቅም ግንባታ ቢሮ | 5,445,800 |
| | 03/01 | ከፍትኛ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች | 3,010,200 |
| | 06/01 | የመምህራን ማሰልጠኛ ተቋም | 1,170,600 |
| | 05 01 | የቴክንክና ሙያ ማሰልጠኛ ኮሌጅ | 2,353,300 |
| 340 | 01 | ጤና | 13,569,900 |
| | 341 | ጤና ጥበቃ ቢሮ | 1,876,000 |
| | 04/01 | ነርስ ማሰልጠኛ ትምህርት ቤት | 1,419,300 |
| | 03 | ሆስፒታሎች | 10,274,600 |
| | 03/01 | ህይወት ፋና ሆስፒታል | 5,200,000 |
| | 03/02 | ምስራቅ አርበኛ ሆስፒታል | 3,684,500 |
| | 03/03 | ሳንባ ነቀርሳ ሆስፒታል | 1,390,100 |
| | 351 | ህዝብ አደረጃጀት ባህል ማ/ጉዳይ ቢሮ | 3,617,200 |
| | | የሴክተር ቢሮዎች የመደበኛ ወጪዎች | 57,827,300 |
| | 400 | ልዩ ልዩ ወጪዎች | |
| | 461 | መጠባበቂያ በጀት | 16,277,000 |
| | 09/00/000/ | ቀበሌ መስተዳደር ጽ/ቤት | 24,266,000 |
| | | | |
| | | ጠቅላላ ድምር | 98,370,300 |

| | | |
|---|---|---|
| 1265 | ቱርስት ማስተናገድ | |
| | | |
| 1279 | ከሌሎች አገልግሎት | 190,000 |
| **1290** | **ቴምብር ሽያጭና ቀረጥ** | **211,500** |
| 1291 | ከቴምብር ሽያጭ | 45,100 |
| 1292 | ከቴምብር ቀረጥ | 166,400 |
| 1400 | ታክስ ያልሆኑ ገቢዎች | |
| **1410-1420** | **ከፍቃድና ከሌሎች ክፍያዎች** | **307,300** |
| 1413 | የሥራ ፈቃድ | 24,900 |
| 1414 | የፍርድ ቤት መቀጫ | 33,600 |
| 1415 | ዳኝነት | 106,700 |
| 1417 | የንግድ ድርጅትና የባለሙያ ምዝገባና የንግድ ፍቃድ ክፍያ | 78,300 |
| 1418 | የመጋዘን ኪራይ | |
| 1429 | ሌሎች ፍቃዶችና ክፍያዎች | 63,800 |
| **1430-1450** | **ከመንግስት የዕቃና የአገልግሎት ሽያጭ** | **1,889,200** |
| 1431 | የመንግስት ጋዜጦች መጽሄቶችና ህተመ. | |
| 1433 | የማስታወቂያ | |
| 1434 | የእንስሳትና ህክምና አገልግሎት | 34,700 |
| 1436 | የመድኃኒትና የሕክምና ዕቃዎች ሽያጭ | 94,300 |
| 1437 | የጤና ምርመራና ሕክምና | 711,200 |
| 1439 | የታተሙ ቅጾች | 218,900 |
| 1441 | የወሀኒ ቤቶች አስተዳድር | 163,900 |
| 1451 | የመንገድ ትራንስፖርት አገልግሎት | 644,800 |
| 1456 | የደን ውጤቶች ሽያጭ | 21,400 |
| 1459 | ከሌሎች ዕቃዎችና አገልግሎቶች | |
| **1460-1470** | **የመንግስት ኢንቨስትመንት ገቢ** | **1,135,200** |
| 1465 | ለመንግስት ሠራተኛች ከተሰጠ ብድር | 65,000 |
| 1468 | ከገጠር መሬት መጠቀሚያ ክፍያ | 100,000 |
| | መደበኛ ያልሆኑ እና ልዩ ልዩ ገቢዎች | |
| 1489 | ልዩ ልዩ ገቢዎች | 970,200 |
| 4000 | ልዩ ልዩ ገበቢች ከለፉት ዓመታት ተመላሽ በጀት | |
| | **ድጎማ** | **120,530,000** |
| 1610 | የፌደራል መንግስት ድጎማ | 117,120,000 |
| 3000 | ከውጭ ብድር | 1,600,000 |
| 2000 | ከውጭ እርዳታ | 1,810,000 |

www.chilot.me

| | | | |
|---|---|---|---|
| 02-01 | አንደኛና ደረጃ ት/ቤት (አንደኛ ሳይክል) | | 596,800 |
| 02-02 | አንደኛና መለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት | | 7613,00 |
| 341 | ጅኒኤላ ቀበሌ ጤና ጥበቃ ጽ/ቤት | | 32,200 |
| 02-01 | ጅኒኤላ ቀበሌ ጤና ክሊሊክ | | 32,200 |
| **006** | **ሐኪም ቀበሌ መስተዳድር** | **3,051,100** | |
| 111 | ሐኪም ቀበሌ መስተዳድር ጽ/ቤት | | 505,000 |
| 127 | ሐኪም ቀበሌ ፖሊስ ጽ/ቤት | | 418,500 |
| 311 | ሐኪም ቀበሌ ትምህርትና አቅም ግንባታ ጽ/ቤት | | 2,058,700 |
| 02-01 | አንደኛና ደረጃ ት/ቤት (አንደኛ ሳይክል) | | 1,302,700 |
| 02-02 | አንደኛና መለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት | | 756,000 |
| 341 | ሐኪም ቀበሌ ጤና ጥበቃ ጽ/ቤት | | 68,900 |
| 02-01 | ሐኪም ጤና ክለኒ.ክ | | 68,900 |
| **007** | **ድሬጠያራ ቀበሌ መስተዳድር** | **3,548,200** | |
| 111 | ድሬጠያራ ቀበሌ መስተዳድር ጽ/ቤት | | 475,000 |
| 127 | ድሬጠያራ ቀበሌ ፖሊስ ጽ/ቤት | | 349,900 |
| 211 | ድሬጠያራ ቀበሌ ግብርናና ገጠር ልማት ጽ/ቤት | | 338,000 |
| 311 | ድሬጠያራ ቀበሌ ትምህርትና አቅም ግንባታ ጽ/ቤት | | 1,891,100 |
| 02-01 | አንደኛና ደረጃ ት/ቤት (አንደኛ ሳይክል) | | 1,093,000 |
| 02-02 | አንደኛና መለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት | | 798,100 |
| 341 | ድሬጠያራ ቀበሌ ጤና ጥበቃ ጽ/ቤት | | 494,200 |
| 02-01 | ድሬጠያራ ቀበሌ ጤና ክሊሊክ | | 127,100 |
| 02-02 | ድሬ ጠያራ ሐሰንጌይ ጤና ጣቢያ | | 367,100 |
| **008** | **ኤረር ቀበሌ መስተዳድር** | **2,141,900** | |
| 111 | ኤረርቀበሌ መስተዳድር ጽ/ቤት | | 430,300 |
| 127 | ኤረርቀበሌ ፖሊስ ጽ/ቤት | | 336,100 |
| 211 | ኤረር ቀበሌ ግብርናና ገጠር ልማት ጽ/ቤት | | 351,700 |
| 311 | ኤረርቀበሌ ትምህርትና አቅም ግንባታ ጽ/ቤት | | 591,900 |
| 02-01 | አንደኛና ደረጃ ት/ቤት (አንደኛ ሳይክል) | | 380,700 |
| 02-02 | አንደኛና መለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት | | 211,200 |
| 341 | ኤረርቀበሌ ጤና ጥበቃ ጽ/ቤት | | 431,900 |
| 02-01 | ኤረር ቀበሌ ጤና ክሊሊክ | | 165,000 |
| 02-02 | ኤረር ጤና ጣቢያ | | 266,900 |
| **009** | **ሶፊ ቀበሌ መስተዳድር** | **2,786,300** | |
| 111 | ሶፊ ቀበሌ መስተዳድር ጽ/ቤት | | 470,100 |
| 127 | ሶፊ ቀበሌ ፖሊስ ጽ/ቤት | | 290,300 |
| 211 | ሶፊ ቀበሌ ግብርናና ገጠር ልማት ጽ/ቤት | | 442,500 |
| 311 | ሶፊ ቀበሌ ትምህርትና አቅም ግንባታ ጽ/ቤት | | 1,305,800 |
| 02-01 | አንደኛና ደረጃ ት/ቤት (አንደኛ ሳይክል) | | 853,400 |
| 02-02 | አንደኛና መለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት | | 452,400 |
| 341 | ሶፊ ቀበሌ ጤና ጥበቃ ጽ/ቤት | | 277,600 |
| 02-01 | ሶፊ ቀበሌ ጤና ክሊሊክ | | 277,600 |
| | **የ9ኙ ቀበሌ የመደበኛ በጀት ድምር** | | **24,266,000** |

www.chilot.me

# የሐረሪ ህዝብ ክልላዊ መንግስት ለ1999 የካፒታል በጀት

| አስፈፃሚ መ/ቤት | ንዑስ ፕሮግራም | ፕሮጀክት | የፕሮጀክቶች ዝርዝር | የፀደቀ በጀት | የፋይናንስ ምንጭ | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | ከመንግስት | እርዳታ | መለያ | ብድር | መለያ |
| | | | **ጠቅላላ ድምር** | **50,159,700** | **46,749,700** | **1,810,000** | | **1,600,000** | |
| 100 | | | **ጠቅላላ ልማት** | **3,047,600** | **2,947,600** | **100,000** | | | |
| 115 | | | **የክልል ምክር ቤት** | | | | | | |
| 119 | | 008 | Gender & child protection | 15,000 | | 15,000 | | | |
| 122 | | | **ጠቅላይ/ፍ/ቤት** | **599,300** | **599,300** | | | | |
| ጠቅላይ/ፍ/ቤት | 01 | 001 | የጠቅላይ ፍ/ቤት እድሳትና ጥገና /ነባር/ | 118,900 | 118,900 | | | | |
| | | 002 | የገጠር ቀ/አከባቢ ችሎት፣ የከፍተኛ ፍ/ቤት ችሎቶችና ቢሮ ግንባታ | 480,400 | 480,400 | | | | |
| 127 | | | **ፖሊስ ኮሚሽን** | **201,000** | **201,000** | | | | |
| ፖሊስ ኮሚሽን | 01 | 003 | የፖሊስ ማሰልጠኛ ማዕከል ውስጥ ቁሳቁስ ሟሟያ | 201,000 | 201,000 | | | | |
| 152 | | | **የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ** | **728,200** | **643,200** | **85,000** | | | |
| የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ | 02 | 003 | የክልል እምቅ ሃብት ገቢና ማህበራዊ ቀዉስ ጥናት | 157,200 | 157,200 | | | | |
| | 01 | 001 | የገ/ኢ/ል/ቢሮ እድሳት | 143,400 | 143,400 | | | | |
| | 01 | 004 | Population devt. strategy integration | 40,000 | | 4,0000 | | | |
| | 01 | 005 | Advocacy | 20,000 | | 20,000 | | | |
| | 02 | 002 | Capacity Building, Monitoring & Evaluation | 25,000 | | 25,000 | | | |
| | 01 | 006 | በክልሉ በተለያዩ አስፈጻሚ መ/ቤቶች በዩኒሴፍ ድጋፍ ለሚከናወኑ ፕሮጀክቶች የመንግስት ድርሻ መቀናጆ | 137,400 | 137,400 | | | | |
| | 01 | 002 | የቢሮ መጋዘን ዘብ ቤትና ደረቅ ሽንት ቤት ግንባታ ፕሮጀክት | 205,200 | 205,200 | | | | |
| 129 | | | **የማረሚያ ቤቶች ኮሚሽን** | **166,000** | **166,000** | | | | |
| የማረሚያ ቤቶች ኮሚሽን | 01 | 002 | የጀነሬተር ግዢ | 166,000 | 166,000 | | | | |
| 153 | | | **ማስታወቂያና ህዝብ ግንኙነት ቢሮ** | **391,200** | **391,200** | | | | |
| ማስታወቂያና ህዝብ ግንኙነት ቢሮ | 01 | 002 | የFM መደበኛ ስርጭት ማስጀመሪያና ቁሳቁስ ማሟያ | 391,200 | 391,200 | | | | |
| | | | **ፍትህና ፀጥታ ጉዳይ ቢሮ** | 946,900 | 946,900 | | | | |
| | 01 | 001 | የፍትህና ፀጥታ ቢሮ ህንፃ እድሳት | 300,000 | 300,000 | | | | |
| | 01 | 002 | የክልሉ ህገ መንግስትና አዋጆችን በሐረሪና በኦሮምኛ ቋንቋ መተርጎም ሥራ | 646,900 | 646,900 | | | | |
| 200 | | | **ኢኮኖሚ ልማት** | **20,318,400** | **20,183,400** | **135,000** | | | |
| 211 | | | **ግብርናና ገጠር ልማት ቢሮ** | **593,800** | **458,800** | **135,000** | | | |
| ግብርናና ገጠር ልማት ቢሮ | 01 | 002 | የዶሮ ጫጩት ማሳደጊያ ግንባታ | 372,100 | 372,100 | | | | |
| | | 004 | የእንስሳት ላብራቶሪ ክልኒክ ዕቃ ሟሟያ | 70,000 | 70,000 | | | | |
| | | 010 | የእርዳታ እህል ማከማቻ መጋዘን እድሳት | 16,700 | 16,700 | | | | |
| | | 011 | Environment & Sustainable Dry land Management Program | 10,000 | | 10,000 | | | |
| | | 012 | Early warning & disaster preparedness | 15,000 | | 15,000 | | | |
| | | 013 | Rural water supply | 80,000 | | 80,000 | | | |
| | | 014 | Water resource development and utilization | 30,000 | | 30,000 | | | |

www.chilot.me

የቀጠለ

| አስፈፃሚ መ/ቤት | ንዑስ ፕሮግራም | ፕሮጀክት | የፕሮጀክቶች ዝርዝር | የፀደቀ በጀት | የፋይናንስ ምንጭ | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | ከመንግስት | እርዳታ | መለያ | ብድር | መለያ |
| 231 | | | **ንግድ ኢንዱስትሪና ከተማ ልማት ቢሮ** | **7,445,600** | **7,445,600** | | | | |
| ንግድ ኢንዱስትሪና ከተማ ልማት ቢሮ | 01 | 007 | የቢሮ ህንጻ እድሳት | 312,000 | 312,000 | | | | |
| | | 001 | የተሽከርካሪ መፈተኛ መስናክል ሜዳ ግንባታ | 96,000 | 96,000 | | | | |
| | | 008 | የመሬት ካሳ ክፍያ | 6,000,000 | 6,000,000 | | | | |
| | | 003 | የኮንስትራክሽን ላፕራቶሪ ፕሮጀክት | 135,100 | 135,100 | | | | |
| | | 004 | የማስተር ፕላንና የፕሮጀክት አፊስ ማቋቋም | 902,500 | 902,500 | | | | |
| 232 | | | **ጥቃቅንና አነስተኛ ንግድ ሥራዎች ማስፋፊያ ጽ/ቤት** | **2,200,000** | **2,200,000** | | | | |
| ጥቃቅንና አ/ን/ሥ/ማስፋፊያጽ/ቤት | 01 | 001 | የህብረተሰብ ሥልጠና ፕሮጀክት | 200,000 | 200,000 | | | | |
| 300 | | 002 | **ክላስተር ዲቨሎፐመንት ግንባታ ፕሮጀክት** | 1,000,000 | 1,000,000 | | | | |
| | | 003 | **የሌአውት ማዕከል ግንባታ ፕሮጀክት** | 1,000,000 | 1,000,000 | | | | |
| 275 | | | **የመንገድ ባለስልጣን** | **10,079,000** | **10,079,000** | | | | |
| | 01 | 001 | የሶስት መንገዶች አስፋልት ግንባታና ዲዛይን ጥናት እና የ4 አጫጭር መንገዶች አስፋልት ደረጃ ማሳደግ | 10,079,000 | 10,079,000 | | | | |
| | | | **ሶሻል ልማት** | **10,009,000** | **8,944,000** | **1,065,000** | | | |
| 311 | | | **የትምህርትና አቅም ግንባታ ቢሮ** | **3,549,400** | **2,969,400** | **580,000** | | | |
| የትም/ አ /ግ /ቢሮ | 02 | 001 | የአርበኞች 1ኛ ደረጃ ት/ቤት ማስፋፋት እድሳትና ጥገና | 360,000 | 360,000 | | | | |
| | 01 | 022 | የትምህርት በሬዲዮ ስቱዲዮ ማስፋፋት | 75,600 | 75,600 | | | | |
| | 01 | 001 | የ1 አዲስ ከፍ/2ኛ ደረጃ ት/ቤት ግንባታ | 1,100,000 | 1,100,000 | | | | |
| | 01 | 005 | የመድሃኒያለም ሙያ ማሰልጠኛ ኮሌጅ ማስፋፋት | 1103500 | 1,103,500 | | | | |
| | 01 | 006 | የሐረር 2ኛ/ደ/ት/ቤት ማስፋፋት | 125,000 | 125,000 | | | | |
| | 01 | 003 | የትምህትና አቅም ግንባታ ህንጻ ጣሪያ ዕድሳትና ጥገና ፕሮጀክት | 60,600 | 60,600 | | | | |
| | 01 | 004 | 1 ከ/2ኛ ደረጃ ት/ቤት ወደ ቴክኒክና ሙያ ደረጃ ማሳደግ/ነባር/ | 1,100 | 1,100 | | | | |
| | 02 | 008 | የፕላዝማ መለዋወጫ ግዢ | 125,000 | 125,000 | | | | |
| | 01 | 008 | የሐረር ከ/2ኛ/ደ/ት/ቤት የአስተዳደር ቢሮ ግንባታ | 10,300 | 10,300 | | | | |
| | 01 | 025 | የሁለት 1ኛ /ደ/ት/ቤቶች እድሳትና ጥገና | 2,500 | 2,500 | | | | |
| | 02 | 002 | የኤረር ወልዲያ 1ኛ ደ/ማስፋፋት ግንባታ | 2,800 | 2,800 | | | | |
| | 02 | 007 | የኮረሚ 1ኛ ደ/ት/ቤት ማስፋፋት ግንባታ | 3,000 | 3,000 | | | | |
| | 02 | 009 | Teacher in development programe | 90,000 | | 90,000 | | | |
| | | 010 | Basic education USA | 310,000 | | 310,000 | | | |
| | | 011 | Basic education UNICEF | 180,000 | | 180,000 | | | |
| 341 | | | **የጤና ጥበቃ ቢሮ** | **4,300,600** | **3,830,600** | **470,000** | | | |
| የጤና ጥበቃ ቢሮ | 02 | 001 | የም/አ/ሆ/ል ጀነሬተር ግዢ | 77,800 | 77,800 | | | | |
| | 02 | 002 | የነርስ ማሰልኛ ተቋም ማሻሻያ | 832,800 | 832,800 | | | | |
| | 02 | 003 | የሀ/ፋ/ሆ/ል የካርድ መጋዘንና የፋርማሲ ግንባታ | 110,000 | 110,000 | | | | |
| | 02 | 005 | የጤና ቢሮ የጽ/ቤት ግንባታ | 2,660,000 | 2,660,000 | | | | |
| | 02 | 006 | ከሳ/ ነ/ሆ/ል እስከ ሀ/ፋ/ሆ/ል ምፋብ ቤት የሚያገናኝ የላስትራና መንገድና በረንዳ ስራ ፕሮጀክት | 150,000 | 150,000 | | | | |
| | 01 | 018 | Integrated RH &service IEC (UNFPA) | 210,000 | | 210,000 | | | |
| | 01 | 019 | Health & Nutrition (UNICEF) | 180,000 | | 180,000 | | | |
| | 01 | 020 | Higgins & Environmental Sanitation (UNICEF) | 110,000 | | 30,000 | | | |
| | 01 | 021 | HIV AIDS UNICEF | *50,000* | | *50,000* | | | |
| 351 | | | **ህዝብ አደረጃጀት ባህልና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮ** | **1,759,000** | **1,744,000** | **15,000** | | | |
| ህዝብ/አ/ባ/ማ/ራዊ ጉዳይ ቢሮ | 01 | 002 | የሐረሪ ሙዚየም አዳራሽ ኮርኒስ ሥራ | 94,000 | 94,000 | | | | |
| | | 00 | የሐረሪ ባህል ማእከል ግንባታ | 1,000000 | 1,000000 | | | | |
| | | | የሙዚየም ግንባታ ፕሮጀክት | [illegible]00,000 | 500,000 | | | | |

www.chilot.me

የቀጠለ

| አስፈፃሚ መ/ቤት | ንዑስ ፕሮግራም | ፕሮጀክት | የፕሮጀክቶች ዝርዝር | የፀደቀ በጀት | የፋይናንስ ምንጭ | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | ከመንግስት | እርዳታ | መለያ | ብድር | መለያ |
| | | | የሁለገብ እስቲዲየም ግንባታ ፕሮጀክት | 150,000 | 150,000 | | | | |
| | | 006 | Gender & child protection | | | 15,000 | | | |
| 351 | 02 | | **የሐረሪ ቋንቋ አካዳሚ ጽ/ቤት** | 400,000 | 400,000 | | | | |
| **የሐረሪ ቋንቋ አካዳሚ ጽ/ቤት** | | 001 | ሀረሪና አረምኛ የክልሉ መንግስት የሥራ ቋንቋ የሚሆንበትንዝርዝር አፈፃፀም ማጥናት እና የሐረሪ መዝገበ ቃላት ማዘጋጀት | 400,000 | 400,000 | | | | |
| | | | **ለ9 የአከባቢ ቀበሌ መስተዳድሮች ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ** | **9,000000** | **9,000,000** | | | | |
| 09/2/001/111 | 01 | 001 | አሚር ኑር አካባቢ ቀበሌ መስተዳድር ፕሮጀክቶች ማስፈፀሚያ | 1,000,000 | 1,000000 | | | | |
| 09/2/002/111 | 01 | 001 | አባድር አካባቢ ቀበሌ መስተዳድር ፕሮጀክቶች ማስፈፀሚያ | 1,000,000 | 1,000,000 | | | | |
| 09/2/003/111 | 01 | 001 | ሸንከር አካባቢ ቀበሌ መስተዳድር ፕሮጀክቶች ማስፈፀሚያ | 1,000,000 | 1,000,000 | | | | |
| 09/2/004/111 | 01 | 001 | አቦከር አካባቢ ቀበሌ መስተዳድር ፕሮጀክቶች ማስፈፀሚያ | 1,000,000 | 1,000,000 | | | | |
| 09/2/005/111 | 01 | 001 | ጀንኤላ አካባቢ ቀበሌ መስተዳድር ፕሮጀክቶች ማስፈፀሚያ | 1,000,000 | 1,000,000 | | | | |
| 09/2/006/111 | 01 | 001 | ሐኪም አካባቢ ቀበሌ መስተዳድር ፕሮጀክቶች ማስፈፀሚያ | 1,000,000 | 1,000,000 | | | | |
| 09/2/007/111 | 01 | 001 | ኤረር አካባቢ ቀበሌ መስተዳድር ፕሮጀክቶችማስፈፀሚያ | 1,000,000 | 1,000,000 | | | | |
| 09/2/008/111 | 01 | 001 | ድሬ ጠያራ አካባቢ ቀበሌ መስተዳድር ፕሮጀክቶች ማስፈፀሚያ | 1,000,000 | 1,000,000 | | | | |
| 09/2/009/111 | 01 | 001 | ሶፊ አካባቢ ቀበሌ መስተዳድር ፕሮጀክቶች ማስፈፀሚያ | 1,000,000 | 1,000,000 | | | | |
| 121 | | | **ለገጠር ፍ/ቤቶች ችሎት ግንባታ** | **1,247,600** | **1,247,600** | | | | |
| | 01 | 001 | ድሬ ጠያራ ቀበሌ መስተዳድር ገጠር ፍ/ቤት ችሎት ግንባታ | 415,800 | 415,800 | | | | |
| | 01 | 001 | ኤረር ቀበሌ መስተዳድር ገጠር ፍ/ቤት ችሎት ግንባታ | 415,900 | 415,900 | | | | |
| | 01 | 001 | ሶፊ ቀበሌ መስተዳድር ገጠር ፍ/ቤት ችሎት ግንባታ | 415,900 | 415,900 | | | | |
| 211 | | | **ግብርናና ገጠር ልማት ቢሮ** | **1,590,900** | **1,590,900** | | | | |
| | 01 | 003 | የገበሬዎች ማሰልጠኛ ሰርቶ ማሳያ ማእከላት ግንባታና ቁሳቁስ ማሟያ | 1,377,800 | 1,377,800 | | | | |
| | | 005 | የእንጨት ሃይል ኢነርጂ አቅርቦት | 63,100 | 63,100 | | | | |
| | 01 | 004 | የድሬ ጠያራ አሮፓላን ማረፊያ አጥር ግንባታ | 150,000 | 150,000 | | | | |
| | | | **ጤና** | | | | | | |
| 341 | 02 | 007 | በታህጻሰ ልማት ፈንድ ስተሰራው ጤና ጣቢያ ማጠናቀቂያ የግንባታ ፕሮጀክት | 600,000 | 600,000 | | | | |
| 311 | | | **የትምህርትና አቅም ግንባታ ቢሮ** | **2,086,200** | **2,086,200** | | | | |
| | 01 | 010 | የሁለት 1ኛ ደረጃ ት/ቤቶች ግንባታ | 278,300 | 278,300 | | | | |
| | 01 | 012 | የሦስት 1ኛደረጃ ት/ቤቶች ደረጃ ማሳደግና ማስፋፋት | 277,200 | 277,200 | | | | |
| | 01 | 024 | የሦስት 1ኛ ደረጃ ት/ቤቶች ፈርኒቸር ግዢ | 20,600 | 20,600 | | | | |
| | 01 | 023 | የሦስት 1ኛ ደረጃ ት/ቤቶች የትምህርት መሳሪያ ኢኩፕመንት ግዢ | 20,600 | 20,600 | | | | |
| | 02 | 003 | የቀላድ አምባ 1ኛ ደረጃ ት/ቤት ማስፋፋት | 32,700 | 32,700 | | | | |
| | 02 | 005 | የአዉ በርኸድሌ 1ኛ ደረጃ ት/ቤት እድሳት ጥገና | 22,400 | 22,400 | | | | |
| | 02 | 006 | የጅጎል አካባቢ አዲስ 1ኛ ደረጃ ት/ቤት ግንባታ | 360,000 | 360,000 | | | | |
| | 01 | 015 | የሶፊ አፈር ደባና ቡርቃ 1ኛ ደረጃ ት/ቤቶች የት/ መሳሪያና ኢኩፕመንት ግዢ | 20,900 | 20,900 | | | | |
| | 02 | 012 | የሁለት ከ/2ኛ ደ/ት/ቤት የመማሪያ ክፍሎች ፈርኒቸርና ኢኩፕመንት | 1,053,500 | 1,053,500 | | | | |
| | | | **ባህል** | | | | | | |
| 351 | 02 | 005 | የአው በርከሌ አድባር ጥገና ፕሮጀክት | 150,000 | 150,000 | | | | |
| 417 | | | **የሐረር ከተማ ውሃና ፍሳሽ አገልግሎት** | 2,110,000 | | 510,000 | | 1,600,000 | |
| | | | Water supply & sanitation project (IDA) | 1,600,000 | | | | 1,600,000 | |

www.chilot.me

የሐረሪ ህዝብ ክልላዊ መንግስት

# ሐረር ነጋሪ ጋዜጣ

# HARAR NEGARI GAZETA

OF THE HARARI PEOPLE REGIONAL STATE

11ኛ አመት ቁጥር 6
11th year No 6

ሐረር ነሐሴ 18 ቀን 1998
Harar Aug 24/2006

| ያንዱ ዋጋ ብር 4:00<br>Unit Price Bir. 4:00 | በሐረሪ ሕዝብ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ | የፖስታ ሣጥን ቁጥር 272<br>P.o .Box |
|---|---|---|

## ማውጫ

አዋጅ ቁጥር 58/1998 ዓ.ም
የሐረር ከተማን በህግ ለማቋቋም የወጣ አዋጅ......ገጽ 464

## አዋጅ ቁጥር 58/1998 ዓ.ም

## የሐረር ከተማ አዋጅ

ከተሞች አመቺ ሁኔታዎች ከተፈጠሩላቸው ከባቢያዊ ልማት፤ መልካም አስተዳደር እና የአገልግሎት አቅርቦትን በማረጋገጥ ረገድ፤ ከፍተኛ ሚና ሊጫወቱ የሚችሉ መሆናቸውን በመገንዘብ፤

የሐረሪ ህዝብ ክልል መንግስት ለከተማይቱ እድገትና ልማት የሚያስፈልገውን አመቺ ሁኔታ ለመፍጠር ቁርጥ ውሳኔ የወሰነ በመሆኑ፤

የክልሉ ዋና ከተማ የሆነችው የሐረር ከተማን ፈጣን እድገቷ ዕውን ለማድረግ የክልሉን ህገ- መንግስታዊ ተጨባጭ ሁኔታን ያጤነ አደረጃጀቱ ጫና የማያስከትልና ኢኮኖሚያዊ የሆነ የህግና የተቋም ማዕቀፍ እንዲኖራት ማድረግ በማስፈለጉ፤

የሐረሪ ህዝብ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት በተሻሻለው የክልሉ ህገ-መንግስት አንቀጽ 45(2) እና 51(2)ሠ መሠረት የሚከተለውን አውጇል::

## ምዕራፍ አንድ

## ጠቅላላ

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ አዋጅ «የሐረር ከተማ አዋጅ ቁጥር 58/1998 ዓ.ም» ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል::

2. **ትርጓሜ**

   የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጓሜ የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ:-

www.chilot.me

1. «የሐረር ከተማ ም/ቤት» ማለት በክልሉ ህገ-መንግሥት አንቀጽ 46(1) የተመለከተው የክልሉ ህገ-አውጪ ምክር ቤት ነው::
2. «ቢሮ» ማለት በሐረሪ ህዝብ ክልላዊ መንግስት የንግድ ኢንዱስትሪና ከተማ ልማት ቢሮ ነው::
3. «ከንቲባ» ማለት የክልሉ መንግሥት ፕሬዝዳንት ነው::
4. «ምክትል ከንቲባ» ማለት የክልሉ መንግስት ምክትል ፕሬዝዳንት ነው::
5. «የከንቲባ ኮሚቴ» ማለት በክልሉ ህገ-መንግስት አንቀጽ 46(2) የተመለከተው የክልሉ ከፍተኛ የህግ አስፈፃሚ አካል የሆነው የመስተዳድር ም/ቤት /ካቢኔ/ ነው::
6. «የማዘጋጃ ቤት አገልግሎት» ማለት የመንገድ ሥራ አገልግሎት፣ የእሳትና ድንገተኛ አገልግሎት፣ የክብር መዝገብ ስራዎችን ጨምሮ የነዋሪዎች የዕለት ተዕለት አገልግሎት፣ የመሬትና የቤት ልማት እና አስተዳደር አገልግሎት፣ የከተማ ጽዳትና ውበት አገልግሎት እና የከንቲባ ኮሚቴው የሚወስናቸውን ሌሎች አገልግሎቶችን ይጨምራል::

## 3. የተፈፃሚነት ወሰን

ይህ አዋጅ ተፈፃሚነቱ ለሐረር ከተማ ብቻ ይሆናል::

## 4. የሐረር ከተማ ህጋዊ ሰውነት

1. ይህ አዋጅ የሐረር ከተማ የራሷ ህጋዊ ሰውነት ያላት ከተማ አድርጎ አቋቁሟታል:: ህጋዊ ሰውነቱ ስለተሰጣትም በዚህ አዋጅ በተቋቋሙ አካላቶችዋ አማካይነት በዚህ አዋጅ የተሰጣትን ሥልጣን በሥራ ላይ ለማዋልና ተግባራቱን ለማከናወን፣ ውል ለመዋዋል፣ የንብረት ባለቤት ለመሆን፣ ንብረቱን ለማስተዳደር እንዲሁም ለመክሰስ እና ለመከሰስ የህግ ችሎታ ይኖራታል:: ከተማይቱ የሚኖራት ውል የመዋዋል የህግ ችሎታ በህግ መሠረት ከአገር ውስጥ አበዳሪዎች እና ከአገር ውጪ አበዳሪዎች የመበደር ችሎታን ያካትታል፤
2. ህጋዊ ሰውነት ስለማግኘቷ ምስክር ይሆን ዘንድ የመስተዳድሩ ምክር ቤት የምዝገባ ሰርተፍኬት ለሐረር ከተማ ይሰጣል::

# ምዕራፍ ሁለት

# ራዕይ፤ አላማ፤ ሥልጣንና ተግባራት

## 5. ራዕይ

የሐረር ከተማ:-

1. ታሪካዊነቷን የጠበቀች ንፁህ፣ የኗሪዎቿ ደህንነት የተረጋገጠበት፤ ለመኖሪያነትና ለመሥሪያነት አመቺ ሥፍራ የሆነች፤
2. የልማት ማዕከል የሆነች፤ መሠረታዊ የሆኑ የማዘጋጃ ቤት አገልግሎቶች በተቀላጠፈና ፍትሃዊ በሆነ መልኩ የሚቀርብባት እና
3. መልካም አስተዳደር የሰፈነባት የህዝቦች መቻቻልና አብሮ የመኖር ተምሳሌትነቷን ይዛ የምትቀጥል ፋይዳ ያላት የምስራቅ አፍሪካ የቱሪስት መስህብ ሆኖ ማየት::

## 6. ዓላማ

የሐረር ከተማ ከዚህ የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሯታል:-

1. የከተማይቱ ኗዋሪዎችን ፍላጎት መሠረት በማድረግ የማዘጋጃ ቤት አገልግሎቶችን ማቅረብ ወይም መቅረቡን ማረጋገጥ፤
2. የከተማይቱንና የኗሪዎቿን ፈጣንና ዘላቂ ልማት መደገፍ፣ ለልማቱም አመቺ ሁኔታዎችን መፍጠር::

## 7. ሥልጣን

1. የሐረር ከተማ በፌዴራል፤ በክልል ህገ-መንግስት፤ በዚህ አዋጅና በሌሎች ህጎች የተደነገገው ሥልጣኑ ይኖራታል::
2. የዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ1 አጠቃላይ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ከተማይቱ ከዚህ የሚከተለው ዝርዝር ሥልጣን ይኖራታል:-
   ሀ. ራዕይዋንና ዓላማዎቿን ከግብ ለማድረስ ከመንግስታት፤ ከግሉ ሴክተር እና ከበጎ ፍቃደኛ ሴክተሮች ጋር አጋርነት የመመሥረት፤
   ለ. ድርጅታዊ አወቃቀሯን የመወሰን፣ ሠራተኞቿን ማስተዳደር እና የነሱንም የሥራ ሁኔታዎች የመወሰን፤

www.chilot.me

ሐ. ግብርን፣ የአገልግሎት ክፍያን እና ሌሎች ገቢዎችን በህግ መሠረት የመወሰን፣ የማስተካከል እና የመሰብሰብ፤

መ. በፕላን ህግ መሠረት የከተማ ፕላን እንዲዘጋጅ የማድረግ፣ የማጽደቅ እና የማስፈጸም ይህን እውን ለማድረግ ለህዝብ ጥቅም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ አግባብ ባለው ህግ መሠረት ተመጣጣኝ ካሳ በቅድሚያ በመክፈል የግል ንብረትን የመውሰድ እና

ሠ. የከተማ ጉዳዮችን በመጀመሪያና በይግባኝ ደረጃ የሚያዩ ልዩ ችሎቶች መሰየማቸውን ማረጋገጥ ናቸው::

## 8. ተግባርና ኃላፊነት

1. የሐረር ከተማ ራዕይዋንና ዓላማዎቿን እውን ለማድረግ የሚያስፈልጉትን ተግባራት የመከወን ወይም መከናወናቸውን የማረጋገጥ ኃላፊነት ይኖርባታል::
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ የሐረር ከተማ ከዚህ የሚከተሉት ዝርዝር ተግባራት ይኖሯታል:-

ሀ. የአገልግሎት አቅርቦት አቅም እና ሁኔታዎች በፈቀዱት መጠን የሐረር ከተማ ከዚህ የሚከተሉትን አገልግሎቶች ማቅረብ ወይም መቅረባቸውን ማረጋገጥ ይኖርባታል:-

I. የከተማ መንገዶችን፣ የፈሳሽ ቆሻሻ መተላለፊያዎችን፣የተፋሰስ መስመሮችን፣ ፓርኮችን፣ መናፈሻዎችን እና የመዝናኛ ሥፍራዎችን መሥራትና ማስተዳደርን፣ የጎርፍ መከላከልንና መቆጣጠርን፣ የደረቅ ቆሻሻ ማስወገድን እና የብክላ ቁጥጥርን የሚያካትቱ የአከባቢ አገልግሎቶች መስጠት፤

II. የአምቡላንስ አገልግሎትን መስጠት፣የቤት ልማት ፕሮግራሞችን ማካሄድ፣ ለተጣሉ እንክብካቤ ማድረግ፣ የመቃብር ቦታ አቅርቦትን እና የቄራ አገልግሎትን፣ የውል ሰነድ ምዝገባ አገልግሎትን እና መሠረታዊ የስታትስቲካዊ መረጃዎችን የመያዝና የማቅረብ አገልግሎትን መስጠት፤

III. ውሃ፣ መብራትን፣ ስልክን እና የከተማ ትራንስፖርትና መናኸሪያ አገልግሎትን የመሳሰሉ የህዝብ አገልግሎቶችን ማቅረብ ወይም መቅረባቸውን ማረጋገጥ የእሳት አደጋ መከላከልና መቆጣጠርን::

ለ. ኢንቨስትመንትንና ቱሪዝምን ለማስፋፋት፣ የማይክሮ ፋይናንስና የብድርና ቁጠባ ፕሮግራሞችን እንዲሁም የድህነት ቅነሳ ፕሮግራሞችን ለማፋጠንና የከተማይቱንና የኗሪዎቿ ዘላቂ ልማትን ለማጠናከር ከሚመለከታቸው አካላት ጋር አብሮ መሥራት፤

ሐ. የመንግሥት ፖሊሲዎችን፣ ህጎችን እና አስታንዳርዶችን የማስከበር ተግባራትን መቆጣጠር፤

መ. ዝርዝር የልማት ፕላኖችን ማዘጋጀትንና ማስፈጸምን ጨምሮ እቅድ ማቀድ፤

ሰ. ነዋሪዎች የመኖሪያ ቤት ባለቤት የሚሆኑበትን ሁኔታ ማመቻቸትና ማበረታታት እዲሁም ነባር የመንግስት ቤቶችን የማከራየትና የመሸጥ::

# ምዕራፍ ሦስት

# አመራርና አደረጃጀት

## 9. ዘይቤ

የሐረር ከተማ የምክር ቤት ከንቲባ አመራር ዘይቤ ይኖራታል::

## 10. የዘይቤው ትርጓሜና ይዘት

በምክር ቤት ከንቲባ ሥርዓት መሠረት ፖሊሲ ማውጣት በህዝብ የተመረጠው የክልሉ ምክር ቤት ሥልጣን ሲሆን ከፍተኛው የአስፈጻሚነት ሥልጣን ደግሞ የከንቲባውና የከንቲባው ኮሚቴ ይሆናል::

www.chilot.me

## 11. የአመራር አካላት

የሐረር ከተማ ከዚህ የሚከተሉት አካላት ይኖሯታል፡-

1. የከተማ ም/ቤት፤
2. ከንቲባ፤ ም/ከንቲባ እና የከንቲባ ኮሚቴ፤
3. የማዘጋጃ ቤት ሥራ አስኪያጅ እና ምክትል ሥራ አስኪያጅ፤
4. አስፈላጊ የሆኑ የሥራ ክፍሎችና ሠራተኞች፤

## 12. ስለከተማዋ ምክር ቤት

የከተማዋ ምክር ቤት በህዝብ የተመረጠው የክልሉ መንግስት ህግ አውጪ ምክር ቤት ነው:: ም/ቤቱም ከዚህ የሚከተሉት ዝርዝር ሥልጣንና ኃላፊነቶች ይኖሩታል::

1. የፌዴራልና የክልል ፖሊሲዎችን በመከተል ከባቢያዊ፣ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ፖሊሲዎችን እና ከፍተኛ ውሳኔዎችን ማስተላለፍና አፈፃፀማቸውን ማረጋገጥ፤
2. የከተማ ህጎችን ማጽደቅ እና በአግባቡ መፈፀማቸውን ማረጋገጥ፤
3. አግባብ ባለው ህግ መሠረት የማዘጋጃ ቤት ስራ አስኪያጅ ሹመትን ማጽደቅ፤
4. የከተማይቱን ስትራክቸራል ፕላን ማጽደቅ እና በአግባቡ መፈጸሙን ማረጋገጥ፤

## 13. ከንቲባውና ም/ከንቲባው

1. የክልሉ መንግስት ፕሬዝዳንት ከንቲባና የከተማዋ ዋና ሥራ አስፈጻሚ ሹም ነው::
2. የክልሉ ምክትል ፕሬዝዳንት የከተማው ም/ከንቲባ ነው::
3. ከንቲባው ከዚህ የሚከተሉት ሥልጣንና ኃላፊነቶች ይኖሩታል፡-
   ሀ. የከንቲባ ኮሚቴውን ይሰበስባል፣ የኮሚቴ አባላቱን ሥራ ይመራል፣ ያቀናጃል፤
   ለ. የአፈጻጸም የሥራ አመራርና የሙያ ብቃትን መሠረት በማድረግ የማዘጋጃ ቤት ሥራ አስኪያጅን አግባብ ባለው ህግ መሠረት ያሾማል፣ አፈጻጸሙን/ሟን/ ይቆጣጠራል፣ ይገመግማል፤
   ሐ. ከተማይቱ ከሌሎች ወገኖች ጋር በምታደርገው ግንኙነት ከተማይቱን ይወክላል፣ ኦፊሴላዊ ሥነ ሥርዓቶችን ይመራል፤
   መ. ከምክር ቤቱ የሚሰጡትን ሌሎች መሰል ተግባራት ያከናውናል፤
4. ምክትል ከንቲባው የሚከተሉት ሥልጣንና ኃላፊነቶች ይኖሩታል::
   ሀ. ከንቲባው በማይኖርበት ጊዜ ከንቲባውን ተክቶ ይሠራል፤
   ለ. በከንቲባው ተለይቶ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል::

## 14. የከንቲባው ኮሚቴ

1. የከተማው ከንቲባ ኮሚቴ በክልሉ ህገ-መንግስት ከፍተኛ የህግ አስፈፃሚነት ስልጣን የተሰጠው የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት/ካቢኔ/ ነው ::
2. የከንቲባ ኮሚቴው በከንቲባው እየተመራ ከዚህ የሚከተሉት ከማዘጋጃ ቤት አገልግሎት ጋ ተያያዥ የሆኑ ተግባርና ኃላፊነቶችን ያከናውናል::
   ሀ. የመንበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና የልማት ፖሊሲ ሀሳቦች ያመነጫል፣ ይወያይባቸዋል፤ ለምክር ቤቱም የውሳኔ ሃሳብ ያቀርባል፤የፖሊሲ ሃሳቦችን ምክር ቤቱ ሲያፀድቃቸውም በአግባቡ መፈጸማቸውን ያረጋግጣል፤
   ለ. በከተማይቱ ሥልጣን ሥር በሚወድቁ ጉዳዮች ላይ የከተማ ህግ ያዘጋጃል፤ ይህንኑም ለምክር ቤቱ ያቀርባል፤ ሲጸድቅም በአግባቡ መፈጸሙን ያረጋግጣል፤
   ሐ. የመንግሥት እና የከተማይቱ ፖሊሲዎች፣ ህጎች እና እስታንዳርዶች መከበራቸዉ ያረጋግጣል፤
   መ. የማዘጋጃ ቤቱን ድርጅታዊ አወቃቀር የሠራተኛውን አጠቃላይ የስምሪት ዕቅድ፣ የደመወዝ እስኬልና የሥራ ሁኔታ ይወስናል፣ ኤጀንሲዎችን፣ ጽ/ቤቶችንና ሌሎች ተቋማትን በህግ መሠረት ያቋቁማል፤

ሠ. የማዘጋጃ ቤት አገልግሎት ሥራውን ያቀናጃል፣ ይመራል፣ በአግባቡ መፈጸማቸውን ያረጋግጣል፤

ረ. የከተማይቱን ዓመታዊ በጀት እና የሥራ ፕሮግራም ያጸድቃል በተግባር ላይ መዋሉንም ያረጋግጣል፤

ሰ. የከተማይቱ የገቢ ምንጮች መወሰን፤ ግብርን እና የአገልግሎት ክፍያን በህግ መሠረት መወሰን ወይም ማስተካከል፤ የገቢ ክፍፍልን ጨምሮ ከመንግስት ስለሚገኘው የገንዘብ ድጋፍ በህግ መሠረት መወሰን ወይም ማስተካከል፣ ብድርን መፍቀድ፤

ሸ. የህዝብን ተሳትፎ ከማረጋገጥ አኳያ በከንቲባ ኮሚቴ የሚመራ ባለድርሻ አካላትን ያካተተ የአማካሪ ም/ቤት ያቋቁማል፣ ዝርዝሩ በመስተዳድሩ ም/ቤት መመሪያ ይወሰናል፤

ቀ. ምክር ቤቱ ወይም ከንቲባው የሚሰጡትን ሌሎች መሰል ተግባራት ያከናውናል፤

3. የከንቲባ ኮሚቴው መደበኛ ስብሰባ በወር አንድ ጊዜ ይሆናል ሆኖም አስቸኳይ ስብሰባ እንዲደረግ ሲታመን በማንኛውም ጊዜ ከንቲባው አስቸኳይ ስብሰባ ሊጠራ ይችላል ::

4. የከንቲባ ኮሚቴው የራሱን የስብሰባ ሥነ ሥርአት መመሪያ ሊያወጣ ይችላል ::

## 15. የማዘጋጃ ቤት አገልግሎት ሥራ አስኪያጅ እና ም/ሥራ አስኪያጅ

1. ሥራ አስኪያጅ አግባብ ባላው ህግ መሠረት ይሾማል፤

2. የሥራ አስኪያጁ ተጠሪነት ለከንቲባው ይሆናል፤

3. ለማዘጋጃ ቤት አገልግሎቶች ዘላቂ ልማት እና ቀልጣፋና ፍትሃዊ አቅርቦት ኃላፊነት የተጣለበት ሥራ አስፈፃሚ እንደመሆኑ የማዘጋጃ ቤት አገልግሎቶች ሥራ አስኪያጅ ከዚህ የሚከተሉት ሥልጣና ኃላፊነት ይኖረዋል::

ሀ. የማዘጋጃ ቤት አገልግሎቶችን ሥራ አመራር ያቅዳል፣ ያቀናጃል፣ ይመራል፣ ያስተባብራል፤

ለ. ወደ ግል መዛወር የሚገባቸውን አገልግሎቶች አስመልክቶ ለከንቲባው ኮሚቴ ሃሳብ ያቀርባል፤ ተቀባይነት ያገኘውን ሃሳብ ይተገብራል:: ይህንኑ ለመተግበርም በሙሉ ወይም በከፊል ወደ ግሉ መዛወር የሚገባቸውን ወይም የሚችሉትን የማዘጋጃ ቤት አገልግሎቶች ይለያል፣ ወደ ግሉ የሚዛወርበት መንገዶችና ሁኔታዎች ይቀይሳል፣ መደረግ የሚገባቸውን ዝግጅቶች በዝርዝር ያመለክታል፣ ወደ ግል የማይዞር ፕሮግራም በአገልግሎቶች አቅርቦት ቅልጥፍና እና ፍትሃዊነት ላይ የሚያስከትለውን ጫና ያሳያል፤

ሐ. የአገልግሎት አቅርቦት እስታንዳርዶች እና የሥራ አፈፃጸም መለኪያዎች ያዘጋጃል፣ ለከንቲባው ኮሚቴ ያቀርባል፤ ሲያጸድቁም በአግባቡ መፈጸማቸውን ያረጋግጣል፤

መ. ወደ ግል የተዛወሩት አገልግሎቶች አመራር ቀልጣፋ እና ውጤታማ ይሆን ዘንድ የአቅም ግንባታ ፕሮግራሞች ይቀይሳል ያስፈጽማል፤

ሠ. የማዘጋጃ ቤት ሥራዎችንና ኃላፊነቶች ውጤታማ እና ቀልጣፋ በሆነ መልኩ ለመወጣት የሚያስፈልጉ ኤጀንሲዎችን፣ መመሪያዎችን እና የሥራ ክፍሎችን አስጠንቶ ለከንቲባ ኮሚቴ ውሳኔ ያቀርባል ሲጸድቅም ተግባራዊ ያደርጋል::

ረ. በከተማው የሠራተኛ አስተዳደር ደንብ መሠረት የማዘጋጃ ቤት ሠራተኞችን ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል፤ አስፈላጊ ሲሆንም የሥነ ሥርዓት እርምጃ ይወስዳል::

ሰ. ለሥራው አስፈላጊ የሆኑ ኃላፊዎችን አግባብ ባለው ህግ መሠረት እንዲሾሙ ሃሳብ ያቀርባል::

ሸ. የማዘጋጃ ቤት አገልግሎቶችን የሚመለከቱት የምክር ቤት ውሳኔዎች እና የመንግሥት ህጎች እና እስታንዳርዶች በአግባቡ መፈጸማቸውን ያረጋግጣል::

www.chilot.me

ቀ. የማዘጋጃ ቤት አገልግሎቶችን ዓመታዊ የሥራ ፕሮግራም እና አብሮ የሚሄደውን በጀት የማዘጋጀቱን ሂደት ይመራል፣ ለከንቲባው ኮሚቴ ያቀርባል፣ሲጸድቅም ተግባራዊ ያደርጋል።

በ. የተለያዩ የአሰራር ሥልቶችን እና የታሪፍ ማሻሻያ ሃሳቦች ለከንቲባ ኮሚቴው ያቀርባል ሲጸድቅም ተግባራዊ ያደርጋል።

ተ. በምክር ቤት ስብሰባዎች ላይ ይገኛል፤ ሲጠየቅም ማብሪያዎች ይሰጣል፤ ከተማይቱ ስላለችበት አጠቃላይ ሁኔታም ለከንቲባ ኮሚቴውና ለምክር ቤቱ መረጃ ይሰጣል።

ቸ. ኅብረተሰቡ ለሚያቀርባቸው አቤቱታዎች እና ጥያቄዎች አፋጣኝ ምላሽ ይሰጣል፤ በአገልግሎቶች አሰጣጥ ረገድ መልካም አስተዳደር መስፈኑን ያረጋግጣል።

ኀ. ከተማይቱ ስላለችበት አጠቃላይ ሁኔታ በየጊዜው ለህዝብ ያሳውቃል፤ በአካባቢያዊ ጉዳዮች ላይ ለመወያየት ህዝባዊ መድረኮችንና ስብሰባዎችን ያደራጃል።

ነ. በየወቅቱ የእንቅስቃሴ ሪፖርት ለከንቲባው ኮሚቴ ያቀርባል።

ኘ. ምክር ቤቱ፤ ከንቲባው እና ከንቲባ ኮሚቴው የሚሰጡትን ሌሎች መሰል ተግባራት ያከናውናል ።

4. ምክትል ሥራ አስኪያጅ

ሀ. ም/ሥራ አስኪያጅ አግባብ ባለው ህግ መሠረት ይሾማል።

ለ. የምክትል ሥራ አስኪያጁ ተጠሪነት ለሥራ አስኪያጅ ይሆናል።

ሐ. የምክትል ሥራ አስኪያጅ ተግባርና ኃላፊነት፡-

I. ዋና ሥራ አስኪያጅ በማይኖርበት ጊዜ ተክቶ ይሠራል፤

II. ከሥራ ናአስኪያጁ ተለይተው የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል።

## ምዕራፍ አራት
## ስለ ግንኙነት

### 16. አጋርነት

1. ሐረር ከተማ ከፌዴራል መንግስት ወይም ከመምሪያዎቻቸው ወይም ከወኪሎቻቸው ወይም ከሌሎች ከተሞች ጋር በጋራ ወይም በትብብር በውል ወይም በሌላ ሁኔታ በመሥራት ሥልጣኗን ሥራ ላይ ልታውል ወይም ማንኛ ውንም ተግባሯን ልትከውን ወይም በመዋዕለ ንዋይ አቅርቦት ልትሳተፍ ትችላለች።
2. አቅሙ ሲፈቅድና ሥራውንም ማዘጋጃ ቤቱ ቢሰራው ይበልጥ ውጤታማ ይሆናል ተብሎ ሲገመት ያ ሥራ እንዲሰጠው ሥራ አስኪያጁ ለከንቲባ ኮሚቴው ሲያመለክት፤ አግባብ ካለው የመንግስት አካል ጋር በመስማማት ያንን የመንግሥት ሥራ ለመሥራት ይችላል፤ ሥራውን ለመሥራት የሚያስፈልገው ወጪ በሁለቱ ወገኖች ስምምነት ይወሰናል።

## ምዕራፍ አምስት
## በከተማይቱ እና በመሐበረሰቡ መካከል ስለሚኖረው ግንኙነት

### 17. መርህ

1. በመኅበረሰቡና በከተማይቱ አስተዳደር መካከል የሚኖረው ግንኙነት የሚመራው የከተማይቱ ሥልጣን ሁሉ የሚመነጨው ከህዝቡ ነው በሚለው መርህ ነው።
2. የከተማይቱን ምክር ቤት አባላት የሚመርጠውና ከኃላፊነትም የሚያነሳው ህዝቡ ብቻ ይሆናል፤ የዚህም ማስፈጸሚያ ሥነ ሥርዓት በሀገሪቱ የምርጫ ህግ እንደተዘረዘረው ይሆናል።
3. ህዝቡ በውሳኔ አሰጣጥ ሂደት ላይ መሳተፍ ይኖርበታል፤ አዲስ ግብር መጣል ወይም ነባሩን ማስተካከል፤ በመሰሉ ከባድ ጉዳዮች ላይ የከንቲባው ኮሚቴ የደረሰውን የቅድሚያ ስምምነት ለማግኘት ከፍተኛ ጥረት ማድረግ ይጠበቅበታል።

## 18. የህዝብ ተሳትፎ

1. ፎረሙ፣ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች እና የግሉ ሴክተር በዓመቱ የሥራ ፕሮግራም አብሮ በሚሄደው በጀት፣ የፕሮጀክት ሃሳቦችና አፈፃጸማቸው በእንቅስቃሴ ዘገባዎች እና በፋይናንስ ኦዲት ሪፖርቶች ላይ ሊወያዩ፣ ሊከራከሩና ሃሳባቸውን ሊገልጹ ይገባል::
2. የሐረር ከተማ እድገት በዋናነት የሚመለከታቸው ሁሉ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 በተመለከቱት ጉዳዮች ላይ መወያየት፣ መከራከርና ሃሳባቸውን መግለጽ ይችሉ ዘንድ ቢያንስ በስድስት ወር አንድ ጊዜ ህዝባዊ መድረክ ያዘጋጃል::
3. ፎረሞች በተለይም ባህላዊ የማህበረሰብ መሪዎች፣ ተሳትፎአቸው ዝቅተኛ የሆነ የማህበረሰቡ ክፍሎች እና የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ለከተማይቱ ጉዳዮች በሚዘጋጁ መድረኮች ላይ እንዲሳተፉ ይጋበዛሉ ይበረታታሉ::
4. ያሉትን ተስማሚ ዜዴዎች ሁሉ በመጠቀም ፎረሙ ስለከተማዋ አጠቃላይ ሁኔታ፣ ስላሉት ችግሮች እና ስለተከሰቱትም አዳዲስ ነገሮች እንዲያውቁ ያደርጋል፣ መረጃ ይሰጣል::
5. ህዝብ ለሚያቀርባቸው ጥያቄዎችና አቤቱታዎች ፈጣንና በጎ ምላሽ የማግኘት መብት አለው::

# ምዕራፍ ስድስት

# የከተማይቱ ፋይናንስ

## 19. የበጀት ዓመት

የሐረር ከተማ የበጀት አመት የክልሉ መንግስት የበጀት ዓመት ነው:-

## 20. የከተማይቱ የገቢ ምንጮች

የሐረር ከተማ ከዚህ የሚከተሉት የገቢ ምንጮች ይኖሯታል::

1. ከንብረት የሚሰበሰብ ግብር እና ኪራይ፣
2. ሌሎች ግብሮች፣
3. የአገልግሎትና የተጠቃሚ ክፍያዎች፣
4. የምዝገባ እና የፍቃድ ማውጫ /ማደሻ ክፍያዎች/፣
5. የገቢ ማግኛ ፕሮግራሞች፣
6. ስጦታዎችና ሌሎች ድጋፎች፣
7. ብድር፣
8. ከመንግስት የሚገኝ ገቢ እና ስጦታ /ድጎማ/ እና
9. ሌሎች ምንጮች ናቸው::

## 21. የፋይናንስ አስተዳደር

1. የከንቲባ ኮሚቴው ገቢዎችን ለማደራጀትና ለማስተዳደር ሥልጣን አለው::
2. የማዘጋጃ ቤቱ ቀላል እና ውጤት-ተኮር የሆነ የፋይናንስ አስተዳደር ሥርዓት ይኖረዋል::
3. ከንቲባ ኮሚቴው ለሐረር ከተማ የፋይናንስ መመሪያ ያወጣል::

## 22. ሂሳብ

1. ከንቲባ ኮሚቴው በዚህ ህግ ወይም በሌላ አግባብ ባለው ህግ መሠረት የሚሰበሰበው ገንዘብ የሚቀመጥበት የባንክ ሂሳብ በሐረር ከተማ ስም ይከፈታል::
2. ማዘጋጃ ቤቱ ትክክለኛ የሆነና የተሟላ የሂሳብ መዛግብት ይይዛል::

## 23. በጀት

1. የሐረር ከተማ የራሷን በጀት ለማዘጋጀት፣ ለማጽደቅና ለማስተዳደር ሥልጣን ይኖራታል፣ ሂደቱ በሞላ አሣታፊ መሆን ይኖርበታል::
2. ሥራ አስኪያጁ ከከንቲባው ጋር በመመካከር የየዓመቱን ሥራ ዕቅድና የበጀቱን ረቂቅ ያዘጋጃል::
3. የበጀትና ዕቅድ ረቂቁ በቅድሚያ ለባለድርሻ አካላት እንዲወያዩበት በጥልቀት እዲመረምሩት እና በበለጠ እንዲያዳብሩት ይቀርባል::
4. የተሻሻለው ቅጂ ደግሞ ለከንቲባ ኮሚቴው ቀርቦ ይጸድቃል::
5. በጀቱ ቢያንስ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ማመልከት ይኖርበታል፣
   ሀ. በዓመቱ ውስጥ እውን እዲሆኑ የታሰቡት ዓላማዎች፣ ተግባራትና እንቅስቃሴዎች፣
   ለ. ይሁን ተብሎ ሀሳብ የቀረበበት የካፒታልና መደበኛ ወጪ፣
   ሐ. ይገኛል ተብሎ የታሰበው ገቢ እና ምንጩ፣
   መ. ውጤት አመላካቾች::

www.chilot.me

6. ሁኔታዎች ሲያስገድዱ የከንቲባ ኮሚቴ በጀት ማስተካከያ ሊያደርግ ይችላል፤ በተለያዩ ርእሶች መካከል ገንዘብ ሊዘዋወር ስለሚችልበት ሁኔታ መመሪያ ያወጣል::

## 24. የፋይናንስ ዘገባዎች

1. የማዘጋጃ ቤቱ ሥራ አስኪያጅ ዓመታዊ የፋይናንስ ዘገባዎችን ያጠናቅራል፤ ለከንቲባ ኮሚቴውም ያቀርባል::
2. የከንቲባ ኮሚቴው ከዘገባው በመነሳት ተገቢ የሆነ የማስተካከያ እርምጃ ይወስዳል::

## 25. ኦዲት

1. ተጠሪነቱ ለማዘጋጃ ቤት አገልግሎት ሥራ አስኪያጅ የሆነ የውስጥ ኦዲተር ይኖራል፤
2. የውስጥ ኦዲተሩ የከተማይቱ ሀብት በፀደቀ የፋናንስ ደንብ መሠረት እየተዳደረ መሆኑን እለት በእለት ያረጋግጣል፤
3. የክልሉ መንግስት ዋናው ኦዲተር፤ የከተማይቱ ገንዘብ በአግባቡ በሥራ ላይ መዋሉን፣ በአግባቡ መወራረዱን እና የከንቲባውም ሪፖርት የከተማይቱን ትክክለኛ ሁኔታ የሚያንፀባርቅ መሆኑን ለማረጋገጥ የከተማይቱን ሂሳብ በየዓመቱ ይመረምራል፤
4. ዋናው ኦዲተር የታሰበው ውጤትና ለውጥ መገኘቱን ለማረጋገጥም ቢያንስ በ5 ዓመት አንድ ጊዜ የከተማይቱን አፈጻጸም ይመረምራል::

# ምዕራፍ ሰባት
# የሰው ኃይል አስተዳደር

## 26. የሰው ኃይል የማስተዳደር ሥልጣን

ማዘጋጃ ቤት በራሱ የሰው ኃይል አስተዳደር ህግ መሠረት ሠራተኞቹን ለመቅጠር፤ አጠቃላይ የሥራ ሁኔታዎችን ለመወሰን ፤ለማስተዳደርና በነሱም ላይ የሥነ ሥርዓት እርምጃ ለመውሰድ ሙሉ ሥልጣን ይኖረዋል::

# ምዕራፍ ስምንት
# ስለ ከተማ ነክ ጉዳዮች ችሎት

## 27. ሥልጣን ስለ መስጠት

1. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 28 የተዘረዘሩት ከተማነክ ጉዳዮችን በመጀመሪያ ደረጃ ተቀብሎ ውሳኔ እንዲሰጥ ለክልሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት በዚህ አዋጅ ስልጣን ተሰጥቶታል፤ የከፍተኛው ፍ/ቤት በሚወስነው ውሳኔ ቅሬታ ያለው ወገን በይግባኝ ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሊያቀርብ ይችላል::
2. የክልሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት በዚህ አዋጅ አንቀጽ 28 ሥር የተዘረዘሩት ጉዳዮችን ብቻ የሚያዩ ችሎት ወይም ችሎቶችን ይሰይማል::

## 28. የችሎቱ ሥልጣን

ችሎቱ ከሚከተሉት በሚመነጩ ጉዳች ላይ ሁሉ ብቸኛ ሥልጣን ይኖረዋል፡-

1. የከተማ ፕላን፣ የህንፃ ግንባታ እና የቤቶችና የቦታ አስተዳደር ህግጋት አፈፃጸምን በተመለከተ፤
2. በከተማ ቤትና በቦታ የመጠቀም መብት፤
3. የከተማ ግብር፤ ኪራይ፤ የአገልግሎት ክፍያ እና ሌሎች ክፍያዎች፤
4. የማዘጋጃ ቤቱ አገልግሎትን የተመለከቱ ጉዳዮች፤
5. የቤቶችና የከተማ ቦታ አጠቃቀም ለተሰጠው ዓላማ መዋል፤ አለመዋሉን በተመለከተ፤
6. ከዚህ በላይ ከተዘረዘሩት ውጪ የሆነው የተራፊክ ደንብ መጣስ፣ ጤናና የአካባቢ ንጽህና አጠባበቅ፣ እና ሌሎች ተመሳሳይ የከተማ ነክ ጉዳዮች ደንብ መተላለፎችን በተመለከተ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የማየትና የመወሰን ስልጣን ይኖረዋል:: ፍ/ቤቱ እነዚህን የተዘረዘሩትን ጉዳዮች ብቻ የሚያይ ችሎት ሊሰይም ይችላል::

www.chilot.me

**29. ተፈፃሚ የሚሆኑ ህጎች**

ከተማ ነክ ችሎቶች አግባብነት ያላቸውን የመንግስትና የከተማይቱን ህጎች በሙሉ ተፈጻሚ ያደርጋሉ::

## ምዕራፍ ዘጠኝ
## የከተማ ፕላን

**30. የከተማይቱ የከተማ ፕላን የማዘጋጀት፣ የማፅደቅ እና የማስፈጸም ስልጣን**

1. የመንግስት የከተማ ፕላን ህግ እና በውስጡም የተካተቱ መርሆዎች፣ እስታንዳርዶች እና መለኪያዎች እንደተጠበቁ ሆነው ከተማይቱ የከተማዋን ፕላን ዝግጅት ለመጀመር፣ ለማዘጋጀት ወይም እዲዘጋጅ ለማድረግ፣ ለማጽደቅ፣ ለመከለስ እና ለማስፈጸም ሥልጣን ይኖራታል፤ ፕላኑ ከዘመኑ ቴክኖሎጂ እና ልማት ጋር የተቀናጀ አሰራር የሚከተል ይሆናል::
2. ቢሮው የፕላን ቅጂውን በተረከበ በሦስት ወር ጊዜ የፕላን ህጉ የሚጠይቃቸውን ነገሮች ማሟላቱን የማረጋገጥ ሥልጣን ይኖረዋል:: የሦስት ወሩ የጊዜ ገደብ ሲያልቅ የፕላን ህጉ የሚጠይቃቸውን ነገሮች እንዳሟላ ተደርጎ ይቆጠራል::

**31. ነዋሪዎች በፕላን ሂደት የሚኖራቸው መብት**

1. ነዋሪዎች በፕላን ሂደቱ ላይ ለመሳተፍ ሙሉ መብት ይኖራቸዋል ፤
2. የከተማይቱ ም/ቤት ነዋሪዎች ውጤታማ በሆነ መልኩ በፕላን ሂደቱ ላይ ሀሳባቸውንና አስተያየቶቻቸውን የሚገልጹባቸውን መንገዶች እና ዘዴዎች ያበጃል::

## ምዕራፍ አሥር
## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

**32. የንግድ፣ ኢንዱስትሪና ከተማ ልማት ቢሮ**

1. ቢሮው ከተሞች ጉዳይ ላይ ተጠሪ የሆነ የመንግስት አካል ነው፤ የመንግስት እና የሐረር ከተማ የመገናኛ ነጥብ በመሆንም ያገለግላል::
2. ቢሮው መንግስት ለሐረር ከተማ የሚያደርገውን የፋይናንስ፤ የቴክኒክ እና የማቴሪያል ድጋፍ ያመቻቻል እዲሁም የተሻሉ የአሠራር ዘዴዎችን በማስተዋወቅ ይረዳል ፤ በሌላ በኩል የመንግስት ህግ፣ እስታንዳርዶች እና ፖሊሲዎች በከተማይቱ መከበራቸውን ያረጋግጣል::
3. ቢሮው መንግስትን በከተማ ጉዳዮች ላይ ያማክራል::

**33. አዳዲስ አሰራሮችን ስለመሞከር**

1. የሐረር ከተማ ከቢሮው ጋር በቅርብ በመመካከር አዳዲስ የአመራር እና የአስተዳደር ሥልቶችን ኢንዲሁም ሥልጣኗን የምትገብርበትን እና ግዴታዎቿን የምትወጣበትን አዳዲስ ዘዴዎችን ለማፍለቅና ለመሞከር ትችላለች::
2. ቢሮው ሙከራው የሚያካሂድበትን የጊዜ ገደብ ይወስናል፤ ሂደቱንም ይደግፋል፤ ይከታተላል::
3. ከተማይቱ ከውጭም ሆነ ከአገር ውስጥ የእህትማማቾችን ግንኙነት መመሥረት ትችላለች::

**34. መብትና ግዴታዎችን ስለማስተላለፍ**

1. በአዋጅ ቁጥር 7/90 እና በሌሎች ህጎች ለሐረር ከተማ ማዘጋጃ ቤት የተሰጡት ሥልጣንና ተግባራት እንዲሁም መብትና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ መሠረት ለሐረር ከተማ ተላልፏል::
2. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 8 የተዘረዘሩት የማዘጋጃ ቤት አገልግሎት በአሁኑ ወቅት እየሰጡ ያሉ ተቋማት አገልግሎቶችን ባሉበት ሁኔታ እየሰጡ ይቀጥላሉ::
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) የተደነገገው ቢኖርም የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት የማዘጋጃ ቤት አገልግሎት እየሰጡ ያሉ ተቋማትን መብትና ግዴታዎቻቸውን ለሐረር ከተማ የማስተላለፍ፤ እንደ አስፈላጊነቱ በዚህ አዋጅ መሠረት በከተማዋ እየተሰጡ ያሉትን

አገልግሎቶች ለሌሎች ተቋማት እንዲተላለፍ በህግ መሠረት የማድረግ ስልጣን ይኖረዋል።

## 35. የተሻሩ ህጎች

ይህንን አዋጅ የሚቃረን ማናቸውም ህግ፣ ደንብ መመሪያ ወይም የአሠራር ልምድ በዚህ አዋጅ በተመለከቱ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም።

## 36. ደንብና መመሪያ የማውጣት ሥልጣን

1. የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ለዚህ አዋጅ አፈፃጸም የሚያስፈልገውን ደንብና መመሪያ ማውጣት ይችላል።

## 37. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በሐረር ነጋሪ ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

ሐረር ነሐሴ 18 ቀን 1998 ዓ.ም
ሙራድ አብዱልሃዲ
የሐረሪ ህዝብ ክልላዊ መንግስት
ፕሬዝዳንት

የሐረሪ ህዝብ ክልል መንግስት

# ሐረር ነጋሪ ጋዜጣ

# HARAR NEGARI GAZETA

OF THE HARARI PEOPLE REGIONAL STATE

| | | |
|---|---|---|
| 11ኛ ዓመት ቁጥር7<br>11th year No 7 | | ሐረር ነሐሴ 18/1998<br>Harar Aug 24/2006 |
| ያንዱ ዋጋ ብር 0.50<br>Unit priece Bre.0.50 | በሐረሪ ሕዝብ ክልላዊ መንግስት<br>ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ | የፖስታ ሣጥን ቁጥር 272<br>P.O.Box 272 |


## ማውጫ

አዋጅ ቁጥር 59/1998 ዓ.ም
የሐረሪ ሕ/ክልል ውሃና ፍሳሽ አገልግሎት ባለስልጣን ማቋቋሚያ አዋጅን እና ማሻሻያ አዋጆችን ለማሻሻል የወጣ አዋጅ
ገጽ474

## አዋጅ ቁጥር 59/ 1998

## የሐረሪ ሕዝብ ክልል የውሃና ፍሳሽ አገልግሎት ባለስልጣን ማቋቋሚያ አዋጅንና ማሻሻያ አዋጆችን ለማሻሻል የወጣ 3ኛ ማሻሻያ አዋጅ

የሐረሪ ህ/ክ/መንግስት የውሃና ፍሳሽ አገልግሎት ባለስልጣን መስሪያ ቤት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 15/1991ን እና ማሻሻያ አዋጆች ቁጥር 22/1992ን እና ቁጥር 26/1993ን አሁንም ማሻሻል አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

በተሻሻለው የሐረሪ ህዝብ ክልል ህገ-መንግስት አንቀጽ 51/2/ሀ/መሰረት የሚከተለው ታውጇል።

### 1. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ «የሐረሪ ህዝብ ክልል ውሃና ፍሳሽ አገልግሎት ባለስልጣን ማቋቋሚያ አዋጅንና ማሻሻያ አዋጆችን ለማሻሻል የወጣ 3ኛ ማሻሻያ አዋጅ ቁጥር 59/1998 ዓ/ም» ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

### 2. ትርጓሜ

በዚህ አዋጅ ውስጥ:-

1.«አዋጅ» ማለት የክልሉ ውሃና ፍሳሽ አገልግሎት ባለስልጣን ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 15/1991 ነው።

2.«መጀመሪያ ማሻሻያ» ማለት አዋጁን ለማሻሻል የወጣው አዋጅ ቁጥር 22/1992 ነው ።

www.chilot.me

3. «ሁለተኛ ማሻሻያ » ማለት አዋጁንና የመጀመሪያውን ማሻሻያ አዋጅ ለማሻሻል የወጣ አዋጅ ቁጥር 26/1993 ነው ::

3. ማሻሻያ

የሐረሪ ህዝብ ክልል የውሃና ፍሳሽ አገልግሎት ባለስልጣን ማቋቋሚያ አዋጅ እና ማሻሻያ አዋጆች እንደሚከተለው እንደገና ተሻሽለዋል::

ሀ. በአዋጁ አንቀጽ አስራ ስድስት ስር የሚከ ተሉትን አዲስ ንዑሳን አንቀጾች ከ13 እስ ከ 22 ድረስ ያሉት ተጨምረዋል:-

13. በክልሉ የውሃ ሐብትን የተመለከቱ መረጃዎችን ይሰበስባል ያጠናቅራል፤

14. በክልሉ የውሃ ሐብት ጥናትና ዲዛይን ያከናውናል፤

15. በክልሉ የሚካሄዱ የውሃ ሐብት ፕሮ ጀክቶችን ያስፈጽማል ፤

16. የገጠሩ ህብረተሰብ በውሃ ሐብት ልማት ስራ ላይ እንዲሳተፍ ያደራጃል፣ ያስተምራል፣ለህብረተሰቡ የቴክኒክ ድጋፍ ይሰጣል፤

17. የመጠጥ ውሃ ኮንስትራክሽን ስራዎች ን ያካሄዳል ፤

18. የክልሉ ህዝብ በተመጣጠነ ዋጋ ጥራ ት ያለው ውሃ እንዲያገኝ የውሃ ታሪ ፍ ከማዕከላዊ መንግስት የውሃ ፖሊሲ በመነሳት ያወጣል፤

19. የመጠጥ ውሃ አቅርቦት ማግኛ የሆኑ ጂኦሎጂካልና ሃይድሮሎጂካል መረጃ ዎችን ይሰበስባል፣ ጥናት ያካሂዳል፤

20. የመጠጥ ውሃ አቅርቦት ጥናትና ዲዛ ይን ያከናውናል፤

21. የኮንስትራክሽን ስራዎች በዲዛይናቸው መሰረት መፈጸማቸውን ይቆጣጠራል ፤

22. ለምህንድስና ስራዎች ዝርዝር የስራና የዋጋ ተመን ያዘጋጃል::

ለ. የመጀመሪያ ማሻሻያ አንቀጽ 1፣2፣3፣4፣ 5፣7፣8፣እና 11 ተሰርዟል::

ሐ.የሁለተኛ ማሻሻያ አንቀጽ 3 ተሰርዟል::

4. መብትና ግዴታን ስለማስተላለፍ

አዋጅ ቁጥር 47/97 አንቀጽ 10 እና በሌሎች ህጎች ለክልሉ ግብርናና ገጠር ልማት ቢሮ የተሰጡ ከገጠር መጠጥ ውሃ ጋር ተያያዥ የሆነ መብትና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ መሰረት ለክልሉ ውሃና ፍሳሽ አገልግሎት ባለስልጣን ተላልፏል::

5. የመሸጋገሪያ ድንጋጌ

በዚህ አዋጅ መሰረት የተላለፉ መብትና ግዴታዎች አስፈላጊው መዋቅር ተዘርግቶ ስራ ላይ እስከ ሚውል ድረስ ስራዎቹ ባሉት ደንቦችና መመሪያዎች ባሉበት ሁኔታ ይቀጥላል::

6. የተሻሩ ህጎች

የአዋጅ ቁጥር 47/97 አንቀጽ 10 ንዑስ አንቀጽ 51፣52፣53፣54፣56፣57፣58፣59፣ 60 እና 72 ላይ ለክልሉ ግብርናና ገጠር ልማት ቢሮ ስለ ገጠር መጠጥ ውሃ የተሰጡት ስልጣንና ተግባራት ተሽሯል::

7. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ ከዛሬ ነሐሴ 18 ቀን 1998 ዓ/ም ጀምሮ የፀና ይሆናል::

ሐረር ነሐሴ 18 ቀን 1998

ሙራድ አብዱልሃዲ

የሐረሪ ህ/ክ/መንግስት ፕሬዝዳንት

www.chilot.me

የሐረሪ ህዝብ ክልላዊ መንግስት

# ሐረር ነጋሪ ጋዜጣ
# HARAR NEGARI GAZETA
OF THE HARARI PEOPLE REGIONAL STATE

| | |
|---|---|
| ፲፩ኛ ዓመት ቁጥር 8<br>11th year No 8 | ሐረሪ ነሐሴ 18ቀን 1998<br>Harar Aug 24, 2006 |

| | | |
|---|---|---|
| ያንዱ ዋጋ ብር 4:00<br>Unit price 4:00 | በሐረሪ ሕዝብ ክልላዊ መንግስት<br>ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ | የፖስታ ሣጥን ቁጥር<br>272<br>P.O.Box 272 |

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር 60/1998 ዓ/ም
የሐረሪ ህ/ክ/መ/ ይቅርታ አስፈፃሚ አካልና የሚፈፀምበት ሥነ-ሥርዓትን ለመደንገግ የወጣ አዋጅ———ገጽ 475

## አዋጅ ቁጥር 60/ 1998 ዓ/ም
## ይቅርታ አስፈፃሚ አካል እና የሚፈፀምበት ሥነ-ሥርዓትን ለመደንገግ የወጣ አዋጅ

የሐረሪ ህዝብ ክልላዊ መንግስት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት ስልጣን ውጭ በሆነ ወንጀል ጉዳዮች ፍርድ ለተበየነበት ሰው ይቅርታ የማድረግ ስልጣን እንዳለው፤በተሻሻለው የክልሉ ህገ-መንግስት ይቅርታ እንደሚደረግ የተደነገገ በመሆኑ፤

የይቅርታ ጉዳዮችን ውሳኔ የሚሰጥ አካል ማቋቋም እና መወሰን በማስፈለጉ፤

ይቅርታን በወንጀል ህግና በሌሎች የተደነገጉትን ከህገ-መንግስቱ ጋር በማጣጣም ይቅርታ የሚሰጥ በት ሥነ-ሥርዓት በህግ ማስቀመጥ በማስፈለጉ ፤

የህግ ታራሚዎች የተወሰነባቸው የቅጣት ውሳኔ በሙሉ ወይም በከፊል ቀሪ እንዲሆን ወይም የቅጣቱ አፈፃፀም አይነት በቀላሉ ሁኔታ እንዲፈፀምላቸው የሚጠይቁበት ሥነ-ሥርዓት በማስፈለጉ ፤

በተሻሻለው የሐረሪ ህዝብ ክልል ህገ-መንግስት አንቀጽ 47 (2) (7) እና 51(2)(ሀ) መሰረት የሚከተለው ታውጇል ፡፡

www.chilot.me

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ

**1. አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ "የይቅርታ አሰፈፃሚ አካልንና የሚፈጸምበት ሥነ-ሥርዓት አዋጅ ቁጥር 60/1998 "ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል::

**2. ትርጓሜ**

1. " ክልል " ማለት በኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ህገ-መንግስት አንቀጽ 47(1)(9) መሰረት የተቋቋመው የሐረሪ ህዝብ ክልል ነው ::
2. " ምክር ቤት " ማለት የሐረሪ ህዝብ ክልል መንግስት ከፍተኛው የህግ አውጪ አካል ነው ::
3. "ሰው" ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው ::
4. "ፍርድ" ማለት በወንጀል ጉዳይ በፍርድ ቤት የመጨረሻ ውሳኔ የተወሰነ ውሳኔ ዋና ቅጣት ፣ ተጨማሪ ቅጣት ወይም የጥንቃቄና ጥበቃ ውሳኔ ነው ::
5. "የይቅርታ ጥያቄ " አንድ ፍርድ በሙሉ ወይም በከፊል ቀሪ እንዲሆን ወይም የቅጣቱ አፈፃፀምና አይነት በቀላል ሁኔታ እንዲፈፀም የሚቀርብ ጥያቄ ነው ::
6. "ፍርድ ቤት" ማለት በተሻሻለው የሐረሪ ህዝብ ክልል ህገ-መንግስት አንቀጽ 67 እና በክልሉ ፍርድ ቤቶች ማቋቋሚያ አዋጅ ቁ.3/1988 መሰረት የተቋቋመ በህግ የተሰጡትን ጉዳዮች የሚያስተናግድ እና ከሞት ቅጣት ውጪ ያሉትን ውሳኔ የሰጠ ፍርድ ቤትን ይጨምራል ::
7. "ፕሬዝዳንት " ማለት የሐረሪ ህዝብ ክልል ርዕሰ መስተዳድር ማለት ነው ::
8. "ይቅርታ ጠያቂ" ማለት ይቅርታ የተጠየቀበት ፍርድን የሚመለከት ሰው ነው ::
9. " ይቅርታ " ማለት በወንጀል ድርጊት ምክንያት የተፈረደን ፍርድ በሙሉ ወይም በከፊል እንዲሻር ወይም የቅጣቱ አፈፃጸምና አይነት በቀላል እንዲፈጸም የሚደረግ በአስፈፃሚ አካል የሚወሰድ አስተዳደራዊ እርምጃ ነው::

**3. የይቅርታ ዓላማ**

የወንጀል ቅጣት የተወሰነባቸውን የህግ ታራሚዎች ይቅርታ እንዲደረግላቸው በማድረግ በመንግስትና በህብረተሠብ ላይ የሚፈጠረውን አላስፈላጊ ጫና መቀነስና የህዝብን ደህንነትና ጥቅም ማስከበር ይሆናል::

## ክፍል ሁለት
## ይቅርታ እንዲሰጥ ስልጣን ስለ መስጠትና የይቅርታ ስራ አስፈፃሚ አካላት

**4. ይቅርታ እንዲሰጥ ስልጣን ስለ መስጠት**

ፕሬዝዳንቱ በዚህ አዋጅ መሰረት ይቅርታ እንዲሰጥ ስልጣን ተሰጥቶታል ::

**5. የፕሬዝዳንቱ ስልጣንና ተግባር**

ፕሬዝዳንቱ:-

1. በቦርዱ የውሳኔ ሐሳብ መሰረት ወይም በራሱ ምክንያት ይቅርታ ለመስጠት ወይም ለመከልከል ይችላል ::
2. በቅድመ ሁኔታው ይቅርታ ተደርጎላቸው ቅድመ ሁኔታውን ያላሟሉትን ወይም የጣሱትን በተመለከተ ከቦርዱ የሚቀርብለትን የውሳኔ ሐሳብ መሰረት በማድረግ ይቅርታውን ለመሰረዝ ይችላል ::

**6. የቦርድ መቋቋም**

1. የይቅርታ ጉዳዮችን የሚመረምርና ለፕሬዝዳንቱ የውሳኔ ሐሳብ የሚያቀርብ የይቅርታ «ቦርድ» እየተባለ የሚጠራ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል ፤
2. የቦርዱ ተጠሪነት ለፕሬዝዳንቱ ይሆናል ::

**7. የቦርድ ስልጣንና ተግባር**

ቦርዱ የሚከተሉትን ስልጣን እና ተግባር ይኖሩታል :-

1. በህግ አግባብ የሚቀርቡለትን የይቅርታ ጥያቄዎች በመመርመር በቅድመ ሁኔታ

www.chilot.me

ወይም ያለ ቅድመ ሁኔታ ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል እንዲሻር ወይም የቅጣቱ አፈፃፀም በቀላል እንዲፈፀም ወይም ይቅርታ የሚያሰጥ ሆኖ ያላገኘው እንደሆነ ቅጣቱ እንዲጸና ለፕሬዝዳንቱ የውሳኔ ሐሳብ ያቀርባል ፡፡

2. እንደ አስፈላጊነቱ ክሱን የተከታተለውን አቃቤ ህግ እና ሌላ ማንኛውም ባለ ስልጣን ወይም ግለሰብ እንዲቀርብ ወይም በጽሁፍ እንዲያቀርብ ያደርጋል፡፡

3. በፕሬዝዳንቱ በቅድመ ሁኔታ ላይ የተመሰረተ ይቅርታ የሚሰጣቸው ሰዎች ቅድመ ሁኔታውን አላሟሉም ወይም ጥሰዋል የሚል ክስ ሲቀርብላቸው ጉዳዩን መርምሮ ለፕሬዝዳንቱ የውሳኔ ሐሳብ ያቀርባል ፡፡

4. የይቅርታ ጥያቄዎች አፋጣኝ መልስ የሚያገኙበት መንገድ በማስጠናት ተግባራዊ ያደርጋል፡፡

5. ይቅርታ ሊያስጠ የሚችሉ ምክንያቶችን በማስጠናት ተግባራዊ ያደርጋል ፡፡

6. ይቅርታ የሚደረግላቸው የህግ ታራሚ ዎችን መርምሮ ለቦርዱ የሚያቀርብ አጥኚ ኮሚቴ በመሰየም የማጣራት ሄደቱን ሊያሰራ ይችላል ፡፡

7. ሌሎች በህግ የሚሰጡትን ተግባራት ያከናውናል ፡፡

## 8. የቦርድ አባላት

ቦርዱ የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል ፡-

1. የፍትህና ፀጥታ ጉዳይ ቢሮ ኃላፊ ሰብሳቢ ፤
2. የጤና ቢሮ ኃላፊ አባል ፤
3. የህዝብ አደረጃጀት ፤ ባህልና እስፖርት፣ ሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮ ኃላፊ አባል ፤
4. የክልሉ ፖሊስ ኮሚሽን ኮሚሽነር አባል፤
5. የማረሚያ ቤቶች ኮሚሽን ኮሚሽነር አባል፤
6. እንደ አስፈላጊነቱ በቦርዱ አቅራቢነት በፕሬዝዳንቱ የሚመረጡ ህብረተሰቡን የሚወክሉ ከሁለት የማይበልጡ ሰዎች አባል ፤
7. የጽ/ቤቱ ኃላፊ ፀሐፊና አባል ናቸው ፡፡

## 9. የቦርዱ ሰብሳቢ ሥልጣንና ተግባር

የቦርዱ ሰብሳቢ የሚከተሉት ስልጣንና ተግ ባር ይኖሩታል ፡-

1. ቦርዱን በሊቀመንበርነት ይመራል ፤
2. ይቅርታ የተደረገላቸው ወይም የተከለ ከሉ ሰዎች በተመለከተ የፕሬዝዳንቱን ውሳኔ በቦርዱ ጽ/ቤት በኩል ለሚመለ ከታቸው አካላት እንዲተላለፍ ያደር ጋል ፤
3. ስለ ቦርዱ የስራ አካሄድ በየ6 ወሩ ለፕሬዝዳንቱ ሪፖርት ያቀርባል ፤
4. በፕሬዝዳንቱ የሚሰጡትን ከስራው ጋር ተዛማጅነት ያላቸውን ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል ፡፡

## 10. የቦርዱ የስብሰባ ሥነ-ሥርዓት

1. ከቦርዱ አባላት መካከል ሁለት ሦስተኛው ከተገኙ ምልዓተ ጉባዔ ይኖራል ፤
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ቢኖርም የይቅርታ ጥያቄ የቀረበበትና ጉዳዩ አጣዳፊ ሆኖ የተገኘ እንደሆነ ከአባላቱ ከግማሽ በላይ ከተገኙ ስብሰባው ሊካሄድ ይችላል ፤
3. ቦርዱ ውሳኔውን በአብላጫ ድምጽ ያሳልፋል ድምጹ በእኩል በተከፈለ ጊዜ የቦርዱ ሰብሳቢ የተቀበለው ሐሳብ የቦርዱ የውሳኔ ሐሳብ ይሆናል ፡፡የአነስተኛ ድምጽ ሐሳብም በሪፖርት መልክ ይቀርባል ፤
4. ቦርዱ በሦስት ወር አንድ ጊዜ መደበኛ ስብሰባ ይኖረዋል ፤
5. አስቸኳይ ስብሰባ መጥራት ሲያስፈልግ የቦርዱ ሰብሳቢ ጥሪ ሊያደርግ ይችላል ፤
6. ቦርዱ የራሱ የስብሰባ ሥነ-ሥርዓት መመሪያ ይኖረዋል ፡፡

## 11. የቦርዱ ጽህፈት ቤት

1.የፍትህና ፀጥታ ጉዳይ ቢሮ አካል የሆነ የይቅርታ ቦርድ ጽ/ቤት ከዚህ በኃላ ጽ/ቤት እየተባለ የሚጠራ ይኖራል ፤

2. ጽህፈት ቤቱ የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነት ይኖሩታል ፤

ሀ. የይቅርታ ማመልከቻዎችን ይቀበላል ፤ አስፈላጊ የሆኑ መዛግብቶችንና ሰነዶችን ያሰባስባል ፤

ለ. የቦርዱን መዛግብትና ሰነዶች በአግባቡ ይይዛል፣ ይጠብቃል ፤

ሐ. በቦርዱ የውሳኔ ሐሳብ የተሰጣቸውና በፕሬዝዳንቱ የፀደቁትን ወይም ሳይፀድቁ የቀሩትን የውሳኔ ሃሳቦች በአግባቡ ይይዛል፣ ይጠብቃል፣ ስታስቲክ ያዘጋጃል፤

መ. ሞዴል የይቅርታ ምስክር ወረቀት አዘጋጅቶ እንዲፀድቅ ለቦርዱ ያቀርባል ፣ ይቅርታ ለተደረገላቸው ሰዎች በፀደቀው የይቅርታ ሰርተፊኬት አስፈላጊውን መረጃ እየሞላ ለቦርዱ ሰብሳቢ ያቀርባል ፤

ሠ. ይቅርታ የተሰጠበትን ወይም የተከለከለበትን ውሳኔ በመዝገብ ያስፍራል ፤ መዝገቡንም ይጠብቃል ቦርዱ በሚሰጠው መመሪያ መሰረት መዝገቡን ለህዝብ ክፍት ያደርጋል፤

ረ. ሌሎች ከይቅርታ ጉዳዮች ጋር ተዛማጅነት ያላቸውን ስራዎች ያከናውናል ፡፡

12. <u>የቦርድ ጽህፈት ቤት ኃላፊ ተግባርና ኃላፊነት</u>

የቦርዱ ጽሕፈት ቤት ኃላፊ የሚከተሉትን ተግባርና ኃላፊነት ይኖረዋል፡-

1. ጽሕፈት ቤቱን ይመራል፤ይቆጣጠራል፤
2. ለቦርዱ አባላት የስብሰባ ጥሪ ያስ ተላልፋል፣ለቦርዱ ስብሰባ አስፈላጊ የሆኑ ሰነዶች መድረሱን ያረጋግጣል ፤
3. በዚህ አ ዋጅ አንቀጽ 17(4) መሰረት የተሰጠውን ውሳኔ መሰረት በማድረግ ለሚመለከተው አካል ትዕዛዝ ያስተላልፋል ፤
4. የቦርዱ ጸሐፊ ሆኖ ያገለግላል፤
5. ከቦርዱ ሰብሳቢ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባሮች ያከናውናል ፡፡

## <u>ክፍል ሦስት</u>
## <u>ስለ ይቅርታ ጥያቄ አቀራረብ ፤ስለ ይቅርታ መሠረዝ ማስረዳት</u>
## <u>ንዑስ ክፍል አንድ</u>
## <u>ስለ ይቅርታ አቀራረብ</u>

13. <u>ስለ ይቅርታ ጥያቄ አቀራረብ</u>

1. በወንጀል ጉዳይ ፍ/ቤት ተከሶ የመጨረሻ ፍርድ የተፈረደበት ማንኛውም ሰው የተወሰነው ፍርድ በሕግ ይቅርታ የሚያስከለክል ካልሆነ በቀር የይቅርታ ጠያቂው ራሱ ወይም በባለቤቱ፣ በቅርብ ዘመዶቹ፣ በወኪሉ ወይም በጠበቃው አማካይነት ማቅረብ ይችላል ፤
2. ከዚህ በላይ የተደነገገው እንደ ተጠበቀ ሆኖ የፍትህና ፀጥታ ጉዳይ ቢሮ ፣ ማረሚያ ቤቶች ኮሚሽን ይቅርታ ሊደረግላቸው የሚገባቸውን ሰዎች በመምረጥ በበኩላቸው የይቅርታ ጥያቄ ማቅረብ ይችላሉ፡፡ መ/ቤቶቹ የይቅርታ ጥያቄ ለማቅረብ የወሰኑ እንደሆነ የይቅርታ መጠየቂያውን ደብዳቤ ቅጂ ይቅርታ ለተጠየቀለት ሰው እንዲደር ሰው ማድረግ ይኖርባቸዋል ፤
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ2 በተደነገገው አኳኋን ይቅርታ እንዲደረግለት የተጠየቀለት ሰው ይቅርታውን ለመቀበል የማይፈልግ የሆነ እንደሆነ የይቅርታ መጠየቂያው ደብዳቤ ቅጂ በደረሰው በ15 ተከታታይ የስራ ቀናት ውስጥ በጽሁፍ ለቦርዱ ማስታወቅ አለበት ፤
4. ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ካልሆነ በቀር ከላይ በንዑስ አንቀጽ 3 በተደነገገው ጊዜ ገደብ ውስጥ ይቅርታ እንዲደረግለት የቀረበለትን ጥያቄ አለመቀበሉን ካላሳወቀ ይቅርታውን እንደተቀበለ ይቆጠራል ፣ ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት አጋጥሞ ለማስታወቅ ያልቻለ ሰው ያጋጠመውን ችግር ገልፆ ችግሩ ከተወገደለት ዕለት ጀምሮ በ15 ተከታታይ የስራ ቀናት ውስጥ ማሳወቅ አለበት ፤
5. ይቅርታ የተጠየቀበት ፍርድ በህግ ይቅርታ የሚያሰጥ መሆኑን ይቅርታ ጠያቂው እንዲያቀው ይደረጋል?

14. **የይቅርታ ጥያቄ ማመልከቻ መያዝ ያለበት ዝርዝር ነገሮች**

የይቅርታ ጥያቄ ማመልከቻ ይቅር ጥያቄውን በተመለከተ በተለይ የሚከተሉትን መረጃዎች መያዝ ይኖርበታል ፡-

1. ሙሉ ስም /እስከ አያት / እድሜ፣የእናት ሙሉ ስምና አድራሻ ፤

2. የመንግስት ሠራተኛ የነበረ እንደሆነ የኃላፊነቱ ደረጃ፤
3. ወንጀሉን ከመፈፀሙ በፊት ለ5 ዓመታት ይኖርበት የነበረው ቦታ ሙሉ አድራሻ፤
4. የተከሰሰበት የወንጀል ድርጊት ፣ ተጠያቂነት የሆነበት ወንጀልና የተፈረደበት ፍርድ፣ የፈረደውን ፍ/ቤት፣የፍርድ አፈፃፀም የሚገኝበት ደረጃ እና የክሱ መዝገብ ቁጥር ፤
5. ከደንብ መተላለፍ ውጪ ቀድሞ ተከሶ የተፈረደበት የወንጀል ድርጊት፣ የተወሰነውን ቅጣትና የፍርድ አፈፃፀም፤
6. በማረሚያ ቤት ፣ በፀባይ ማረሚያ፣ በግዛት ወይም ግዞት ስፍራ የሚገኝ ከሆነ የሚገኝበትን ተቋም ወይም ስፍራ፤
7. ይቅርታ ሊደረግለት የሚገባበት ምክንያት ፤
8. የይቅርታ ጥያቄውን የሚደግፍ በአባሪነት የተያዙ መረጃዎች ካሉ ዝርዝራቸውን ፤
9. ከይቅርታ ጥያቄው ማመልከቻ ጋር የተያያዙ መረጃዎች ካሉ መረጃዎቹ የሚገኙበት ስፍራ ፤
10. የይቅርታ ጥያቄውን የሚደግፍ በስጋ ወይም በጋብቻ፤ ከጠያቂው ጋር ዝምድና የሌላቸው ከሦስት ያልበለጡ ግለሰቦች እንዲሁም ድርጅቶችና ማህበራት ሙሉ ስምና አድራሻ እና ይቅርታውን የሚደግፉበት ምክንያት፤
11. ከመንግስት የሚፈለግ እዳ መኖር አለመኖር ፤
12. ከወንጀል ድርጊት ተጠቂ የሆኑት ግለሰቦች መካሱን፤ ለመካስ መጣሩን ወይም ያሉበትን ሁኔታ የሚገልጽ ፤
13. ቀደም ሲል ይቅርታ ተደርጎ እንደሆነ ወይም የይቅርታ ጥያቄ ቀርቦ ውድቅ ሆኖ እንደሆነ ውሳኔው የተሰጠበትን ቀን፤
14. የይቅርታ ጥያቄው በሌላ ሰው ስም የሚያመለክት ከሆነ ይህንኑ ለመፈጸም መብት የሚሰጠውን ህጋዊ ምክንያት፡፡

15. **<u>የይቅርታ ጥያቄ ማቅረቢያ ጊዜ</u>**

በዚህ አዋጅ አንቀጽ 13 መሰረት የይቅርታ ጥያቄ የሚያቀርብ ሰው የይቅርታ ጥያቄውን ?

1. ፍርዱ ከተሰጠ በኃላ በማናቸውም ጊዜ፣ የይቅርታ ጥያቄ አቅርቦ ጥያቄው ውድቅ ከተደረገ ከ6 ወር ቡሐላ፤
2. የ6 ወር ጊዜ እንደተጠበቀ ሆኖ በአፋጣኝ ታይቶ ምላሽ ማግኘት ያለበት የይቅርታ ጥያቄ ከሆነና ከቦርዱ አባላት በሦስት አራተኛ ድምጽ ከተደገፈ 6 ወር ሳይጠብቅ በማናቸውም ጊዜ ማቅረብ ይችላል ፡፡

16. **<u>የይቅርታ ጥያቄ ማመልከቻ ስለ መመርመር</u>**

ቦርዱ የይቅርታ ጥያቄ ሲቀርብለት ከዐቃቤ ህግ መዝገብ ወይም ከፍርድ መዝገብ በተጨማሪነት በዚህ አዋጅ አንቀጽ 14 የተመለከቱትን መረጃዎች እንዲሁም ከማና ቸውም ሰው የሚቀርቡለትን ማስረጃዎችና ጥቆማዎችን እንዲሁም በራሱ የሚያገኛ ቸውን ማናቸውም የይቅርታ ጥያቄውን የሚደግፍ ወይም የሚቃወሙ ማስረጃዎችን መመርመር ይኖርበታል ፡፡

**<u>ንዑስ ክፍል ሁለት</u>**

**<u>ይቅርታ ስለ መሰረዝና ስለ ማስረዳት</u>**

17. **<u>ይቅርታን ስለመሰረዝ</u>**

1. የይቅርታ ውሳኔ ለይቅር ተባዩ ከመድረሱና ተቀባይነት ከማግኘቱ በፊት የይቅርታውን ውሳኔ ለመሰረዝ የሚያስችሉ ምክንያቶች ካሉ የይቅርታው ውሳኔ ሊሰረዝ ይችላል፣
2. የይቅርታ ውሳኔው ለይቅርታ ተባዩ ከመድረሱና ተቀባይነት ካገኘ በኃላ የይቅርታ ውሳኔው በማጭበርበር ወይም በማታለል የተገኘ መሆኑን ከተረጋገጠ የይቅርታ ውሳኔ ዋጋ አይኖረውም ፣
3. በቅድመ ሁኔታ ላይ የተመሰረተ ይቅርታ ቅድመ ሁኔታው መጣሱ ከተረጋገጠ የይቅርታ ውሳኔው ዋጋ አይኖረውም ፣

4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) እና (3) መሰረት ውሳኔው ከተሰረዘ ይቅርታ ተባዩ የይቅርታ ውሳኔ ከመሰጠቱ በፊት ወደ ነበረው ቦታ እንዲመለስ ቦርዱ ይወስናል ።

**18 ይቅርታ ሲሰረዝ መሟላት ያለበት ሥነ-ሥርዓት**

1. ይቅርታ ስለ መሰረዝ የሚያበቁ ምክንያት ከተገኘ ምክንያቱ በግልጽና ይቅርታ የተደረገለት ሰው በሚገባው ቋንቋ በጽሁፍ ተዘጋጅቶ ለይቅርታ ተባይ እንዲደርሰው ይደረጋል ።
2. ይቅርታ ተባዩ ጽሁፍ በደረሰው ቢበዛ በ20 ቀናት ውስጥ መልሱን ማቅረብ ይኖርበታል ።

**19. ይቅርታን ስለ ማስረዳት**

1. ማንኛውም ይቅር ተባይ ይቅርታ የተደረገለት መሆኑን የሚያረጋግጠው በዋናው በይቅርታ የምስክር ወረቀት ነው ፣
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው ቢኖርም ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ዋናው የይቅርታ ምስክር ወረቀት ለማጥፋቱ አሳማኝ ማስረጃ ያለው ይቅር ተባይ ይቅርታ የተደረገለት መሆኑን ትክክለኛነቱ በተረጋገጠ የይቅርታ ምስክር ወረቀት ቅጂ ማረጋገጥ ይችላል።

## ክፍል አራት
## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

**20. ተፈፃሚነት ስለማይኖራቸው ህጎች**

ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረን ማናቸውም ህግ ተፈፃሚነት አይኖረውም።

**21. የመተባበር ግዴታ**

ማንኛውም ሰው ይህን አዋጅ ለማስፈፀም የመተባበር ግዴታ አለበት።

**22. መመሪያ ስለ ማውጣት**

ለዚህ አዋጅ ለበለጠ አፈፃፀም ፕሬዝዳንቱ መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል ።

**23. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ አዋጅ በሐረሪ ሕዝብ ክልል ምክር ቤት ከፀደቀበት ከነሐሴ 18 ቀን 1998 ዓ/ም ጀምሮ የፀና ይሆናል።

ሐረር ነሐሴ 18 ቀን 1998 ዓ/ም
ሙራድ አብዱልሃዲ
የሐረሪ ሕዝብ ክልላዊ መንግስት
ፕሬዝዳንት

www.chilot.me